5ኛ ዕትም

ፋይናንስ ማኔጅመንት ፩

የፋይናንስ አመራር ጥበቦችና መሰረታዊ የአካውንቲንግ ክህሎቶች

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

@ETHIO_PDF_BOOKS

የመፅሃፉ መቅድም በረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር አጥላው አለሙ፣
በአ.አ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋክልቲ መምህርና ተመራማሪ

Scanned with CamScanner

የምሁራን አስተያየት

ፋይናንስ ማኔጅመንትን ማወቅ ማለት ንግድን ማወቅ ማለት ነው፡፡ ገቢ እንዴት እንደምትፈጥር፣ አስበለሊያ የት እንድምትሄድ አታውቅም፡፡ ገቢ እንዴት እንደምትፈጥር፣ አስበለሊያ የት እንድምትሄድ፣ የጥሬ ገንዘብ ክምችት እጥረት ወጭ እንዴት እንደምትቆጥብ፣ የጥሬ ገንዘብ ክምችት እጥረት ሲፈጠርብህ ምን ማድረግ እንደምትችል ማወቅ እንዳይፈጠርብህና ሲፈጠርብህ ምን ማድረግ እንደምትችል ማወቅ ይኖርብሃል፡፡ ንግድ ፋይናንስ መር በሆነ እውቀት የሚሰራ እንደመሆኑ መጠን እንዲህ መሰል መፅሀፍት ወሳኝ የመሆናቸውን ያክል መንግስትም እንዲህ መሰል ስልጠናወችና ልዩ ልዩ ፋይናንስ ነክ አትም ግንባታዎች እንዲሰጡ በትኩረት መስራት ይኖርበታል፡፡ እንዲህ መሰል መፅሐፍትን ሳዘጋጁትም መንግስት ድጋፍ ቢያደርግ፣ ማህበረሰቡም ክብር ቢሰጣቸው የበለጠ ብዙ ለመስራት ይበረታታሉ፡፡ በመጽሐፉ ውስጥም በቀጣይ ቢካተት የምለው መንግስት የሚከተላቸው የፋይናንሲንግና የግብር ፖሊሲዎች እንዲሻሻሉ የሚያግዙ ጥናታዊ ተሞክሮዎች ቢቀርቡ እላለሁ፡፡ በአገራችን ጀማሪ የስራ ፈጣሪዎች ብድር ለማግኘት መያዣ የሚጠየቁበት ሁኔታ የሚቀርበት ወይም የሚቀየስበት፣ እንዲሁም ጀማሪ ቢዝነሶች ራሳቸውን እስኪችሉ ድረስ የግብር እፎይታ የሚያገኙበት ዕድል ቢመቻች ሳይደናቀፉ በስራቸው እንዲቀጥሉ ያበረታታቸዋል፡፡ ብዙ ወጣቶችንና ምሁራኖችን ወደ ውጭ አገር የሚሰደዱበት መስራት እያቃታቸው ሳይሆን ለመስራት የሚያበረታታ አስቻይ ሁኔታ ስላልተፈጠረላቸው ነው፡፡ ግብር ሰብሳቢው አካልም በቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራርን ቢከተል የንግዱን ማህበረሰብ ጊዜና ወጭ ይቆጥብለታል፡፡ በተረፈ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ብዙ ቁም ነገሮች አንባቢያን ወደ ተግባር ቢለውጧቸው ይጠቀሙባቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ቶማስ ዜናዊ ገ/ማርያም(MA ,PhD Candidate in Development Studies, UNISA)

ቲ.ዜድ.ጂ. ጀነራል ዴቨሎፕመንት ሪሰርች፤ ኮንሳልታንሲ እና ትሬይኒንግ ሰርቪስ መስራችና ማኔጂንግ ዳይሬክተር

ማውጫ

መቅድም 1
መግቢያ
የፋይናንስ ማኔጅመንት ጥበብ አስፈላጊነት!! ___ 5

ገንዘብን ማእከል ያደረገ ውጤት ተኮር አመራርነት

የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ውጤታማነት ለማወቅ የምንጠቀምባቸው ቁልፍ መስኪያዎች ___ 16
ውጤታማ የገንዘብ አስተዳደር እንዴት ይለካል? ___ 23
የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ማወቅ ምን ምን ጥቅሞች ይኖሩታል? ___ 25
አንድ ድርጅት የፋይናንስ አፈፃፀሙን ለመለካት ከምን ይጀምር? ___ 26
ምን ምን ጉዳዮች በልኬቱና ግምገማው ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል? ___ 28

የፋይናንስ ማኔጅመንትና የአካውንቲንግ ሪፖርቶች ትስስር ___ 34

የሃብትና ዕዳ ሚዛን መግለጫ ___ 60
የገቢና ወጭ ሪፖርት መግለጫ ___ 76
የጥሬ ገንዘብ መግለጫ

Scanned with CamScanner

የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት፣ከታክስ ሥርዓቱ ጋር ያለው ግንኙነት፤ የሚታዩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው!!

የምክር አገልግሎት ለንግዱ ማህበረሰብ የሚኖረው ፋይዳ ምንድ ነው? 99

የግብር ምንነት፣ ዓይነቶችና አስገዳጅ ሁኔታዎች!!

ግብር ምንድነው? 115

የስራ ማስኬጃ ካፒታልን በምርጥ ደረጃ ለማስተዳደር

የስራ ማስኬጃ ካፒታል ምንድን ነው? 130

የስራ ማስኬጃ ካፒታል ለአንድ ድርጅት ምን ያህል ወሳኝ የማኔጅመንት ክፍል ነው? 133

የስራ ማስኬጃ ካፒታልን በብቃት ለማስተዳደር ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው ጉዳዮች!! 138

የስራ ማስኬጃ ካፒታል የሚለካው መቼ ነው? 138

የጥሬ ገንዘብ ክምችትን በላቀ ደረጃ ለማሳደግና ለማስተዳደር የሚያስችሉ መላዎች

ካሽ ፍሎው በአገር ደረጃ!! 147

የበላይ አመራሩ ለድርጅቱ የካሽ ፍሎው ችግር እንዴት መንስኤ ይሆናል? 153

ድርጅቱን ለካሽ ፍሎው ስጋት የሚጥሉ መንስኤዎች!! 153

በድርጅቶች ላይ የሚታዩ የካሽ ፍሎው ችግር አይነቶች!! 155

አንድ ድርጅት ሊኖረው የሚገባ የካሽ ፍሎው መጠን!! 171

አንድ ሰው በትክክል ማስተዳደር ያለበት ጥሬ ገንዘቡን ነው ወይስ የጥሬ ገንዘብ ዝውውሩን? 171

በአንድ ድርጅት ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ የገንዘብ ፍሰት አይነቶች!! 173

13ቱ የጥሬ ገንዘብ ማኔጅመንት መፍትሔዎች!! 175

በአጣብቂኝ ችግር ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ምንጮች!

ምን አይነት የአጭር ጊዜ የገንዘብ አቅራቢዎችን ልንጠቀም እንችላለን፡ የትኛውስ የተሻለ ነው? 187

የውጤታማ ኢንቨስትመንት መንገድ!!

የተጀመሩትንም ሆነ አዲስ የሚጀመሩ ኢንቨስትመንቶችን ውጤታማ ማድረግ እና ውጤታማነታቸውን የመለኪያ ዘዴዎች!! 202

ዓለማቀፍ ተሞክሮ አዳዲስ የቢዝነስ ሀሳቦችን ወደ መሬት ከማውረድ አንፃር !! 206

Scanned with CamScanner

የፋይናንስ እንቅስቃሴን ለማሳደግ አማራጭ መፍትሔዎች!! — 207
የፋይናንሻል ውጤታማነት መለኪያዎች!! — 209

የድርጅቶችን ትርፋማነት የሚያሳድጉ ልዩ ልዩ መንገዶች

የአንድን ድርጅት ትርፋማነት በተሻለ ደረጃ ማሳደግ እንዴት ይቻላል? — 216

የወጭ አመራር ጥበብ

ትርፋማነትን ለማሳደግ ገቢን ማሳደግ ወይስ ወጭን መቀነስ — 222
ቋሚና ጊዜያዊ ወጭዎች!! — 224
ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች — 227
ወጭ ቀጣቢ ስርአትን ማስፈን ያለው ፋይዳ — 229
ወጭዎችን መቀነስ የሚቻለው እንዴት ነው? — 229
የንግዱ ማህበረሰብ ወጭ ቀጣቢ አሰራርን ከሠራተኞች ጋር እንዴት እንደሚፈጥር? — 231
የአካውንቲንግና የፋይናንስ ልዩ ልዩ ቃላቶችና ትርጉማቸው — 234
"ፋይናንስ ማኔጅመንት - 2" — 248

መቅድም

በረዳት ፕ/ር ዶ/ር አጥላው አለሙ

(በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩልቲ የኢኮኖክሚስ መምህርና ተመራማሪ)

ቢዝነስ መስራት በማያቋርጥ ራስን የማስተማር መስመር ውስጥ የሚከት ነው:: አዲስ ሃሳብን ፈጥሮ ወደ ቢዝነስ ለሚገባውም ሆነ ቢዝነሱን ለማስፋፋት የሚያስበው የሚያልፈው በዚሁ መስመር ነው:: አዳዲስ ችግሮችን ለመፍታት፣አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀምና፣ አዳዲስ የቢዝነስ ዕውቀቶችን ለማግኘት፡ በሚደረግ ጥረት ውስጥ መማር ይኖራል::በመማርም እድገት ይከተላል::

ከእነዚህ መሠረታዊ እውቀቶች ውስጥ ታዲያ አንዱ የገንዘብ አመራርን በተመለከተ ያለው ነው:: እንደስራ ፈጣሪም ሆነ የድርጅት አመራር ስለ ቢዝነሱ የፋይናንስ አፈፃፀም ከሌሎች ጋር ለመወያየት፣በራስ የመተማመን መንፈስን ለመገንባት፣ስለፋይናንስ መሠረታዊ የሆኑ እውቀቶች መኖራቸው በጣም አስፈላጊ ነው:: እንደ ድርጅት አመራር ከቢዝነስ ጋር የተያያዙ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን ማወቅ ለሌሎች የሚወከል ጉዳይ ሊሆን አይችልምና::

በአገራችን ብዙውን ጊዜ ንግዶች የሚሠሩት በልማድ ነው:: በተለይ ደግሞ ትክክለኛ የፋይናንስ እውቀት ኖሮት ገንዘቡን ኢንቨስት የሚያደርግ ፣ ገንዘቡን ከሌላ ቦታ ለኢንቨስትመንት (ከባንክም ሆነ ከኢንቨስተሮች ሲያሰባስብ፣) ገንዘብ ወጭ ያደረገበትንም ቢዝነስ ሲመራ ልማዳዊ አወሳሰኖችና አተገባበሮች እንጂ በእውቀት የተደራጀ ውሳኔና አሠራር እምብዛም አይታይም:: ከእንዲህ መሰል ልማዳዊ አሰራሮችን

Scanned with CamScanner

ወደ ዘመናዊ አሰራር ለመለወጥ ታዲያ የፋይናንስ ዕውቀት በእጅጉ ያስፈልጋል።

በመሆኑም ይህ መፅሐፍ በአቅራቢውና በደንበኞች መካከል መግባባት እንዲፈጠር፣ በባንኮችና በድርጅቶች መካከል መረዳዳት እንዲዳብር፣ በድርጅቶች ውስጥም ባሉ አመራሮች መካከል የጋራ ውይይትና የአሠራር ማሻሻያዎችን ለማድረግ፣ ፋይናንስ ነክ እውቀቶች መሠረታዊ መግባቢያዎች መሆናቸውን በመረዳት የተዘጋጀ ነው። ይህ መፅሐፍ ለግል ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን መንግስታዊ ለሆኑና ላልሆኑ ተቋማት ጭምር ተመሳሳይ ጥቅምን የሚሠጥ ነው። የፋይናንስ ፅንሰ ሃሳቦችን በቀላሉ ለመረዳት በሚያስችል መልኩ በአማርኛ ቋንቋ መዘጋጀቱ ደግሞ የበለጠ ችግር ፈቺ መፅሐፍ እንዲሆን ያደርገዋል።

በተለይ ደግሞ በቀረጥ ሰብሳቢው መ/ቤትና በንግዱ ማህበረሰብ መካከል መግባባት እንዲፈጠር፣ የቀረጥና ጉምሩክ መሥሪያ ቤት ባለሙያዎችንም ለደንበኞቻቸው በሚገባ ቋንቋ ለማስረዳት ይህን የፋይናንስ ማኔጅመንት መፅሐፍ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ይህን እውቀት ካለመያዝ የተነሳ የንግድ ማህበረሰቡ አባላት ከታክስ መስሪያ ቤቱ ጋር ለአላስፈላጊ ክርክሮችም ሆነ ላልተፈለጉ ቅጣቶች እንዲሁም ህግ ነክ የይግባኝ ክሶች የሚዳረጉ በመሆናቸው በሁለቱ አካላት መካከል ጥሩ መግባባቶች እንዲፈጠር መፅሐፉ በላቀ ደረጃ ያግዛቸዋል።

መንግስት እና የሚመለከታቸው የሙያ ማህበራት እንዲህ መሠል መፅሐፍትንና እውቀቶችን በብዙሃኑ ዘንድ እንዲዳረሱ፣ በአጫጭር ስልጠናዎች እንዲታገዙ የማድረግ ኃላፊነቶችን ቢወጡ ደግሞ በአገር ደረጃ ይህ በመስኩ የሚኖረው ግንዛቤ በእጅጉ እንዲዳብር ያግዛልና ቢታሰብበትም መልካም ነው።

የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምንም እንኳን ለትርፍ የተቋቋሙ ባይሆኑም የሚያከናውኗቸው ልዩ ልዩ ግዢዎች፣ አስተዳደራዊ ወጭዎችና የሚመሯቸው ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች ከገንዘብና ከበጀት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ገንዘብ ነክ አፈፃፀማቸውን ጥሩ ለማድረግ ይህ መፅሃፍ በእጅጉ ይረዳቸዋል።

መፅሐፉ ከድርጅቶችም አልፎ በግለሰቦች ገንዘብ ነክ አስተዳደሮች ላይ፣ በግብር ምንነትና ስርአቶች ላይ፣ በኢንቨስትመንት ላይ፣ በጥሬ ገንዘብና የሥራ ማስኬጃ አስተዳደሮች ላይ፣ በመሠረታዊ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀቶች ላይ ፣ እነዚህ የፋይናንስ ሪፖርቶችም ለውሳኔ ጥቅም ላይ እንዴት እንደሚውሉ፣ ለአጭር ጊዜ ገንዘብ ነክ ችግሮችም ድርጅቶች ምን ምን አይነት የገንዘብ ምንጮችን እንደሚጠቀሙ በስፋት የሚያብራራ ሲሆን በተለይ ደግሞ የፋይናንስ ነክ ቋንቋን ከማሳደግ አንፃር በፋይናንስ ነክ የቃላት ትርጓሜዎች (ፋይናንሻል ተርሚኖሎጂ) ላይ ሠፊ ትንተናን ይዞ የቀረበ በመሆኑ እያነበቡ ወደተግባርም ቢቀይሩት ብዙዎችን ይጠቀማል።

ብዙውን ጊዜም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የምታዘበው ፈተና ለማለፍ ብቻ እነዚህን የአካውንቲንግና የፋይናንስ ትምህርቶችን በሚገባ ሳይገነዘቧቸው ያልፋሉ። ወደ ተግባራዊው የስራ አለም ሲገቡ ለፈተና ብቻ ሸምድደው ያለፏቸው እውቀቶች ይረሷቸዋል ወይም ከተግባር ጋር ለማስተሳሰር ሲሳናቸው ይስተዋላል። ይህ መፅሐፍ ታዲያ ተመርቀው በስራው አለም ውስጥ ላሉትም ሆነ በዩኒቨርስቲ የትምህርት ገበታ ላይ ለሚገኙት የተማሩትን በሚገባ እንዲያስታውሱ፣ ወደ ራሳቸው የግል ህይወት እንዲቀይሩትም ሆነ በሚሠሩባቸው ድርጅቶች ላይ እውቀታቸውን ወደ ተግባር እንዲያዛምዱት ያግዛቸዋል።

አገራችን የአለም ንግድ ድርጅት አባል በመሆን ሁሉንም የነፃ ገበያ ህጎችን ተግባራዊ ወደማድረግ የምታመራ በመሆኗ በተለይ በግሉ ዘርፍ

Scanned with CamScanner

የውስጥን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደዘመናዊ የአሠራር ስርአት ራሳቸውን በማላደግ ተወዳዳሪ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ከእነዚህም የአመራር ስርአቶች ውስጥ የፋይናንስ ስርአት አይነተኛ አመራርን የሚጠይቅ ነውና በእንዲህ መሠል መፅሐፍት መታገዙ አስፈላጊም ወቅታዊም ይሆናል።

«ፋይናንስ ማኔጅመንት 1» በሚል መጠሪያ የተሰየመው ይህ መፅሐፍ በተለያዩ ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ የዘርፉ ምሁራንም በተጋባዥነት እውቀታቸውንና ልምዳቸውን ያካፈሉበት መሆኑ ይታያል። መልካም ንባብ!!

መጽሐፉ አሁን በስራ ላይ ላሉትም ሆነ ወደፊት ወደ ንግድ ስራ ለሚገቡ መሰረታዊ የሆነ የገንዘብ አስተዳደር፤ የሂሳብ አያያዝና ሙያዊ ምክሮችን እንዲሁም በታክስ ስርዓቱም ዙሪያ ጥሩ መረጃዎችን የያዘ በመሆኑና በሚገባን ቋንቋ የተጻፈ ስለሆነ ጥሩ ድጋፍ ይሆናል እላለሁ።መፅሃፉ ከንግዱ ማህበረሰብ በተጨማሪም ለፋይናንስና አካውንቲንግ ተማሪዎች ጭምር ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ አምናለሁ።

ይትባረክ አምባው
የተፈቀደለት የሒሳብ ባለሙያ)

መግቢያ

የፋይናንስ ማኔጅመንት ጥበብ አስፈላጊነት!!

‹‹ነገ ሲሞት እንደሚችል ሠው ዛሬን ደስ ብሉህ ዋልባት፤ ዘላለም እንደሚኖር ሰው ደግሞ ዛሬን ተማርባት!››

ማህተመ ጋንዲ

የፋይናንስ ማኔጅመንት በአገራችን እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ የሆነ እውቀት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ገንዘብ የግለሰቦችም ሆነ የድርጅቶች የደም ስር እንደመሆኑ መጠን ይህን ወሳኝ አንጡራ ሃብት በተገቢው መንገድ ማስተዳደር ካልተቻለ የሀልውና መጨረሻ በመሆን ድርጅቱንም ሆነ ግለሰቡን ከስራ ውጭ የሚያደርግ በመሆኑ ነው። ከውጭ ወደ አገር ውስጥ በመምጣት ከአገር በቀል ድርጅቶች

ጋር የሚሠሩ ኢንቬስተሮች ስለአገራችን ኩባንያዎች ችግሮች ሲናገሩ ሁለት ቁልፍ ችግሮች ናቸው የሚሏቸው የፋይናንስ አስተዳደራችንንና ድርጅታዊ የማኔጅመንት ድክመታችንን ነው፡፡ በተለይ ለአዲስ ጀማሪ የንግድ ድርጅቶች በገበያው ላይ እንዳይቆዩ፣ እንዲሁም አነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዳያድጉ በአቢይ ማነቆነት የሚታየው ይህ መፅሐፍ የተነሳበት የፋይናንስ ችግር ነው፡፡ በእርግጥ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በፌደራል መንግስት ደረጃም ሆነ በመንግስት ስር ባሉ የልማት ድርጅቶች ላይ ተዘውትሮ የሚታየው የፋይናንስ ጉዳይ ዋነኛው ነው፡፡

ሆነ በሠኔ ወር 2010 ዓ.ም በበጀት ማፅደቅ ዙሪያ በፓርላማ ቀርበው የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ይህንን ያስረዳሉ፡፡ እንደአሳቸው ገለፃም በኢንቬስትመንት መረጣና አስተዳደር ዙሪያ ፕሮጀክቶችን የመጀመር እንጂ የመጨረስ ችግር በስፋት እንደታየ፣ በዚህም የተነሳ መጠነ ሰፊ ገንዘብ እንደሚፈጅ፤ እንዲሁም በክልሎች ደረጃ በበጀት በትክክል የመተዳደር ባህል አለመኖሩ፣ በዚህም የተነሳ አንዳንድ ክልሎች ደመወዝ ለመክፈል እስኪቸገሩ ሲደርሱ እንደሚችሉ፣ ሠፋፊ የመንግስት የልማት ድርጅቶች እስከ 400 ቢሊየን ብር የሚደርስ ከአቅም በላይ የሆነውን የብድር አወሳሰድ ስንመለከት በአገር ደረጃ የኮርፖሬት ፋይናንስ አስተዳደር ጥበብ ማነስ የተነሳ በድምሩ አገሪቱ ከአጠቃላይ ምርቷ አንፃር የብድር መጠኗ ከ60 በመቶ በላይ መድረሱ ለከፍተኛ የብድር ጫና ውስጥ እንደከተታት ይታወቃል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም አገሪቱ የአገር ውስጥ ገቢዎቿን በሚገባ መሰብሰብና ማስተዳደር ባለመቻሏ አመታዊ የበጀት እድገቷ ከተለመደው የ10 በመቶ እድገት ወደ 3 በመቶ ዝቅ ማለቱ ይታወቃል፡፡ እንዲሁም የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ክምችት የጥቂት ቀናት የገቢ ምርቶችን ብቻ ወደሚሸፍን ደረጃ ማሽቆልቆሉን ተከትሎ ከፍተኛ የምንዛሬ እጥረት

የተከሰተ ሲሆን በጥቅሉ ወደ 13.5 ቢሊዮን ዶላር የሚደርስ የገቢና ወጪ ምንዛሬ ክፍተት ውስጥ እንዳስገባት፣ የውጭ እዳዋም ወደ 24.7 ቢሊዮን ዶላር እንደደረሰ ይታወቃል፡፡ ይህ መሠል ከፍተኛ የብርና የዶላር ቀውስ ውስጥ የገባችው አገራችን እንደ ጊዜያዊ መውጫ በመንግስት እጅ ስር ሲተዳደሩ የነበሩና የአገሪቱ ወሳኝ ሃብቶች የሚባሉ የልማት ድርጅቶችን በከፊል በመሸጥ በአገር ደረጃ የተከሰተውን የብርና የዶላር ፍሠት *(Cash flow)* ወደ መፍታት የተደረሰበት ውሳኔ ላይ ተደርሷል፤ በ2010 ዓ.ም፡፡

እነዚህን በአገር ደረጃ መጠነ ሰፊ ቀውሶች ስንመለከት የፋይናንስ ማኔጅመንት ምን ያህል ወሳኝ የደም ስርነቱ ይታየናል፡፡ በእርግጥ ከአገር አልፈን ወደ ኩባንያዎችና ተቋማት ደረጃ ስናልፍ ይህንኑ ተመሳሳይ ችግር እንታዘባለን፡፡ በመሆኑም ይህ በአይነቱ አዲስና በአገር ደረጃም በአማርኛ ቋንቋም በመዘጋጀት የመጀመሪያው የሆነ የፋይናንስ ማኔጅመንት መፅሐፍ መሠረታዊ የሚባሉ እውቀቶችንና ጥበቦችን በማካተት ለማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡ ‹‹እውቀት ሃይል ነው›› ፤ በተለይ የህልውና መሠረት በሆነው ገንዘብ ዙሪያ የሚኖር እውቀት ደግሞ ከሃይልም በላይ ነው፡፡

ይህን መፅሐፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳኝ በአገራችን የሚታየውን የገንዘብ ነክ አስተዳደር የእውቀት ችግሮች እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ ከማሰብ ነው፡፡ የግል ድርጅቶችም ሆኑ የመንግስት ድርጅቶች ላይ የሚታየው የገንዘብ ነክ ችግር ብዙ ገንዘብ በማግኘት ላይ ብቻ የሚፈታ አይደለም፡፡ እንደዛ ቢሆን ኖሮ ብዙ ርዳታዎች፣ ብድሮችና የአገር ውስጥ ገቢዎች ያሏት አገር ወደዚህ አዘቅት ውስጥ መግባት ባልቻለች ነበር፡፡ ብዙ ገንዘብ ማግኘት ብቻውን የፋይናንስ ችግርን በዘለቄታዊነት ቢፈታ ኖሮ ለስራቸውና ለኢንቬስትመንታቸው የሚበቃ ገንዘብን ከግላቸውም ሆነ ከባንክ ብድር አግኝተው ሳለ ብዙ ነጋዴዎች መልሰው ችግር

ውስጥ ሲገቡ ባልታየ ነበር። በእርግጥም ብዙ ገንዘብ ማግኘት ብቻውን የግለሰቦችን ህይወት በዘላቂነት ቢቀይር ኖሮ አይተውት የማያውቁትን ገንዘብ በሎተሪ መልክ ያሸነፉ 90 በመቶ እድለኞች ህይወታቸው ባልተመሳቀለ ነበር። ከፍተኛ የነዳጅና የማእድን ሃብት ያላቸው እንደ ናይጀሪያ ያሉ አገራት በዓለም በድሆች ብዛት አንደኛ ባልሆኑ ነበር።

በመሆኑም የፋይናንስ ማኔጅመንት ጥበብ ከየትኛውም ገንዘብ በፊት የሚያስፈልግ መሠረታዊ ጉዳይ ሲሆን ይህን እውቀት ወደ እለት ከእለት ተግባር ውስጥ ለመቀየር እስከተቻለ ድረስ የፋይናንስ ማነስና መብዛት እምብዛም ውጤቱ ላይ ለውጥ አያመጣም። እንዲህ ቢሆን ኖሮ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ የገባችው ጃፓን ከ1960ዎቹ ወዲህ ኢኮኖሚዋን ወደላቀ የእድገት ደረጃ ማሸጋገር ባልቻለች ነበር። ይህን የፋይናንስ ማኔጅመንት መፅሐፍ ሳዘጋጅ እንደ ቢዝነስ ሠው ነው። እኔም እውቀቶቼን በሚገባ ካለመታጠቅ ብዙ እድሎች ያመለጡኝ በመሆናቸው፣ ጥበቦቹን በዩኒቨርስቲ ደረጃ በመማር ብዙ ነገሮችን መለወጥ በመቻሌ፣ በተለይ የሁለተኛ ዲግሪዬን ስሠራ የወሰድኳቸው የአካውንቲንግ፣ የኮርፖሬት ፋይናንስ፣ የኢኮኖሚክስ፣ የኮስት አካውንቲንግ ፣ የፋይናንስ መር ኳንቲታቲቭ አናሊሲስ ሳብጀክቶች በእጅጉ አግዘውኛል። በንግድ ውስጥ ያሉኝን ተሞክሮዎቼንና በአካዴሚክ ደረጃ ከወሰድኳቸው የፋይናንስና አካውንቲንግ እውቀቶች ጋር በማጣመር ይህን መፅሐፍ የትኛውም ሠው በቀላሉ ሊረዳው በሚችለው መልኩ ለማዘጋጀት ችያለሁ። መፅሐፉም የበለጠ ምሉዕነት ይኖረው ዘንድ በፋይናንስ ዘርፍ ልዩ ሙያውና የማማከር ብቃቱ ያላቸውን ታዋቂ ምሁራንም በተመረጡ ርዕሠ ጉዳዮች ዙሪያ በመጋበዝ እንዲሳተፉ ለማድረግ ተሞክሯል።

በመፅሐፉ ውስጥ የተዳሠሡ ልዩ ልዩ ጥበቦች ለግለሰቦች፣ ለአነስተኛና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች ፣ ለትልልቅ ኮርፖሬሽኖች፣ ለመንግስት

የልማት ድርጅቶችና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች በሙሉ እንዲጠቅም ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። እነዚህ ሁሉ አካላት ገንዘብን ከአቅራቢዎች የማምጣት (ከኢንቬስተሮች ፣ ባንኮችና ሊጋሾች)፣ ገንዘቡን ወደ ሥራ ለመቀየር የሚያስችልን ጉዳይ፣ ወይም ኢንቬስትመንት ወይም ፕሮጀክት የመምረጥ ፣ የተመረጠውን ሥራ በስራ ማስኬጃ ካፒታል የማስተዳደርና ወደውጤታማነት የመቀየር ተልእኮ ያላቸው ናቸው። በግለሰብ ደረጃ ስንሄድም ብዙ የኢንቬስትመንት ፕሮጀክቶች አሉ፣ ከፍሎ መማር ፣ የንብረት መግዛት (ቤት ፣ መኪናና የቤት እቃዎች) ፣ ገንዘብ የሚያመጡ የኢንቬስትመንት ውሳኔዎችን የማድረግ፣ በህይወት ውስጥ እንደ ጋብቻና መውለድ የመሣሉ ከገንዘብ ጋር ትስስር ያላቸው ውሳኔ የማሳለፍ ፣ የንብረት ግዥዎችን ለማድረግ መሬትን፣ ቤትንና መኪናን ለመግዛት (በባንክ ሞርጌጅ፣ ከቤተሰብ ወይም ከእቁብ) በመበደርና ብድርን የማስተዳደር ኃላፊነትን የመወጣት የመሣሉ ህይወታዊ ውሳኔዎች ያደርጋሉ።

እንዲሁም ለኑሮ የሚያስፈልጉ የግልና የቤተሰብ (የልጆች ት/ቤት ጭምር) መሠረታዊ የፍጆታ ካፒታልን በትክክል ሳይጓደሉ የማስተዳደር ኃላፊነትን ይጠይቃል። እነዚህን ሁሉ ከገንዘብ ጋር የተሳሰሩ ልዩ ልዩ ወጪዎች ለማሟላት ደግሞ ወደ ግል የባንክ አካውንት ሊገቡ የሚችሉ ገቢዎችን ለማምጣት አዋጭ ሥራዎች ማስራትን ይጠይቃል። ተቀጥሮ በመስራት በየወሩ ወይም በየቀኑ የሚያገኘውን ክፍያ ወደ ግል የባንክ አካውንቱ ያስገባል፣ ሌሎች ድርጅቶች ላይ አክሲዮን ከገዛም በትርፍ ክፍፍል መልክ በአመቱ መጨረሻ ተጨማሪ ገቢ ይኖረዋል። የራሱን ሥራ በመፍጠርም አመታዊ ትርፍ ሊያገኝ ይችላል። ወደግለሰቡ የባንክ አካውንት የሚገቡ ገቢዎች ማለትም ጥሬ ገንዘብ ወይም «ካሽ» ግለሰቡ ለወርሃዊና አመታዊ የህይወት ፍጆታው ሊበቃው ፣ ላይበቃው ወይም ደግሞ የሚተርፈው አይነት ይሆናል። እንዲሁም በግሉ የሂሳብ

አካውንት ላይ ያለው ካሽ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ለሚያደርጋቸው ከላይ የተጠቀሱ ልዩ ልዩ የንብረት ግዥዎች ሊወጣም ይችላል። ለንብረት ግዥዎች ተጨማሪ ገንዘብን በብድር መልክ ካመጣም ይህንንም ብድር ሊከፍል የሚችለው ከግሉ የባንክ አካውንት ላይ በማንሳት ነው። ይሁን እንጂ በአካውንቱ ላይ ያለው የጥሬ ገንዘብ (ካሽ) ፍሠት መጠን በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ ለሚያወጣቸው እነዚህ ዝርዝር ወጪዎች ሊበቃውም ላይበቃውም ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደሩ ሚዛኑን ይስትና የግለሰቡ የባንክ አካውንት ላይ ጥሬ ገንዘብ ባለመኖሩ የኑሮ መሠረታዊ ፍጆታ (Living Capital) ሳይቀር ላይሟላለት ይችላል። ይህ መፅሐፍ ይህን ሁሉ ይዳስሳል።

የፋይናንስ እውቀት ከሌሎች የቢዝነስ ሳብጀክቶች ጋር ሲነፃፀር በባህሪው ከበድ ስለሚል በአመራር ላይ ያሉ ባለሙያዎች በተቻለ መጠን የአካውንቲንግ ሪፖርቶች ሲቀርቡላቸው የማፈግፈግ ዝንባሌ ያሳያሉ። ብዙ አመራሮች ፋይናንስ ነክ ጉዳዮችን በኮሌጅ ቆይታቸው ውስጥ በተግባራዊ ደረጃ ስለማይማሯቸው ሊሆን ይችላል። በዚህ የተነሳም ተገቢ የፋይናንስ ግንዛቤውን በማጣታቸው ፋይናንስ ነክ ጉዳዮች ሲነሱ ትንታኔና ማብራሪያ ለመስጠት በራስ መተማመኑ የላቸውም። ይህ ብቻ አይደለም፤ ፋይናንስ ነክ ከህሉቶች ከቁጥር ጋር የተያያዙ ናቸው። ለሂሳብ ነክ ትምህርት ብዙም ፍቅር የሌላቸው ሠዎች ደግሞ በጣም ብዙ በመሆናቸው ይቸገራሉ። አካውንቲንግ ነክ መሠረታዊ ጭብጦች የሌሉት የንግድ አመራር ፋይናንስ ነክ ግንዛቤው ሊኖረው አይችልም። ምክንያቱም ፋይናንስ ነክ ውሳኔዎች የሚደረጉት አካውንቲንግ ነክ መረጃዎችን በመጠቀም ነውና።

ይህ መፅሐፍ በግለሰብም ይሁን ለግል ንግድ አመራሮች እንዲሁም ለመንግስት ድርጅት መሪዎች ከላይ ያለውን ክፍተት በመሙላት ረገድ አይነ ለመግለጥ ያግዛል የሚል እምነት አለኝ። ይህ መፅሐፍ

አንድን ሠው የአካውንቲንግና የፋይናንስ እውቀት ጥሩ ወደሚባል ደረጃ የማሸጋገር አቅም አለው። እነዚህን እውቀቶች በተገቢው ደረጃ ማወቅ ባለመቻል ብዙውን ጊዜ ከድርጅቱ የፋይናንስ ዲፓርትመንት ባለሙያዎች ጋር ለመግባባት ከፍተኛ ችግር መኖሩ ይታወቃል። እንደውም አንዳንድ የድርጅቱ የሂሳብ ባለሙያዎች የድርጅቱን ባለቤቶች ወይም የበላይ አመራሮች በአካውንቲንግና ፋይናንስ ረገድ ያላቸውን ደካማ እውቀት ቀድመው ስለሚረዱት ሊያጭበረብሯቸው ሁሉ ይችላሉ። ወይም የተሳሳቱትን እንዳልተሳሳቱ፤ ያልተሳሳቱትንም እንደተሳሳቱ በማድረግ እነሱ በፈለጉበት መንገድ ያስኬዷቸዋል። በመሆኑም መሠረታዊ የአካውንቲንግና የፋይናንስ መርሆዎችን ማወቅ ከእንዲህ መሠል አንዳንድ አጭበርባሪ ባለሙያዎች ይታደጋል።

የበላይ ድርጅታዊ አመራሮች የድርጅቱን ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ከበድ ከበድ ያሉ ውሳኔዎችን የሚያሳልፉ እንደመሆናቸው መጠን በውሳኔዎቻቸው ዙሪያ ከፋይናንስ ነክ ጉዳዮች አንፃር ውሳኔያቸው ያለውን ትስስርና ውጤት በበቂ ሁኔታ ለመገንዘብ ከሂሳብ ባለሙያዎቻቸው ጋር ትርጉም ያለው ውይይት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም የድርጅቱ ሌሎች ዲፓርትመንታዊ ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው በመሆናቸው ስለፋይናንስ በቂ የሚባል እውቀት በሌለ ቁጥር ይህን ትስስር ለመረዳትና አንዱ በሌላው ላይ ያለውን አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖ ለመረዳት ይቸገራሉ። በዚህም ሳቢያ እያንዳንዱ ድርጅታዊ ውሳኔ ከፋይናንስ አንፃር የሚኖረውን እንድምታ አያውቁትም።

በመሆኑም በአመራር ደረጃ ያሉ ግለሰቦች እንዲሁም በትልልቅ ድርጅቶች ላይ በቦርድ አባልነት የሚሳተፉ ባለሙያዎች ምንም እንኳን በሌላኛው የቢዝነስ ዘርፍ በቂ እውቀት ቢኖራቸውም በፋይናንስ ዙሪያ የተደራጀ እውቀት ከሌላቸው እውቀታቸው ጎደሎ ነው የሚሆነው። ስለፋይናንስ በቂ እውቀት የሌላቸው የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮችም

ሆኑ የቦርድ አባላት የተሟላ ሃሳብን የማቅረብም ሆነ የተዋጣላቸው ውሳኔዎችን ለማድረግ አይችሉምና። አመራሮችም ሆኑ የቦርድ አባላት ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ዘርፈ ብዙ የሆኑ እውቀቶችን በሚገባ የያዙ መሆን አለባቸው። ይህ መሆን ያለበት የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት እንዲችሉ ነው። በተለይ ፋይናንስ ነክ መሠረታዊ ግንዛቤዎችን መያዝ ደግሞ ለበላይ አመራሮችና የቦርድ አባላት ለድርድር የሚቀርብ ጉዳይ አይደለም። ፋይናንስ ነክ ስኬትና ውድቀት የድርጅቱን የወደፊት ቆይታ የሚወስን ነውና። በመሆኑም ገንዘብ ነክ እውቀቶችና ባህሪያት በየትኛውም እድሜ ውስጥ ሊማሯቸውና ሊያዳብሯቸው የሚችሏቸው ክህሎቶች በመሆናቸው ይህ መፅሐፍ ትልቅ ሚናን ይጫወታል።

ወደ ዩኒቨርስቲና ኮሌጅ ተማሪዎች ስናመራ ደግሞ ተማሪዎች በተለያዩ ዘርፎች የቢዝነስ ፣ የፋይናንስ ፣ የአካውንቲንግ ፣ የኢኮኖሚክስ፣ የማኔጅመንት ፣ የማርኬቲንግ ፣ የአድሚኒስትሬሽን ትምህርቶችን ይማራሉ። በሌሎች ዘርፎች ደግሞ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት፣ ሄልዝ ማኔጅመንት እየተባለም ይማራሉ። ከተማሩና ከተመረቁም በኋላ በተለያዩ የድርጅት የሥራ ዘርፎች ውስጥ ተመድበው ይሠራሉ። ይሁን እንጂ የትኛውም የዲፓርትመንት ሥራ ከፋይናንስ ዲፓርትመንት የአሠራር ስርአት ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ተማሪዎች በኮሌጅ ቆይታቸው ወቅት ጥሩ የሚባል የአካውንቲንግና ፋይናንስ ግንዛቤን ይዘው ቢወጡ በእጅጉ ይመከራል። በእርግጥም በዩኒቨርስቲ ደረጃ በልዩ ልዩ ሙያዎች ለሚማሩ ምሁራን ይህ መፅሐፍ በአገራችን ቋንቋ የተዘጋጀ በመሆኑ በቀላሉ የሚረዱት ነውና እንደተጨማሪ አጋዥ መፅሐፍ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የአካውንቲንግና የፋይናንስ ትምህርቶችን ለተማሪዎች ከባድ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው አንዱ ምክንያት እነዚህ የትምህርት አይነቶች (ሳብጀክቶች) የሚጠቀሟቸው ቋንቋዎችና ቃላት ለመረዳት የሚከብዱ

ጭምር መሆናቸውም ነው። ለዚያም ነው ይህን መሠል መፅሐፍም ከአሁን ቀደም በአገር አቀፍ ደረጃ በአማርኛ ተዘጋጅቶ ያላየ ነው። በቀጣይ ግን ብዙ የዘርፉ ምሁራን የተሻሉ የፋይናንስና የአካውንቲንግ መፅሐፍትን እንዲያዘጋጁም እንደባለሙያ አደራ ለማለት እወዳለሁ። ኮርፖሬት ፋይናንስ እንደ ሳይንስ እውቀት ነው፤ የሚተገበርም ጥበብ ነው።

በመጨረሻም እነዚህን የአካውንቲንግ ፅንሠ ሃሳቦች ከፋይናንስ መርሆዎች ጋር በማዛመድ የተለያዩ የማጣቀሻ መፅሐፎችን በመጠቀም ለመፃፍ ያነሳሳኝን ፤ ያስጀመረኝንና ያስጨረሰኝን እግዚአብሔር ከልብ አመሠግነዋለሁ። መልካም ንባብና ትግበራ ለሁላችሁም። አመሠግናለሁ!!!

ሣብዕ ትረካ TUBE

Scanned with CamScanner

ሣብዕ ትረካ TUBE

ገንዘብን ማእከል ያደረገ ውጤት ተኮር አመራርነት

‹‹ገንዘብ መኖር በጣም ጥሩ ነገር ነው:: በገንዘብ የሚገዙ ነገሮችንም መያዝ እንዲሁ:: ሆኖም በገንዘብ በማይተመኑ ጉዳዮችም ትኩረት ስጥ ::›› ጆርጅ ሉሪሞር

የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ውጤታማነት ለማወቅ የምንጠቀምባቸው ቁልፍ መለኪያዎች

ገንዘብ ነክ ውጤታማነት የአንድን ድርጅት የገንዘብ ጤናማነት የምንፈትሽበት መለኪያ ሲሆን ይህም ምን ያህል ድርጅቱ በቢዝነሱ ውስጥ የተሻለ ስኬት እንዳስመዘገበ የምንመለከትበትን እድል የሚሰጥ ነው። ገንዘብ ነክ ውጤታማነት ስንል በገንዘብ የማይለኩ ሌሎች የውጤት መመዘኛ መንገዶች እንዳሉ የሚጠቁመን ነው።

የአንድ ድርጅት ገንዘብ ተኮር ውጤታማነት ማማር ወይም አለማማር ሊመዘንና ሊለካ ይገባል። ይህም የሚጠቅመው ድርጅቱ አፈፃፀሙ ደካማ ሆኖ ከተገኘ በቀጣይ በሚደረግ ማሻሻያ ማስተካከያ ለማድረግ፣ የበላይ አመራሮችም ከአሁን ቀደም ከፈፀሟቸው የውሳኔ ድክመቶች እንዲማሩ ጭምር ነው። ድርጅቱ ገንዘቡን ጥቅም ላይ በማዋልና በማስተዳደር ወደ ውጤት ሲቀየር ይህን አፈፃፀም የሚመሩ የፋይናንስ ኃላፊዎችና የድርጅቱ የበላይ አመራሮች ውጤቱ ሲያምር ሊመሰገኑ፣ ውጤቱ ሳያምር ሲቀር ደግሞ ሊኮነኑ ይችላሉ።

የድርጅቱን ውጤት ወደ አፈፃፀም ሪፖርትነት ለመቀየር የሚያስችሉ የፋይናንስ ውጤት መግለጫዎች ‹‹ፋይናንሻል ስቴትመንት›› በመባል የሚጠሩ ሲሆን እነዚህም ‹‹የትርፍና ኪሳራ መግለጫ›› ወይም ‹‹ኢንካም ስቴትመንት›› ፣ ‹‹የድርጅቱ ሃብትና እዳ መግለጫ›› ወይም ‹‹ባላንስ ሽት››፣ ‹‹የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር መግለጫ›› ወይም ‹‹ካሽ ፍሎው›› በመባል የሚጠሩ ሲሆን እነዚህን ሪፖርቶች በመጠቀም የድርጅቱ ወቅታዊ አፈፃፀም ምን እንደሚመስል የተለያዩ መለኪያ ውጤቶችን በመጠቀም ለማወቅ እንችላለን። እነዚህ የገንዘብ ሪፖርቶችን በመጠቀም የምናሰላቸው የውጤት ማሳያዎች ‹‹ፋይናንሻል ሬሾ›› በመባል ይጠራሉ። በእነዚህ ሬሽዮ አማካኝነትም የድርጅቱን ትርፍና

ትርፋማነት፣ ምርታማነት ፣ የሃብት አጠቃቀም ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል ጤናማነት ፣ የድርጅቱን አጠቃላይ የሃብት መጠን ፣ የተጣራ የሃብት መጠን እንዲሁም የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ መጠን ለማወቅ የሚያስችሉን ሲሆን ድርጅቱን ከባለፈው ተመሳሳይ አመት ወይም ወር አፈፃፀሙ አንፃር ያመጣቸው መሻሻሎችን ወይም ድክመቶችን በአንፃራዊነት ለማወቅ እንዲሁም የድርጅቱን አፈፃፀም በተመሣሣይ ንግድ ዘርፍ ውስጥ ካሉ ሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶች አንፃር ውጤቱን ለማነፃፀርና የፋይናንስና የቢዝነስ አሠራር ብቃቱን ለማወዳደር ይጠቅሙናል። ይህ መሠሉ የፋይናንስ ውጤቶችን የተንተራሰ ፋይናንስ ነክ ውሳኔና የቢዝነስ አመራር ፐርፎርማንስ ማኔጅመንት ወይም ውጤት መር አመራር በመባል ይታወቃል።

እንደሚታወቀው አንድን ቢዝነስ ለመጀመር ገንዘብ ኢንቬስት የሚደረግበት ሲሆን ፣ በስራ ሂደት ውስጥም ለድርጅቱ የተለያዩ የሥራ ማስኬጃዎች ገንዘብ ያስፈልጋል። ይህ ሁሉ ሆኖ ታዲያ በድርጅቱ ላይ ኢንቬስት ያደረጉ ባለቤቶችን የሚያስደስት ውጤት ሊያመጣ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ድርጅቱ ኢንቬስት የተደረገበትን ገንዘብ የሚያባክን ከሆነ በቀጣይም ለባለቤቶች የሚያከፋፍለው የትርፍ ድርሻ ስለማይኖር በዚህ ድርጅት ላይ በቀጣይ ኢንቬስት የሚያደርግ ባለሃብትም ሆነ የሚያበድር የገንዘብ ተቋም አይኖርም። ገንዘብ ነክ የውጤት መለኪያ ለአንድ ድርጅት አመራሮች ምን ያህል በብቃት ቢዝነሱን ስለመምራታቸው የሚያመላክታቸው ሲሆን ከአሁን ቀደም ከነበረው ውጤት አንፃር የዛሬው በምን ያህል የተሻለ ስለመሆኑ የሚያሳያቸው ነው። ከዚህም በመነሳት በቀጣይ ደግሞ ምን አይነት ገንዘብ ነክ ክፍተት ሊኖርባቸው እንደሚችል በማመልከት ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። በዚህ ብቻ አያበቃም አንድ ድርጅት የዛሬው ገንዘብ ነክ ውጤታማነቱን ከባለፈው አመታት

ጋር በማነፃፀር በምን እንደተሻለና እንዳልተሻለ ብቻ ሳይሆን ድርጅቱ በሚሰራበት የንግድ ዘርፍ ውስጥ ካሉ ሌሎች ተወዳዳሪዎች አንፃር በምን እንደሚሻልና እንደሚያንስ ለማወቅም ይጠቅመዋል፡፡

የአንድ ድርጅት የንግድ ሥራ ውጤታማነት የመጨረሻ መለኪያው በገንዘብ ደረጃ ያስመዘገባቸው ውጤቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በጥራት የተሻለ ተወዳዳሪ መሆን የቻለ ድርጅት በገበያው ላይ መሪ እንዲሆን የሚያበቃው ሲሆን ይህም ደግሞ የድርጅቱን አመታዊ ገቢያቸው መጠን ከፍተኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ በአመታዊ ገቢ በአንድ ንግድ ዘርፍ ውስጥ ያሉትን ድርጅቶች በማወዳደር የትኛው ከየትኛው የበለጠ የገበያ ብልጫ እንዳለው የምንረዳ ሲሆን ይህም የገበያ ብልጫ የሚያሳየው የድርጅቱን ውስጣዊ የአሠራርና የምርታማነት ብቃት ይሆናል፡፡ በመሆኑም አንድ ድርጅት በገቢው መጠን ማነስ በተወዳዳሪነት ማነሱን ስለሚጠቁመው ራሱን በቀጣይ እንዲያሻሽል እድል ይሰጠዋል፡፡ ይሁን እንጂ የራሱን የፋይናንስ ውጤታማነት መለካት ካልቻለ ለከተሞ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር በማወዳደር ያለበትን የውድድር ደረጃ መረዳት ካልቻለ ራሱን ለማሻሻል በእጅጉ የሚቸገር ነው የሚሆነው፡፡

ከዚህ ባሻገር አንድ በኮርፖሬሽን የሚተዳደር ድርጅት አክሲዮን ለመሸጥ ቢፈልግ በፋይናንስ ውጤታማነቱ ከሌሎች አማራጭ አክሲዮን ሻጭ ድርጅቶች የተሻለ ተመራጭ መሆኑን ማሳየት የሚችለው የገንዘብ ውጤታማነቱን በሚጠቁሙ መለኪያዎች በኩል ነው፡፡ የኢትዮ ቴሌኮምና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኩባንያዎች የሼር ድርሻቸው ለግል ባለሃብቶች እንዲተላለፍ በተወሰነ ሠሞን ብዙ ሠዎች የየትኛውን ድርጅት ሼር መግዛት እንዳለባቸው ሲጠይቁ ነበር፡፡ ይህም የሚያሳየው እነዚህ ሼር ለመግዛት የሚፈልጉ ኢንቬስተሮች ከመግዛታቸው በፊት በገበያው ላይ ያለውን አማራጭ የኢንቬስትመንት እድል በቅድሚያ ካጠኑ በኋላ የሚወስኑ መሆናቸውን ነው፡፡ እንደሚታወቀው አንድም

አክሲዮን ይግዛ ብዙ ሺህ አክሲዮኖች ይግዛ ፤ የአክሲዮኑ ዋጋ አንድ ብርም ይሁን መቶ ሺህ ብር ሁሉም በአክሲዮን ገበያ ውስጥ ‹‹ኢንቬስተር›› በመባል ነው የሚጠሩት፡፡ የወደፊት ትርፍን ታሳቢ አድርገው ዛሬ ላይ ገንዘባቸውን ወጪ አድርገዋልና፡፡

አንዳንድ ድርጅቶች በሺዎች የሚቆጠሩ የሼር መጠኖች ያሏቸው ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ በሚሊዮን የሚቆጠር የሼር ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ እንደ ‹‹*IBM*›› የመሠሉ ግዙፍ ኩባንያዎች ደግሞ 1.3 ቢሊዮን የሚደርሱ ሼሮች ያሉት ሲሆን ከአንድ የሼር ባለቤትነት እስከ ብዙ ሺህ የሼር ባለቤትነትን የያዙ 560 ሺህ የሚደርሱ ባለሃብቶችን በባለቤትነት የያዘ ግዙፍ ድርጅት ነው፡፡ እነዚህ ባለቤቶች በቀጣይ ይህ ኩባንያ ምን ያህል የሼር ድርሻ ክፍፍል(ዲቪዳንድ) ሊኖራቸው እንደሚችል፤ እንዲሁም የሼር ድርሻ ካፒታላቸውስ በምን ያህል እያደገ ስለመሆኑ ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው ሲሆን ይህን መረዳት የሚችሉት የድርጅቱ የበላይ አመራሮች ይፋ በሚያደርጉቸው የድርጅቱ የገንዘብ ነክ ሪፖርቶች አማካኝነት ነው፡፡ የአይቢኤም ገንዘብ ነክ ውጤታማነት ከፍ ሲል እነዚህ ባለአክሲዮኖች የባለቤትነት ድርሻቸውን ለሌላ ባለሃብት ለመሸጥ ቢፈልጉ ከፍ ባለ ዋጋ መሸጥ የሚያስችላቸው ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ዝቅ ሲል የእነሱም የሼር የገበያ ዋጋ *(Stock value)* ዝቅ ይላል፡፡ ይህ ከፍና ዝቅ ማለት ደግሞ በተለይ አይቢኤም ከሌሎች በቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ ካሉ መሰል ተወዳዳሪዎቹ አንፃር በመመልከት ነው፡፡

የአይቢኤምም ሆነ የሌሎች ተወዳዳሪዎች የገንዘብ አፈፃፀም ሪፖርት ለህዝብ ይፋ ስለሚሆን ለማነፃፀር አይከብድም፡፡ አክሲዮን ገዢዎችም ከየትኛው ድርጅት መግዛት እንዳለባቸው የሚያውቁትና የሚወስኑት በዚህ መሠሉ የገንዘብ መረጃ ላይ በመንተራስ ነው፡፡ ከየትኛው ድርጅት አክሲዮን እንግዛ?፤ ከኢትዮ ቴሌኮም? ወይስ ከኢትዮጵያ አየር

Scanned with CamScanner

መንገድ? የሚለውም ውሳኔ የሚታወቀው በእነዚህ ለህዝብ ይፋ ሊሆኑ ከሚገባቸው የድርጅቶቹ ገንዘብ ነክ አፈፃፀም በኩል ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፣ አንድ ድርጅት ሌላን ድርጅት ሊገዛው ይፈልጋል፤ ወይም አንድ ድርጅት ከሌላው ድርጅት ጋር ውህደት በማድረግ ከፍተኛ አቅምንና ተወዳዳሪነትን መገንባት ይፈልጋል ብንል ይህ በምን መልኩ ተፈፃሚ ይሆናል? የሚለው ቅድመ ጥያቄ አለ። እንዲህ መሠል የድርጅት ግዥና ውህደት በቢዝነሱ ቋንቋ ‹‹አኩይዚሽንና መርጀር›› እውን የሚሆነው ገዥው ድርጅት የተገዥውን ድርጅት በገንዘብ የሚተመን አፈፃፀሙንና ሃብቱን በትክክል ከተመነ በኋላ ነው። የድርጅቱ የካሁን ቀደም ገንዘብ ነክ አፈፃፀም ምን ይመስላል? ዛሬ ላይ ያለው ገንዘብ ነክ ውጤቶች ምን ይመስላሉ? ድርጅቱ ወደፊት ምን አይነት አፈፃፀም ሊኖረው ይችላል? ምን ያህል ካፒታል በቀጣይ ይፈልጋል? ያልተጠበቁ የገበያ ለውጦችን እንዴት ማለፍ ይችላል? ምንስ ያህል ሃብት አለው? በማለት ገንዘብ ነክ ምርመራ (ፋይናንሻል ዱ ዳይሊጀንስ) የሚደረግበት ሲሆን የሃብት ተመኑም ከእነዚህ የገንዘብ ነክ ሪፖርቶች በመነሳት የሚከናወን ነው።

እንዲህ መሠል ምርመራዎችንና ሃብት ነክ የእጅ ትመናዎችን (Asset valuation) የሚሠሩ ባለሙያዎች በዋናነት የሚጠቀሙት የድርጅቱን ገንዘብ ነክ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርቶች ነው። በውጤቱ መሠረት ግዥው ይፈፀም አይፈፀም ፣ ኢንቬስት ይደረግበት ወይስ ይቅር የሚለው በዚህ መልክ ነው የሚለየው። እነዚህ የፋይናንስ ባለሙያዎች የድርጅቱን የገቢና ወጪ መግለጫ ሪፖርቶች በመጠቀም የካሁን ቀደም አፈፃፀሙን ይገመግማሉ፤ የድርጅቱን የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርቱን በመጠቀም ደግሞ አሁን ላይ ድርጅቱ ያለበትን የፋይናንስ ደረጃ ይገመግማሉ፤ የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መግለጫ ሪፖርት በመመልከት ደግሞ ወደፊት ምን ያህል ጥሬ

ገንዘብ እንደሚያስፈልገው፣ ምን አይነት የካፒታል እቃዎች ወጪዎች እንደሚጠይቅ ይጠቁማሉ። እንዲሁም ከእነዚህ የፋይናንስ ሪፖርቶች የሚወሠዱና የሚቀመሩ ፎርሙላዎችን በመጠቀም (ፋይናንሻል ሬሽዮ) አንዱን ድርጅት ከሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶች አንፃር ለማነፃፀር ይቻላል ማለት ነው።

የአንድ ድርጅት የፋይናንስ ውጤት መግለጫ ሪፖርቶች ሌላም ጠቀሜታ አላቸው። እንደሚታወቀው አንድ ድርጅት ቢዝነስ ሲጀምርም ሆነ በቢዝነስ ሥራ ውስጥ በየመካከሉ ተጨማሪ የስራ ማስኬጃ ሲፈልግ ከባንኮች ይበደራል። ይሁን እንጂ ባንኮች ገንዘባቸውን ከማበደራቸው በፊት ታዲያ ድርጅቱ የተበደረውን ገንዘብ በትክክል ተጠቅሞበት የሚፈልገውን የብድር መጠን በሚፈለገው የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ የሚመልስ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ። ይህን ደግሞ ማወቅ የሚችሉት በድርጅቱ የፋይናንስ አፈፃፀም መለኪያዎች ነው። እነዚህን የሚያውቁት የድርጅቱን ቢያንስ የባለፉት ሶስት አመታት የሂሳብ መግለጫዎችና የወደፊት ዓመታትን በትንበያ የሚሰሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ነው። እነዚህ የሂሳብ መግለጫዎች ታዲያ የገቢና ወጪ ሪፖርት ወይም ‹‹ኢንካም ስቴትመንት›› ፣ የሃብትና እዳ ሚዛን ማሳያ ሪፖርት ወይም ‹‹ባላንስ ሽት›› የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ማሳያ ሪፖርት ወይም ‹ካሽ ፍሎው ስቴትመንት›› እና ከእነዚህ ሁሉ የተውጣጡ ፋይናንሻል ሬሽዮዎች ናቸው።

በአጠቃላይ የአንድ ድርጅት የገንዘብ ነክ ውጤት ማሳያ ሪፖርቶች ዋና አላማቸው ለቀጣይ ውሳኔ የሚያበቁ ገንዘብ ነክ መረጃዎችን ለማቅረብ ነው። እንደሚታወቀው ከየትኛውም ውሳኔ በፊት ትክክለኛ መረጃ ያስፈልጋል። በተለይ ደግሞ በቁጥር መልክ የሚቀርቡ መረጃዎች በትክክለኛ የፋይናንስ ባለሙያዎች የቀረቡ ከሆነ ለትክክለኛ ውሳኔ የሚያበቁ ይሆናሉ። በዚህ ረገድ የድርጅቱ የበላይ አመራሮች (ቦርዱን

ጨምሮ) የድርጅቱን ውስጣዊ አፈፃፀም ስኬታማ መሆን አለመሆኑን በመረዳት በቀጣይ የሚሻሻሉ አሰራሮችን ለማሻሻል እንዲረዳቸው ያግዛቸዋል። እንዲሁም ለድርጅቱ ባለቤቶች ምን ያህል ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚችል ምን ያህልስ ካፒታላቸው እያደገ ስለመሆኑ፣ በዚህ ድርጅት ላይ በቀጣይ ኢንቬስት ለማድረግ ለሚፈልጉ ወይም ያላቸውን የሃብት ድርሻ ለመሸጥ ወይም ለማሳደግ ለመወሰን የገንዘብ ነክ ሪፖርቶቹ ከፍተኛ እገዛን ያደርጋሉ። አንድን ድርጅት ለመግዛት ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር ለመዋሃድ፣ ወይም ግዥውንም ሆነ ውህደቱን ለመሰረዝ ወይም የመግዣ ገንዘቡን የማወቅ የግድ እነዚህ ሪፖርቶች መሠረታዊ ናቸው። ከባንክ ብድር ለመውሰድ ሲፈለግም አበዳሪ ተቋማት እነዚህን ሪፖርቶች ማየት ቀዳሚው መስፈርታቸው ነው። በእርግጥ ድርጅቱ ያለበትን ተከፋይ ግብር ለማወቅና ለግብር ሰብሳቢውም ለማሳወቅ ካለእነዚህ የድርጅቱ የገንዘብ አፈፃፀም መለኪያ ሪፖርቶች የሚሆን አይደለም። በመሆኑም እነዚህን ወሳኝ ሚና ያላቸው ገንዘብ ነክ ሪፖርቶች እንደባለቤት፣ እንደአመራር፣ እንዲሁም እንደገንዘብ ተንታኝና የድርጅቱ ሠራተኞች ጭምር ምንነታቸውን ሊያውቋቸው፣ ሊያነቧቸው ፣ ለውሳኔ የሚያበቃ መረጃ ሊወስዱባቸው ያስፈልጋል። በቀጣይ እነዚህ ገንዘብ ነክ መግለጫዎች ምን እንደሆኑ እንመለከታለን።

በቅድሚያ ስለገንዘብ አፈፃፀም ማሳያ ሪፖርቶች ማለትም ‹‹ፋይናንሻል ስቴትመንት›› በመባል ስለሚጠሩት ማወቅ ያስፈልጋል። እነዚህ ሪፖርቶች በሂሳብ ባለሙያ በየሩብ አመቱ ወይም ደግሞ በየአመቱ የሚዘጋጁ የአካውንቲንግ ሪፖርቶች ሲሆኑ አላማቸውም ድርጅቱ የባለፈው ሩብ አመት ወይም ያለፈው በጀት አመት ገንዘብ ነክ አፈፃፀሙ ምን እንደሚመስል የሚጠቁሙን ሲሆኑ በተጨማሪ የድርጅቱ ሃብት ምን እንደሚመስልና ይህስ ሃብት ከምን ከም

የገንዘብ ምንጮች የተገኘ ስለመሆኑ በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህ የፋይናንስ ሪፖርቶች በድርጅቱ የሂሳብ ባለሙያዎች የሚዘጋጁ፣ ከድርጅቱ ውጭ ባሉ ገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያዎች ማለትም ኦዲተሮች እንደገና ተገምግመው የሚያልፉ ናቸው። ሪፖርቶቹ ተቀባይነት ባላቸው የአካውንቲንግ ሪፖርቶች አዘገጃጀት ደንቦች መሠረት የሚዘጋጁ ናቸው። እነዚህ በአገር ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው የሂሳብ መግለጫ አዘገጃጀት ደንቦች ከአሁን ቀደም በአገራችን ይህ ነው ለማለት ቢያስቸግርም‹‹ጋፕ›› በመባል ከሚጠራው (GAAP ሲተነተን "Generally Accepted Accounting Principles") ተቀራራቢ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በመንግስት ደረጃ የአገሪቱ የመንግስትም ይሁኑ የግል ድርጅቶች "IFRS" በሚባል "Internationally Accepted Financial Reporting System" የሚባለውን ደንብ በሚከተል መልኩ ሪፖርቶቹን እንዲያዘጋጁ የግልና የመንግስት ድርጅቶች ለሁሉም ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ መመሪያ ማውጣቱ ይታወቃል። የገንዘብ መግለጫ ሪፖርቶች የአዘገጃጀታቸው መርህ ከ "ጋፕ" ወደ " አይ ኤፍ አር ኤስ" ቢለወጥም የተወሰነ ልዩነት ቢኖረውም የሪፖርቶቹን ምንነትና አጠቃላይ ትርጉም ግን አይቀይረውም።

ውጤታማ የገንዘብ አስተዳደር እንዴት ይለካል?

አንድ የቢዝነስ አመራር ብቃቱ ሊለካ የሚችለው በድርጅቱ በገንዘብ ነክ ውጤታማነቱ ነው። በእርግጥ ገንዘብ ነክ ውጤታማነቱ ብቻውን ዘላቂ የድርጅቱ ሙሉ የአፈፃፀም ብቃት ማሳያ ሊሆን አይችልም። ገንዘብ ነክ ውጤቶችን ሊያሳኩ የሚችሉ ከገንዘብ ውጭ ያሉ ሌሎች የአፈፃፀም ብቃቶችም መሠረታዊ ናቸውና። አንድ ገበሬ ትኑ ነው የሚያስብለው በአዝመራ መሠብሰቢያ ወቅት ባመረተው የእህል ብዛት ቢሆንም ይህን ምርት ለመሰብሰብ ግን ከአስተራረስ ፣ ከማዳበሪያ ፣

ክትትሎ ፣ ከጥበቃና ምርጥ ዘር መረጣ ጀምሮ ትጋት ሊኖረው ይገባል። ምርት የመሰብሰብ ስራ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የሚሠራ በመሆኑ የአፈፃፀም ውጤታማነቱም የሚለካው በዚሁ መንገድ ነው። የመጀመሪያዎቹ ስራዎች በትክክል ካልተሰሩ የመጨረሻው ውጤት የሚያምር አይሆንም።

በተለያዩ ድርጅቶች ላይ እንደታዘብኩት ከፋይናንስ አንፃር ብዙውን ጊዜ የሚሠሩ ሥራዎች ደካማ ሲሆን የሂሳብ ባለሙያዎቹ እንደዋና ሥራ አድርገው የሚቆጥሩት የመዝገብ አያያዝና በአመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች በተለይም ለግብር አከፋፈል አንፃር የሚያደርጓቸውን አፈፃፀሞች ነው። እርግጥ ነው አንድ ድርጅት የአካውንቲንግ ደንብና ህጉን በጠበቀ መንገድ ዶክመንቶች በትክክል መያዛቸው ፣ ገቢና ወጪዎች በትክክል ቅደም ተከተል ውስጥ መጣጣማቸው ፣ የባለቤቶችና የድርጅቱ የገንዘብ አወጣጥና አገባብ መለያየታቸው (ቢዝነስ ኢንቲቲ ፕሪንሲፕል)፣ ድርጅቱም የአካውንቲንግ ደንብን በጠበቀ መልኩ የፋይናንስ ሪፖርቶች መሠራታቸው ፣ በትክክለኛው ጊዜ ተከፋይ ግብሮች መከፈላቸው መሠረታዊ ቢሆንም እነዚህ የአካውንቲንግ ስራዎች ግን መነሻ እንጂ መድረሻ አይደሉም።

መድረሻው ምንድነው?

የድርጅቱ የአካውንቲንግ ሲስተም አያያዙና አደረጃጀት በዓለም ላይ የተጨበጨበለት ቢሆንም የድርጅቱ የፋይናንስ አፈፃፀም ግን ወደ ኋላ የቀረ ከሆነ ፣ ድርጅቱ በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ ውስጥ ተወዳዳሪነቱን የሚጠቁም የእትራፊነት መጠን የማያሳይ ከሆነ፤ ኢንቬስተሮች ድርጅቱን ሲመሰርቱ ኢንቬስት ካደረጉበት ገንዘብ በላይ የላቀ ጥቅም የሚያስገኝ አፈፃፀም ከሌለው የመዝገብ አያያዝ ውበት ምን ያደርጋል? ስለሆነም የአንድ ድርጅት ሥራ አመራር ውጤታማነቱ በዋናነት

የሚለካበት ይህ የፋይናንስ አፈፃፀሙ ነው። የድርጅቱ የአካውንቲንግ ሪፖርቶች የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚጠቅሙ ግብአቶች እንጂ በራሳቸው ግብ አይደሉም።

የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ማወቅ ምን ምን ጥቅሞች ይኖሩታል?

አንድ ሠው ጤናማነቱ የሚታወቀው የጤናው ደረጃ ተመርምሮ ሲታወቅ እንደሆነ ሁሉ የአንድም ድርጅት ገንዘብ ነክ ጤናማነቱ የሚታወቀው በዚሁ መንገድ ሲለካ ነው። ይህን መሠል የገንዘብ አፈፃፀም ልኬት ድርጅቱ አሁን ላይ የፋይናንስ ደረጃው በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚጠቅመው ሲሆን እንዲሁም የወደፊቱን ገንዘብ ነክ አፈፃፀም ከዛሬው በመነሳት ለመተንበይ፤ የድርጅቱን ደካማና ጠንካራ የፋይናንስ አፈፃፀም ለመለየት፤ ከባለፉት አመታት አፈፃፀም አንፃር በምን ያህል ደረጃ መሻሻል እንደታየ እንዲሁም ድርጅቱ ከመሠል ተወዳዳሪ ድርጅቶች አንፃር በምን ያህል ደረጃ እንደተሻለ (እንዳልተሻለ) ለማወዳደር ያግዛል።

በሌላ አገላለፅ የድርጅቱን የዛሬ አፈፃፀም እንዲሁም ‹‹ቨርቲካል›› በሆነ እይታ ከድርጅቱ የትናንት አፈፃፀም አንፃርና፤ የወደፊቱንም ለመተንበይ የሚያግዝ እንዲሁም ‹‹ሆሪዞንታል›› በሆነ እይታ ከተወዳዳሪዎቹ አንፃር የት ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ያግዛል። በልኬቱ መሠረትም አስፈላጊውን ተጣይ ማሻሻያ ለማድረግ፤ ድክመትን ለመለየትና በዚህም ላይ ለመስራት ይጠቅማል። የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ማወቅ ካልቻልን ግን ይህን ሁሉ ለማድረግ አንችልም።

በመሆኑም የፋይናንስ አፈፃፀማችን የልኬት ስርአት ሊኖረው ይገባል። ይህ የልኬት ስርአት ድርጅቱ ቀድሞ ለማሳካት ካቀዳቸው ግቦች

Scanned with CamScanner

እንዳለ መረጃዎችን በመሰብሰብ ፣ በማደራጀትና እንግር ዛሬ ላይ የት በመተንተን የምናውቅበት፣ በመረጃው መሠረትም አስፈላጊውን ቀጣይ የማሻሻያ እርምጃ ለማድረግ የሚያስችል ስርአት ነው። በዚህ የልኬት ስርአት ውስጥ ወሳኝ የምንላቸው አፈፃፀም ጠቋሚዎችን ማለትም «Key Performance Indicators» ወይም «KPI» የምንጠቀም ሲሆን እነዚህ የአፈፃፀም ጠቋሚ ግቦችን እንዴት መለካት እንደምንችል የራሳቸውን የአመለካከት መርህ የምንከተል ይሆናል። ይህ «የአፈፃፀም መለኪያ ቀመር» ወይም « Performance Measure » በመባል ይጠራል። ለምሳሌ አንድ ድርጅት ከቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎች «KPI» ውስጥ «ምርታማነትን ማሳደግ» የሚል ጠቋሚ ግብ ቢያስቀምጥ፣ ይህን ስመለካት የምንችለው እንዴት ነው የሚለውን ለማወቅ አንድ ወይም ሁለት ቀመሮችን እንመርጣለን። (ለምሳሌ አመታዊ የሽያጭ መጠንን ለድርጅቱ አጠቃላይ ሃብት ማካፈል እንዱ የምንመርጠው መለኪያ ሊሆን ይችላል)። ክብደት በኪሎ ግራም ፣ ቁመት በሜትር እንደሚለካው መሆኑ ነው። በዚህም የአፈፃፀም መለኪያ ስልት ምን ያህል ቀድመን ካስቀመጥነው ግብ ላይ ደርሰናል፤ ወይም ኋላ ቀርተናል ፤ ወይም ደግሞ ከግባችን በላይ የተሻለ ፈፅመናል የሚለውን አወዳድረን ለማወቅ ያግዛል።

እንደ ድርጅት የፋይናንስ አፈፃፀሙን ስመለካት ከምን ይጀምር?

የመጀመሪያው ነገር የድርጅቱን ፋይናንስ አፈፃፀም ስኬታማነት ለመለካት ምን ምን ጉዳዮችን መለካት ይጠበቅበታል ከሚለው ነው። የድርጅቱ የፋይናንስ ውጤታማነት ከሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ይመሰረታል። የመጀመሪያው ወደ ገንዘብ ውጤት የሚወስዱ ነገሮች ራሳቸው ገንዘብ ያልሆኑ አንድ ምድብ ሲሆኑ እነዚህ ሲፈፀሙ

ደግሞ የሚመጡት ገንዘብ ነክ ውጤቶች ሁለተኛው ምድብ ናቸው። ብዙውን ጊዜ አንድ ድርጅት ከገንዘብ ነክ አፈፃፀሙ አንፃር የሚታዩት ከድርጅቱ የገንዘብ አፈፃፀም መግለጫዎች (ፋይናንሻል ስቴትመንት) በመነሳት የሚሰሉ ውጤቶች ናቸው፤ እንደ አብይ መለኪያ የሚታዩት። ማለትም ከድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ፤ ከድርጅቱ የሃብትና ሚዛን መግለጫና ከድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር መግለጫ በመነሳት የሚሠሉ የፋይናንስ ጥመርታ ውጤቶች (ፋይናንሻል ሬሽዮስ) ናቸው (ከዚህ በፊት የተገለፁ ናቸው)።

ይሁን እንጂ እነዚህ ጥመርታ ስሌቶች ምንም እንኳን ድርጅቱ ከአሁን ቀደም ካደረጋቸው ቢዝነስ ነክ ስራዎቹ ዛሬ ላይ የመጡ ውጤቶች ቢሆኑም የዛሬው ምርጥ አፈፃፀሙ የወደፊቱን የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ሊያመለክቱ ግን አይችሉም። ይህ ምን ማለት ነው፤ አንድ የድርጅቱ ሾፌር መኪና እየነዳ ካሰበበት ደረሰ፤ አደራረሱ ደግሞ በምን ያህል ፍጥነት እና በምን ያህል የነዳጅ ፍጆታ ምን ያህሉን ርቀት በምን ያህል ጊዜ ፈጅቶ እንደደረሰ ከመኪናው ዳሽ ቦርድ ላይ ማወቅ ይቻላል። ከዳሽ ቦርድ ላይ በምንወስደው መረጃ ወጪ ቆጣቢና ፈጣን በሆነ አንዳድ ከታሰበው ቦታ ስለመድረሱ መናገር ይቻላል። ይሁን እንጂ ይህ ማለት በቀጣይም ተመሳሳይ ውጤታማነት ይኖረዋል ብሎ ለመደምደም አይቻልም። የቀጣዩ ውጤት የሚወሰነው ሾፌሩ በአዲስ መልክ በሚያርገው ዝግጁነትና ቅልጥፍና እንዲሁም በመኪናው ቀጣይ ጤናማነት ብቻ ነው። ስለሆነም እነዚህም ሁለት ጉዳዮች አብረው የሚመዘኑ መሆን አለባቸው። ውጤቱን የሚወስኑትና፤ በቀጣይም የሚያስቀጥሉት እነዚህ ናቸውና።

ወደ ድርጅትም ስንሄድ የድርጅቱን የመጨረሻ ገንዘብ ነክ ውጤቶች በአመቱ መጨረሻ በምን ያህል መለካታቸው አንድ ነገር ሆኖ ሳለ ለዚህ ውጤት መሳካት ሚና የተጫወቱ የድርጅቱ ሠራተኞችና አመራሮች

Scanned with CamScanner

የሞራልና የችሎታ ብቃት እንዲሁም የድርጅቱ የተሳለጠ የቢዝነስ አሠራር ስርአትና የደንበኞችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ከድርጅቱ ጋር ለመስራት ያላቸው እርካታና ፍቅር ቀጣዩን ውጤት የሚያሳምር ወይም ደግሞ የሚያደናቅፍ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የድርጅቱን ገንዘብ ነክ አፈፃፀም (ፋይናንሻል ፐርፎርማንስ) እንመዝን ስንል የተገኘውን ገንዘብ ነክ ውጤት በአንድ በኩል መለካት የሚጠበቅብን ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ወደዚህ ውጤት ለመብቃት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ድርጅታዊ ጉዳዮችንም አብረን መመዘንና በምዘና ውጤቱም መሠረት አስፈላጊውን ቀጣይ ማሻሻያ ለማድረግ መዘጋጀት ይኖርብናል፡፡ ለገንዘቡ ውጤታማነት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ልዩ ልዩ ድርጅታዊ ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥተን የምንለካቸው ከሆነ የእነሱ ደካማ መሆን የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም ደካማ ያደርገዋል፡፡ የእነሱ ጠንካራ መሆን የድርጅቱን የፋይናንስ አፈፃፀም የተዋጣለት ያደርገዋል፡፡ እነዚህ ከገንዘብ ውጭ ያሉ ነገሮችን ለገንዘቡ የአፈፃፀም ውጤታማነት ከፍተኛ ሚና ያላቸው ድርጅታዊ ጉዳዮች ‹‹ኢንታንጀብል አሴት›› በመባል ይጠራሉ፡፡ ስለሆነም ልኬቱ በገንዘብ ላይ ብቻ በማነጣጠር ሌሎችን ችላ እንዳይል ሁለቱንም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚመለከት መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይህ መሠል የአፈፃፀም ልኬት ስርአት ‹‹ባላንስድ ስኮርካርድ›› በመባል የሚጠራ ሲሆን በዶ/ር አቡሽ አያሌውና በባልደረቦቹ የተዘጋጀውን የባላንስድ ስኮርካርድ መፅሐፍ ለበለጠ ግንዛቤ ማንበብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ምን ምን ጉዳዮች በልኬቱና ግምገማው ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል?

በዋናነት የምንመለከተው የድርጅቱን የተወዳዳሪነት ብቃቱንና ይህም የሚገለፅባቸውን ነው፡፡ የአንድ ድርጅት የተወዳዳሪነት ብቃት በገበያ ላይ ባለው ተመራጭነቱ ላይ ይመሠረታል፡፡ ደንበኞች ከሌሎች

ተወዳዳሪዎች በተሻለ ድርጅቱን በምን ያህል መጠን ሊመርጡት እንደቻሉና እንደማይችሉ ለማወቅ የምንችለው ድርጅቱ በገበያ ላይ ባለው ተዕፅኖ ፈጣሪነቱ ማለትም ‹‹ማርኬት ፓወር›› እና ድርጅቱ ባመጣው የላቀ ትርፋማነቱ ማለትም ‹‹አባቭ አቬሬጅ ፕሮፊት›› ነው፡፡ በመሆኑም በአንድ በኩል ፋይናንስ ነክ ውጤቱ በሌላ በኩል ደግሞ የገበያ ድርሻው አብይ የቢዝነስ አሠራሩ ፍሬዎች ሲሆኑ እነዚህን ለማምጣት ድርጅቱን ለተመራጭነት ይበቃ ዘንድ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ (የስኬት መዘውር) በመባል የሚጠሩት የድርጅቱ የአሠራር ሂደት ማለትም (ፕሮሰስ) እና ድርጅታዊ የሠራተኞችና አመራር የአፈፃፀም ባህል ፍሬዎቹን የሚያስገኙልን ግንድና ስር ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሁለት የስኬት መዘውሮች፣ ገበያ ነክና ፋይናንስ ነክ የስኬት ፍሬዎችን ያስገኛሉ ማለት ነው፡፡ ሁለቱ የስኬት መዘውሮች በጣም ጥሩ ደረጃ ላይ መኖራቸውን ልኬቱ ካረጋገጠ እነዚህን ተከትለው የሚመጡት ሁለቱ ፍሬዎች በጥሩ ውጤት እንደሚሳኩ መተማመን ይቻላል፡፡ ሁለቱ ፍሬዎች በጥሩ ስኬት ላይ መገኘታቸው የሚያመላክተው ካሁን ቀደም ሁለቱ የስኬት መዘውሮች በጥሩ ሁኔታ መፈፀማቸውንም ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሁለቱ ፍሬዎች ‹‹ላጊንግ ኢንዲኬተርስ›› በመባል ሲጠሩ ሁለቱ የስኬት መዘውሮች ደግሞ ‹‹ሊዲንግ ኢንዲኬተርስ›› በመባል ይጠራሉ፡፡

የሚለኩት ጉዳዮችን በዚህ መልክ ካስቀመጥን በቀጣይ መደረግ ያለበት ከእነዚህ አራት አጠቃላይ ጉዳዮች ማለትም ሁለት የስኬት ውጤቶች (ፍሬዎች) እና ሁለት የስኬት መዘውሮች ውስጥ እያንዳንዳቸው ቢያንስ አራት አራት ቁልፍ የሚባሉ የአፈፃፀም ስኬትን የሚያሳዩ ጉዳዮች ማለትም ‹‹ኪይ ፐርፎርማንስ ኢንዲኬተርስ›› እንለያለን፡፡ እነዚህንም በግብ መልክ እናስቀምጣለን፡፡ ለምሳሌ ‹‹የሜዲያክ ኩባንያ የ2011ዓ.ም ተፈፃሚ ቁልፍ ግቦች›› በሚል በቁጥር የሚገለፁ ፣ በጊዜ

Scanned with CamScanner

ገደብ የሚቀመጡ ፣ ሊለኩ የሚችሉ ፣ ሊደርስባቸው የሚችሉ ግቦችን እንቀርፃለን። እነዚህን ቢያንስ አስራ ስድስት የሚደርሱ ልዩ ልዩ ተፈፃሚ ግቦችም በየሩብ አመቱ በምን ያህል መጠን እንደተፈፀሙ ወደ መለካት እናመራለን። በየወሩና በየሳምንቱ የሚለኩ ግቦችም ይኖራሉ። በዚህ ደረጃ የድርጅቱን የአፈፃፀም ስርአት ዘረጋን ማለት ይሆናል።

ከዚህ በመቀጠል ይህን የክትትልና ግምገማ ስራ በኃላፊነት ሊሠሩ የሚችሉ ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ ኃላፊነትን በመስጠት እንዲሠሩ ማድረግ የሚቻል ሲሆን በተቀመጠው የልኬት ጊዜ ሠሌዳ መሠረት ግቦቹ በምን ያህል የአፈፃፀም ደረጃ እየተሳኩ ስለመሆናቸው፤ የትኛው ዲፓርትመንት ወይም ክፍል ከየትኛው ዲፓርትመንት (ክፍል) የተሻለ ስለመፈፀሙ፤ የትኛው ቡድን ወይም ግለሰብ የተሻለ አፈፃፀም እንዳለው ፤ የትኛውስ እንዳልተሻለ ለመለየት ይቻላል።

ይህን ለማድረግ ታዲያ በቅድሚያ እያንዳንዱን ልኬት የሚመለከት የአፈፃፀም መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል። አንድን ነገር ለመለካትና በትክክልም ለመገምገም መረጃ (ዳታ) ላይ መንተራስ የሚያስፈልግ ሲሆን ተሰብሳቢ ዳታውም በበቂ ሁኔታ የተሰበሰበ ፣ የተደራጀና የተተነተነ መሆን ይጠበቅበታል። ከእነዚህ መረጃዎች የተገኘውን የልኬት ውጤትም በግራፍ መልክ የአፈፃፀም ደረጃውን ማሳየት የሚቻል ሲሆን ውጤቱ ቀድሞ እናሳካለን ተብሎ ከተቀመጠው ግብ አንፃር በምን ያህል ፐርሰንት እንደተፈፀመ ልዩነቱን ማነፃፀርም ያስፈልጋል። እንዲሁም ካለፈው አመት ተመሳሳይ ወር ወይም ሩብ አመት ወይም የአመቱ መጨረሻ ውጤት አንፃር የዘንድሮው ውጤት በምን ያህል እንደተሻሻለ ወይም እንዳልተሻሻለ ማወዳደር ያስፈልጋል። ይህ ብቻ አይደለም በዘርፉ ውስጥ ካሉ ተመሣሣይ ተወዳዳሪ ድርጅቶች አፈፃፀም አንፃር በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከዘርፉ ከሚገኙ ተሰብሳቢ ዳታዎች አንፃር ማወዳደር ይቻላል። ስለሆነም መረጃ መር ድምዳሜ ላይ

የምንደርስባቸው ሶስት የአፈፃፀም ግምገማ ውጤቶች አሉ ማለት ነው፤ የምንደርስባቸው ከቀድመን ካስቀመጥናቸው ግቦች አንፃር፤ ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ጊዜ አፈፃፀም ጋር እንዲሁም በዘርፉ ውስጥ ካሉ መሠል ተወዳዳሪ ድርጅቶች ጋር። ይህንንም የልኬት ውጤትና ድምዳሜ ከበላይ አመራር ጀምሮ ሁሉም ዲፓርትመንትና በሁሉም ዲፓርትመንት ውስጥ ያሉ ሠራተኞች እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል።

ከዚህ መሠል መረጃ መር ድምዳሜና ንፅፅር በኋላ በቀጣይ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ምን አይነት እርምጃዎችን በመውሰድ ቀጣይ የአፈፃፀም ማሻሻያዎች ያስፈልጋሉ የሚል ውሳኔ ነው። አራቱን ዋና ዋና ተፈፃሚ የውጤት ማሳያዎችና በእያንዳንዱ ውስጥም ያሉትን ግቦች እንዴት እየሠራን እንደምንገኝ ፣ የትኞቹስ ላይ ወደኋላ እንደቀረን የምንረዳ ሲሆን ጥንካሬዎቻችንን የበለጠ ለማስቀጠል፤ ደካማ በሆንባቸው ላይ ደግሞ የበለጠ ለመሻሻል የሚያስችል እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። በጣም ጥሩ ውጤቶችን ብናሳካ እንኳን በቂ ነው በሚል አሳቤ ሳንዘናጋ የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል መሻሻል ማድረግ ይጠበቅብናል። መለወጥ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ፣ በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎችም ሰዎችን በኃላፊነት በመመደብ፤ የማሻሻያ ወይም የለውጥ እርምጃውም በትክክል እየተከናወኑ ስለመሆናቸው በመከታተል ማሻሻያውን ተፈፃሚ ማድረግ ይቻላል። እንዲሁም ስልጠና ለሚያስፈልጋቸው ሠዎች ወይም ክፍሎች ተጨማሪ የስልጠናና የማበልፀጊያ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በተመሳሳይ መልኩ ጥሩ ደረጃ ለፈፀሙ ደግሞ የማበረታቻ ሽልማትን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ አፈፃፀምን መሠረት ያደረጉ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችና ማበረታቻዎች ቀጣይ አፈፃፀሙን ወደተሻለ ደረጃ ይወስዱታል።

Scanned with CamScanner

ይህ መሠል አሠራር ምድር በፀሐይ ላይ እንደምትዞረው ሁሉ ማቆሚያ የለውም:: ግብ መቅረፅና የአፈፃፀም እቅድ ማውጣት፣ ግቡን ለማሳካት በእቅዱ መሠረት መፈፀም፣ የተፈፀሙትን ስራዎችና ውጤቶች መለካት፣ በቁልፍ ውጤት ጠቋሚ ግቦች ላይ የተንተራሰ ውጤቶች መለካት፣ በቁልፍ ውጤት ጠቋሚ ግቦች ላይ የተንተራሰ መረጃ መር የልኬት ግምገማና ንፅፅር ማድረግ፣ በግምገማ ድምዳሜው መሠረት ቀጣይ የማሻሻያ የለውጥ እርምጃ የመውሰድ እንዲሁም ሽልማቶችን ማድረግ ድርጅቱ እስካለና እስከሠራ ድረስ የሚፈፀሙ የማያባሩ ሽክርክሪቶች ናቸው:: ይህ ሲሆን ነው የድርጅቱ ገንዘብ ነክ ግቦች በየጊዜው እየተሻሻሉና እያደጉ የሚቀጥሉት:: የባለቤቶች ሃብትም በየጊዜው ሊያድግ የሚችለው ይህን መሠል ተራማጅና እንደ ውጫዊው ነባራዊ ክስተት ተለማጭ አሠራርን ገቢራዊ በማድረግ ነው። ይሁን እንጂ በፋይናንሻል ሪፖርት ላይ ብቻ የተንተራሱ ገንዘብ ነክ ውጤቶችን ያውም በበጀት አመቱ መጨረሻ ላይ ብቻ እየለኩ ዘላቂነቱን የጠበቀ አፈፃፀም እውን ለማድረግ አይቻልም:: በመሆኑም የአፈፃፀም ልኬት ስርአቱን ከድርጅቱ ራዕይና ስትራቴጂ ጋር በማስተሳሰር ያለማቀድ፣ ገንዘብ ነክና ከገንዘብ ውጭ ያሉ ግቦችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አለመቅረፅ፣ አስፈፃሚ ግቦችን በየአመቱ ከማሳደግ ይልቅ በዚያው ቋሚ ማድረግ ፣ በተፈፀሙ ግቦች ላይ የተንተራሰ ልኬትን አለማድረግና በልኬቱ ውጤት መሠረት በየጊዜው አዳዲስ የአሠራር ፈጠራዎችንና የማሻሻያ እርምጃዎችን አለመውሰድ ማለት በየጊዜው ሠርቪስ እንደማይደረግለት መኪና አንድ ቀን ድርጅቱም በከባድ ጉዳት መቆሙ ወይም ከቢዝነሱ መውጣቱ አይቀርም::

የፋይናንስ ማኔጅመንትና የአካውንቲንግ ሪፖርቶች ትስስር

- የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት *(Income Statment)* ምንድነው? እንዴት ይዘጋጃል? እንዴትስ በቀላሉ እንብቦ መረዳት ይቻላል?
- የሐብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት *(Balance sheet)* ምንድነው? እንዴት ይዘጋጃል? እንዴትስ አንብቦ በቀላሉ መረዳት ይቻላል?
- የጥሬ ገንዘብ ሚዛን መግለጫ ሪፖርት *(cash flow)* ምንድነው? እንዴትስ በቀላሉ አንብቦ መረዳት ይቻላል?

Scanned with CamScanner

የሃብትና ዕዳ ሚዛን መግለጫ

(Balance sheet)

በተለመደው የአካውንቲንግ ስያሜው ‹‹ባላንስ ሽት›› በመባል የሚጠራ ሲሆን ከስሙ እንደምንረዳው የአንድን ድርጅት የኢንቬስትመንት መጠን፣ የኢንቬስትመንቱን ምንጮችና ኢንቬስትመንቱ በምን በምን መልኩ ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሚገኝ የሚጠቁመን ሪፖርት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድን ድርጅት እንውሰድ፤ ‹‹ሚዲያክ›› የተባለውን የግል ድርጅት በአዲስ መልክ ሲቋቋም የኢንቬስትመንት ካፒታል ያስፈልገዋል፤ ለምሳሌ 130 ሚሊየን ብር አስፈለገው እንበል፡፡ ከዚህ ውስጥ ባለቤቶቹ 22 ሚሊየን ብር ሸፈኑ፤ ቀሪውን 108 ሚሊየን ብር ደግሞ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አበደራቸው፡፡ ስለዚህ የዚህ ድርጅት አጠቃላይ የኢንቬስትመንት ካፒታል 130 ሚሊየን ብር ሲሆን፣ ይህ ሃብት ግን የተገኘው 22 ሚሊየኑ ከባለቤቶቹ፤ 108 ሚሊየኑ ደግሞ በእዳ መልክ ነው፡፡ የድርጅቱ 130 ሚሊየን ብር አጠቃላይ ሃብት ሲሆን በልዩ መጠሪያው ‹‹አሴት›› በመባል የሚታወቅ ሲሆን የባለሃብቶቹ 22 ሚሊየን ብር ደግሞ በባለቤቶች የተከፈለ ካፒታል ወይም ‹‹ኦውነርስ ኢኩይቲ›› በመባል ይጠራል፡፡ በእዳ መልክ የተገኘው (ተከፋይ ዕዳ) ደግሞ ‹‹ክሬዲተርስ ኢኩይቲ›› በመባል ይጠራል፡፡ እነዚህን ስያሜዎች በደንብ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

ወደ አጠቃላይ የድርጅቱ ሃብት ወይም ‹‹አሴት›› ስንመለስ ይህ የተመደበ ካፒታል ማለትም 130 ሚሊየን ብር ወደ ሥራ ሲውል በምን በምን ላይ ገንዘቡ እንደዋለ ያመላክተናል፡፡ ለምሳሌ ድርጅቱ አምራች ከሆነ በዚህ ገንዘብ መሬት፤ ማሽነሪና ጥሬ እቃዎች ገዝቶበት ሊሆን ይችላል፡፡ ቀሪው ገንዘብ ደግሞ ባንክ ሊኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ ‹‹ሚዲያክ›› ድርጅት ስራውን ሲጀምር የአሴት (አጠቃላይ ሃብቱ) በእነዚህ ሶስት

ጉዳዮች ላይ እንደዋለ ሊያሳየን ይችላል፡፡ እነዚህ ወጭዎችም በዚሁ ሥር ይመዘገባሉ፡፡

የሃብትና ዕዳ መግለጫ ማለትም ባላንስ ሽት አንድ ጊዜ የሚሠራና ለወደፊትም የሚሆን ሪፖርት ነውን?

አንድ ጊዜ የሚሠራና ቋሚ ሆኖ የሚቀጥል አይደለም፡፡ እንደሚታወቀው በየጊዜው የድርጅቱ እንቅስቃሴ ውስጥ ባንክ ያለው ጥሬ ገንዘብ ጥቅም ላይ እየዋለ፤ ድርጅቱም ምርቱን እየሸጠ ተጨማሪ ትርፍ እያገኘ ይቀጥላል፡፡ እንዲሁ ደግሞ መጀመሪያ ከነበረው የባንክ ተከፋይ እዳ በተጨማሪ ከአቅራቢዎች በዱቤ ወይም ደግሞ ተጨማሪ ብድር ከባንክ ሊወስድ ይችላል፡፡ ሁለቱም የመጀመሪያውን የእዳ መጠን ከፍ ያደርጉታል፡፡ ድርጅቱ በሽያጭ መልክ ያልሰበሰባቸው ገቢዎች ይኖሩታል፤ እነዚህም የድርጅቱ ያልተሰበሰቡ ሃብቶች(አሴት) ማለት ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መጀመሪያ ከገዛቸው ማሽነሪዎች ውጭ ተጨማሪ ማሽን ሊገዛ ይችላል፡፡ በአመቱ መጨረሻ ግብር ተከፍሎበት የመጣው ትርፍ ደግሞ ተጨማሪ የሃብት ምንጭ ሲሆን እዚህ ጋር ከአንድ አመት በላይ ለድርጅቱ ጥቅም የሚሰጡ ሀብትና ንብረቶች ብቻ ሳይሆኑ በተለያየ ምክንያት ከሥራ ውጭ ሆነው በመጋዘን የተቀመጡ ወይም ለሽያጭ የቀረቡም ጭምር በዚህ ስር ይመደባሉ፡፡ ንብረቶች በጊዜ ሂደት እያረጁ ይመጣሉ፤ የትኛውም ነገር በጊዜ ውስጥ እንደሚያረጀው ሁሉ፡፡ ይህን በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚፈጠር የንብረቶች እርጅና ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ‹‹ዲፕርሴሽን›› በመባል የሚጠራ የእርጅና ተቀናሽ ማስሊያ መንገድ አለ፡፡ የተለያዩ ንብረቶች የተለያየ የእርጅና ማስሊያ መንገድ አላቸው፤ ለምሳሌ አንድ መኪና በየአመቱ ከዋጋው ላይ 20 በመቶ ያረጃል፡፡ ይህም ማለት መኪናው የገዛነበትን ዋጋ ያህል በ5 አመት ውስጥ ያረጃል፡፡ ለምሳሌ በሁለት ሚሊዮን ብር የተገዛ ቪያኖ

Scanned with CamScanner

መርሰዲስ መኪና በአመቱ 20 በመቶ ማለትም በ400 ሺህ ብር ያህል ያረጃል። ይህም ማለት በአምስተኛ አመት መጨረሻ ላይ የመኪናው የመዝገብ ላይ ዋጋው ዜሮ ብር ይሆናል።

ይህ ጥቅሙ ምንድነው?

ንብረቶች ባሉበት አይቀጥሉም። በየአመቱ የእርጅና ተቀናሽ ማሰቡ ድርጅቱ በዚህን ያህል ገንዘብ ለንብረቶቹ እድሳት ወጭ ሊያደርግ ከመቻሉም ባሻገር የንብረቶቹ ውጤታማነትም እየተዳከመ ስለሚመጣ የአዲስነታቸውን ያህል ጥቅም አይሰጡም የሚል መልእክት ነው ያለው። በየአመቱ ያን ያህል ገንዘብ ቢያስወጡም ይህን ያህል ወጪ ግን ሊኖራቸው ይችላል የሚል ነው። ይህ አስተሳሰብ ታዲያ በረዥም ጊዜ ንብረትነት *(Long Term Asset)* ስር የተመዘገቡ ንብረቶች በየአመቱ በእርጅና ተመናቸው ልክ ቅናሽ ይኖራቸዋል ለማለት ነው። ለምሳሌ ‹‹ሜዲያክ›› ኩባንያ የገዛው ኮሮላ ሲገዛ 400 ሺህ ብር ሲሆን በበጀት አመቱ መጨረሻ ግን 320 ሺህ ብር ነው በሪፖርቱ ላይ የሚመዘገበው። በሁለተኛው አመት ደግሞ ከዚህ ሌላ 80 ሺህ ብር ይቀንሳል ማለት ነው። ተቀናሹ እንደየንብረቱ አይነት ይለያያል። ለምሳሌ ህንፃ ከሆነ በአመቱ የሚቀንሰው ከመጀመሪያው ተመዝጋቢ ተመን ላይ 5 በመቶ ብቻ ነው። ይህም ማለት አንድ ህንፃ በአሴት ምዝገባው ላይ ማለትም ‹‹ቡክ ቫልዩ›› 10 ሚሊዮን ብር ዋጋ ቢኖረው፣ በአመቱ 5 በመቶ እየተቀነሰለት ሂዶ በ20ኛው አመት ላይ መዝገቡ ላይ የሚሰፍረው ዋጋው ዜሮ ይሆናል ማለት ነው።

የመዝገብ ዋጋ ምን ማለት ነው?

የአንድ ድርጅት ንብረት ሁለት አይነት ዋጋ አለው። የመጀመሪያው የመዝገብ ዋጋው በአካውንቲንግ መጠሪያ ስያሜው ‹‹ቡክ ቫልዩ››

ሲባል ለምሳሌ የህንፃው የ20ኛ አመቱ ዋጋው ዜሮ ብር ነው። ይህ ማለት ግን ህንፃው ሙሉ በሙሉ ዋጋ ቢስ ሆነ ማለት አይደለም። በንብረት እርጅና ተቀናሽ ህግ መሠረት መዝገቡ የሚያውቀው ህንፃው አገልግሎቱን እንደጨረሰ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ህንፃ በጨረታ ይሸጥ ቢባል መቶ ሚሊዮን ብር ሊሸጥ ይችላል። ምክንያቱም የገበያ ሽያጭ ዋጋው በማደጉ ነው። ይህ ገበያ የሰጠው የህንፃው ዋጋ የባለቤቶቹን የሃብት ድርሻ ‹‹ኢኩይቲ›› ያሳድጋል። ስለሆነም የድርጅቱ ገንዘብ ነክ እንቅስቃሴ በእያንዳንዷ ቀን የሚቀያየር በመሆኑ የሃብትና እዳ ሚዛን መግለጫ ሪፖርቱም ሶስት ክፍሎች ማለትም ‹‹አሴት›› ፣ ‹‹ሊያቢሊቲ›› እና ‹‹ካፒታል›› በየቀኑ ይቀያየራሉ ማለት ነው።

ለምሳሌ በ ‹‹ሜዲያክ›› ድርጅት በአሴት ስር ተመዝግበው የነበሩ የጥሬ እቃዎች የገንዘብ ተመን ጥሬ እቃዎቹ በስራ ላይ ውለው ከፊሎቹ ብቻ ቀርተው ሊሆን ይችላል። የተመረቱና ተሸጠው ያልተሰበሰቡም እንደዚሁ። ስለሆነም ባላንስ ሽት ውስጥ ያሉ ሶስቱ አቢይ ክፍሎች ተቀያያሪ መሆናቸውን ማወቅ የሚገባ ሲሆን ‹‹ታይምሊነስ›› በተባለው የአካውንቲንግ መርህ መሠረት አንድ የባላንስ ሽት ሪፖርት የተሰራው በየካቲት 15/2010 ዓ.ም ከሆነ ይህ መግለጫ የሚያገለግለው በዚህ ቀን ላይ ያለውን የድርጅቱን የሃብት የገንዘብ ተመን ሁኔታ ብቻ ነው የሚሆነው።

የሃብትና እዳ ‹‹ባላንስ ሽት›› መግለጫ ምን ምን ነገርችን ይይዛል?

ሶስቱን ጉዳዮች ሲሆን ማለትም ሃብት(አሴት) ፣ ተከፋይ ዕዳ(ሊያቢሊቲ) እና የባለቤቶች የተከፈለ ካፒታል መጠን (ኢኩይቲ) ሲሆን እያንዳንዳቸውም በየራሳቸው የሚከተሉትን ይይዛሉ፤

Scanned with CamScanner

1ኛ. ሃብት(Asset)፡- የምንላቸው ለአጭር ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ *(Current Asset)* እና ለረዥም ጊዜ አገልግሎት የሚሰጡ *(Long Term Asset)* በማለት ለሁለት እንከፍላቸዋለን። ለአጭር ጊዜ አገልግሎት የሚሰጡ ሃብቶች የምንላቸው በአንድ የበጀት አመት ውስጥ ወደ ጥቅም ለመዋል ወደገንዘብ ሊቀየሩ የሚችሉ ናቸው። እነዚህም ጥሬ ገንዘቦች (በባንክ ወይም በእጅ ላይ ያሉ) ‹‹ኢንቬንተሪ›› ፤ ተሸጠው ያልተሰበሰቡ ገንዘቦች (አካውንት ሪሲቬብልስ)፤ የእቃ ክምችቶች (ጥሬ እቃዎች፣ በመመረት ላይ ያሉና ተመርተው ያለቁ ሸቀጦች ክምችት) በአካውንቲንግ እንዲሁም ቀድመው የተከፈሉ ገንዘቦች (የቀብድ ክፍያ፣የኪራይ ክፍያና የኢንሹራንስ ክፍያ) በመባል የሚጠሩ ናቸው።

እንዲሁም ለረዥም ጊዜ አገልግሎት የሚሠጡ ሃብቶች *(Long Term Assets)* የምንላቸው ደግሞ ከአንድ አመት በላይ ለሆነ ጊዜ ግልፅ ጥቅም ለድርጅቱ መስጠት የሚችሉ ማለታችን ነው፤ ይህም ለ ‹‹ሚዲያኮ›› ድርጅት የተገዙ ማሽነሪዎችን፣ መኪናዎችን፣ የቢሮ እቃዎችንና ሌሎችንም ከአመት በላይ ማገልገል የሚችሉ ንብረቶችን ሁሉ ይመለከታል። እንዲሁም አንድ ሁለት በማለት ልንቆጥራቸው የማንችላቸው ነገርግን የንግዱን ተወዳዳሪነት የሚጨምሩ የንግድ የፈጠራ መብት(ፓተንት)፣ የቅጅ መብት(ኮፒ ራይት) ሁሉ በዚህ ሥር የሚካተቱ ሲሆን አንድ ድርጅትም ሲመሠረት ሥራውን ለመጀመር የወጣባቸው ዋጋ እንጂ ትክክለኛ የገበያ ላይ የአገልግሎት ዋጋቸው አይደለም። ይህ መሠሉ የገበያ ተመን ዋጋ በአካውንቲንግ መጠሪያ ስያሜው ‹‹ማርኬት ቫልዩ›› በመባል ይታወቃል። ለምሳሌ በ ‹‹ሚዲያኮ›› ድርጅት በ20ኛ አመቱ ዜሮ ብር ተብሎ በመዝገብ ላይ የሠፈረን ንብረት ሌላ ገዥ ድርጅት ንብረቱን በገዛው እለት የሀንዛው ዋጋ በመቶ ሚሊዮን ብር ተብሎ በድርጅቱ በረጅም ጊዜ የሃብት አይነት ዝርዝር ውስጥ ያካትተዋል። ይህም የሚያሳየው ለሻጩ ድርጅት የመዝገብ

ዋጋው ዜሮ ብር የሆነ ንብረት በገዥው ድርጅት የሂሳብ መዝገብ ላይ በዚያው ዕለት 100 ሚሊዮን ብር ይሆናል።

ስለሆነም የአንድ ድርጅት የረዥም ጊዜ ሃብት የምንላቸው ንብረቶች *(Long Term Assets)* ወደ መዝገቡ የሚገባው የተጣራ ተመናቸው ነው፤ ማለትም በየአመቱ የእርጅና ተቀናሻቸው እየተነሳላቸው ነው። ይህ የተጣራ ንብረት ወይም *‹‹Net Asset››* በመባል ይጠራል፤ ወይም *‹‹Net Long term Asset››* ይባላል።

ከዚህ ባሻገር የእርጅና ተቀናሽ ወጭ ምንም እንኳን ድርጅቱ በየአመቱ ምን ያህል ገንዘብ ወጭ ባያደርገውም ድርጅቱ እንደ ወጪ ግን ሊይዘው ይችላል። በመጨረሻም ግብር ተቀናሽ ሊደረግለት ይችላል። ይህን በድርጅቱ ገቢና ወጪ ሪፖርት ወይም በትርፍና ኪሳራ ሪፖርት (ኢንካም ስቴትመንት) ላይ በቀጣይ የምንመለከተው ይሆናል። የእርጅና ተቀናሽ ገንዘብ እንደገና በድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር መግለጫ ሪፖርት (ካሽ ፍሎው ሪፖርት) ላይም የሚጫወተው ሚና ያለ በመሆኑ በዚህ ላይ ስንመጣ እንመለከተዋለን። ዋናው በዚህ ክፍል ግን በድርጅቱ አሴት ስር ያለው የሎንግ ተርም አሴት ዝርዝር ውስጥ ያሉ ንብረቶች በየአመቱ የእርጅና ተቀናሽ ተመን ማለትም ‹‹ዲፕርሲሽን›› የሚታሰብላቸው መሆኑና ትክክለኛ ተመናቸውም በአመቱ ይህ ተቀንሶ ያለው መጠን መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው አቢይ የባላንስ ሸት ክፍል ‹‹ሊያቢሊቲ›› በመባል የሚጠራው ሲሆን ይህም ‹‹ተከፋይ እዳ›› የሚለውን ይወክላል። ይህም ተከፋይ እዳ ልክ እንደ አሴት ሁሉ የአጭር ጊዜ *(Shor Term Liability)* እና የረዥም ጊዜ ተከፋይ እዳ *(Long Term Liabilit* በመባል ይጠራል። የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳ ማለት በአንድ የበጀ አመት ውስጥ ሊከፈል የሚገባ ማለት ሲሆን የረዥም ጊዜ ተከፋይ እ ማለት ደግሞ ከአንድ አመት በላይ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሊከፈል የሚገ

Scanned with CamScanner

እዳ እንደማለት ነው።

የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳዎች ማለት ድርጅቱ በቀጣይ አንድ የበጀት አመት ውስጥ ሊከፍላቸው የሚገቡ በዱቤ የተገዙ የአቅራቢ ተከፋይ ገንዘቦች፣ ድርጅቱ ከባንክ ለረዥም ጊዜ ተበድሮ ነገርግን በቀጣይ አንድ የበጀት አመት ውስጥ ብቻ ከዚህ የብድር እዳ ላይ የሚከፈለውን መጠን ያካትታል። እንዲሁም ያልተከፈሉ ውዝፍ እዳዎች (ከባለፈው አመት ወይም ወር ወዲህ የተሻገሩ) በተለይም ያመዝገብና ግብር እንዲሁም ሥራው ሳይሠራ ቀድሞ ከደንበኞች የተከፈለ (ቀብድ) በዚህ ስር ይመዘገባሉ። የዚህ ክፍል ዋና ባህሪው በቀጣይ አንድ በጀት አመት ውስጥ ብቻ ሲከፈሉ የሚገባቸውን እዳዎች የሚያሳይ መሆኑ ነው።

> የበጀት አመት የሚለው ስያሜ በአሴት (ሃብት) መዝገብም ውስጥ ሆነ በእዳ (ሊያቢሊቲ) መዝገብ ውስጥ ሃብትና እዳን፣ የአጭርና የረዥም ጊዜ በማለት ከፍሎት ይታያል። ለምን ሁለት አመት ወይም አንድ አመት ተኩል ጊዜን እንደመለያ አንጠቀምም?

አንድ ድርጅት በጀት ሲይዝ፣ ሂሳብ ሠርቶ ግብር ሲከፍል እንዲሁም የሥራ አፈፃፀሙ የአሁኑን ከባለፈው ጋር ሲያነፃፅር ሊጠቀመው የሚገባ የጋራ መግባቢያ ጊዜ ያስፈልጋል። ይህም በዓለም ደረጃ እንደ መግባቢያ ጊዜ የሚወሰደው አንድ አመት ነው። በእርግጥ ዘመንም ሲቆጠር፣ እድሜያችንም ሲቆጠር ይህን አንድ አመት ታሳቢ ያደረገ ነው። እንዲት አገርም በጀት ስትይዝ አንድ የሥራ አመትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ድርጅቶች የአንድ አመት በጀታቸው ምን ያህል እንደሆነ የቀጣዩን የሥራ አመት ታሳቢ ያደረገ ተመን ይተምናሉ። ይህ በተለይ በልዩ መጠሪያው ‹‹የሥራ ማስኬጃ ካፒታል›› ወይም

‹‹Working Capital›› በመባል የሚጠራ ሲሆን የአንድ ድርጅት የአንድ አመት የተጣራ ካፒታል ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ፤ ለአንድ አመት ያህል ያሉንን ‹‹ሾርት ተርም አሴት›› (የአጭር ጊዜ ሃብት) ላይ ተከፋይ የሚሆኑ የአንድ አመት እዳዎች (የአጭር ጊዜ እዳ) ማለትም ‹‹ሾርት ተርም ሊያቢሊቲ›› በመቀነስ የሚገኝ ነው። ማለትም በአንድ አመት ውስጥ ጥሬ ገንዘብ በቀላሉ የሚቀየሩ ሃብቶቻችን ምን ያህል በአንድ አመት ውስጥ ተከፋይ የሚሆኑ እዳዎችን ይሸፍናሉ የሚለውን ይመልሳል። እንደሚከተለው እንየው፡-

የተጣራ ሥራ ማስኬጃ ገንዘብ = የአጭር ጊዜ ሃብት - የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳ

ቀመሩ የሚያሳየው በአንድ አመት ውስጥ ወደ ገንዘብ የሚቀየሩ ‹‹ሾርት ተርም አሴቶች›› ምን ያህል በዚያው የበጀት አመት ውስጥ ሊከፈል የሚገባውን እዳ ይሸፍናሉ የሚለውን ነው። ውጤቱ ኔጌቲቭ ከሆነ ያን ያህል መጠን ገንዘብ ድርጅቱ በተጨማሪነት ሊያገኝ ይገባል (ከባለቤቶች ወይም ከባንክ ብድር) የሚለውን የሚጠቁመን ሲሆን እንዲሁ ደግሞ ውጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ ድርጅቱ ያለበትን እዳ ባለው ገንዘብ ለመሸፈን ከበቂ በላይ አቅም አለው እንደማለት ነው። ለምሳሌ የ ‹‹ሚዲያክ›› የአጭር ጊዜ የሂሳብ መግለጫ የሃብት ሪፖርት (Current Asset) 22 ሚሊዮን ብር ቢሆን፣ የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳው (Current Liabilty) 35 ሚሊዮን ብር ቢሆን ከላይ ባለው ቀመር መሠረት፤

የተጣራ ስራ ማስኬጃ = የአጭር ጊዜ ሃብት - የአጭር ጊዜ እዳ

= 22,000,000 - 35,000,000

= -13,000,000

ይህ የሚያሳየን ድርጅቱ በቀጣይ በጀት አመት በአጭር ጊዜ ሃብትነት አሉኝ የሚላቸው ጥሬ ገንዘቦች፣ የእቃ ክምችቶችና ለደንበኞች ተሸጠው

Scanned with CamScanner

ያልተሰበሰቡ ገቢዎች ሁሉ ተደምረው ካለው ተከፋይ ዕዳ መጠን በታች መሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም ‹‹ሚዲያክ›› የ13 ሚሊዮን ብር የሥራ ማስኬጃ ጉድለት ስለሚኖርበት ከወዲሁ ሊያስብበት እንደሚገባ የባላንስ ሽት ሪፖርቱ ይጠቁመዋል ማለት ነው፡፡

የተጣራ ሃብት ነው በማለት ታሳቢ የሚያደርጉት፣ የድርጅቱ የባንክ እዳ፣ ውዝፍ የግብርና የደመወዝ እዳ እንዲሁም በዱቤ ከድርጅቱ የተገዙ እቃዎችና ንብረቶችን ሳይከፍሉ ይህ ሁሉ የእኔ ነው ማለት አይቻልም ይላሉ የሂሳብ ባለሙያዎች፡፡ ይህን መሠል የተጣራ ሃብት

በአካውንቲንግ ስያሜው ‹‹Net worth›› እንለዋለን፣ ወይም ‹‹Net Asset›› ይባላል፣ ወይም ‹‹Shareholders Equity›› በመባል ይጠራል፡፡ የሚከተለው ቀመር ይህንን ያሳያል፤

- የባለቤቶች የተጣራ ሃብት = አጠቃላይ የድርጅቱ ንብረቶች - አጠቃላይ የድርጅቱ እዳዎች
- አጠቃላይ የድርጅቱ ሃብቶች (Total Assets) = የአጭር ጊዜ ሃብቶች (Short Term Assets) + የረዥም ጊዜ ሃብቶች (Long Term Assets)
- አጠቃላይ የድርጅቱ እዳዎች (Total Liabilties) = የአጭር ጊዜ እዳዎች (Short Term Liabilities) + የረዥም ጊዜ እዳዎች (Long Term Liabilities)

የባለቤቶች የተጣራ ሃብት በሂሳብ መዝገብ ላይ ያለው ብቻ ነው ወይስ ከአሁን ቀደም እንዳነሳነው ሀንፃ የተለያየ ዋጋ ይኖረዋል?

የባለቤቶች የተጣራ ሃብት ወይም ‹‹ኢኩይቲ›› በማለት የምንጠራው ከላይ ባለው የሂሳብ መዝገብ ልኬት መሠረት ከአጠቃላይ ሃብቱ ላይ ተቀናሽ የሚያደርገው አጠቃላይ ዕዳ ሲነሳ የሚመጣውን ነው፡፡ እንዲሁም ከድርጅቱ የሃብትና እዳ መግለጫ ሳንወጣ ሌላው

ልንመለከተው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር የድርጅቱን ከአንድ አመት ውጭ ሊከፈል የሚገባውን እዳውን ነው፡፡ ይህ ‹‹ሎንግ ተርም ሊያቢሊቲ›› በመባል የሚጠራ ሲሆን ይህም ድርጅቱ ንብረት ሲገዛ ወይም ተጨማሪ የማስፋፊያ ኢንቬስትመንት ለማድረግ ሲፈልግ ከአንድ አመት በላይ በሆነ ስምምነት ሊበደር ይችላል፡፡ የድርጅቱ የአንድ አመት (የአጭር ጊዜ) እና የረዥም ጊዜ እዳዎች በአንድ ላይ ሲደመሩ የድርጅቱን አጠቃላይ ተከፋይ እዳ *(Total Liabilties)* በመዝገቡ ላይ ያሳያሉ፡፡

የድርጅቱ አጠቃላይ ሃብት *(Total Assets)* እና የድርጅቱ አጠቃላይ እዳ *(Total Liabilities)* ምን ያመላክቱናል?

የድርጅቱ አጠቃላይ ሃብት እለኝ የሚላቸው ሃብቶቹ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የተጣራ ሃብት የሚባል አይደለም፡፡ የድርጅቱ የተጣራ ሃብት ወይም (Net Assets) ለመባል ድርጅቱ ያሉበትን እዳዎች ሁሉ መከፈል አለበት፡፡ ይህ ከድርጅቱ የሚጠበቅ አጠቃላይ እዳ (Total Liabilities) ሙሉ በሙሉ ከተከፈለ በኋላ ያለው ቀሪ ሃብት ነው የድርጅቱ የተጣራ ሃብት የሚባለው፡፡ እንግዲህ የእኔ ነው ማለት የማይቻል መሆኑን ያሳየናል፡፡ ይህን የተጣራ ሃብት ነው እንግዲህ የድርጅቱ ባለቤቶች የእኔ ማለት የሚችሉት፡፡ ይህ የባለቤቶቹ የመዝገብ ሃብት ወይም ‹‹Book Value of Equity›› በመባል ይጠራል፡፡ ልክ እንደ ህንፃው ሁሉ የድርጅቱም ባለቤቶች የተጣራ ዋጋ የመዝገብ ሃብትና የገበያ ሃብት በመባል ለሁለት ይከፈላል፡፡

የአንድ ድርጅት የባለቤቶች መዝገብ ላይ የሰፈረው የካፒታል ሀብት መጠን በገበያ ላይ ምን ያህል ተመን እንዳለው ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው?

እንግዲህ ይህ የሃብትና እዳ ማሳወቂያ ወይም (ባላንስ ሽት) ሪፖርት አንዱ ድክመት ነው። ድክመቱ ምንድነው ድርጅቱ በገንዘብ በቀላሉ ቆጥሮ የሚተምናቸውን ንብረቶች ብቻ በወረቀት ላይ የሚያሠፍር ሲሆን ድርጅቱ በገንዘብ በቀላሉ መተመን የማይችላቸውን ነገር ግን በድርጅቱ ገንዘብ አመንጭ ሃብትነት የሚታወቁትን የማይቆጠሩ ንብረቶች አለመመዝገቡ ነው። ለምሳሌ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የድርጅት የፈጠራና የቅጅ መብቶች በድርጅቱ አሴት ስር ሊመዘገቡ የሚገባ ሀብት ናቸውና። ይሁን እንጂ የገንዘብ ተመናቸው ስለማይታወቅ አይመዘገቡም፤ ሃብት መሆናቸው ቢታወቅም። እነዚህ ብቻ አይደሉም፤ ለድርጅቱ ገቢ ማደግ ከፍተኛ ሚና ያላቸው የድርጅቱ ብራንድ፤ ድርጅቱ ከአሁን ቀደም ያፈራቸው ቋሚ ደንበኞች፤ ከአቅራቢዎች ጋር ያዳበራቸው የደንበኝነት ትስስሮሾች፤ የሠራተኞች ምርጥ ውጤታማ የሥራ ባህል፤ የድርጅቱ አመራሮች ምርጥ ብቃት ሁሉ የድርጅቱ ገንዘብ አመንጭ ሃብት ናቸው። መኪናና ህንፃ በሃብትነት ተመዝግበው እነዚህስ ሃብቶች ለምን አልተመዘገቡም ስንል ድርጅቱ በቀላሉ በገንዘብ ሊተምናቸው ስላልቻለ ነው። ስለሆነም ወቅታዊ ተመን ስላልወጣላቸው በሂሳብ መዝገቡ ላይ ያልገቡ ሃብቶች አሉ ማለት ነው። እነዚህ ቢገቡ ኖሮ የድርጅቱን አጠቃላይ ሃብት ያንሩት ነበር። ከዚህ ሁሉ ሀብት ላይ አጠቃላይ ተከፋይ እዳ ቢነሳለትም በፊት ከነበረው የባለቤቶች የመዝገብ ላይ የተጣራ ሃብት *(Book Value of Equity)* በላይ ከፍ ያለ መጠን ይኖራቸው ነበር፤ ባለቤቶቹ። ይህ ብቻ አይደለም የድርጅቱ ቋሚ ንብረቶች *(Long Term Assets)* በመዝገብ ላይ ያለው መጠናቸው በየአመቱ ተቀናሽ የሚደረግላቸው የእርጅና ተመን ታሳቢ ተደርጎ

እንጂ ትክክለኛ የገበያ ተመናቸው ወጥቶላቸው አይደለም። የባለቤቶች የመዝገብ ላይ ሃብትም እነዚህን የቀነሱ ተመኖች ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። የህንፃውንና የማሽኑን እንዲሁም የመኪኖቹን የገበያ ዋጋ አስልቶ ቢያስቀምጥ የድርጅቱ አጠቃላይ የሃብት መጠን ይጨምር ነበር፤ ይህን ተከትሎም የባለቤቶች የተጣራ ሃብት ያድግ ነበር።

ይህን ለመከላከል ነው በድርጅት ትክክለኛ ወቅታዊ የዋጋ ተመን ላይ (ቢዝነስ ቫልዌሽን) ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች የድርጅቱን የመዝገብ ዋጋ ላይ ብቻ ሳይንተራሱ የድርጅቱን የፈጠራና የቅጅ መብቶች፤ የሠራተኛና አመራሮች ብቃቶችና ችሎታዎች፤ ድርጅቱ ከደንበኞችና አቅራቢዎች ጋር የፈጠራቸውን ጠቃሚ ትስስሮች እንዲሁም የድርጅቱን ብራንድ ከግምት ውስጥ በማስገባት ድርጅቱ ከአሁን ቀደም እያተረፋቸው የመጡ የትርፍ መጠኖችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ወደፊት ምን ያህል ትርፍ ሊያመጣ እንደሚችል ታሳቢ በማድረግ የዛሬ ትክክለኛ አጠቃላይ የድርጅቱን የሃብት ተመን (ዋጋ) የሚያወጡለት። ይህ መሰል ድርጅታዊ የሃብት ትመና ስልት ቢዝነስ ቫልዌሽን በመባል ይጠራል።

የድርጅቱን የወደፊቱን ሃብት አመንጭነት ታሳቢ ማድረግ ለምን ያስፈልጋል? የዛሬው (የዚህ አመቱ) ተመን ብቻ በቂ አይደለምን?

እንደሚታወቀው አንድ ንብረት ንብረት የሚባለው ዛሬም ወደፊትም ጥቅም የሚያመጣ በመሆኑ ነው። ዛሬ ላይ አንድ ቤት (መሬት) ወይም መኪና ስንገዛ ታሳቢ የምናደርገው ለአጭር ጊዜ ጥቅም በሚል ብቻ ሳይሆን ረዘም ላሉ አመታት ጭምር ይጠቅመናል በሚል ነው። ይህን ታሳቢ ያደረገ ግዥን ነው የምንፈፅመው።

Scanned with CamScanner

ድርጅትን በተመለከተ ልክ እንደ ቋሚ ንብረት ሁሉ የባለቤትነት ድርሻን ከአክሲዮን ገበያ (ስቶክ ማርኬት) ሄደን ስንገዛ የአጭር ጊዜ ጥቅም (ትርፍ) ብቻ ታሳቢ አድርገን ብቻ ሳይሆን በየአመቱ ረዘም ላሉ አመታት ልጠቀምበት እችላለሁ በሚል ነው። እንደውም አንዳንድ ወላጅ ለልጆቹ ሁሉ አክሲዮን (ስቶክ) በመግዛት በስጦታ (በውርስ መልክ) ይሰጣል። ይህ መሠሉ የአንድን ድርጅት ሃብት አመንጭነት ረዘም ላሉ አመታት የማየትና ዋጋ የመስጠት አስተሳሰብ በአካውንቲንግ ደንብ ‹‹*Going Concern Principle*›› በመባል ይጠራል። አንድ ድርጅት ቀጣይነት ያለው እድሜ አለው የሚል አስተሳሰብ ነው።

ከዚህ በመነሳት ባለቤቶች ንብረታቸውን (ኢኩይቲ) በአክሲዮን መልክ ለሌላ ለመሸጥ ሲፈልጉ ድርጅቱ ዛሬ ላይ ያለው አጠቃላይ ብቃቱ (በመዝገብ ላይ የሠፈሩትም ሆኑ ያልሠፈሩት ንብረቶች) ወደፊት ለቀጣይ አምስትና አስር አመታት ምን ያህል ትርፍ ሊያመጡ እንደሚችሉ ተመን ይወጣላቸዋል። ይህ የቢዝነሱ ትክክለኛ የሃብት ተመን ወይም የገበያ ዋጋ በመባል የሚጠራ ሲሆን የአጠቃላይ ንብረቱን ዋጋ በእጅጉ የሚጨምረው ይሆናል። ከዚህም ላይ ተቀናሽ የሚሆነው አጠቃላይ እዳ ተቀናሽ ሆኖ የሚገኘው የባለቤቶች የተጣራ ንብረት (ኔት ዎርዝ ወይም ኢኩይቲ) በመዝገብ ላይ ካለው (ቡክ ቫልዩ ኦፍ ኢኩይቲ) ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ልዩነት ይኖረዋል። በዚህ መንገድ የሚገኘው የባለቤቶች የተጣራ ሃብት ‹‹Market Capitaliazation›› የሚል ልዩ መጠሪያ አለው። የባለቤቶች የገበያ ተመን የተጣራ ሃብት መሆኑ ነው። እንግዲህ ሚዲያክ ድርጅት ሁለት ሚሊዮን አክሲዮኖች ቢኖሩት፤ በቢዝነስ ቫልዌሽን ስራት መሠረት የአንድ አክሲዮን የገበያ ተመን 10 ሺህ ብር ቢሆን የባለቤቶች አጠቃላይ የተጣራ ሃብት (የአክሲዮኖች ብዛት x የአንድ አክሲዮን ዋጋ) ይሆናል። ይህም ማለት ‹‹2 ሚሊዮን x 10 ሺህ ብር = 20 ቢሊዮን ብር›› እንደማለት ነው።

ይህ ተመን የቢዝነሱን ቀጣይ የማደግ እድሎች ፤ የአመራሩን ብቃት ፤ የድርጅቱን ብራንድ፤ የቅጅና የፈጠራ መብቶች እንዲሁም ከደንበኞችና አትራቢዎች ጋር ያለውን የተገነባ የትስስር እድል ጭምር ያካትታል። ይህ እንግዲህ ባለቤቶቹ በገበያው ተመን መሰረት ያላቸው የተጣራ ሃብት ሲሆን የሂሳብ መዝገብ ዋጋቸው ግን 5 ሚሊዮን ብር ወይም ከዚያም በታች ሊሆን ይችላል።

ይህን ልዩነት የፈጠሩት እንግዲህ በድርጅቱ አጠቃላይ ሃብት ውስጥ በአካውንቲንግ ሠነዶች ላይ የማይሠፍሩት በገንዘብ በቀላሉ የማንተምናቸውና የማንቆጥራቸው ሃብቶች (ኢንታንጅብል አሴትስ) በመኖራቸው ነው ። በመዝገብ ላይ የሰፈሩ ተቆጣጣሪ ሀብቶች ደግሞ የገበያ ተመናቸው ሳይሆን ከግዥ ዋጋቸው የእርጅና ተቀናሽ የሚደረግባቸው ቋሚ ንብረቶች በመኖራቸው ነው። እንዲሁም የድርጅቱ የሂሳብ መዝገብ የባለፈውን ጊዜ ገንዘብ ነክ አፈፃፀም እንጂ የወደፊቱን አመታት ትርፍ አመንጭነት ታሳቢ አድርጎ በድርጅቱ ንብረት ዝርዝር ውስጥ ስለማይመዘግብም ነው። ይህ የወደፊት ትርፍ ለምን ተመን እየወጣለት አይመዘገብም? ስንል ደግሞ ምላሹ ልክ እንደሌሎች ተቆጣሪ ሃብቶች በቀላሉ የሚተመን ስላልሆነ፤ ለመተመን ሌሎች ባለሙያዎችንም ሆነ ረዘም ያለ ስራን ስለሚጠይቅ የሃብትና እዳ ሪፖርቶች በመዝገብ ላይ ባሉት ተቆጣጣሪ ሀብቶች ላይ ብቻ መሠረት ያደርጋል። እነዚህ ማስረጃ ዶክመንት ያላቸው በመሆናቸው (ለምሳሌ የተገዛበት ደረሰኝ)። ይሁን እንጂ ድርጅቱ ባለበት ሙሉ ለሙሉ በሌላ ድርጅት የሚሸጥ ከሆነ ወይም ደግሞ ሌላ ባለሃብት በድርጅቱ ላይ የባለቤትነት ድርሻ እንዲኖረው ስንጋብዝ ወይም ደግሞ በስቶክ ማርኬት ውስጥ ተመዝግበን አክሲዮን ለመሸጥ ስንፈልግ ግን የድርጅቱን ትክክለኛ የባለቤቶች የተጣራ ሃብት ‹‹ቢዝነስ ቫልዌሽን›› በማሠራት የገበያ ተመኑን (Market Value of Equity) ማወቅና የአንድን

Scanned with CamScanner

እክሲዮን ዋጋ ግምት መተመን እንችላለን። ከዚህ ውጭ ግን በየጊዜው የሚቀርበው የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት የመዝገብ ተመኑ (ቡክ ቫልዩ) ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

የድርጅቱ የተጣራ ሃብት ኔጌቲቭ ሲሆን አይችልም?

አጠቃላይ የድርጅቱ ሃብት ከአጠቃላዩ የድርጅቱ እዳ በታች ሲሆን ውጤቱ ኔጌቲቭ ነው የሚሆነው። ይህ ደግሞ ያጋጥማል። ይህ ማለት ምንድነው? የአንድ ድርጅት አጠቃላይ እዳ ከአጠቃላይ ሃብቱ በለጠ ማለት ነው። ይህም ማለት ድርጅቱ እዳው ከአቅሙ በላይ መሆኑን ነው የሚያሳየን። ይሁን እንጂ የሂሳብ መዝገቡ ላይ የሠፈረው ይህ ሊያሳይ ቢችልም የባለቤቶች ሃብት (ኢኩይቲ) ኔጌቲቭ ሆነ ማለት ግን የድርጅቱ አፈፃፀም ደካማ ሆኗል ማለት ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም የድርጅቱ የመዝገብ ሂሳብ (ቡክ ቫልዩ) የድርጅቱን ወቅታዊ የገበያ ተመን ዋጋ (ማርኬት ቫልዩ) ላያሳይ ስለሚችል። በዚህ የተነሳ በዘንድሮው አመት ኢኩይቲ ኔጌቲቭ ሊሆን ይችላል፤ ይህ የሚያሳየው የባለፈውን አመት የፋይናንስ አፈፃፀም ነው። ድርጅቱ በዘንድሮው አመት ጥሩ አፈፃፀም ኖሮት ውጤቱን ወደ ፖዘቲቭ ሊቀይረው ይችላል። ይሁን እንጂ በሚቀጥለው አመትም እንዲሁም በሶስተኛው አመትም ይሄው ነገር ከተደገመ በተዘዋዋሪ የሚጠቁመው የድርጅቱ ገቢ ፈጣሪ የሆኑት በሂሳብ መዝገብ ውስጥ ያልተመዘገቡት የማይቆጠሩ ሃብቶች የገበያ ዋጋቸው ወይም የሃብት አመንጭነት አቅማቸው መዳከሙን ነው። ለዚያም ነው ኢንቬስተሮችም ሆኑ አበዳሪ ባንኮች የባለፉት ሶስት አመታትን የፋይናንስ ሪፖርት ማየት የሚፈልጉት። ይሁን እንጂ ይህ ኔጌቲቭ ኢኩይቲ ጉዳይ የአንድ አመት ውጤት ብቻ ከሆነ ግን ባንኮች የድርጅቱን የገበያ ተመን በማየት ሊያበድሩ ይችላል፤ ኢንቬስተሮችም ኢንቬስት ሊያደርጉ ይችላሉ።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌው አማዞን ዶት ኮም የተባለው የአሜሪካ ኩባንያ ሲሆን በሰኔ 2005 (እ.ኤ.አ) አጠቃላይ እዳው *(Total Liability)* 2.6 ቢሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን በመዝገብ ላይ የሚታየው የተጣራ ሃብት ደግሞ "-64 ሚሊየን ዶላር" ነበር። ይሁን እንጂ በዚያው ወር የድርጅቱ የባለቤቶች የገበያ ተመን ሃብት መጠን 15 ቢሊዮን ዶላር ነበር። ይህ የሚያሳየው የድርጅቱ መዝገብ *(Book Value Of Equity)* ላይ የሚታየው የተጣራ ሃብት ምን ያህል ከዜሮ በታች በ64 ሚሊዮን ዶላር የወረደ መሆኑን ሲሆን የገበያ ዋጋው ደግሞ ተወንጭፎ እናየዋለን። በዚህ የተነሳም አበዳሪዎች በድርጅቱ የገበያ ዋጋ በመተማመን ያበደሩት ሲሆን ኢንቬስተሮችም ያለ ስጋት ከድርጅቱ አክሲዮኖችን ሸምተዋል። በእርግጥም ምን ያህል ይህ የሠራ መሆኑ የታወቀው ከአምስት አመታት ቆይታ በኋላ የድርጅቱ የመዝገብ ላይ የተጣራ ሃብት *(Book Value Of Equity)* ከነበረበት -64 ሚሊዮን ዶላር ወደ 5 ቢሊዮን ዶላር ሲያሻቅብ በዚያው አመት የድርጅቱ የገበያ ተመን የተጣራ ሃብት ደግሞ *(Market Value Of Equity)* ወደ 50 ቢሊዮን ዶላር ተሸቀንጥሯል።

የባላንስ ሸት መዝገብ አዘገጃጀት!!

የባላንስ ሸት መዝገብ ያለፈውን ጊዜ ለምንል ዛሬ ላይ ከሆን የሚዘጋጀው ከዛሬ በፊት ያለውን የበጀት አመቱን ጊዜ የገንዘብ አፈፃፀም ለማሳየት የሚሠራ ይሆናል። እንዲሁ ደግሞ ዛሬ ላይ ሆኖ የድርጅቱን የቀጣይ ተራ የበጀት አመት ወራት አፈፃፀም አሊያም የድርጅቱን የቀጣይ የአንድ አመት ወይም የሶስት አመታት ወይም የአምስት አመታት አፈፃፀም በትንበያ መልክ ሊዘጋጅ ይችላል። ይህ መሠል የወደፊቱን የድርጅቱን የፋይናንስ ትንበያ በመንተራስ የሚዘጋጅ ባላንስ ሸት "ፕሮፎርማ ባላንስ ሸት" ወይም "ፎርካስትድ ባላንስ ሸት" በመባል ይጠራል። ይህ እንዴት ይሠራል? ለምንስ ይጠቅማል? የሚለውን

ሠፋ ባለ መልኩ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ በፋይናንስ ትንበያ ክፍል ላይ ስለተዳሰሰ ማንበብ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ባላንስ ሽት ወይም በአገርኛ ቋንቋ ‹‹የሃብትና እዳ ሚዛን›› መግለጫ ሪፖርት ከአሁን ቀደም ለማየት እንደሞከርነው ሶስት አይነት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚህም አሴት (ሃብት)፣ ሊያቢሊቲ (እዳ) እና ኢኩይቲ (የባለቤቶች ሃብት) በመባል የሚጠራ ሲሆን አሴትና ሊያቢሊቲ ደግሞ የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ በሚል እንደገና እያንዳንዳቸው ለሁለት ይከፈላሉ። የአሴት (የሃብት) መዝገቦች በስተግራ በኩል ሲዘረዘሩ ሊያቢሊቲ (እዳ) እና የባለቤቶች ሃብት (ኢኩይቲ) ደግሞ በስተቀኝ ይሠፍራሉ። በግራና በቀኝ የሠፈሩ የገንዘብ ተመኖች ደግሞ በመጨረሻ እኩል መሆን አለባቸው። ይህም የሚሆነው በአካውንቲንግ የሂሳብ ሪፖርት ዝግጅት ላይ ሂሳቦች ጥንድ ጥንድ እየሆኑ ስለሚመዘገቡና በመጨረሻም በዚህ መልክ ስለሚዘጉ ነው፣ ይህ ‹‹ደብል ኢንትሪ ሲስተም›› በመባል ይጠራል።

‹‹አሴት = ሊያቢሊቲ + ኢኩይቲ›› የሚለው ቀመርም የሚያሳየው ይህንኑ ነውና። በግራና በቀኝ የሚቀመጡትና ሁለቱም ክፍሎች እኩል መሆንን እንደ አንዲት እርግብ ግራና ቀኝ ክንፎች እንመስለዋለን። እርግቧ ሚዛኗን ጠብቃ ትብር ዘንድ በግራና በቀኝ በኩል ያሉት ክንፎቿ እኩል መጠንና ክብደት ሊኖራቸው ይገባል። ባላንስ ሽትም ይህንኑ ባህሪ አለው። ‹‹ባላንስ›› የሚለው ቃልም ሚዛኑን የጠበቀ ለማለት ነው። እስኪ የሚዲያክ ኩባንያን ባላንስ ሽት እንደሚከተለው እናጢነው።

የሚዲያክ ኩባንያ

የሠኔ 2010 ዓ.ም

የባላንስ ሽት መግለጫ

ሐብቶች (Assets)	2010 ዓ.ም		እዳዎችና የባለቤቶች ሃብት (Liabilities & Equity)	2010 ዓ.ም	
የአጭር ጊዜ ሃብቶች(Current Assets			*የአጭር ጊዜ እዳዎች (Current Liabilities)*		
- ጥሬ ገንዘብ (Cash)	22,000,000	00	- ተከፋይ እዳዎች (Account Payables)	27,000,000	00
- ተሠብሳቢ ሂሳቦች (Account Receviables)	13,000,000	00	- የአጭር ጊዜ ተከፋይ ብድሮች (Short Term Debts)	3,000,000	00
- የእቃ ክምችት (Inventories)	15,000,000	00			
አጠቃላይ የአጭር ጊዜ ሃብቶች (Total Current Assets)	*50,000,000*	*00*	*አጠቃላይ የአጭር ጊዜ እዳዎች (Total Short Term Liabilities)*	*30,000,000*	00
የረጅም ጊዜ ሃብቶች (Long Term Assets)			የረዥም ጊዜ እዳዎች (Long Term Liabilities)		
- የእርጅና ተቀናሽ የተደረገባቸው ቋሚ ንብረቶች (Net Properties)	80,000,000	00	የረዥም ጊዜ ብድሮች (Long term Debts)	78,000,000	00

Scanned with CamScanner

አጠቃላይ የረጅም ጊዜ ሃብቶች (Total Long Term Assets)	80,000,000	00	አጠቃላይ የረጅም ጊዜ እዳዎች	28,000,000	00
			አጠቃላይ ዕዳ (Total Liabilities)	108,000,000	00
አጠቃላይ ሐብቶች (Total Assets)	130,000,000	00	የባለቤቶች ሃብት (Stock holers Equity)	-	
			- የጋራ ተመን (Common Stock)	9,000,000	00
			- ተቀማጭ ትርፍ (Retained Earnings)	13,000,000	00
			አጠቃላይ የባለቤቶች ሐብት (Total Shareholders Equity)	22,000,000	00
			አጠቃላይ እዳና የባለቤቶች ሐብት (Total Liabilities & Equity)	130,000,000	00

ከባላንስ ሽት መግለጫ ምን እንማራለን?

የመጀመሪያው ነገር መግለጫው ግልፅ በሆነ መንገድ የድርጅቱን ሃብትና እዳ መጠን የሚያሳይ ሲሆን የባለቤቶቹንም የተጣራ የመዝገብ ሃብት ምን ያህል እንደሆነ ያሳየናል፡፡ እንዲሁም ተጨማሪ ጉዳዮችንም ሃብት ምን ያህል እንደሆነ ያሳየናል፡፡ ለምሳሌ ባለሃብቶች የተጣራ ሃብት የገበያ ዋጋ ሊጠቁመን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ባለሃብቶች የተጣራ ሃብት የገበያ ዋጋ (Market Value) ከመዝገቡ ላይ ካለው ሃብት አንፃር በምን ያህል እንደሚበልጥ ነው፡፡ ለምሳሌ የሚዲያክ ኩባንያ የመዝገብ ላይ የተጣራ ሃብት (ኢኩይቲ) 21 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ በቢዝነስ ቫልዌሽን የገበያ ላይ ዋጋው 60 ሚሊዮን ብር ቢተመን በገበያና በመዝገብ ዋጋው መሃከል የምን ያህል ብልጫ እንዳለ ለመረዳት እንችላለን፡፡

$$\text{የገበያ ዋጋ ለመዝገብ ዋጋ} = \frac{\text{የባለቤቶች ሃብት የገበያ ዋጋ}}{\text{የባለቤቶች ሃብት የመዝገብ ዋጋ}}$$

$$= \frac{60 \text{ ሚሊዮን}}{22 \text{ ሚሊዮን}}$$

$$= 2.7 \text{ እጥፍ}$$

አንድ ድርጅት በገበያ ላይ ውጤታማ ተወዳዳሪ ነው ለማለት ውጤቱ ከ‹‹1›› መብለጥ ያለበት ሲሆን ከ‹‹1›› በታች ከሆነ ግን የሚያመለክተው የድርጅቱ የገበያ ዋጋ ከመዝገብ ዋጋው ያነሰ መሆኑንና ይህም በቀጥታ ከፍ ያለ ገቢ የማመንጨትና፣ የተሻለ ትርፋማ የመሆን አቅሙ ደካማ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ በስቶክ ማርኬት (የአክሲዮን ገበያ) ውስጥ ኢንቬስተሮች አክሲዮን ለመግዛት የማይመርጡት ወይም ዝቅተኛ ዋጋ የሚሰጡት ነው የሚሆነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከዚሁ የባላንስ ሽት መዝገብ ውስጥ የምንመለከተው ድርጅቱ ለኢንቬስትመንቱም ሆነ ለስራ ማስኬጃው የሚያስፈልገውን

Scanned with CamScanner

ፋይናንስ ከምን ከምን ምንጭ ሊያገኝ እንደቻለ ያሳየናል። ይህም ማለት ከባለቤቶች ምን ያህል እንደተዋጣ፤ ከብድር ደግሞ ምን ያህል መገኘቱን ያሳየናል። ከዚህ አንፃር በብዛት ጥቅም ላይ የሚውለው መለኪያ የብድር እዳና የባለቤቶች አበርክቶት ጥመርታ *(Debt to Equity Ratio)* የምናይበት ነው። የድርጅቱ ካፒታል ከባለቤቶች ጋር ሲነፃፀር ምን ያህሉ በእዳ የተሸፈነ ነው የሚለውን ያሳየናል።

$$\text{የብድርና የባለቤቶች አበርክቶት ጥመርታ (Debt to Equity Ratio)} = \frac{\text{አጠቃላይ ብድር}}{\text{አጠቃላይ የባለቤቶች ድርሻ}}$$

የሚዲያክ ኩባንያን ስንወስድ የወሰደው የብድር መጠን 81 ሚሊዮን ሲሆን (የአጭር ጊዜ ብድር 3 ሚሊዮን፤ የረዥም ጊዜ ብድር ደግሞ 78 ሚሊዮን) ፤ የባለቤቶች አበርክቶት ደግሞ 22 ሚሊዮን ነው። ይህም ማለት ‹‹81/22= 3.9›› ሲሆን ወደ አራት እጥፍ በሚሆን ደረጃ የድርጅቱ ካፒታል በብድር መልክ የተገኘ መሆኑን ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የድርጅቱን ባለቤቶች የተጣራ ሃብት (ኢኩይቲ) ከመዝገብ ዋጋው ይልቅ የገበያ ዋጋውን ተጠቅመን ልናሰላው እንችላለን።

ሌላው ከሃብትና እዳ ሚዛን የምንረዳው ቁም ነገር የድርጅቱን የሥራ ማስኬጃ ጤናማነት ለማወቅ ነው። የአንድ ድርጅት የሥራ ማስኬጃ ጤናማነት የሚታወቀው በአንድ የበጀት አመት ውስጥ ድርጅቱ ባለው ሊከፍለው በሚችለው ሃብት መጠን *(Short Term Asset)* እና በዚያው አመት ተከፋይ ሊሆን በሚችለው እዳ መጠን *(Short Term Liabilities)* ነው። ይህም የሚያሳየን ምን ያህል የድርጅቱ የአንድ አመት ገንዘብ ነክ ሃብቱ የዚያን አመት እዳ መክፈል ይችላል የሚለውን ለመገንዘብና ካልቻለም ከወዲሁ አማራጭ የገንዘብ ምንጮችን እንድንፈልግ ነው። እነዚህ መለኪያዎች ‹‹ከረንት ሬሽዮ›› እና ‹‹ኩዊክ ሬሽዮ›› በመባል የሚጠሩ ሲሆን እንደሚከተለው እንያቸው፡-

$$\text{ከረንት ሬሽዮ} = \frac{\text{የድርጅቱ የአጭር ጊዜ ሃብቶች (current Assets)}}{\text{የድርጅቱ የአጭር ጊዜ እዳዎች (Current Liabilities)}}$$

$$\text{ኩዊክ ሬሽዮ} = \frac{\text{የአጭር ጊዜ ሃብቶች- የእቃ ክምችቶች (Inventories)}}{\text{የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳዎች (Current Liabilities)}}$$

በሁለቱ መሃከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

በሁለቱ መሃከል ያለው ልዩነት በኩዊክ ሬሾዮ ማለትም በፈጣን ጥመርታ ውስጥ የእቃ ክምችቶችን ዋጋ ተመን መቀነሳችን ነው። ‹‹ኩዊክ›› ማለት ፈጣን ማለት ሲሆን ድርጅቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ገንዘብ ሊቀይራቸው የሚገቡ ሃብቶችን ብቻ እንዲያመለክት ነው። ምንም እንኳን የእቃ ክምችት የምንላቸው (ጥሬ እቃዎች ፣ እየተመረቱ ያሉና ተመርተው ያለቁ ሸቀጦች) በድርጅቱ የአጭር ጊዜ ግብአቶች ውስጥ የተመዘገቡና በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ወደ ጥሬ ገንዘብ የሚቀየሩ በመሆናቸው በዚያው አመት ድርጅቱ ያሉበትን የአጭር ጊዜ እዳዎች ለመክፈል ያስችላሉ ቢባልም ወደ ጥሬ ገንዘብ የሚቀየሩበት ጊዜ ግን የሚታሰበውን ያህል ፈጣን ላይሆን ይችላል። የእዳ መክፈያ ጊዜው ደግሞ ፋታ ላይሰጥ ይችላል፤ ስለዚህ የበለጠ ሠላም ለማግኘት ሲባል ብቻ የድርጅቱ አመራሮች ከከረንት ሬሽዮ ይልቅ ኩዊክ ሬሽዮን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ዋናው ጉዳይ ግን ሁለቱም ከፍ ያለ ውጤትን ቢያሳዩ (የከፋይ ውጤቱ ከ ‹‹1›› ቁጥር በላይ ከፍ ቢል ይመረጣል) ። ይህ ውጤት ለአምራች ድርጅቶች ደግሞ ከረንት ሬሽዮ ከ‹‹2›› በላይ ፤ ኩዊክ ሬሽዮ (አሲድ ሬሽዮ) ከ ‹‹1.5›› ፤ በላይ ለችርቻሮ ንግድ ዘርፍ ላይ ያሉ ከረንት ሬሽዮ ከ ‹‹1.5›› በላይ፤ አሲድ ሬሽዮ ከ ‹‹0.7›› በላይ፤ ለአገልግሎት ዘርፍ ሰጭዎች ደግሞ ከረንት ሬሽዮ ከ ‹‹1.5›› በላይ

Scanned with CamScanner

እንዲሁም ኩዊክ ሬሽዮ ከ ‹‹1.4›› በላይ ቢሆን በእጅጉ ይመከራል፡፡ ይህም ምክንያቱ በበጀት አመቱ ውስጥ ድርጅቱ በጥሬ ገንዘብ እጥረት የተነሳ ሥራው እንዳይስተጓጎል ሊገጥመው ከሚችል የጥሬ ገንዘብ አደጋ ‹‹ሊኩይዲቲ ሪስክ›› ድርጅቱን ለመጠበቅ ነው፡፡

የጥሬ ገንዘብ እጥረት አደጋ ማለትም ‹‹ሊኩይዲቲ ሪስክ›› መፈጠር ድርጅቱን ሳልተጠበቀ የሥራ መስተጓጎል ችግር ውስጥ ሊዘፍቀው ይችላል፡፡ በቀጣይ በሪስክ መከላከል ዙሪያ ለማየት ተሞክሯል፡፡

ለምሳሌ የሚዲያክ ኩባንያን ሊኩይዲቲ ሬሽዮ እንዲህ እንመለከተዋለን፣

$$\text{ከረንት ሬሽዮ} = \frac{\text{ከረንት ሰሴት}}{\text{ከረንት ሲያቢሲቲ}}$$

$$= \frac{50{,}000{,}000}{30{,}000{,}000}$$

$$= \underline{1.6}$$

$$\text{ኩዊክ ሬሽዮ (ስሲድ ሬሽዮ)} = \frac{\text{ከረንት ሰሴት - የስቃ ከምችት}}{\text{ከረንት ሲያቢሲቲ}}$$

$$= \frac{50{,}000{,}000 - 15{,}000{,}000}{30{,}000{,}000}$$

$$= \frac{35{,}000{,}000}{30{,}000{,}000}$$

$$= \underline{1.2}$$

ይህ ቁጥር ከ ‹‹1›› በታች ከሆነ ከፍተኛ አደጋ በቀጣይ እንዳለ ይጠቁማል፡፡ እዳውን በወቅቱ ለመክፈል የሚቸገር ስለሚሆን፡፡ አንዳንድ ድርጅቶች ትርፋማ ይሆኑና የጥሬ ገንዘብ ችግር ውስጥ የሚገቡ አሉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከፍተኛ ትርፍ ሪፖርታቸው ላይ ታየ ማለት ባንክ ላይ ጥሬ ገንዘብ አለ ማለት ላይሆን ይችላልና ነው፡፡ በመሆኑም በድርጅቱ ትርፍ ላይ ብቻ ከመተማመን ይህን ሰሌት መጠቀሙ በእጅጉ ይመከራል፡፡ እነዚህ ሰሌቶች የድርጅቱን የስራ ማስኬጃ ካፒታል በሚገባ ለማስተዳደር የሚጠቅሙ በመሆናቸው በመፅሐፉ የስራ ማስኬጃ አስተዳደር ክፍል ውስጥ በስፋት ስለተነሱ ይመልከቷቸው፡፡

እንግዲህ እስካሁን ስለሃብትና ሚዛን መግለጫ ሪፖርት ያየን ሲሆን ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉትና እነዚህም በግራና በቀኝ ተከፍለው በሪፖርት ላይ እንደሚታዩ ሁለቱም ክፍሎች በመጨረሻ ውጤታቸው እኩል መሆን እንዳለበት (ለምሳሌ የሚዲያክ ሪፖርት ግራና ቀኝ አጠቃላይ ውጤት 130 ሚሊዮን ብር ሆኖ ይታያል)፡፡

ከዚህም የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት የተለያዩ መረጃዎችን ልንመለከትበትና የድርጅቱን የአሁን ጊዜ የሃብትና እዳ ደረጃ እንዲሁም የሥራ ማስኬጃ ጤናማነት ለመፈተሽ የሚያስችለን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በቀጣይ ደግሞ ስለ ድርጅቱ ሁለተኛ ሪፖርት ማለትም የገቢና ወጭ ወይም በሌላኛው ስሙ የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት ምንነትና የመረጃውን ፋይዳ የምንመለከት ይሆናል፡፡

ለምሳሌ መላኩ የተባለ ባለአክሲዮን የሚዲያክ ኩባንያ አንድ ባለሃብት ቢሆንና ድርጅቱ ካሉት አንድ ሺህ 100 አክሲዮኖች ውስጥ 100 አክሲዮን ቢኖሩት የዚህ ሠው አመታዊ ትርፉ ‹‹100x የአክሲዮን ትርፋማን ይሆናል፡፡ ከትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ የአንድ አክሲዮን ትርፋማነት›› 13,230 ብር ቢሆን የመላኩ ትርፍ 100 x 13,230=1,323,000 ያህል መጠንን ይሆናል፡፡ አቶ መላኩ ድርጅቱ

ሙሉ በሙሉ የድርጅቱን ትርፍ ቢያከፋፍል በአመቱ መጨረሻ ይህን ገንዘብ ይዘው ይሄዱ የነበረ ሲሆን ይሁን እንጂ ድርጅቱ 25 በመቶ ብቻ እንዲከፋፈል በመወሰኑ የአቶ መላኩ የዚህ አመት የትርፍ ድርሻ ሊደርሳቸው ከነበረው ትርፍ ውስጥ 25 በመቶውን ብቻ ነው ወደቤታቸው ይዘው የሚሄዱት። ይህም 330,750 ብር ያህል ገንዘብ ነው። የተቀረው 75 በመቶ ትርፍ ደግሞ ከትርፍ የተገኘ ተቀማጭ በሚል ከባለቤቶቹ ሃብት (ኢኩይቲ) ጋር ይደመራል። ይህም ማለት የባለቤቶቹ በባላንስ ሽት ላይ የተመዘገበው ሃብታቸው በዚህን ያህል የአመቱ ትርፍ መጠን ይጨምራል ማለት ይሆናል። ማለትም የአቶ መላኩ ሃብት በ 992,250 ብር ያህል ያድጋል ማለት ነው (ይህ መሰሉ የሃብት እድገት ‹‹Capital Gain›› ይባላል)።

ይህ ከትርፉ ተቀናሽ ተደርጎ ለምን ተቀማጭ ይሆናል፤ ለምንስ ለባለቤቶቹ ሙሉ በሙሉ አይከፋፈልም?

ይህ የሚሆነው የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ክምችት ለማሳደግ ነው። አንድ ድርጅት በየአመቱ ስራውን እያሠፋ ስለሚመጣ፤ ተጨማሪ የሥራ ማስኬጃ ገንዘቦች ያስፈልጉታል። እንዲሁም በስራ ሂደት ውስጥ ያልተጠበቁ የጥሬ ገንዘብ ፍላጎቶች ሊከሰቱበት ይችላሉ። እነዚህን መሸፈን የሚችለው በቂ የጥሬ ገንዘብ ክምችት ሲኖረው ነው። አለበለዚያ ወደ ብድር ሊሄድ ይችላል። ብድሩ ደግሞ የወለድ ወጭ ስላለው አስገዳጅ ካልሆነ በስተቀር ቀዳሚ ምርጫ አይደለም። እንዲሁም ድርጅቱ የተለያዩ የማስፋፊያ ስራዎችን ለማድረግ ሲፈልግ ወይም ሌላ ኢንቬስትመንት ለማድረግ ሲያስብ የሚጠቀመው በጥሬ ገንዘብ መልክ ተቀማጭ የሆነውን የራሱን ውስጣዊ ሃብት ነው *(Internal Fund)*። ስለሆነም ድርጅቱ ሁለት ጉዳዮችን ሚዛናዊ አድርጎ ትርፉን ይጠቀምበታል። የመጀመሪያው የድርጅቱን ባለቤቶች በአመቱ መጨረሻ

ሊያረካ የሚችል የትርፍ ክፍፍልን ማድረግ፤ ሁለተኛው ደግሞ የድርጅቱን የወደፊት ጤናማ ስራና እድገት ማስጠበቅ ነው። የትርፍ ክፍፍል አለመክፈል ባለቤቶቹን አያስደስትም። መጠቀም ይፈልጋሉና። አለበለዚያ በየአመቱ የትርፍ ክፍፍልን ወደ ሚከፍል ድርጅት ሊያመሩ ይችላሉ፤ ያላቸውን ድርሻ በመሸጥ። እንዲሁም ድርሻቸውን ሸጠው ባይወጡ እንኳን ሌላ ጊዜ ተጨማሪ ካፒታል አዋጡ ቢባል ደስተኛ አይሆኑም። ስለዚህ ድርጅቱ ይጎዳል ማለት ነው።

ሣብዕ ትረካ TUBE

Scanned with CamScanner

የገቢና ወጪ ሪፖርት መግለጫ

(Income statement)



ይህ በልዩ መጠሪያው የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት በመባል የሚጠራ ሲሆን አንድ ድርጅት ሪፖርቱ ከመውጣቱ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ምን ያህል የተጣራ ትርፍ ወይም ኪሳራ እንዳመጣ የሚያሳይ ነው። የአንድ የንግድ ድርጅት ትልቁ አላማው ደንበኞችን አስደስቶ ማገልገል ይሁን እንጂ ይህን ድርጅት የከፈቱ ባለቤቶችን ደግሞ በትርፍ ማስደሰትም ሌላኛው አላማው ነው:: ድርጅቱ የሚጠበትበትን ደንበኛን በሚያመርታቸው ሸቀጦች አገልግሎቶች ያረካ ዘንድ በሃብትና እዳ መግለጫው (Balance sheet) ላይ ያሉ ሃብቶችን (Assets) በስራ ላይ ያውላል:: እነዚህ ሃብቶች ከባለቤቶች (ኢኩይቲ) እንዲሁም በተከፋይ እዳ መልክ (ሊያቢሊቲ) የተገኙ ሃብቶችን በመጠቀም የተሰሩ ስራዎች

አማካኝነት የመጡ ገቢዎችንና የወጡ ወጪዎችን ተንተርሶ የሚሠራ ነው:: ይህ ሪፖርት የአንድን ድርጅት የትርፋማነት ደረጃ የሚያሳይ ነው:: ባላንስሽት የድርጅቱን ሃብቶችና እዳዎች በሆነ ጊዜ ላይ የሚጠቁም ሲሆን የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ደግሞ ድርጅቱን በዚህ ቀን እና ዓመት በማለት የትርፍና ኪሳራ መጠኑን የሚጠቁመን ነው::

የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያ ሶስት መስመሮች ‹‹የተጣራ ሽያጭ›› ወይም ‹‹ገቢ›› የመጀመሪያው መስመር ሲሆን በሁለተኛው መስመር ደግሞ ገቢውን ለማምጣት የወጡ የማምረቻና ምርቱንም ለመሸጥ የወጡ ወጪዎችን ነው:: ይህ በልዩ የአካውንቲንግ መጠሪያው ‹‹ለተሸጡ ምርቶች የወጡ ወጭዎች›› ወይም *‹‹Cost of sales››* በሚል ይታወቃል:: ሶስተኛው መስመር ‹‹ያልተጣራ ትርፍ›› ወይም ‹‹ግሮስ ፕሮፊት›› በመባል የሚጠራው ሲሆን ይህም ከሽያጭ ገቢው *(Revenue)* ላይ ለተሸጡ ምርቶች የወጡ ወጭዎችን *(Cost of sales)* በመቀነስ የሚገኝ ውጤት ነው::

ለምሳሌ የበለጠ ለመረዳት የ ‹‹ሜዲያክ›› ኩባንያ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት በመንተራስ ሶስቱን መስመሮች እንመልከት::

የሜዲያክ ኩባንያ

የትርፍና ኪሳራ መግለጫ

ሠኔ 30/2010 ዓ.ም

የሽያጭ ገቢ	100,000,000
የሽያጭ ወጭ	-70,000,000
አጠቃላይ ትርፍ	30,000,000

Scanned with CamScanner

ከዚህ ሪፖርት እንደተመለከትነው ‹‹ያልተጣራ ትርፍ›› (Gross Profit) የሚለው ውጤት የድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ማለት አይደለም፡፡ ይህ ምርቱን (አገልግሎቱን) በቀጥታ ባመረትንበት (ከገዛንበት) ወጪ እንዳር ከሽያጭ ብቻ ያገኘነው ትርፍ ማለት ነው፡፡ ይህ ከሽያጭ ብቻ ያገኘነው ትርፍ እንጂ ድርጅቱ ሌሎች ወጪዎችም ያሉበት በመሆኑ እነሱን ማስላት ይጠይቃል፡፡ አጠቃላይ ትርፍ ማለት የተጣራ ትርፍ ማለት ስላልሆነ ሌሎች የሚቀነሱ ወጭዎች እንዳሉ ነው የሚነግረን፡፡

ከእነዚህ የወጪ አይነቶች መሃከል ልዩ ልዩ የማርኬቲንግ ወጪዎች እንዲሁም አጠቃላይ አስተዳደራዊ ወጪዎች የሚያካትት ሲሆን አዳዲስ ምርትና አገልግሎት ለማውጣት የወጡ የምርምር ወጪዎች እንዲሁም የእርጅና ተቀናሽና (ዴፕሪሲሽን) እና የሊዝ ወጪዎች (አሞርታይዜሽን) ይጨምራል፡፡ የሚዲያክ ኩባንያን ቀጣይ ሪፖርት እንመልከት፡፡ እነዚህ ወጪዎች ማለት አጠቃላይ ሥራውን ለመሥራት የሚወጡ ሲሆኑ ያለነዚህ ዝርዝር ወጪዎች ሥራውን ሠርቶ ግርድፉን ትርፍ (አጠቃላዩን ትርፍ) ለማግኘት የማይቻል በመሆኑ እነዚህ ወጪዎች በጥቅል ስያሚያቸው ‹‹የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች›› *(Operating Expenses)* በማለት እንጠራቸዋለን፡፡ እነዚህን ወጪዎች ከአጠቃላዩ ትርፍ ስንቀንስ ታዲያ ከአጠቃላይ ድርጅታዊ ስራው የተገኘን ትርፍ ወይም ‹‹ኦፕሬቲንግ ፕሮፊት›› *(Operating profit)* እናገኛለን፡፡ እስኪ የሚዲያክ ኩባንያን ሪፖርት አብረን እንመልከት፡፡

የሚዲያክ ኩባንያ
የሠኔ 30 2010 ዓ.ም
የትርፍና ኪሣራ መግለጫ

የሽያጭ ገቢ (Revenue)		100,000,000
የሽያጭ ወጪ (Cost of sales)		70,000,000
ያልተጣራ ትርፍ (Gross profit)		100,000,000
የሽያጭ ወጪ (Selling)		-2,000,000
አጠቃላይና አስተዳደራዊ ወጪ (General Admin.)		-7,000,000
የጥናትና ምርምር ወጪ (Research Dvt.)		-500,000
የእርጅና ተቀናሽ ወጭ (Depreciation)		-500,000
የሊዝ ወጭ (Amortisation)		-100,000
ከቢዝነሱ የተገኘ ትርፍ (Operating income)		19,900,000
ከሌላ ምንጭ የተገኙ ገቢዎች (Other income)		1,000,000
ከወለድ የተገኘ ገቢ (Interest income)		00.00
የወለድ ወጭ (Interest Exp.)		-2,000,000
ከግብር በፊት ትርፍ (pre tax income)		18,900,000
ግብር (30%) (tax)		5,5670,000
የተጣራ ትርፍ (Net income)		*13,230,000*
የአክሲዮን ትርፋማነት (Earning per share)	*13,230*	
የትርፍ ክፍፍል መጠን (dividened)	*(25%) (3,307,500)*	
ወደ ድርጅቱ ካፒታል የተዛወረ (Retained earning) (75%)	*9,992,500*	

ከሪፖርቱ ላይ የወሰድ ገቢና ወጪ ምንድን ናቸው?

ድርጅቱ የወሰድ ገቢ የሚላቸው ደንበኞች ዱቤ ገዝተው በወቅቱ ባለመክፈላቸው የተገኘ የቅጣት ገቢ እንዲሁም ድርጅቱ በአመቱ መጨረሻ በባንክ ካስቀመጠው ገንዘብ የተገኘ የተቀማጭ ወለድ ገቢ ናቸው:: የወለድ ወጪ የሚባሉት ደግሞ ድርጅቱ ከባንክ ለተበደረው ገንዘብ የሚከፍለው እንዲሁም ከዱቤ አቅራቢዎች በዱቤ ገዝቶ ወይም ግብሩን በወቅቱ ባለመክፈሉ የከፈለውን የቅጣት ወጪን ያካትታል:: እነዚህ ወጪዎች ለድርጅቱ ስራዎች የወጡ ቀጥተኛ ወጪዎች ወይም ደግሞ ስራው ያስገኛቸው ገቢዎች ባለመሆናቸው ከኦፕሬሽናል ወጪዎችና ከድርጅቱ የሽያጭ ገቢ ውስጥ አልተካተቱም::

የአክሲዮን ትርፋማነት ምን ማለት ነው?

ይህ ማለት ድርጅቱ ብዙ አክሲዮኖች ያሉት ሲሆን ባለቤቶቹም ከአንድ አክሲዮን ጀምሮ ብዙ አክሲዮኖችን በባለቤትነት የያዙ ኢንቨስተሮች ይኖሩታል:: በመሆኑም ኢንቨስተሮቹ ከአንዱ አክሲዮን ምን ያህል የትርፍ ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ የሚያመላክታቸው ነው:: ይህም የድርጅቱን አጠቃላይ አመታዊ ትርፍ በድርጅቱ አጠቃላይ የአክሲዮን ብዛት ልክ በማካፈል የሚገኝ ውጤት ነው:: የ‹‹ሚዲያክ ኩባንያ›› በአጠቃላይ 1000 ያህል አክሲዮኖች ያሉት ሲሆን አመታዊ የተጣራ ትርፉም እንደተመለከተው 13,230,000 ያህል ነው::

‹‹የአክሲዮን ትርፋማነት መጠን ማለትም ‹‹*Earning Per share*›› = የተጣራ ትርፍ÷ የሼር ድርሻ ብዛት›› ሲሆን

ይህም 13,230 ያህል መጠን ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ማለት ደግሞ አንድ የድርጅት ባለቤት ከአንድ አክሲዮን 13,230 ብር ያህል ትርፍ እንዳገኘ የሚያሳይ ሲሆን ትርፉ ሙሉ ለሙሉ ለባለቤቶች ቢከፋፈል

ባሉት የአክሲዮኖች ብዛት ልክ ተባዝቶ ተከፋይ ይሆናል ማለት ግለሰቡ ነው::

ይህ መጠን የድርጅቱ ትርፍ ካደገ ያድጋል፤ ከቀነሰም ይቀንሳል:: እንዲሁም የድርጅቱ አክሲዮኖች ብዛት ከጨመረ የአክሲዮን ትርፋማነት መጠን ይቀንሰዋል:: የድርጅቱ አክሲዮኖች ብዛት ቋሚ ሆኖ ላይቆይ ይችላል:: አንድ ድርጅት ለሠራተኞቹና አመራሮቹ የባለቤትነት ድርሻ ይኖራቸው ዘንድ ሲፈልግ አክሲዮን ይሸጥላቸዋል:: ይሁን እንጂ ያሉት ነባር አክሲዮኖች በቀደምት በባለቤትነት በመያዛቸው በነባሮቹ ላይ አዳዲስ አክሲዮኖችን በመጨመር ለሠራተኞች ሊያድል ይችላል:: እንዲሁም አንድ ድርጅት ከሌላ ድርጅት ወይም ከሌሎች ባለሃብቶች ተበድሮ ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ ብድሩን በገንዘብ ከመክፈል እዳውን ወደ አክሲዮን ድርሻ ሊቀይርላቸው ይችላል (በስምምነት):: ይህን ለማድረግም ተጨማሪ አክሲዮኖችን በአዲስ መልክ ማካተት ይኖርበታል:: በእነዚህ ሁለት ምክንያቶች የድርጅቱ ነባር የአክሲዮኖች ብዛት ይጨምራል::

በዚህም መሠረት የሚዲያክ ኩባንያ ለአበዳሪዎቹ 300 ያህል አክሲዮኖችን በ2010 ላይ ቢያስተላልፍ አጠቃላይ የአክሲዮኖች ብዛት ከበፊቱ ጋር ተደምሮ 1,300 ይሆናል:: የበፊቱ የአንድ አክሲዮን ትርፋማነት 13,230 ብር የነበረ ሲሆን አሁን ግን የአክሲዮኑ አጠቃላይ ብዛት 1,300 በመሆኑ የአክሲዮን ትርፋማነቱ 10,177 ብር ይሆናል:: አክሲዮኑ እንዲበዛ ባደረግነው ቁጥር የትርፋማነት ድርሻው ይቀንሳል፤ ይህ ‹‹ዳይሉትድ ኧርኒንግ ፐር ሼር›› በመባል ይጠራል::

ጉዳዩን ሻይ እንደመጠጣት ብንመለከተው፤ ስኳሩን ከሻዩ ላይ ጨምረን ጥሩ ጣዕም እናገኝ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ተጨማሪ ውሃ በሻዩ ላይ ብንጨምር የስኳሩ ጣፋጭነት ይቀንሳል:: ይህ ዲይሊዩሽን ይባላል:: ድርጅቱ ከፈለገ ደግሞ የአክሲዮን መጠኑን ከባለቤቶች በመግዛት ቁጥሩን

ሊቀንሰው ይችላል፤ ይህ *‹‹Share repurchase››* በመባል የሚጠራ ሲሆን የአክሲዮን ትርፋማነቱን ያሳድገዋል። ድርጅቶች ከሚፈልጉት በላይ የጥሬ ገንዘብ ክምችት ሲኖራቸው በጥሩ ዋጋ ከነባር ባለቤቶች አክሲዮናቸውን መልሰው ይገዟቸዋል።

ከትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ምንድን ነው የምንረዳው?

ይህ መሠል ሪፖርት ሲዘጋጅ ለድርጅቱ አመራሮች፤ ለድርጅቱ ባለቤቶች እንዲሁም ለአበዳሪ ድርጅቶችና በድርጅቱ ላይ ድርሻ እንዲኖራቸው ለሚፈልጉ ኢንቬስተሮች ጭምር የሚሠጠው ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ይኖራል። የድርጅቱ አመራሮች ድርጅቱ ከትርፋማነቱ አንፃር የት ቦታ ላይ እንዳለ፤ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በምን ያህል እንደተሻለ ወይም እንደቀነሰ፤ ከሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶች አንፃር በአትራፊነቱ በምን ያህል ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ምን አይነት ወጭዎች ላይ ማሻሻያ እንደሚያስፈልጋቸው፤ ከድርጅቱ ሃብት አንፃር ትርፋማነቱ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፤ የድርጅቱ ምርታማነት በምን ያህል ደረጃ እንዳተሻሻለ ይጠቁማቸዋል። እንግዲህ ይህ ሁሉ መረጃ የሚገኘው ከድርጅቱ ገቢና ወጭ ወይም የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት ላይ ብቻ ነው። ድርጅቱ ከባንክ መበደር ሲፈልግ ባንኩ ምን ያህል ገንዘቡን ወስዶ የመመለስ አቅም እንዳለው ከሚመዝንባቸው ሪፖርቶች ውስጥ አንዱ የዚህ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ነው። በተጨማሪም የድርጅቱ ባለቤቶች ኢንቬስት ካደረጉት ገንዘብ አንፃር ምን ያህል ትርፋማ መሆን እንደቻሉ፤ ምን ያህልስ የትርፍ ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚችል፤ በድርጅቱ ላይ በቀጣይ ኢንቬስት አድርጎ ለማሳደግ ትርፋማነቱ ምን ያህል ሳቢነት እንዳለው፤ የሚረዱበት ነው። ሌሎች ኢንቬስተሮችም በዚህ ድርጅት ላይ ኢንቬስት ለማድረግ ቢፈልጉ በቅድሚያ ከሚመለከቷቸው ሪፖርቶች ውስጥ የአሁንና የባለፉት

ዓመታት የድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርትን ነው። አንድም ድርጅት ሌላን ድርጅት ለመግዛት ሲፈልግም የድርጅቱን የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት የአሁኑን አመትና የባለፉትን አመታት መግለጫዎች በማጤን ነው።

በአጠቃላይ ይህ መግለጫ የድርጅቱን ገንዘብ ነክ የአፈፃፀም ብቃቱን የሚያመላክት ሲሆን ለባለቤቶችም ከአክሲዮናቸው አንፃር ምን ያህል እንዳተረፉ ወይም የትርፍ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ይጠቁማቸዋል። እንዲሁም የድርጅቱን የገበያ ዋጋ ለማወቅም ከዚህ ሪፖርት የምንወስዳቸው መረጃዎች መሠረታዊ ናቸው።

ሪፖርቱን በማየት ብቻ እነዚህን ሁሉ እንዴት መለየት ይቻላል?

ሪፖርቱን በማየት ብቻ አይደለም። ከሪፖርቱ ከምንወስዳቸው ዳታዎች ተነስተን ትንታኔ የምንሠጥባቸው ልዩ ልዩ ቀመሮችን እንጠቀማለን። እነዚህ ‹‹ፋይናንሻል ሬሽዮ›› በመባል የሚጠሩ ሲሆን ከድርጅቱ የፋይናንስ ሪፖርት የምናገኛቸውን ዳታዎች በመጠቀም የምንቀምራቸው ነው። አስፈላጊውን ቀመራ ካደረግን በኋላ ቀመራው ያስገኛቸውን ውጤቶች በመንተራስ ትርጉም ወይም ድምዳሜ ላይ ለመድረስ እንችላለን። ስለሆነም የትርፍና ኪሳራ መግለጫው ሪፖርት ጥሬ መረጃ ብቻ ስለሆነ ከዚህ ይልቅ ጥሬ መረጃውን በመጠቀም ወደ መተንተን ማምራት ይጠበቅብናል ማለት ነው። እነዚህን የመተንተኛ ቀመሮች ታዲያ እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

ከሽያጫችን መጠን አንፃር ምን ያህል አተረፍን፦ ይህ ማለት የሽያጭ ገቢያችን ምን ያህል ያልተጣራ ትርፍን *(Gross Profit)*፤ የተጣራ ትርፍን *(Net Profit)* እንዲሁም የአፈፃፀም ትርፍን *(Operational Profit)* አስገኝልን የሚለውን የሚመልስ ነው። እነዚህ

Scanned with CamScanner

ቀመሮች በአጠቃላይ ሶስት አይነት ሲሆኑ የሚገለፁትም በመቶኛ ወይም በፐርሰንት ነው። እንደሚከተለው እንያቸው፡-

1. ግሮስ ማሪጂን፡- ከአጠቃላዩ የሽያጭ ገቢ ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ ምን ያህል ያልተጣራ ትርፍ አገኘን የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል። ይህም የሚያሳየን ድርጅቱ ምርቱን በቀጥታ ለማምረት ከወጣበት ወጪ አንፃር በምን ያህል ጭማሪ ባለው የመሸጫ ዋጋ መሸጥ መቻሉን ያሳያል።

የዚህ ቀመር መግለጫም ይህን ይመስላል፤

$$\text{ግሮስ ማሪጂን} = \frac{\text{ግሮስ ፕሮፊት}}{\text{የሽያጭ ገቢ}}$$

የሚዲያክ ኩባንያን ብንወስድ ከመግለጫው ላይ እንዳየነው ያልተጣራ ትርፉ *(Gross Profit)* 30,000,000 ብር ሲሆን አጠቃላይ የሽያጭ መጠኑ ደግሞ 100,000,000 ብር ነው። የድርጅቱ ግሮስ ማሪጂን ታዲያ፤

$$\text{ግሮስ ማሪጂን} = \frac{30{,}000{,}000 \times 100\%}{100{,}000{,}000}$$

$$= 30\%$$

ይህም የሚያሳየው ድርጅቱ በ30 በመቶ ብልጫ ከምርቱ በቀጥታ ከወጣበት የማምረቻ ወጪ በላይ በሆነ ዋጋ መሸጡን ነው። በዚህ ብልጫ መሸጡም ምርቱን ለማምረት የወጡ ቀጥተኛ ያልሆኑ ሌሎች ድርጅታዊ ወጪዎችን ለመሸፈን ያግዛል። ለምሳሌ የድርጅቱ ግሮስ ማሪጂን ዜሮ ቢሆን ይህ የሚያሳየው ድርጅቱ ምርቱን ለማምረትና ለማከፋፈል በቀጥታ ያወጣቸውን ወጪዎች መሸፈን የቻለ ቢሆንም ሌሎች በድርጅቱ ውስጥ ቢዝነሱን ለመስራት የሚያግዙ ልዩ ልዩ

ወጪዎችን ግን የሚሸፍን አይደለም። የምርቱ የመሸጫ ዋጋ የምርቱን ቀጥተኛ የማምረቻ ወጪ እንጂ ሌሎች ወጪዎችን አይሸፍንም።

በመሆኑም ድርጅቱ ከተጣራ ትርፍ ይልቅ የተጣራ ኪሳራን ይከናነባል። ይህ የሚሆነው የመሸጫ ዋጋው በጣም ዝቅ በማለቱ ነው። ወይም አንዳንዴ ድርጅቱ በኪሳራ ለመሸጥ ሲገደድ ዋጋ በጣም ያወርዳል። ዋጋ ሲወርድ ሽያጭ ይጨምራል፤ ይሁን እንጂ ግሮስ ማሪጂን በጠበበ ቁጥር ሌሎች ወጪዎችን ለመሸፈን ብዙም የማይችል በመሆኑ የድርጅቱ የመጨረሻ የተጣራ የትርፍ ውጤት *(Net Profit)* በጣም ሊያንስ ወይም ኪሳራ ውስጥ *(Loss)* ሊገባ ይችላል ማለት ነው። ምንም እንኳን የተለያዩ ድርጅቶች የራሳቸው ግሮስ ማሪጂን መጠን ቢኖራቸውም ይህ መጠን እንደየንግድ ዘርፉ በአማካይ ሊኖር የሚገባው መጠን ይለያያል። ለምሳሌ አምራች ድርጅቶች ቢያንስ 35%፤ በችርቻሮ ላይ የተሰማሩ 31%፤ አገልግሎት ሠጭ ተቋማት ደግሞ 50% ቢኖራቸው ይመከራል።

2. የአፈፃፀም ትርፋማነት(ኦፐሬቲንግ ማሪጂን)፡- ይህ የሚያሳየው ድርጅቱ ቢዝነሱን ለመስራት የሚያስፈልጉ ሁሉንም ወጪዎች ሸፍኖ የሚገኘው ትርፍ "ኦፐሬቲንግ ኢንካም" በመባል የሚጠራ ሲሆን ይህም ድርጅቱ የወለድና ትርፍ ግብር ወጪዎች ሳይታሰቡበት ያለውን ትርፍ ይመለከታል። ይህን መለካት የሚያስፈልገው ድርጅቱ ምን ያህል ወጪ ቆጣቢነቱን ማለትም የአፈፃፀም ልህቀቱን *(Operational Excellence)* ነው። ይህን ውጤት በተመሳሳይ የንግድ ዘርፍ ውስጥ ካሉ ሌሎች ድርጅቶች ጋር በማነፃፀርም ምን ያህል በአንፃራዊነት የተሻለ ወጪ ቆጣቢ አሠራርን እንደተከተለ ሲሆን የዘንድሮውን ከባለፉት አመታት የድርጅቱ ኦፐሬቲንግ ማሪጂን ጋር በማነፃፀር ደግሞ ምን ያህል የድርጅቱ ወጪ ቆጣቢ አሠራር ከአመት ወደ አመት መሻሻሉን ወይም አለመሻሻሉን የምንታዘብበት መሣሪያ

Scanned with CamScanner

ነው።

ኦፐሬቲንግ ማርጂን ማለትም ከእያንዳንዷ የአንድ ብር ሽያጭ ውስጥ ምን ያህል ኦፐሬሽናል ትርፍ ማግኘታችንን ሲሆን ይህም በመቶኛ የሚሰላ ይሆናል።

$$\text{ኦፕሬቲንግ ማርጂን} = \frac{\text{ኦፕሬቲንግ ትርፍ} \times 100\%}{\text{ጠቅላላ ሽያጭ}}$$

ለምሳሌ የሚዲያክ ኩባንያ ኦፐሬቲንግ ማርጂን እንደሚከተለው ነው፤ ከገቢና ወጪ ሪፖርቱ ላይ እንደተመለከትነው የድርጅቱ ኦፐሬቲንግ ትርፍ (ኢንካም) 19 ሚሊዮን ብር ሲሆን የድርጅቱ የወቅቱ አጠቃላይ ሽያጭ ደግሞ መቶ ሚሊዮን ብር መሆኑን እናያለን። በመሆኑም የድርጅቱ ኦፐሬቲንግ ማርጂን ‹‹19,000,000÷100,000,000 x 100% =19%›› ይሆናል። ይህም ማለት ድርጅቱ ከእያንዳንዷ የአንድ ብር ሽያጭ ገቢ ውስጥ 19% ወይም ‹‹19 ሣንቲም›› የኦፐሬቲንግ ገቢ ትርፍ ይኖረዋል። ይህ ውጤት ለሚዲያክ ድርጅቱ ከባለፈው አመት ያነሰ ውጤት ከሆነ ወጪ አጠቃቀሙ (ኢፊሺንሲው) ጥሩ አለመሆኑን ያመለክታል። ይሁን እንጂ ከሌሎች ተወዳዳሪዎቹ ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ሆኖ ከተገኘ የሚዲያክ አመራሮች ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ እየሠሩ መሆናቸውን ይህም መሆኑ በገበያ ዋጋ ላይ በዋጋ ተወዳዳሪነታቸውን እንደሚያጎላው ይጠቁመናል። በአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ (አቪዬሽን) ውስጥ ዝቅ ባለ ዋጋ የበረራ አገልግሎት የሚሰጡ አየር መንገዶች ትልቁ ትኩረታቸው ይህንን የኦፐሬሽናል ወጪ መቀነስ መቻላቸው ነው። ከፍ ያለ ኦፐሬሽናል ማርጂን ያለው አየር መንገድ ዝቅ ባለ ዋጋ አገልግሎት ለመስጠት ያስችለዋል። ኦፐሬቲንግ ማርጂኑ ዝቅተኛ የሆነ አየር መንገድ የአገልግሎት ዋጋውን ቀንሶ ለመወዳደር ቢፈልግ ኪሳራ ውስጥ ነው የሚገባው። ስለዚህ ‹‹ኦፐሬሽናል ኤክሰለንስ››

(የኦፊሻሀም ልሁቀት) ማለትም ምርጥ ወጪ ቆጣቢ የቢዝነስ አሠራር በሌላ አገላለፅ ከፍተኛ ‹‹ኤፊሽንሲ›› መፍጠር የላቀ ጥቅም አለው።

በእርግጥ አንዳንድ ድርጅቶች ከፍተኛ ኤፊሽንሲ ወይም ወጪ ቆጣቢነት ይኖራቸውና ኦፐሬቲንግ ማርጂናቸው ግን ከፍተኛ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ2010 ዎልማርት የተባለው የሱፐርማርኬት ቼይን ኦፐሬቲንግ ማርጂኑ 5.6% የነበረ ሲሆን የሱ ተወዳዳሪ የነበረው ኖርድስትሮም ደግሞ 9.7% ነበር። ለዚህ ምክንያቱ ዎልማርት እንደ ውድድር ስትራቴጂ የተጠቀመው በዝቅተኛ ዋጋ መሸጥ ስለነበር ነው። በዝቅተኛ ዋጋ በመሸጥ ብዙ መሸጥ ይችላል፤ ብዙ በሸጠ ቁጥር ደግሞ ምንም እንኳን ኦፐሬቲንግ ማርጂኑ ዝቅተኛ ቢሆንም ከብዛት ግን ከሌሎች ተወዳዳሪዎቹ ከፍተኛ ትርፍን እንዲያጋብስ ያስችለዋል። የሆነውም ይሄው ነበር። በዚያው አመት የዎልማርት የሽያጭ ገቢ ከኖርድስትሮም ጋር ሲነፃፀር በ45 እጥፍ የበለጠ ነበር። ይህም የሚያሳየው ኦፐሬቲንግ ማርጂን በዝቅተኛ ዋጋ ብዙ ሽያጭን ለማስመዝገብ እንደ ስልት በሚይዙ ድርጅቶች(ዋጋ መር የውድድር ስትራቴጂን ሲመርጡ) ይህ መጠን ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል። ማለትም ዝቅተኛ ኦፐሬቲንግ ማርጂን ሁልጊዜ ወጪ ከማብዛት ጋር ላይያያዝም እንደሚችል መታዘብ ያስፈልጋል።

3. ኔት ፕሮፊት ማርጂን፡- ይህ የሚያሳየው ድርጅቱ ሁሉንም ወጪውን ማለትም ቢዝነስ ለመስራት የሚያስፈልገውን ወጪ፣ የብድር ወለድ ወጪና ለመንግስትም ያለበትን የገቢ ግብር ከፍሎ ከእያንዳንዷ የሽያጭ ብር ውስጥ ለባለቤቶች ምን ያህል መጠን ይተርፋቸዋል የሚለውን ነው። ይህን ለማስላት መጀመሪያ የድርጅቱን የተጣራ ትርፍ ማወቅ የሚያስፈልግ ይሆናል። እንደሚከተለው እናሠላዋለን።

Scanned with CamScanner

$$\text{ኔት ፕሮፌት ማሪጂን} = \frac{\text{የተጣራ ትርፍ} \times 100\%}{\text{ሽያጭ}}$$

$$\text{የሚዲያክ ኩባንያ ኔት ፕሮፌት ማሪጂን} = \frac{13{,}230{,}000 \times 100\%}{100{,}000{,}000}$$

$$= 13.23\%$$

ይህም ማለት ከእያንዳንዷ የሽያጭ ገቢ ብር ውስጥ ሁሉም ተከፋይ ወጪ ተሸፍኖ ለድርጅቱ ባለቤቶች 13.23 ሣንቲም ወደ ኪሳቸው መግባት ይችላል እንደ ማለት ነው። ኔት ፕሮፌት ማሪጂኑ ከአመት ወደ አመት በተሻሻለ ቁጥር ቢዝነሱ ጥሩ እየሆነ መሄዱን ሲጠቁም፤ በአንፃሩ ደግሞ እየቀነሰ ከመጣ ግን ወይ ድርጅቱ የገበያው ውድድር ጠንክሮበታል፤ አልያም ደግሞ ወጪው እየጨመረ መጥቷል ማለት ነው።

4. የሐብት አጠቃቀም፡- ይህ የሚያሳየን ድርጅቱ ካሉኝ ከሚላቸው ሃብቶች አንፃር ምን ያህል ገቢ እያገኘባቸው ነው የሚለውን ነው። የድርጅቱን የሃብት መጠን የምናገኘው ከድርጅቱ የሃብትና እዳ ሚዛን መግለጫ ሪፖርት ላይ ሲሆን የድርጅቱን የሽያጭ ገቢ መጠን ደግሞ ከድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ ሪፖርት ላይ ይሆናል።

የድርጅቱ ሃብት የምንለው ‹‹አሴት›› ሲሆን ይህም ጊዜያዊ ሐብት (ከረንት አሴት) እና የረዥም ጊዜ ሃብት (ሎንግ ተርም አሴት) በማለት ለሁለት እንከፍለዋለን። አጠቃላይ ሃብት የምንለው የሁለቱን ድምር ውጤት ሲሆን፤ የረዥም ጊዜ ሃብት የምንላቸው ደግሞ ብዙውን ጊዜ ቋሚ ንብረቶችን ነው። በእርግጥ ከእነዚህ ውጭ የማይቆጠሩ የምንላቸው ሃብቶች *(Intangible Assets)* በተለይም እንደ የንግድ ስያሜ ዝና (ብራንድ)፤ የቅጅና የፈጠራ መብቶች በረዥም ጊዜ ሃብቶች ውስጥ

መስፈር የሚችሉ ቢሆንም በየጊዜው ግን የዋጋ ተመናቸውን በቀላሉ ማወቅ ስለማይቻል በሪፖርቱ ላይ አይኖሩም። በመሆኑም ቋሚ ንብረቶች የተገዙበትን ዋጋ ተመን ከሐብትና እዳ (ባላንስ ሽት) ሪፖርት ላይ በመውሰድ ብቻ የምናሠላ ይሆናል።

የሐብት አጠቃቀም ስሌት የሚነግረንም ምን ያህል ያሉንን ሃብቶች ደንበኛው ላይ እሴት ከመጨመር አንፃር በሚገባ ተጠቅመንባቸዋል የሚለውን ለማሳየት ነው። አንዳንድ ድርጅቶች ብዙ ሃብት ይዘው በአመቱ የሚሸጡት መጠን ውስን ነው፤ አንዳንዶች ደግሞ በትንሽ ሃብት (ንብረት) ብዙ የሽያጭ ገቢን ያስገባሉ።

የሐብት አጠቃቀም በሚከተሉት ሁለት ቀመሮች የሚሠላ ይሆናል፡

$$\text{Asset turnover (የሽያጭና የሐብት ጥመርታ)} = \frac{\text{ሽያጭ}}{\text{አጠቃላይ ሃብት}}$$

በዚህም መሠረት ከሚዲያክ ኩባንያ ባላንስ ሽት ውስጥ አጠቃላይ ብዛት *(Total Asset)* 130,000,000 ብር ሲሆን ከዚሁ ኩባንያ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ ደግሞ አጠቃላይ ሽያጩ መቶ ሚሊዮን ሆኖ እናገኘዋለን።

$$\text{የሚዲያክ ኩባንያ አሴት ተርኖቨር} = \frac{100{,}000{,}000}{130{,}000{,}000}$$

$$= 0.77$$

ይህ ጥመርታ የድርጅቱን አጠቃላይ ሃብት የተንተራሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ደግሞ የድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ *(Cash)* በአጠቃላይ ሃብት ውስጥ የሚካተት በመሆኑ የጥሬ ገንዘቡ ክምችት ግን ቢዝነሱን ለመስራትና ሽያጩን ለማሳደግ ሁልጊዜ ጥቅም ላይ ላይውል ስለሚችል የሃብት

Scanned with CamScanner

አጠቃቀማችንን በደንብ ሊያሳይ ይችላል:: ስለዚህ በተጨማሪ ማነፃፀሪያ የቋሚ ንብረቶችን የሃብት አጠቃቀም የሚያሳይ ሬሾን ልንጠቀም እንችላለን::

የሚዲያክ ኩባንያ የሽያጭና ቋሚ ንብረቶች ጥምረት *(Fixed Asset Turnover)*

$$\text{ቋሚ ንብረቶች} = \frac{\text{አጠቃላይ ሽያጭ}}{\text{ቋሚ ንብረቶች}}$$

$$= \frac{100,000,00}{80,000,000}$$

$$= 1.25$$

በዚህም መሠረት ዝቅተኛ የሽያጭና የሐብት ጥመርታ *(Asset Turnover)* ያለው ድርጅት ከሚሠራበት ሐብት አንፃር ዝቅተኛ ሽያጭ እያስመዘገበ መሆኑን ነው:: ይህ ሃብት በሌላ አመራር ቢመራ ኖሮ ወይም ሌላ ቦታ ኢንቬስት ቢደረግ ኖሮ ሊያመጣ ከሚችለው የሽያጭ ገቢ በታች እየሠራ መሆኑን ነው የሚጠቁመን:: ስለዚህ ቀጣይ የአሠራር ወይም የኢንቬስትመንት ማሻሻያ ለማድረግ ይህ መረጃ ይጠቅመናል ማለት ነው:: እንዲሁም የድርጅቱን የኢንቬስትመንት ተመላሽ ለማስላት የድርጅቱን የተጣራ ትርፍ ለድርጅቱ አጠቃላይ ሃብት *(Total Asset)* በማካፈል የሚገኝ ሲሆን ይህም የሚያሳየው ኢንቬስተሮች ሃብታቸውን ኢንቬስት አድርገው ምን ትርፍ አስገኙላቸው የሚለውን የሚጠቁም ነው::

$$\text{የኢንቨስትመንት ተመላሽ} = \frac{\text{የተጣራ ትርፍ}}{\text{አጠቃላይ ሃብት}}$$

$$= \frac{13,200,000 \times 100\%}{130,000,000}$$

$$= 10\%$$

ይህንንም ውጤት በመጠቀም ባለቤቶች ሌላ ቦታ ሃብቱን ኢንቬስት ቢያደርጉት ሊያመጡ ከሚችሉት የኢንቬስትመንት ተመላሽ መጠን አንፃር ለማወዳደር ያግዛቸዋል::

Scanned with CamScanner

የጥሬ ገንዘብ መግለጫ

(Cash Flow) ሪፖርት!!



በውሃ ታንከር የተመሰለው የጥሬ ገንዘብ ሂደት

የጥሬ ገንዘብ የድርጅቱ ወሳኝ መንቀሳቀሻ ኦክስጅን ነው፡፡ ድርጅቱ በባንክ የሚኖረው የጥሬ ገንዘብ መጠን ከፍና ዝቅ ማለት በቢዝነሱ ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ውጤትን ያስከትላል፡፡ የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ክምችት ከፍ ማለቱ የሚጠቅመው ሊከፈሉ የሚገባቸውን ወጪዎችን እንዲሁም ለድርጅቱ ሥራ የሚያስፈልጉ ወጪዎች በአግባቡ ለመክፈል የሚጠቅም ሲሆን ድርጅቱ ሥራውን ለማስፋፋት በሚፈልግበትም ጊዜ ተጨማሪ ካፒታል ለመመደብ የሚችለው በአካውንቱ ውስጥ ያለው ጥሬ ገንዘብ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡

እንዲሁም ድንገተኛ ጥሬ ገንዘብ የሚፈልጉ አጋጣሚዎች ቢፈጠሩ ድርጅቱ ጥሩ የሚባል የጥሬ ገንዘብ ክምችት ካለው ብቻ ነው ያንን ድንገተኛ ክስተት ሊያልፍ ወይም መልካሙን አጋጣሚ ሊጠቀምበት የሚችለው፡፡

የጥሬ ገንዘብ ክምችት መኖር ከአቅራቢዎች የተገዙ ጥሬ እቃዎች ወይም ምርቶች በተባለው ጊዜ ውስጥ ያለተጨማሪ ወለድ (ቅጣት) እና ካለ ትገዛብት መክፈል ይችላሉ፡፡ የባንክ ብድሮች በተባለላቸው ጊዜ ውስጥ ካለተጨማሪ የወለድ ቅጣትና ትገዛብት መክፈል ይችላሉ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም የጥሬ ገንዘብ ክምችት በበቂ ሁኔታ መኖር ለባለሃብቶች የትርፍ ክፍፍልን ለማሳደግ እድል ይሠጣቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የአንድን ድርጅት ዋጋ ወይም ግምት እንዲህ ነው ብሉ ለመናገር ማለትም ድርጅቱን ከመግዛት በፊት ወይም ከድርጅቱ የባለቤትነት ድርሻ ከመግዛት በፊት የገበያ ዋጋውን መተመን የሚቻለው የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ መጠንና ቀጣይ ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ እድገቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ አንድ የድርጅት አመራር ለዚህ ዓመትም ሆነ ለቀጣይ ዓመታት ምን ያህል የሥራ ማስኬጃ ካፒታል እንደሚያስፈልገውና ይህንንስ ለመሙላት ምን ያህል ጥሬ ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ለማወቅ፤ እንዲሁም የድርጅቱን ጤናማ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ምን ላይ እንዳለ ለመገምገም የሚችለው የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ ሪፖርት በማዘጋጀት ነው፡፡

የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ ከድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ ማወቅ አይቻልም?

የድርጅቱ ገንዘብ መጠን ማለት በድርጅቱ ባንክ አካውንት ላይ በዛሬ ቀን ያለውን የገንዘብ መጠን ‹‹ካሽ ባላንስ›› ብቻ የሚያሳይ ነው፡ ድርጅቱ በሩብ አመት ወይም የበጀት አመቱ መጨረሻ የድርጅቱ

የትርፍና ኪሳራ እና የባላንስ ሽት ሪፖርት ቢሠራም እነዚህ ሪፖርቶች የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ መጠን በትክክል የማሳየት እድሉ የላቸውም። በተለይ አንድ ድርጅት በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርቱ ላይ ከፍተኛ ትርፍ አስመዘገበ ማለት ይህን ያህል ገንዘብ ባለፈው አመት መጨረሻ ላይ በነበረው የድርጅቱ አካውንት ላይ በነበረው የጥሬ ገንዘብ መጠን ላይ ተጨመረ ማለት አይደለም። ለምሳሌ የሜዲያክ ኩባንያ የ2010 ዓ.ም የተጣራ ትርፍ 13,230,000 ብር ነው ማለት ድርጅቱ በ2009 ዓ.ም የበጀት አመት መጨረሻ በባንኩ አካውንት ላይ በነበረው ባላንስ ላይ ይህን ያህል ገንዘብ ተጨምሯል ማለት አይደለም። የ2009 ዓ.ም የሜዲያክ ኩባንያ አካውንቱ ላይ ያለው ጥሬ ገንዘብ 10,000,000 ብር ቢሆን የ2010 ዓ.ም ትርፍ ደግሞ ከላይ የተገለፀው ቢሆን ድርጅቱ አካውንት ላይ በበጀት አመቱ መጨረሻ ላይ 23,230,000 ብር ይኖራል ብለን እንጠብቃለን። ይህ ግን አይሆንም።

ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ነገር በአካውንቲንግ ደንብ መሠረት አንድ ተሸጦ ማስከፈያ ኢንቮይስ የተቆረጠለት ምርት (አገልግሎት) ገንዘቡ ከገዥው ተከፋይ ሆኖ ወደ ድርጅቱ የባንክ አካውንት ገቢ ባይሆንም እንደ ድርጅቱ ገቢ ተደርጎ ግን ይመዘገባል (የጊዜ ጉዳይ እንጂ የሽያጭ ገቢው መግባቱ አይቀርምና)። ይህ በአካውንቲንግ ደንብ ‹‹ሬቨኒዩ ሪኮግኒሽን ፕሪንሲፕል›› በመባል ይጠራል። ለገቢ እውቅና የመስጠት ደንብ ማለት ነው። በትርፍና ኪሳራ ሪፖርት ላይ ይህ እንደ ገቢ ተቆጥሮ ይሠራል። ድርጅቱ እንደገቢ ይቁጠረው እንጂ ወደ ባንክ ግን ገና አልገባም። ባንክ አካውንት ላይ ያልታየን ገንዘብ ጥሬ ገንዘብ ማለት አይቻለም። ዛሬ ብንፈልገው ገንዘቡ ባንክ ውስጥ የለምና። እንዲሁም ድርጅቱ የተለያዩ እቃዎችን በዱቤ ሊገዛ ይችላል። ወይም ያለበትን የዱቤ ክፍያ ሊያራዝም ይችላል። ይህም ማለት ለግዥ ይወጣ የነበረው ጥሬ ገንዘቡ ግን ከባንክ አልወጣም። ነገር ግን የትኛውም ተከፋይ

ወጭ በአካውንቲንግ ደንብ መሠረት ለድርጅቱ ሥራ ማስኬጃ የተፈፀመ በመሆኑ እንደ ወጪ ይያዛል፤ ይህ ‹‹ኮስት ሪኮግኒሽን ፕሪንሲፕል›› ይባላል። የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ወጪ መሆኑ የማይቀር ስለሆነ ለወጪ እውቅና ለመስጠት እንደ ወጪ ተደርጎ የትርፍና ኪሳራ ሪፖርቱ ላይ ይሰፍራል። ይህ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ እንደ ወጪ ቢያዝም ከድርጅቱ አካውንት ላይ የተከፋይ ወጪውን መጠን ያህል ጥሬ ገንዘብ ግን ወጪ አልተደረገም። እንዲሁም በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ ግብርን ለማስቀነስ በሚል እንደወጪ ተቆጥረው የሚያዙ ነገር ግን ወጪ ያልሆኑ ነገሮች አሉ፤ እነዚህም የእርጅና ተቀናሽ ወጪዎች ዲፕሪሴሽንና አሞርታይዜሽን በመባል የሚጠሩ ናቸው። እነዚህ ወጪዎች በድርጅቱ ትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ ይገኛሉ። ነገር ግን ጥሬ ገንዘብ ከድርጅቱ አካውንት ወጪ የማይፈፀምባቸው ናቸው። እንዲሁም ትልልቅ የካፒታል ወጪ የምንላቸው ለምሳሌ የመኪና ወይም የህንፃ ወይም የማሽን የግዥ ወጪዎች የሚመዘገቡት በድርጅቱ የሃብትና እዳ ሪፖርት መግለጫ ላይ ሲሆን እንደ ወጪ ተይዘው በድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ የሚቀመጡት ግን በእርጅና ተቀናሽ ወጪያቸው መልክ ነው። እነዚህ የካፒታል ወጪዎች እንዲሁም የጥሬ እቃዎች *(Inventories)* ግዥዎች በበጀት አመቱ ውስጥ ሲፈፀሙ ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ሆኗል። ይሁን እንጂ ይህ ወጪ በድርጅቱ ባላንስ ሽት ላይ እንጂ በትርፍና ኪሳራ ሪፖርት ላይ ስለማይመዘገብ ይህ ሪፖርት ከባንክ ያለውን ቀሪ ጥሬ ገንዘብ በትክክል አያሳይም። የጥሬ ዕቃዎች የግዥና ወጪ እንደ ወጪ የሚያዘው ጥሬ ዕቃው ወዳለቀበት ምርት ተቀይሮ የተሸጠው መጠን ብቻ ነው።

Scanned with CamScanner

የድርጅቱን የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ ለማወቅ እንጠቀምበትም?

በድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት (Income Statement) ላይ ያሉ ገቢዎች ሁሉ አልገቡም ማለት አይደለም፤ በሪፖርቱ ላይ እንደ ወጭ የተያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ሁሉ ከድርጅቱ ባንክ አካውንት አልወጡም ማለት አይደለም። ያልተሰበሰቡ የሽያጭ ገቢዎች እንዳሉ ሁሉ ወደ አካውንቱ የገቡ ጥሬ ገንዘቦችም አሉ። ከአካውንቱ ወጪ ያልሆኑ እንዳሉ ሁሉ ወጪ የተደረጉ የጥሬ ገንዘብ ክፍያዎችም አሉ። ስለሆነም የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርቱ ላይ ያለውን ከግብር በኋላ የተጣራ ትርፍ ወይም የተጣራ ኪሳራ መጠን እንወስድና ከዚህ ላይ እንደ ገቢ ተመዝግበው ነገርግን ገና ያልተሰበሰቡትን ("በአካውንቲንግ ቋንቋ አካውንት ሪሲቬብልስ") እንቀንሳለን። እንደ ወጪ ተይዘው ነገርግን ገና ከባንክ ወጪ ያልተደረጉ ተከፋይ ወጪዎችን (በአካውንቲንግ አጠራር "አካውንት ፔዬብልስ") ደግሞ እንደምራለን። ለምሳሌ የሚዲያክ ድርጅት የ2010 ዓ.ም ትርፍ 13,230,000 ብር ሲሆን በዚህ ውስጥ ግን ገንዘባቸው ገቢ ሳይሆን እንደገቢ የተያመሩ ተሰብሳቢ ሽያጮች በመኖራቸው ከዚህ ትርፍ ላይ ይቀነሳሉ፤ እንዲሁም እንደ ወጪ ተይዘው ነገር ግን ገንዘብ ከባንክ ወጪ ያልተደረገባቸውን ደግሞ መልሰን እንደምራለን። በዚህ መንገድ በአመቱ መጨረሻ ላይ ሰኔ 30/2010 ዓ.ም በድርጅቱ ባንክ አካውንት ላይ ያለውን ትክክለኛ ጥሬ ገንዘብ አወቅን ማለት ነው።

በእርግጥ በዚህ ብቻ አይበቃም። በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርቱ ላይ የእርጅና ወጪ ተቀናሽ ወጪዎች ግብር ለማስመለስ ሲባል የሙ ወጭዎች ናቸው እንጂ በትክክል ከድርጅቱ ባንክ አካውንት ላይ ወጪ ያልተደረጉ በመሆኑ ከተጣራው ትርፍ መጠን ላይ መልሰን ይህን

የእርጅና ተከፋይ ወጪ እንደምራለን። ምክንያቱም ከድርጅቱ አካውንት ላይ ያልወጣን ገንዘብ እንደወጣ አድርጎ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርቱ ላይ ሠፍሯልና ነው። ይህ ግብር ለማስቀነስ እንደ ወጪ ተቆጠረ እንጂ ያን ያህል ታሳቢ የሆነ ገንዘብ ግን በድርጅቱ አካውንት ላይ ስላለ ነው መልሰን የምንደምረው። ስለሆነም የሚዲያክ ኩባንያ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርቱ ላይ የእርጅና ተቀናሽ መጠን ተብሎ 100 500 ሺህ ብር እንዲሁም የሊዝ አሞርታይዜሽን ተቀናሽ ተብሎ ሺህ ብር ሠፍሮ እናያለን። ይህንን መጠን ማለትም በጥቅሉ 600 ሺህ ብር መልሠን በድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ላይ ማለትም በ13,230,000 ብር ላይ መልሠን እንደምራለን።

እንዲሁም በበጀት አመቱ ውስጥ የተፈፀሙ የካፒታልና የጥሬ እቃ ግዥዎች የሚመዘገቡት በድርጅቱ የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት ላይ እንጂ በትርፍና ኪሳራ መግለጫው ላይ ባለመሆኑ ወጪው ግን ከባንክ በመውጣቱ ከተጣራው ትርፍ መጠን ላይ ይህንን ወጪ እንቀንሳለን። እንዲሁም ድርጅቱ በበጀት አመቱ የተበደረው ገንዘብ ካለ የብድሩ ወለድ ብቻ ትርፍና ኪሳራ መግለጫው ላይ የሚመዘገብ ሲሆን (ግብር ተቀናሽ ለማድረግ)፤ ዋናው ብድር ማለትም ‹‹ፕሪንሲፓል›› ግን በትርፍና ኪሳራ ሪፖርቱ ላይ እንደገቢ ባይመዘገብም ወደ ድርጅቱ አካውንት ላይ ግን ገቢ የተደረገ በመሆኑ ዋናውን ብድር ብቻ (ወለዱን ሳይጨምር) በተጣራው ትርፍ ላይ እንደምራለን። ድርጅቱ በበጀት አመቱ ውስጥ የአክሲዮን ድርሻ ሸጦ ገንዘብ ካገኘ ይህም በተጣራው ትርፍ ላይ ይደመራል። የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ አካውንት ጨምሯልና። ድርጅቱ ለባለቤቶች የትርፍ ክፍፍል ካደረገ የተከፈለውን ያህል መጠን ከተጣራው ትርፍ ላይ እንቀንሳለን፤ ጥሬ ገንዘቡ ከባንክ ወጪ ሆኗልና።

Scanned with CamScanner

የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ክምችት መጠን ለማወቅ በድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ላይ የምንደምራቸውና የምንቀንሳቸው ነገሮች ለ?

ለማድረግ ድርጅታዊ ሥራ በክንዋኔዎች

እውን:: ነገሩን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ድርጅታዊ ሥራ ክንውን ማለትም ‹‹አክቲቪቲ›› የጥሬ የተሞላ ነው:: አንዳንዶቹ የሥራ ክንውን ... ወይም የሚቀንስ አልያም ገንዘብ መጠን የድርጅቱን ገቢ የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ደግሞ የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ወጪ የሚጨምር ወይም የሚቀንስ ነው::

ምንም አይነት የሥራ ክንውን ከእነዚህ አይወጣም:: ስለሆነም የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ክምችት የሚወስኑት እነዚህ ክንዋኔዎች ናቸው ማለት ነው:: እነዚህን ልዩ ልዩ ድርጅታዊ ክንዋኔዎች በሶስት እንከፍላቸዋለን:: እነሱም፣ የሥራ አፈፃፀም ክንውኖች *(Operating Activities)*፣ ከኢንቬስትመንት ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎች *(Investing Activities)*፣ እና ከካፒታል ፈንድ ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎች *(Financing Activities)* በማለት ይጠራሉ:: በእነዚህ ሶስት ዋና ዋና ምድቦች ውስጥ ያሉ ክንዋኔዎች የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ የመጨመር ወይም የመቀነስ እድሉ ያላቸው ናቸው:: እያንዳንዳቸውን አብረን እንመልከት::

1.የሥራ አፈፃፀም ክንውኖች (Operating Activities) ፦ ይህ አራት ዋና ዋና ገንዘብ ነክ ክንውኖችን የያዘ ነው:: የመጀመሪያው ክንውን ከሥራ አፈፃፀሙ የተገኘው የተጣራ ትርፍ ወይም ኪሳራ ማግኘት ነው *(Net Income)*:: ሁለተኛው ክንውን ደግሞ በትርፍና ኪሳራ ሪፖርቱ ላይ የተካተቱት የእርጅናና የሊዝ ተቀናሽ ወጪዎችን ማስላት ናቸው፣ ዲፕሪሴሽንና አሞርታይዜሽን:: ካሁን ቀደም ለማየት እንደሞከርነው እነዚህ ወጭዎች ለግብር ሲባል ታሳቢ ተደርገው በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ ቀረቡ እንጂ በትክክል ከድርጅቱ ባንክ ወጭ ስላልተደረጉ የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ ለማስላት መልሠን በተጣራው ትርፍ ላይ እንደምራቸዋለን:: ሶስተኛ ክንውን የምንላቸው በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርቱ ላይ እንደገቢ የተያዙ ነገር ግን ያልተሰበሰቡ ገቢዎች ናቸው፣ አካውንት ሪሲቬብልስ:: በአራተኛ ደረጃ በትርፍና ኪሳራ መግለጫው ላይ እንደተከፈሉ ተቆጥረው በወጪ መልክ የተያዙ ነገር ግን ገና ያልወጡ ናቸው፣ አካውንት ፔዩብልስ:: ተሰብሳቢ ገቢዎች ከአመቱ መጨረሻ ምን ያህል እንደሆኑ ለማወቅ የምንችለው እነዚህ ለብቻው በሚመዘገቡት የድርጅቱ ሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት በበጀት አመቱ ከተሰራው ባላንስ ሽት ላይ ነው:: ይሁን እንጂ የድርጅቱ የሠኔ 30/2010 ዓ.ም ባላንስ ሽት ላይ ያለ ተሰብሳቢ ገንዘብ (አካውንት ሪሲቬብልስ) መጠን ከባለፈው በጀት አመትም የመጣ ድምር በመሆኑ የዚህን አመት ብቻ ለማወቅ ማቀናነስ ያስፈልገናል፣ ማለትም ከ2010ዓ.ም አካውንት ሪሲቬብልስ መጠን ላይ የ2009 መጨረሻ ላይ ያለውን ተሰብሳቢ መጠን ስናነሳ የዚህን አመት የተጣራ ተሰብሳቢ መጠን በግልፅ ማወቅ እንችላለን:: የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ መጠን ለማወቅ ታዲያ ይህን የተጣራ የበጀት አመቱን ተሰብሳቢ መጠን ነው ከድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ላይ የምንቀንሰው::

በሌላ መልኩ የምናገኘው ተከፋይ ወጪ (አካውንት ፔዩብልስ) በዱቤ መልክ ድርጅቱ የፈፀማቸውን ግዢዎች ነገር ግን ወደፊት የሚከፈሉትን ነው:: ይህም ማለት ድርጅቱ ከአቅራቢዎቹ በዱቤ ግዥ በድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መልክ የተበደረው መጠን እንደማለት ነው:: ነገርግን ወጪ አልተደረገም መግለጫ ላይ እንደ ወጪ ተይዟል፣ በተጣራው ትርፍ ላይ ጥሬ ገንዘቡን ለማስላት ይህን ተከፋይ ወጪ ድርጅቱ ተከፋይ ወጪ መልሰን እንደምረዋለን፡ ይህንንም ምን ያህል በድርጅቱ ባላንስሽት ላይ (አካውንት ፔዩብልስ) እንዳሉት የምናውቀው በድርጅቱ ባላንስ ሽት ላይ ካለው ምዝገባ ላይ ነው:: ይሁን እንጂ

ያለው ምዝገባ ከባለፈው አመት የተላለፈውንም ተከፋይ ወጪ የሚይዝ በመሆኑ የዚህን አመት ብቻ ማወቅ ስለሚያስፈልግ ከላይ ለአካውንት ሪሲቬብልስ እንዳደረግነው በማቀናነስ የዚህን ዓመት የተጣራ ተከፋይ ወጪ እናገኛለን:: ይህም ማለት የድርጅቱ የ2010 ዓ.ም የተጣራ ተከፋይ ወጪ ማለት ከ2010 ዓ.ም ተከፋይ ወጪ (አካውንት ፔይብልስ) ላይ የ2009ን ተከፋይ ወጪ (አካውንት ፔይብል) በማንሳት የሚገኝ ነው። ይህን የተጣራ መጠን ነው የጥሬ ገንዘብ ምጣኔውን በትክክል ለማስላት በድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ላይ የምንደምረው::

እንዲሁም የጥሬ እቃ ክምችትን በተመለከተ በ2010 ዓ.ም የተደረጉ ግዥዎች መጠናቸው የሚመዘገበው በድርጅቱ የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት ላይ በድርጅቱ የአጭር ጊዜ ሃብትነት መልክ ነው:: እነዚህ የጥሬ እቃዎች በገቢና ወጪ ሪፖርት ላይ ሁሉም የግዥው መጠን እንደ ወጪ ተደርጎ አይመዘገብም:: እንደ ወጪ የሚመዘገቡት ወደ ምርት ተቀይረው የተሸጡት ብቻ ናቸው:: እነዚህ ድርጅቱ ላደረገው ሽያጭ በቀጥታ በግብአት መልክ የወጡ ጥሬ እቃዎች ወይም ቀጥተኛ አገልግሎቶች በአካውንቲንግ ስያሜያቸው *‹‹Cost of Goods Sold››* ወይም *(Cost of Sales)* በመባል ይጠራሉ:: ሌሉች በመጋዘን ያሉ የጥሬ እቃ ክምችቶች የድርጅቱ ቀሪ ንብረት ተደርገው በባላንስ ሽት ላይ ‹‹ሾርት ተርም አሴትስ›› ዝርዝር ውስጥ ይሠፍራሉ:: ድርጅቱ እነዚህን ጥሬ እቃዎች ሲገዛ ከባንክ አካውንቱ ገንዘብ ወጪ ያደረገ በመሆኑ የጥሬ ገንዘቡን መጠን ከማስላት አንፃር በባላንስ ሽት ላይ ያለውን የጥሬ እቃ ክምችት ዋጋ ተመን (ኢንቬንተሪ) ከተጣራው ትርፍ ላይ እንቀንሳለን:: ይሁን እንጂ ልክ እንደ ተሰብሳቢ ገቢዎች (ሪሲቬብልስ) እና ተከፋይ ወጪዎች (ፔይብልስ) ሁሉ የጥሬ እቃ ክምችት መጠንም ከባለፈው በጀት አመት የተላለፈውን የሚጨምር በመሆኑ በዚህ አመት የተገዛውን ብቻ ለማወቅ የባለፈውን ተመን ከዚህ አመት የኢንቬንተሪ

ተመን ላይ በማንሳት የተጣራውን የዚህ አመት የኢንቨንተሪ ወጪ ለማወቅ እንችላለን:: ይህም የኢንቬንተሪ ወጪ የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ ቀንሷልና ከተጣራው ትርፍ ላይ ተቀናሽ የምናደርግ ይሆናል::

2. የኢንቬስትመንት ክንውኖች (Investing Activities):- በዚህ ክንውን ሥር የምናገኛቸው ክንውኖች ድርጅቱ ወደፊት ጥቅም አገኝባቸዋለሁ ብሎ የሚገዛቸውን ንብረቶች (መኪና፣ ማሽነሪ፣ ቤት፣ መሬት ፣ ህንፃ ፣ ሌላ መሳሪያ) እንዲሁም ድርጅቱ ከሌላ ድርጅት የባለቤትነት ድርሻ አክሲዮን ሲገዛ ወይም ሌላን ድርጅት ሲገዛ ጥሬ ገንዘብ በዚህ መሠል ክንውን መልክ ወጪ ያደርጋል:: የንብረት ግዥ በወጪ መልክ በድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ የማይመዘገብ ሲሆን ከዚህ ይልቅ ግን በእርጅና ተቀናሽ መልክ በየአመቱ በወጪ መልክ ስለሚያዙ ይህንንም የእርጅና ተቀናሽ ወጪ መልሠን ከላይ በተራ ቁጥር 1 ላይ እንዳየነው የጥሬ ገንዘቡን ለማስላት መልሰን ስለደመርነው ገንዘብ ወጪ የተረገባቸውን የንብረት ወጪዎች ከድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ላይ ተቀናሽ እናደርጋለን::

በዚህም መሠረት የሜዲያክ ኩባንያ የ2010 ዓ.ም የካፒታል ወጪዎች 200,000 ብር ያህል መጠን ሲሆን ይህን ያህል ጥሬ ገንዘብ ከድርጅቱ ባንክ አካውንት ወጪ ሆኗል ማለት ነውና በባንክ ያለውን የጥሬ ገንዘብ መጠን ስለሚቀንሰው የካፒታል ወጪ መጠኑን ከድርጅቱ የተጣራ ትርፍ ላይ ተቀናሽ እናደርጋለን::

3. ከካፒታል ፈንድ ጋር የተያያዙ ክንዋኔዎች (Financing Activities):- ይህም ማለት ድርጅቱ ከባለድርሻ ባለቤቶችና ከአበዳሪ ድርጅቶች ጋር የሚኖረውን ትስስር ይመለከታል:: አንድ ድርጅት ከበጀት አመቱ ውስጥ አክሲዮን በመሸጥ ተጨማሪ ባለቤቶችን በመፍጠር ጥሬ ገንዘብ ሊያገኝ ይችላል፤ ከድርጅቱ ባለቤቶች አክሲዮናቸውን መልሶ ሊገዛቸው ይችላል፤ እንዲሁም ለድርጅቱ ባለቤቶች ገንዘብ በትርፍ

Scanned with CamScanner

ክፍፍል ድርሻ መልክ ወጪ ሊያደርግ ይችላል፤ ድርጅቱ ያለበትን የአጭር ጊዜ የሥራ ማስኬጃ ክፍተት ለመሙላት ገንዘብ ከባንክ ሊበደር ይችላል፤ ብድሩን ሊከፍል ይችላል፤ ወይም የረዥም ጊዜ ብድር ሊወስድ ይችላል። ከረዥም ጊዜ ብድሩም ላይ ሊከፍል ይችላል። ከእነዚህ ክንውኖች ውስጥ አንዳንዶቹ የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ መጠን የሚቀንሱ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚጨምሩ ናቸው።

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከትናቸውን ሶስቱን ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብ ፍሰትን የሚወስኑ ክንውኖች በመንተራስ የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ መግለጫ ሪፖርት እንደሚከተለው ማዘጋጀት እንችላለን፤

የሜዲያክ ኩባንያ
ሠኔ 30/2010 ዓ.ም
የጥሬ ገንዘብ መግለጫ ሪፖርት

1. የሥራ አፈፃፀም ክንውኖች (ኦፕሬቲንግ አክቲቪቲስ)

የተጣራ ትርፍ	13,230,000
ዲፕሪሲሽንና ስሞርታይዜሽን	600,000
ያልተሰበሰቡ ገቢዎች ጭማር	-230,000
ያልተከፈሉ ግዥዎች ጭማር	300,000
የጥሬ እቃ (ያሰቀሰተ) ምርት ክምችት ጭማር	-500,000
ከሥራ አፈፃፀም ክንውኖች የተገኘ ጥሬ ገንዘብ	13,400,000

2. የኢንቬስትመንት ክንውኖች (ኢንቬስቲንግ አክቲቪቲስ)

የካፒታል እቃዎች ግዥ	-200,000
ከቢሳ ድርጅት የተገዛ ድርሻ	00
ከኢንቬስትመንት ክንውኖች የተገኘ ጥሬ ገንዘብ	-200,000

3. ከካፒታል ፈንድ ጋር የተያያዙ ክንውኖች (ፋይናንሲንግ አክቲቪቲስ)

የተከፈለ የትርፍ ክፍፍል (dividend)	-3,075,000
ከራሱ ኢንቬስተሮች የተገዙ ስክሲዮኖች	00
የአጭር ጊዜ ብድር ጭማር	2,500,000
የረዥም ጊዜ ብድር ጭማር	1,000,000
ከፋይናንሲንግ የተገኘ ጥሬ ገንዘብ	425,000
የጥሬ ገንዘብ ሚዛን (የ3ቱ ክንዉኖች ድምር)	14,625,000
አጠቃላይ የጥሬ ገንዘብ መጠን	24,625,000

በሠኔ 30/2010 ዓ.ም ላይ (*Ending cash Balance*) በ2009 ዓ.ም የተዛወረውን 10,000,000 ብር ጨምሮ በድርጅቱ የባንክ አካውንት ላይ 24,625,000 ብር ይገኛል ማለት ነው።

ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በ2010 በጀት አመት መጨረሻ ላይ እንደተመለከትነው የድርጅቱ የተጣራ ትርፍ 13,230,000 የነበረ ሲሆን የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ መጠን ስሌት ግን 14,625,000 ሆኖ እናየዋለን። ከመግለጫው ላይ በተለይ በኦፕሬቲንግ ካሽ ፍሎውና በሶስተኛው ረድፍ በሚገኘው የፋይናንሲንግ ካሽ ፍሎው ስር ‹‹ጭማሮ›› የሚል ቃል እናያለን። ይህን ከ2010 እና ከ2009 ዓ.ም ባላንስ ሽት ላይ በመውሰድ

Scanned with CamScanner

ለውጡን በማቀናነስ የሚገኝ ነው ። ለምሳሌ ያልተሰበሰቡ ገቢዎችን (አካውንት ሪሲቬብልስ) ብንወስድ ከ2010 ባላንስ ሽት ላይ ካለው መጠን ላይ የ2009 ዓ.ም አካውንት ሪሲቬብልን በማንሳት የሚገኝ ይሆናል። በዚህም መሠረት ነው ያልተከፈሉ ወጪዎች (አካውንት ፔዩብልስ) ፣ የጥሬ እቃ ክምችት መጠን (ኢንቬንተሪስ) ፣ የአጭርና የረዥም ጊዜ ተከፋይ ብድሮችን *(Debt)* በተመሣሣይ መልኩ ከባለፈው አመት ባላንስሽት አቀናንሰን ነው የምናስቀምጠው።

ማሳሰቢያ፡- የጥሬ ገንዘብ ሚዛን መጠን 14,625, 000 የሆነበት ከሶስቱም ክንውኖች የተገኘ ድምር ውጤት የሚያመለክት ሲሆን ‹‹ አጠቃላይ የጥሬ ገንዘብ ሚዛን›› ደግሞ 24,625,000 ብር የሆነበት የድርጅቱን የ 2010 ዓ.ም ድምር መጠንና የ 2009 ዓ.ም የበጀት አመት መጨረሻ ላይ የነበረውን 10,000,000 ብር በመደመር ነው። ማለትም በድርጅቱ አካውንት ላይ በ2009 በጀት ዓመት 10,000,000 ብር ያህል ጥሬ ገንዘብ የነበረ ሲሆን በዚህ ላይ በ 2010 መጨረሻ ላይ 14,625,000 ብር ጥሬ ገንዘብ ሲታከልበት ‹‹አጠቃላይ የጥሬ ገንዘብ መጠን›› የሚለውን ያሣየናል።

የባለቤቶች የሃብት መግለጫ ሪፖርት

ይህ ሪፖርት ከድርጅቱ የሂሳብና እዳ ሪፖርት (ባላንስ ሽት) ውስጥ የሚወጣ ሲሆን በዋናነትም የድርጅቱን ባለቤቶች የመዝገብ ላይ ሃብት የሚያንፀባርቅ ነው። ይህ የባለቤቶች የመዝገብ ላይ ሃብት እውነተኛውን የገበያ ዋጋ የማያሳይ ነው። ብዙውን ጊዜ የባለቤቶች ሃብት የገበያ ላይ ዋጋ *(Market Value of Equity)* ነው እንደ ትክክለኛ የተጣራ ሃብት የሚታየውና የድርጅቱንም ትክክለኛ እሴት (ዋጋ) የሚያንፀባርቀው። ይህ የባለቤቶች የመዝገብ ላይ ሃብት የሚሰላውም ቀድሞ የተከፈለው የባለቤቶች ሃብት ላይ በተጨማሪነት የተሸጠ የባለቤትነት ድርሻ

(አክሲዮን) ካለ የተሸጠው መጠንና ድርጅቱ ከየዓመቱ የተጣራ ትርፍ ውስጥ የትርፍ ክፍፍል *(Dividend)* ከከፈለ በኋላ የቀረውን ተቀማጭ መጠን *(Retained Earning)* አንድ ላይ በማድረግ ነው። ይህ በአካውንቲንግ አጠራር የተለያየ ስያሜ ያለው ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ‹‹ካፒታል ስቴትመንት››፣ ‹‹ስቴትመንት ኦቭ ስቶክ ሆልደርስ ኢኩይቲ›› በመባል ይጠራል።

የሚዲያክ ኩባንያ

የባለቤቶች ሃብት ማሳያ

ሰኔ 30/2010 ዓ.ም

ተ.ቁ	አይነት	መጠን	
1	ቀድሞ የነበረው ካፒታል	400,000,000	00
2	በበጀት ዓመቱ ከተሸጡ አክሲዮኖች የተገኘ	10,000,000	00
3	ተቀማጭ ትርፍ	13,900,000	00
	አጠቃላይ	423,900,000	00

ይህ ሪፖርት በባላንስ ሽት ላይ የተቀመጠውን የባለቤቶች ሃብት ዘርዘር አድርጐ ለማሳየት የሚጠቅም ካልሆነ በስተቀር የባለቤቶቹን የገቢ ላይ የተጣራ የሃብት ዋጋቸውን *(Net worth)* ስለማይጠቁም ድርጅታዊ ገንዘብ ነክ ውሳኔ ለማድረግ (ለምሳሌ በስቶክ ማርኬት አክሲዮን ሽጦ ካፒታል ለማሰባሰብ) ብዙም የሚረዳ አይደለም።

የግለሰቦች የፋይናንስ ሪፖርት ናሙና!!

የአንድ ግለሰብ አመታዊ የገንዘብ ውሳኔዎችና ወጪዎች የሚከተሉትን ይመስላል። ግለሰቡ አርጌሳ ፋንታሁን የሚባል ስም አለው እንበል። ግለሰቦች የሚያቅዱት ከአዲስ አመት መስከረም መባቻ

ጀምሮ በመሆኑ የባለፈውን አመት የፋይናንስ በጀት የሚዘጉት ጳጉሜ መጨረሻ ላይ ነው ብለን እናስብ:: በመሆኑም የኡርጌሳን የ2011 ዓ.ም አዲስ አመት የገንዘብ ክንውን ትልሞች እንዲህ እንመልከተው::

ኡርጌሳ መላኩ
የጥሬ ገንዘብ መግለጫ ሪፖርት
መስከረም 01/2011 ዓ.ም (በብር)

ህይወታዊ ክንውኖች

የተጣራ ስመታዊ ገቢ	240,000.00
በዚህ ስመት ተሠርተው ያልተወሰዱ ገቢዎች	-40,000.00
ያልተከፈሉ የዚህ ስመት የዱቤ ግዥዎች	50,000.00
ያሳሰቁ የምግብ ከምችቶች	-25,000.00
የስርጅና ተቀናሽ	10 0000
የህይወት ከዋኔ የጥሬ ገንዘብ ሚዛን	235,000.00

የኢንቬስትመንት ክንውኖች

የመኪና ግዥ	-350,000.00
የስከሲዮን ግዥ	-50,000.00
የኢንቬስትመንት ጥሬ ገንዘብ ሚዛን	-400,000.00

የፈንድ አሰባሰብ ክንውኖች

የስመቱ የስቁብ ተከፋይ ስዳ	00.00
በስመቱ ለባንክ የሚከፈል ብድር	-100,000.00
የፈንድ ስሰባሰብ ጥሬ ገንዘብ ሚዛን	-100,000.00
ስጠቃሳይ የስመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ሚዛን	-265,000.00
ከባለፈው ዓመት የተዛወረ ጥሬ ገንዘብ	50,000.00
የተጣራ የገንዘብ ጭማሪ(ቅናሽ)	-215,000.00

ይህ የሚያሳየው በግለሰቡ የባንክ አካውንት ላይ ምንም ጥሬ ገንዘብ የሌለና ነገርግን የ215 ሺህ ብር ጉድለት እንዳለበት ነው የሚያሳየው:: በመሆኑም ኡርጌሳ በአዲሱ በጀት አመት ከላይ ያሉትን ክንውኖች ተግባራዊ ለማድረግ ተጨማሪ 215 ሺህ ብር ገንዘብ ማግኘት ይኖርበታል:: በዚህ የጥሬ ገንዘብ ትንበያ ሪፖርት (ካሽ ፍሎው ፎርካስት) መሠረት እቅዱን ማሳካት ካለበት በጀቱ የማይችል በመሆኑ ሊያጥፋቸው የሚገቡ የኢንቬስትመንት ክንውኖች ወይም ደግሞ ሊያስተራቸው የሚገቡ የብድር ክንውኖች መኖር አለባቸው:: በእቅዱ መሠረት መሄድ ሲፈልግ በ ‹‹ኑሮ ክንውኖች›› *(Operating Activities)* ውስጥ ከተዘረዘሩት ውስጥ የተጣራ ገቢውን ሊያሳድጉለት የሚችሉ ተጨማሪ ገቢ ፈጣሪ ስራዎችን መስራት ይኖርበታል፤ በዚህም እቅድ የተጣራ ገቢውን በ60 ሺህ ብር ከጨመረ የበጀት ጉድለቱን ወደ 155 ሺህ ብር ያወርዳል፤ ሠርቶ በዚህ አመት መከፈል ያለባቸውን ገቢዎቹን በበጀት አመቱ ውስጥ ካስገባ 40 ሺህ ብር ወደ ካዝናው ይገባለታል:: የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ወደ 115 ሺህ ብር ዝቅ ይላል:: ወደሚቀጥለው አመት ሊያሻግራቸው የሚችሉ የዱቤ ግዥዎችን መጠን ከነበረው 50 ሺህ ብር ወደ 100 ሺህ ብር ከፍ ካደረገ በባንኩ አካውንት ላይ

Scanned with CamScanner

ተጨማሪ 50 ሺህ ብር ስለሚኖረው የበጀት ጉድለቱን ወደ 25 ሺህ ብር ያወርደዋል፡፡ እንዲሁ የምግብ ፍጆታ ክምችቱን ማስወገድ ከቻለ (ሲያልቅ ሲያልቅ ብቻ መግዛትን ከመረጠ ልክ እንደ ‹‹Just in time››) በክምችቱ የተያዘው የ25 ሺህ ብር ይለቀቃል፡፡ ይህ ደግሞ የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱን ወደምንምንት ይቀይረዋል፡፡ አይኑን ወደ በጀት አመቱ የኢንቬስትመንት ክንውኖች ጣል ካደረገና የበጀት አመቱን የአክሲዮን ግዥ ማጠፍን ከመረጠ ወጪ ሊደረግ የነበረው የ50 ሺህ ብር ገንዘብ አካውንቱ ላይ ስለሚቀር የበጀት መጠኑ እንደውም በ 50 ሺህ ብር ከፍ ይላል፡፡ ወይም 50 ሺህ ብር ይተርፈዋል፡፡ ይህም ማለት ምናልባት በዚህ ዓመት ሠርግ ደግሶ ማግባትን ከወሰነና ለሠርግ የ ዘጠና ሺህ ብር በጀት ቢይዝ ከላይ ያሉት ክንውኖች ተግባራዊ ከሆኑ በኡርጌሳ አካውንት ላይ ምንም ጥሬ ገንዘብ የማይኖር ሲሆን የ40 ሺህ ብር ጉድለት ስለሚያሳይ ይህን ያህል ገንዘብ ወይ በብድር አልያም ገቢን በማሳደግ መሙላት እንዳለበት ያሳየናል፡፡

እቅዱን እንዳለ ከወሰድነው ደግሞ ኡርጌሳ በዚህ የፋይናንስ እቅድ አመቱን ለመጀመር ካሰበ ከፍተኛ ውጥረትና እንቅልፍ ማጣት እያስተናገደ ሊከርም መሆኑን የትንበያ ሪፖርቱ ያሳየናል፡፡ ይህ ልቀይር ካለ ደግሞ ግለሰቡ በቂ የጥሬ ገንዘብ መጠን ስለሌለው በኢንቬስትመንት ክንውኖች ዝርዝር ውስጥ ያለውን የመኪና ግዥ በዚህ አመት ማጠፍ ይኖርበታል ወይም የመኪናውን ሞዴል መቀየር ይጠበቅበታል፡፡ ኡርጌሳ ግዥውን ካጠፈ ከኢንቬስትመንት ክንውን ብቻ 350 ሺህ ብር ወጪ ሊደረግ የሚችለው ገንዘብ ይቀርለታል፤ ለመኪናው ግዥ ከባንክ ወስዶ በዚህ አመት ሊከፍል የነበረው ገንዘብ ይቀራል፡፡ ይህም ማለት የባንክ አካውንቱ ላይ በአመቱ መጨረሻ ወደ 135 ሺህ ብር ይደርሳል፡፡ እሱን በዚህ ውሳኔው ኡርጌሳ አመቱን በሰላም መክፈል የሚያስችል የገንዘብ ውሳኔን አደረገ ማለት እንችላለን፡፡

ከላይ የምንረዳው ምን ያህል በእውቀት ላይ የተመሠረተ ጠንቃቃ የገንዘብ እቅድና አወሳሰን አስፈላጊ እንደሆነና በዚህ ደረጃ ለማሰብም በቂ የሆነ የፋይናንስ እውቀትና አመራር ምን ያህል እንደሚበጅ ነው፡፡ ግለሰቦችን ወዳልተሳኩ ግኘሮጀች ወይም የገንዘብ ብክነቶች ውስጥ እንዳይሄዱ፤ ያልተጠበቁ ጭንቀቶች እንዳይነኩ ብሎም ከበጀት ጋር ባህሪያቸውን እንዲያጣጥሙ እገዛ ይደረግላቸዋል፡፡

ሣብዕ ትረካ TUBE

Scanned with CamScanner

የኡርጌሳ መላኩ
የተጣራ ገቢ ሪፖርት
ጳጉሜ 5/2011 ዓ.ም

ጠቅላላ አመታዊ ገቢ	582,000.00
የምግብ ፍጆታ ወጪ	40,000.00
የንፅህና ፍጆታ ወጪ	25,000.00
የአልባሳት ወጪ	30,000.00
የትምህርት ወጪ	30,000.00
የቤት ኪራይ ወጪ	48,000.00
የመዝናኛ ወጪ	60,000.00
አስተዳደራዊ (የሠራተኛ ጥበቃ) ወጪ	60,000.00
የትራንስፖርት ወጪ	13,000.00
ስልክና ኢንተርኔት	24,000.00
የውሃና ኤሌክትሪክ ፍጆታ	12,000.00
ጠቅላላ ወጪ	342,000.00
የተጣራ ገቢ ከግብር በፊት	240,000.00
የግብር ተመን	00.00
የተጣራ ገቢ	240,000.00

የኡርጌሳ የተጣራ ገቢ የሚያሳየን በየወሩ የሚወጡ ወጪዎች በአጠቃላይ ተደምረው ያሉትን ነው። በሪፖርቱ ላይ ‹‹አጠቃላይ ገቢው›› የሚያሳየን ደግሞ ንግድ የሚሠራ ከሆነ ከድርጅቱ ትርፍ ግብር ተከፍሎበት ከቀረበው የተጣራ ትርፍ ላይ በትርፍ ክፍፍል የወሰደው (የትርፍ ክፍፍል ግብር ከተከፈለበት በኋላ መሆኑ ነው)። እንዲሁም ከሌሎች የገቢ ምንጮች ያሉትንም ተደምሮ ነው። ተቀጥሮ የሚሠራ ከሆነ የሥራ ግብርና ጡረታ ተቆርጦ ወደ አካውንቱ የሚገባለትን መጠንና ከባለቤቱም ሆነ ከሌላ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ያገኛቸውን አጠቃላይ ገቢዎች ነው።

የኡርጌሳ ልዩ ልዩ ወጪዎች ደግሞ የተዘረዘሩት ሲሆኑ ግለሰቡ በቀጣይ በጀት ዓመት ለማግባት ከወሰነ ዝርዝር የወጪ መጠኑ ሊጨምር ይችላል። ከባለቤቱ የሚመጣም ተጨማሪ ገቢም ይኖረዋል። ኡርጌሳ አመታዊ የተጣራ ገቢውን ለማሳደግ አንድም የተለዩ ገቢ ፈጣሪ ስራዎችን መስራት ሁለትም ልዩ ልዩ ወጪዎችን ወደመቀነስ ማምራት ይኖርበታል። ይህን መሠል ወጪ ቆጣቢና ገቢ ፈጣሪ ውሳኔና አኗኗር ‹‹ኮስት ኢፌክቲቭ›› ኑሮ እንለዋለን። ከላይ ያለው ሪፖርት የሚያሳየው የኡርጌሳን የቀጣይ አዲስ አመት ተተንባይ የገቢና ወጭ ሪፖርት ነው።

Scanned with CamScanner

የኡርጌሳ መላኩ

የተተነበየ የሃብትና እዳ ሚዛን ማሳያ

(Forecasted Balance sheet)

ጳጉሜ 05/2011 ዓ.ም

ሃብቶች (Assets)		እዳዎች (Liabilities)	
የአጭር ጊዜ ሃብቶች (short Term Assets)		የአጭር ጊዜ እዳዎች (Short Term Liabilities)	
• በእካውንቱ ላይ ያለው ጥሬ ገንዘብ (Cash)	75,000.00	• ያልተከፈሉ የዱቤ ግዥዎች	50,000.00
• ያልተሰበሰቡ ገቢዎች (Account Receivables)	40,000.00	• በበጀት ዓመቱ የሚከፈሉ ብድሮች	00.00
• የምግብ ክምችቶች (Inventories)	25,000.00	• በበጀት ዓመቱ የሚከፈሉ የዕቁብ እዳዎች	00.00
• የእክሲዮን ሃብት ተመን	50,000.00		
አጠቃላይ የአጭር ጊዜ ሃብቶች	*190,000.00*	*አጠቃላይ የአጭር ጊዜ እዳዎች*	*50,000.00*

የረዥም ጊዜ ሃብቶች (Long Term Liabilities)		የረዥም ጊዜ እዳዎች (Long Term Liabilities)	
• ቤት	00.00	• የረዥም ጊዜ ብድሮች	00.00
• መኪና	00.00	• የረዥም ጊዜ የእቁብ እዳዎች	00.00
• የቤት እቃዎች ተመን	200,000.00	-	
• የእርጅና ተቀናሽ (Depreciation)	-10,000.00		
አጠቃላይ የተጣራ የረዥም ጊዜ ሃብቶች	*190,000.00*	*አጠቃላይ የረዥም ጊዜ እዳዎች*	00.00
አጠቃላይ ሃብቶች (Total Assets)	*380,000.00*	• አጠቃላይ ዕዳዎች	50,000.00
		• የግለሰቡ ሃብት (Equity)	190,000.00
		• የዓመቱ የተጣራ ገቢ (Earning)	240,000
		አጠቃላይ የእሴት ሃብት (Total Equity)	330,000.00
		አጠቃላይ እዳዎችና የባለቤቱ ሃብት	380,000.00

Scanned with CamScanner

የሒሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት፣ከታክስ ሥርዓቱ ጋር ያለው ግንኙነት፤ የሚታዩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው!!

‹‹ምክንያት በመደርመር ሳትሰራ ብትቀር ብዙዎች ከንፈራቸውን ይመጡብሃል፡፡ ብዙ ገንዘብ ከሰራህ ደግሞ ከብዙዎች ስድናቅት ይገርፍብሃል ፡፡ ዎዳጄ፤ ምርጫው ግን ያንተ ነው!›› ማኖጅ ስሮራ

የምክር አገልግሎት ለንግዱ ማህበረሰብ የሚኖረው ፋይዳ ምንድ ነው?

በመጀመሪያ የማማከር ስራ ለመስራት የትምህርት ደረጃና በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ በቂ እውቀትን የሚጠይቅ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በተቻለ መጠን በየጊዜው በአገር ውስጥ የሚወጡትን አዳዲስ መመሪያዎች፣ ደንቦችና አዋጆችን በመከታተልና በጥልቀት በመተዋወቅ ብቁ መሆንን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት አዘገጃጀት ደረጃዎችን ከሚያወጡ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የሙያ ማህበሮች በየጊዜው የሚለቀቁትን መረጃዎች ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለምሳሌ አዲስ የንግድ ስራ ለመጀመር ለሚፈልጉ ባለሀብቶችም ሆኑ ስራ ፈጣሪዎች ከሁሉም አስቀድመው ከድርጅት አቋም ምርጫ ማለትም የግለሰብ ንግድ፣ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ የሽርክና ማህበር ወ.ዘ.ተ. እና ከታክስ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለመምረጥ ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ ይሄን ጥያቄ ለመመለስና ሙያዊ ምክር ለመስጠት

በመጀመሪያ በ1952 ዓ.ም የወጣውን የንግድ ህግ፣ ንግድ ሚኒስቴር ካወጣው አዋጅና ደንቦች እንደዚሁም ታክስን በተመለከተ የጊዜ ገደብ አዋጅና ደንብ በተጨማሪም በአገሪቱ የወጡ ዝርዝር መመሪያዎችን ይዘት በአግባቡ ለማስረዳት እንደዚሁም ስራ ፈጣሪ ግለሰቦች ወይም ባለሀብቶች በእውቀት ላይ ተመስርተው የሚሻላቸውን እንዲመርጡ ለማድረግ ብቃት ያለው የማማከር አገልግሎት ያስፈልጋል። ይህም ማለት እነዚህን መረጃዎች በደንብ ማንበብን ይጠይቃል። የማማከር አገልግሎት የሚሰጠው ሙያተኛም በእውቀትና በሥራ ልምድ ብቁ መሆን ይጠበቅበታል። የማማከር አገልግሎት የሚሰጠው ሙያተኛ ብቁ ስለሆነ ብቻ አገልግሎቱ ውጤታማ ይሆናል ማለት አይደለም።

ባለሀብቶች በትክክል የሚፈልጉትን ለአማካሪዎቻቸው በግልፅ ማስረዳትና መጠየቅ አለባቸው። በአብዛኛው በማማከር ሂደቱ ባለሀብቶች ትክክለኛውን መረጃ ባለማግኘታቸው አዳዲስ ድርጅቶችን ሲያቋቁሙ መሠረታዊ የሆኑ አሰራሮች ከጅምሩ ተግባራዊ ባለመደረጋቸው ብዙ ድርጅቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሲከስሙ በስፋት ታይተዋል። እንዲህ ያለውን ውድቀት ለማስቀረት በእውቀትና በልምድ የበለፀገ የማማከር አገልግሎት ለንግዱ ማህበረሰብ መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

ባለሀብቶች ንግድ ስራ ከመጀመራቸው በፊት በተቻለ መጠን ቢዝነስ ፕላን አሰርተው ቢጀምሩ ውጤታማ የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው! ለመሰማራት በሚፈልጉት ኢንዱስትሪ ላይ በቂ መረጃ የማግኘት ችግሩ እንዳለ ሆኖ። አልፎ አልፎም የባንክ ብድር ሲጠየቅ ቅድመ ሁኔታውን ለማሟላት ሲባል ብቻ ኮፒ ፔስት የተደረገ ቢዝነስ ፕላን ይዘጋጃል። ይሄም ሌላው ውድቀት ነው። ብዙ ባለሀብቶች ገንዘብ አለኝ ብለው ብቻ በድፍረት ንግድ ስለሚጀምሩ ለውድቀት ሲዳረጉ ይታያል። ለብዙዎቹ ድርጅቶች መክሰር፣ ለአላስፈላጊ የታክስ ቅጣት መዳረግ እና ከሠራተኞች አያያዝ ጋር በተገናኘ ለችግር የሚጋለጡት ባለሞያው

በትክክል ባለማስረዳቱ ወይም ከባለሀብቱ የንግድ እውቀት ጉድለት ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው። የማማከር አገልግሎት ዋና አላማ የንግድ ተቋማት በጠራ እቅድ፣ በእውቀት እንዲመሰረቱና እንዲመሩ ድጋፍ ማድረግ ነው። በተደረገውም ድጋፍ ተቋማቱ ውጤታማ ሲሆኑ የንግድ ማህበረሰቡም ሆነ የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት ላይ የሚኖረው አዎንታዊ ተፅእኖ ከፍተኛ ነው።

የሒሳብ አያያዝና ሪፖርት ከታክስ ስርዓቱ ጋር ያለውን ተዛምዶ!!

ለታክስ ስርዓቱ ተግባራዊነት መሠረቱ ደረጃውን የጠበቀ የሂሳብ አያያዝ ነው። የአንድ ንግድ ድርጅት የሂሳብ አያያዝ ወይም ሪፖርት ለታክስ ምርመራ/ግምገማ መሠረታዊ ነገር ሲሆን እንደ ሪፖርቱ ጥራትና አቀራረብ የታክስ ውጤቱም እንደዚያው ይሆናል። የሂሳብ አያያዝ እና ሪፖርት ዋናውና ተቀዳሚ ዓላማው የድርጅቱን ሀብት፣ ንብረት፣ ዕዳ፣ ገቢና ወጪን በትክክል ለመቆጣጠር እና የሥራ አመራሩም ሆነ ሌሎች ከሪፖርቱ ተጠቃሚ የሆኑ አካላት በዚሁ ሪፖርት ላይ በመመስረት ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጡበት ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው። በአንፃሩ ደግሞ የታክስ ስርዓቱ ዋናው ዓላማ ፍትሐዊ የሆነ የታክስ አሰባሰብ ሥርዓትን በማስፈን የመንግስት (ሕዝብን) ጥቅም ማስከበር ነው።

አሁን በአገራችን በአብዛኛው በባለሞያዎች እየተሰራበት ያለው ከመሰረታዊ እውነታው የተለየ ነው። ማለትም ባለሞያዎችም ሆንን የንግድ ድርጅት ባለቤቶች ተጨንቀን የምንሰራው የታክስ ሰብሳቢው አካል የሚፈልገውን ዓይነት ሪፖርት ማወቅና የሱን ፍላጎት ለማሟላት ነው። ሆኖም ግን አሁን በሂደት እየተተገበረ ባለው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ስርዓቱ ደረጃውን የጠበቀና ሪፖርቱም ለሁሉም ተደራሽ አካላት በቂ መረጃን የሚሰጥ እንዲሆን

የግድ ስለሚል ወደፊት የተሻለ የሪፖርት አቀራረብ የምናይ ይሆናል። የታክስ ሰብሳቢው ባለስልጣንም የታክስ መሰብሰብ ፍላጐትን ብቻ ከማየት ባሻገር የሰመረ የሂሳብ አያያዝና የታክስ ስርዓት እንዲኖር በየጊዜው ከሚያወጣቸው መመሪያዎች አንዱ የሂሳብ ሰነድ አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ ሲሆን ይህ መመሪያ ሁሉንም የሂሳብ ሰነዶችን አካቶ በተሟላ መልኩ የቀረበና ስለ አሰራሩም የሚገልጽ አይደለም። አንድ ቀላል ምሳሌ ማንሳት የበለጠ መሰረታዊ ጉዳዩን ለመረዳት ይጠቅማል። የገንዘብ /ባንክ መክፈያ (CPV) ሰነድ በዓለም አቀፍ የሂሳብ ምዝገባም ሆነ በሂሳብ አያያዝ ሶፍትዌሮች ላይ የሚሰራበት ነው። ጠቀሜታው ክፍያ /ግዥ ለመፈፀም ከክፍያ መጠየቂያ ሰነድ ቀጥሎ የሚሞላ ሰነድ ሲሆን በማኑዋል የሚሰራ ድርጅት የግዢ ሰነዱ ከመክፈያ ሰነድ (CPV) ጋር በማያያዝ ይሄንኑ የሰነድ ቁጥር ማጣቀሻ አድርጐ ለመመዝገብ ይጠቅማል። በሶፍትዌርም የሚሰራው ይሄው የሰነድ ቁጥር ማጣቀሻ ተደርጎ ነው።

በግብር አስገቢው መ/ቤት በኩል ግን ይሄ ሰነድ ቢኖርም ባይኖርም የግዥ ሰነዱ ወይም ክፍያ የተፈፀመበት ደረሰኝ ካለ ግድ አይለውም። በሌላ በኩል ደግሞ በብዙ የታክስ ሰብሳቢ ቅ/መ/ቤቶች ውስጥ የገንዘብ /ባንክ መክፈያ (CPV) ሰነድ ደረሰኝ ለማይገኝላቸው ክፍያዎች ብቻ እንዲውል እያዘዙ እየተሰራበትም ነው። ይሄ አሰራር የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ካወጣው መመሪያ ቁጥር 110/2008 አንፃር ስህተት ነው። በዚሁ መመሪያ ላይ የግዢ ማረጋገጫ ተብሎ ሰነድ ለማይገኝላቸው ግዢዎች የቀረበ የሰነድ ዓይነት አለ። ይሄንን ሰነድ በባለስልጣኑ መ/ቤቱ ስር ባሉ ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች አስፈቅዶ ለማሳተም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በመስሪያ ቤቱ ሰራተኞችም ሆኑ ሃላፊዎች ባለመታወቁ ችግር ነበር። ሌላው ደግሞ የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት መሆን አለበት የሚለው የትርፍ ህዳግ እና ድርጅቶች በራሳቸው

ሰርተው የሚደርሱበት የትርፍ ህዳግ አንዱ አጨቃጫቂ ጉዳይ ነው። ዞሮ ዞሮ ግን የሂሳብ አያያዝ አመዘጋገብና ሪፖርት ጥራት ያለው ከሆነ ለታክስ ሰብሳቢው መ/ቤትም መሠረቱ ይሄው ነው። ስለሆነም መሠረታዊ ከሆነው ከሰነድ አያያዝና አጠቃቀም ጀምሮ የሂሳብ ምዝገባው እልፉ ሪፖርት እስኪዘጋጅ ድረስ ያለውን አሰራር በንግድ ተቋማቱም ሆነ በግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት በኩል በእውቀት እንዲፈፀም ማድረግ ለጋራ ጥቅም ይበጃል።

ጥራት ያለው የሂሳብ ሪፖርት ለማዘጋጀት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች እንዳሉ መዘንጋት የለበትም። የድርጅቶች የሂሳብ አሰራርና የሪፖርት አዘገጃጀት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን አሰራር ተከትለው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የትግበራ ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ በየጊዜው ስለ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ገለፃና ስልጠና እየሰጠ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሞያዎች ይሄንኑ ስልጠና እንዲወስዱ እና ፈቃድ ለማደስም እንደ አንድ መስፈርት እንዲታይ ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቶች ባለሞያዎችን እንዲቀጥሩና ስልጠናውንም እንዲወስዱ በማድረግ ወደ ተግባር እንዲገቡ እየተደረገ ነው። እንግዲህ ጥራት ያለውና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን ሪፖርት ለማግኘት እነዚህ ሁሉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል። የሪፖርት አዘገጃጀቱም በእውቀት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል። ከሰነድ አያያዝና አጠቃቀም ጀምሮ የሂሳብ ምዝገባው እልፉ ሪፖርት እስኪዘጋጅ ድረስ ባለው ሂደት የሒሳብ ባለሞያዎች ተግባርና ኃላፊነት ሰፊ ነው ማለት ይቻላል። ፈቃድ ይዘው ድርጅት ከፍተው የሚሰሩም ሆነ በየድርጅቱ ተቀጥረው የሚሰሩ የሂሳብ ባለሞያዎች ከንግድ ድርጅቶች ባለቤቶች የበለጠ በኃላፊነት መንቀሳቀስ፣ ማስረዳት እና ለተግባራዊነቱ የመጣር ኃላፊነት አለባቸው። በአብዛኛው የንግድ ድርጅት ባለቤቶችም

Scanned with CamScanner

ሆኑ ድርጅቶችን በመምራት ላይ የተሰማሩ ኃላፊዎች በዚህ ጉዳይ ላይ እነስተኛ ዕውቀትና ትኩረት ሊኖራቸው ስለሚችል ትልቁ ኃላፊነት ያለው በሒሳብ ባለሞያዎች ላይ ነው:: የመጨረሻ ውጤቱም ግልፅ ያለው ሪፖርት እና ፍትሐዊ የታክስ አሰባሰብ ስርዓትን ማስፈን ነው::

የንግድ ማህበረሰቡና የገቢር ሰብሳቢው መ/ቤት በሒሳብ ባለሙያዎች ላይ የሚያነሷቸው ቅሬታዎችና ምክንያቶቹ!!

በእርግጥ ነው ቅሬታዎች አሉ:: በሁሉም የእርከን ደረጃ ማለትም ከጀማሪ አካውንታንት እስከ ፋይናንስ ስራ አስኪያጆች እንዲሁም የሙያ ፈቃድ አውጥተው በሚሰሩ የሂሳብ አዋቂዎች ላይ የሙያ ሥነ ምግባር መጉደል አለ:: ስለሂሳብ ባለሞያዎች ከመናገሬ በፊት በአገራችን በአጠቃላይ የሞያ ስነ-ምግባር አለወይ? ስንል በሁሉም ዓይነት የሞያ መስኮች በሚያሳዝን መልኩ ከተወሰኑ ለሙያቸው ክብር ከሰጡ ባለሞያዎች በስተቀር ስነ-ምግባር ሞቷል:: በአሁኑ ጊዜ ከምንጊዜውም በበለጠ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ከየዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ ይመረቃሉ:: ትልቁ የአገሪቱ ችግር የተማረ የሰው ኃይል እጥረት ብቻ ሳይሆን የተማሩና በስራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች የሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ነው:: አገር አቀፍ ጥናት ተጠንቶ ባይረጋገጥም በተግባር ከሚታየው ተሞክሮ አንፃር የአገራችን ገዳዮች እኛው ሀሁ የቆጠርን ልጆችዋ ነን:: ለአገር ከማሰብ ይልቅ የግል ጥቅምን ማስቀደም፣ ይሉኝታ ማጣት፣ መስረቅን (ሌብነትን) እንደ ጀግንነት መቁጠር፣ በመንግስትም ሆነ በየግል ድርጅቶች ለፍቶ ከሚኖረው ሠራተኛ ይልቅ ወሬ በማመላለስ የተጠመዱ ወይም የፖለቲካ አባል የሆኑ ሠራተኞች የበለጠ ተመስጋኞች የሆኑበት ጊዜ ነው:: ስለሆነም የስነ-ምግባር ጉድለቱ በሂሳብ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆን በምህንድስና ዘርፍ፣ በአስመጪዎች፣ በህክምና፣ በህግ ባለሞያዎች፣ በሂሳብና ኦዲት ባለሞያዎች፣ በባንክ እና

ኢንሹራንስ፣ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ፣ በአምራች ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎች፣ በሹቶች ነጋዴዎች፣ በጋዜጠኞች፣ በማስታወቂያ ሰራተኞች፣ በጋራጆች፣ ወዘተ የሚስተዋል ችግር ሆኗል::

ከዚህ አንፃር በሂሳብ ባለሙያዎች ላይ በንግድ ማህበረሰቡም ሆነ በሌሎችም አካላት በየጊዜው ቅሬታ ይነሳል:: ቅሬታው ትክክል ነው:: ለቅሬታው መንስኤ ከስነ-ምግባር መጓደል ባሻገር ባለሞያ ለመባል የሚሰሩ ሀሰተኛ የትምህርትና የሥራ ልምዶች ትልቁን ሚና ይጫወታሉ:: በሀሰተኛ ማስረጃ ሂሳብ የሚሰሩና ፈቃድ ሳይኖራቸው ለገንዘብ ጥቅም ሲሉ ብቻ ማህተም እየፈለጉ የሚያስመቱ አሉ፤ ማህተም የሚመቱትም ትልቅ ስህተት እየሰሩ መሆኑን ማወቅ ይገባል:: በእነዚህና በሌሎችም መሰረታዊ ችግሮች ሳቢያ በሂሳብ ባለሙያዎች በሚዘጋጁ የሂሳብ ሪፖርቶች ጥራትና ትክክለኛነት ላይ የንግዱ ማህበረሰብም ሆነ ግብር ሰብሳቢው አካል ጥያቄ ያነሳል:: የዚህ መፍትሔው የባለሞያዎችን ስነ-ምግባር ለማሻሻልና ብቃታቸውን ለማሳደግ ከሚሰሩ ስራዎች በተጨማሪ በዘርፉ የሚታዩ ህገ-ወጥ ተግባራትን በመከላከል ችግሩን መቀነስ ይቻላል::

ሌላው በዘርፉ የሚስተዋለው ችግር አንዳንድ የንግድ ድርጅቶች ፈቃድ ያላቸውን የሂሳብ ባለሞያዎች መርጠው የሚያሰሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ፈቃድ ሳይኖራቸው ሂሳባቸው እንደሚሰራና የማያውቁት ባለሞያ ማህተምም እንደሚመታ እያወቁም ዝም ብለው የሚያሰሩ አሉ:: በዚህ ሂደት ከሂሳብ ሪፖርቶች ጥራት ጋር በተያያዘ ችግሮች ይከሰታሉ:: በእርግጥ ጥሩ የሚሆነው ማንኛውም ነጋዴ መንግስት ፈቃድ ከሰጠው ባለሙያ ጋር ውል ፈፅሞ ቢሰራ ይመረጣል:: ባለሞያውም በህግ ኃላፊነት አለበት:: ህጋዊ ፍቃድ ከሌላቸው ሙያተኞች ጋር በሚሰራበት ጊዜ ባለማወቅም ይሁን በመሳሳት የሂሳብ ባለሙያዎች ስህተት ይሰራሉ:: ይህ ስህተት ደግሞ ባለሀብቱን ወይም

Scanned with CamScanner

ነጋዴውን ለችግር ይዳርገዋል:: ስለሆነም የንግዱ ህብረተሰብ በትክክለኛ መጠን በትክክል ፈቃድ ካላቸው ጋር ውል ተዋውሎ ማሰራት አለበት፡ ይሄንንም የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በየጊዜው እያሳወቀ ይገኛል:: ይህ ካልሆነ ቋሚ የሂሳብ ሠራተኛ ቀጥሮ ማሰራት ጠቃሚ ይሆናል:: በተጨማሪም በየመስሪያ ቤቱም ሆነ ፈቃድ አውጥተን የምንሰራ የስራ ልምድ ያለን ባለሞያዎች ያለንን እውቀትና ልምድ ከስራችን ላሉ ተከታይ ባለሞያዎች በማካፈል ተተኪ እያፈራን እንዲሁም እውቀታችንን በማካፈል የሚጎድልብን ወይም የምናጣው ነገር የለም፡ በንግዱ ህብረተሰብም ሆነ በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የሚስተዋሉ የሂሳብ አያያዝ እሮሮዎች መቀነስ እንችላለን:: አሁን በብዙ ድርጅቶች ላይ በብዛት የሚታየው ችግር ሲኒየር የሆንን ባለሞያዎች ለጀማሪ የሂሳብ ባለሞያዎች በደንብ ግልጽ አድርገን ስለማናሳያቸው እንዳንዶቹ በሚስጥር ቁልፍ ሲስተሙን ስለምንዘጋባቸው እነዚህ ባለሞያዎች ወደ ስራ ይልመዱ?የምናውቀውን ሳንሰስት ማሳወቅ የሀሊና ትርፍ አለው፡ ከሁሉም በላይ ግን ባለሞያዎች ለሙያችን ክብር ብንሰጥና የሙያውን ሥነ- ምግባር ብንጠብቅ ራሳችንን፣ ደንበኞቻችንን እና አገራችንን እናድናለን:: የህሊና እርካታም እናተርፋለን::

የአገራችን የገቢ ግብር ህጎችና የጐረቤት ሀገራት ተሞክሮ!!

በአገራችን ያለው ከአንድ ዓመት በፊት ተሻሽሎ የወጣው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ዓ.ም እና ደንብ ቁጥር 410/2009 ዓ.ም የተጠበቀውን ያህል ባይሆንም መጠነኛ መሻሻሎችን ይዞ የወጣ ሲሆን ይሄንን አዋጅና ደንብ ለማስፈጸም የሚወጡ ዝርዝር መመሪያዎች ደግሞ በቅርቡ ይወጣሉ ተብሎ ይጠበቃል:: በዚህም የተወሰኑ መሻሻሎችን በግልጽ ለማየት የሚቻል ይሆናል:: በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ህጐችን ከጐረቤት አገሮች ለምሳሌ ከኬንያ ጋር ብናነፃፀረው የታክስ ዓይነቶችና የታክሶች መጠን ከሞላ ጎደል በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያለው ነው:: የጉምሩክ ይሁን እንጂ በአንዳንድ የታክስ ዓይነቶች ላይ ልዩነቶች አሉ:: የጉምሩክ ቀረጥ /ታክስ አከፋፈልንም ስናይ ሱርታክስ ኬንያ አታስከፍልም:: ኢትዮጵያ ውስጥም ይሄ ታክስ ሲጀመር ለተወሰነ ጊዜ ተብሎ የታክስ ህጉ አካል የሆነ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ግን በአገራችን ይሰራበታል:: ዞሮ ዞሮ የታክሱ ስሌት ከሌሎች አገሮች ጋርም ሲነፃፀር ከፍና ዝቅ ማለቱ ብቻውን የንግዱን ማህበረሰብ ያሰራዋል ወይም እያሰራውም ለማለት ይከብዳል::ለንግዱ ማህበረሰብ ግልፅ የሆነና ወቅቱን ያገናዘበ የንግድ ህግ መኖር ወሳኝ ነው:: ለምሳሌ በኢትዮጵያ የ1952ቱ የንግድ ህግ ሳይሻሻል አሁን ለምናስበው ርቀት ብዙ መራመድ የሚያስችል አይመስልም:: ሁሉንም የመንግስት ቢሮክራሲዎች ለንግዱ ማህበረሰብ ቀላል ከማድረግ አንፃር ኬንያ እንደ ምሳሌ የምትወሰድ አገር ናት:: የኬንያ መንግስት የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች ወደ ንግድ ሥራው በቀላሉ እንዲገቡ እና የተንዛዛውን የንግድ ምዝገባ ስርዓት ለማቀላጠፍ ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ቦታ በሚል በነሱ አባባል "huduma" ብለው በአንድ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል የውልና የሰነድ ማረጋገጥን ፣ የንግድ ፈቃድ እና የገቢዎች ባለሥልጣን ስራን በአንድ ማዕከል በማድረግ ባለሀብቶች ከአንዱ መ/ቤት ወደ ሌላው መስሪያ ቤት በመንከራተት እንዳይቸገሩ አድርጓል:: ይሔንን መልካም አሰራር እኛም በመቅዳት እንዳይቸገሩ ...

የንግዱን ማህበረሰብ ከግብር ጋር ስተያያዙ ቅጣቶች የሚዳርጉ መንስኤዎች!!

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

በእርግጥ ነው የንግዱ ማህበረሰብ ለተለያዩ ቅጣቶች ሲዳረግ በብዛት ይታያል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ከእውቀት ማነስ የሚመጡ ችግሮች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም መንግስት አዋጁንና ደንቡን በይፋ አውጥቶ በሥራ ላይ አውላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ወይም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጁ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት ዝርዝር መመሪያዎችን ያወጣሉ፡፡ ነገር ግን መንግስት የሚያወጣቸውንና በስራ ላይ የሚያውላቸውን ህጎች አንብቦና ተረድቶ በሥራ ላይ ከማዋል ጋር በተያያዘ የሚስተዋለው ችግር ሰፊ የሚባል ነው፡፡ በአንድ በኩል በንግዱ ማህበረሰብ በኩል የግንዛቤ ክፍተት በስፋት ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ባለሥልጣን መ/ቤቱ መመሪያዎቹን በመተግበር ሂደት የሚስተዋልባቸውን ክፍተቶች በጥናት በመለየት ቶሎ ቶሎ ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙ አያደርግም፡፡ ለምሳሌ የንግድ ድርጅቶች የትራንስፖርትም ይሁን የቀን የውሎ አበል ሲከፍሉ በአብዛኛው የባለስልጣን መ/ቤቱ ከወሰነው በላይ ይሆናል ምክንያቱም የተፈቀደው መጠን ወቅቱን እና የኑሮ ውድነቱን ያገናዘበ ባለመሆኑና እንዲሁ የሚወጣውም መመሪያ ቢያንስ እስከ አምስት ዓመት ማስተካከያ ሳይደረግበት በስራ ላይ ስለሚውል ነው፡፡ ይህም ቅጣትን ያስከትላል፡፡ በሌሎችም መመሪያዎችም እንዲሁ ተመሳሳይ ችግሮች አሉ፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ሳቢያ ቅጣት የማይቀር ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለንግዱ ማህበረሰብ የሙያ እገዛ የምናደርግ የሂሳብ ባለሞያዎችም ከጥንቃቄ ጉድለት ወይም ከእውቀት ማነስ የሚፈጸም ስህተት ሌላው የንግዱን ማህበረሰብ ለቅጣት የሚዳርግ ጉዳይ ሆኖ በተደጋጋሚ ይታያል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የንግዱ ማህበረሰብም በባለሞያው

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

የሚነገረውን ሀሳብና ምክር ወደ ጐን ብሎ ገቢውን ለማግኘትና ንግዱን ለማስፋፋት በሚል የሚፈጥራቸው ችግሮችም ህግን እስካልተከተሉ ድረስ ቅጣት ማስከተላቸው አይቀሬ ይሆናል፡፡

ለቅጣት የሚያጋልጡ ስህተቶች እንዳይፈጠሩ አስቀድሞ በንግዱ ማህበረሰብም ሆነ በሌሎች አካላት የሚጠበቁ ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ ከንግዱ ማህበረሰብ የሚጠበቀው የሂሳብ አሰራሩና የሪፖርት አዘገጃጀቱ በዘመናዊና በባለሞያዎች ታግዞ እንዲዘጋጅ ማድረግ ይገባል፡፡ ይሄም ለአጋዶው ትክክለኛ አቋሙን እንዲያውቀው ይረዳዋል፡፡ በተጨማሪም ባመነው ሪፖርት መሰረት ታክሱን ከፍሎ ከቅጣት ይድናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየጊዜው በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የሚሰጡትን ትምህርቶች መከታተልና የሚወጡ መመሪያዎችንም ተከታትሎ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ደግሞ አሁን ካለው በበለጠ የንግዱን ማህበረሰብ ለማስተማር ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ህገወጥ የሂሳብ ባለሞያዎችንም በተቻለ መጠን ለመቀነስ በአገሪቱ ካሉ የሙያ ማህበሮችና ፈቃድ ሰጪ አካላት ጋር መስራትን ይጠይቃል፡፡ ሌላው ደግሞ እዚያው የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ውስጥ የሚሰሩ ኦዲተሮች ከአሰራር ውጭ ለንግድ ድርጅቶች ሂሳብ እንደሚሰሩ የሚታወቅ ስለሆነ እንዲህ ያለው አሰራር ጤናማ የታክስ ስርዓት ከመፍጠር አንፃር አሉታዊ ተፅዕኖ ስለሚያስከትል ግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት መቆጣጠር አለበት፡፡

የግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ለንግዱ ማህበረሰብ ያለው ግልፅነቱና የቅሬታ አቀራረብ ስርዓቱ!!

የግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ደንቦችና መርሆዎች ብሎ በየቅርንጫፍና መ/ቤቱ ከለጠፋቸው ውስጥ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት ወ.ዘ.ተ… ይገኙበታል ሆኖም ግን እነዚህ መርሆዎች በአብዛኛው በትክክል እየተሰራባቸው

Scanned with CamScanner

አይደሉም። ይሄንን ለማረጋገጥ የባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት በሚጠራቸው ስብሰባዎች ላይ የንግዱ ህብረተሰብም ሆነ ባለሞያዎች ቅሬታቸውን እና አስተያየቶችን ሲሰጡ ማየታችን የተለመደ ነው። ይሁንና ብዙም ለውጥ የለም። ለምን ቢባል በባለሥልጣን መ/ቤቱ ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ላይ ቶሎ ውሳኔ የመስጠት ችግር ይታያል። በዚህም ምክንያት የንግዱ ማህበረሰብ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችና ማመልከቻዎች ከአንዱ ቢሮ ወደ ሌላ ቢሮ ምንም ውሳኔ ሳያገኙ ወይም በመመሪያው ውስጥ አልተካተተም በሚል ያለ መፍትሄ ሲሽከረከር በግልፅ ይታያል። እንዲህ ያለው ውሳኔን ያለመወሰን አካሄድ አሁን በፍጥነት ካልታረመ በስተቀር ወደፊት በግብር አሰባሰብ ስርዓቱ ላይ የበለጠ ችግር የሚያስከትል ነው የሚሆነው። ለምሳሌ የባለስልጣን መ/ቤቱ ኦዲተሮች አንድን ነጋዴ/ ድርጅት ኦዲት ካደረጉ በኋላ የሚያምንበትንም ሆነ የማያምንበትን ታክስ ሊጠይቁት ይችላሉ። ኦዲተሩን ተከራክሮ የማያዋጣው ሲሆን ወደ አለቆቻቸው ሄዶ መፍትሔ አመጣለሁ ብሎ አይሞክረውም። ምክንያቱም በግልፅ እያየን ያለነው አቤት ተብሎ መፍትሔ የሚያገኝ ጥያቄ በጣም ትንሽ መሆኑን ነው።

በዚህም ምክንያት በትክክለኛው መንገድ ጉዳይን ለማስፈፀም ከመስራት ይልቅ እያንዳንዱ ነጋዴ ወይም ድርጅት ከኦዲተሮች ጋር ድርድር ይጀምራል ማለት ነው። ስለዚህ በትክክል መንግስት ካዝና ውስጥ መግባት የሚገባው ግብር ይቀራል። ከዚህም በተጨማሪ የባለስልጣኑ መ/ቤት የስራ ሃላፊዎች በስብሰባ እና በስልጠና ብዙውን ጊዜ ስለሚያቃጥሉ እነሱንም ማግኘቱ በራሱ ትልቅ ችግር ሲሆን በስራቸው ያሉ የአንዳንድ ሰራተኞችም ስነ-ምግባርና ጸባይ ከፊታቸው የሚያስቀርብ አይደለም። ይሄም የሃላፊዎች ነጸብራቅ ነው፤ ምክንያቱም ሰውን የሚያከብርና ጥሩ አቀባበል የሚያደርግ እንዲሁም

አቤቱታ የሚሰማና የሚወስን ሃላፊ ከስሩም ያሉ ሰራተኞችም እሱን ይመለከታሉ፤ እሱንም ይመስሉታልም።

የአቤቱታ (ቅሬታ) አቀራረብ ስርዓቱን በተመለከተ ታክስ ሰብሳቢው መ/ቤት በየደረጃው የሚሰይማቸው አቤቱታ አጣሪዎች አሉ። እነዚህ አቤቱታ አጣሪ አካላት ቅሬታ ይሰማሉ። አንዳንዶቹም እዚያው ኦዲተሮቹን እንዴት እንደዚህ ተሰራ ብለው ሲሞግቱ ይታያሉ። አንዳንዶቹም ደግሞ ገዢም ብለው ከሰሙ በኋላ መልሰው ለሰራው ኦዲተር እንደገና በጋራ ብታዩት ብለው አቤቱታውን ይመልሱታል። ኦዲተሩስ እንደገና በምን ሁኔታ ነው የሚያየው። በእርግጥ በወቅቱ ያልታዩና ተጨማሪ የተገኙ ሰነዶች ካሉ ማየት የግድ ነው። አለበለዚያ ግን በአብዛኛው የሚወጣው ውሳኔ ከመጀመሪያው የውሳኔ ማስታወቂያ ሪፖርት የተለየ አይሆንም። ምክንያቱም እስካሁን በነበረው ሂደት በአብዛኛው የኦዲተሮችን የስራ ውጤት የሚቀይር አይደለም። አቤቱታ የሚያዳምጡ የኮሚቴ አባላት በተቻለ መጠን በትምህርትም ሆነ በሥራ ልምድ እንዲሁም ነገሮችን 360 ዲግሪ አዟዙሮ ሊያይ የሚችል ብሎም የንግድ ህጉን፣ የገቢ ግብር አዋጁን፣ የታክስ አስተዳደር አዋጁን የተመለከቱ ተዛማጅ ክህሎቶች ሊኖሯቸው ይገባል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ ነጋዴዎችንና ሌሎችን ሰዎችን በውጭ ያስቀመጣችሁትን ገንዘብ አምጡና በአገራችሁ ስሩበት ብለዋል፤ይሄ ከታክስ አኳያ ያለው አንድምታ!!

እርግጥ ነው አሁን አገሪቷ ካለባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት አኳያ ሲታይ በጣም አስፈላጊ ነው። ሆኖም ግን አመጣጡ ወይም አገባብ እንዴት ይሆናል? ነው ዋናው ጥያቄ። በመሰረቱ ጠ/ሚኒስትሩ ይሄን ሃሳብ ሲያቀርቡ ከህግና ታክስ አኳያ ደግሞ በቅርብ የሚመለከታቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚ/ር እና የኢትዮጵያ ገቢዎች

ጉምሩክ ባለስልጣን ይሄንኑ ሃሳብ መነሻ በማድረግ ዘርዘር ያለ መመሪያ ሊያወጡ ይገባል፡፡ ይህም ማለት አንድ ነጋዴ በውጭ አገር ገንዘብ ቢኖረውና ለማምጣትና እዚህ ያለውን ንግዱን ለማሻሻል ወይም አሁን ባለው የምንዛሪ እጥረት ምክንያት ከውጭ አገር ዕቃ ለማስመጣት ሊያውለው ቢፈልግ እንዴት ማድረግ እንደሚችልና ከአላስፈላጊ የታክስ ቅጣት የሚድንበትን መንገድ በደንብ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም አሁን ያለው አሰራር ከሽያጭ ገንዘብ እና ካፒታልን ለማሳደጊያነት ከሚውል ገንዘብ በስተቀር በንግድ ድርጅት የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚገባ ማንኛውም ገንዘብ ምንጩ ያልታወቀ ገቢ ተብሎ ግብር የሚከፈልበት መሆኑን በተግባር እያየን ስለሆነ መንግስት አሁን ካለበት ችግር ነጋዴውን ህብረተሰብ ለማበረታታትና ሌሎችም ያላቸውን የውጭ ገንዘብ ወደ አገራቸው አስገብተው መጠቀም እንዲችሉ ስራ መሰራት አለበት እላለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዲያስፖራ የባንክ አካውንቶችንም በተመለከተ ከንግድ ስራ ጋር ለማያያዝ ዲያስፖራውን ለማበረታታት በባንኮች እየተነገራቸው ያለውና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አሰራር ያሉ ልዩነቶችን በተለይም በአዲሱ የበጀት ዓመት ይሄንንም ማስተካከል የግድ ይላል፡፡

ስለተጋባዥ ጸሀፊው

ይትባረክ አምባው ከበደ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ንግድ ስራ ት/ቤት ተብሎ ከሚጠራው በባንክና ፋይናንስ በዲፕሎማ፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም አሜሪካን አገር ከሚገኘው ሊንከን ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን በማስተርስ ዲግሪ ተመርቀዋል፡፡ በቀድሞው "የኢትዮጵያ ጭነት ማመላለሻ ኮርፖሬሽን" በጀማሪ የሂሳብ ሰራተኛነት፣ በአዲስ ሜካኒካል ኢንተርፕራይዝ ኢ.ማ. በኮስት አካውንታንትነት፣ በኢትዮጵያ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በሲኒየር አካውንታንት ደረጃ፣ በደብረዘይት ማሰልጠኛ ማዕከል በፋይናንስ ሀላፊነት፣ በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን (ኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን) በፋይናንስ ዋና ክፍል ሃላፊነት፣ በኮሜት ትራንስፖርት ኢ.ማ የገቢ ሂሳቦች ዋና ክፍል ሃላፊነት፣ በላቦራ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ ማህበር በፋይናንስ ማኔጀርነት፣ በመጨረሻም በመልቲ ቾይዝ ኢትዮጵያ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር (ዲ.ኤስ.ቲቪ) በፋይናንስ ሃላፊነት ሰርተዋል። ከስምንት ዓመታት በላይ "ይትባረክ አምባው" የተፈቀደለት የሂሳብ አዋቂ ድርጅትን በመከፈት የግል የሂሳብ ሥራና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

አድራሻ፡ ቦሌ ክ/ከተማ፤ ወረዳ 03፤ የቤት ቁጥር 755/27/ሀ-3
ቦሌ ዋናው መንገድ ላይ ጃፓን ኤምባሲ፤ ገነተ ልማት ህንጻ፡ 3ኛ ፎቅ
ስልክ የቢሮ፤ +251 116-18-30-28፤ ሞባይል +251 911-51-40-28
ኢሜል፤ yitbarek41@gmail.com, yitbarek@ethionet.et
ድረ ገጽ፤ http:// www.yaaa-firm.com
ሊንክዲን፤ http://linkedin.com/in/yitbarek-ambaw-41429830

Scanned with CamScanner

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

የግብር ምንነት፣ ዓይነቶችና አስገዳጅ ሁኔታዎች!!

"ከሞትና ከግብር የሚያመልጥ ማንም የለም!"

ቤንጃሚን ፍራንክሊን

ግብር ምንድነው?

ግብር ዜጎች ለአገራቸው ልማትና እድገት ሰርተው በህግ አግባብ የሚከፍሉት መዋጮ ማለት ሲሆን ለዜጎችም የዜግነታቸው መገለጫና የስልጣኔያቸው ምንጭ ነው። በመንግስት በኩል መንግስታዊ ስራዎችን ለመፈፀምና የአገርን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ለመምራት የሚያስችል ገቢ የሚያገኝበት ስርዓት ነው። ግብር ከመንግስታት የምስረታ ታሪክ ጋር አብሮ የተፈጠረ እና እያደገ የመጣ መሆኑን የታሪክ ድርሳናት ያሳያሉ። ከዜጎች የሚሰበሰበው ግብር በአይነት ወይም በገንዘብ ሊሆን ይችላል። መንግስታት መደበኛ የሆነውን መንግስታዊ ስራ ለመስራት እንደዚሁም የሠራዊቱን ልዩ ልዩ ወጪዎች ለመሸፈን ገንዘብ ስለሚያስፈልጋቸው በግብር መልክ በዜጐቻቸው ላይ በመጣል ይሰበስባሉ።

የመንግስት ጥንካሬ ከሚለካባቸው መስፈርቶች መካከል አንዱ የግብር አሰባሰብ ስርዓት ነው። የግብር አሰባሰቡ ስርዓት ውጤታማ መሆኑ ከሚለካበት መስፈርት መካከል አንዱ የአንድ አገር ኢኮኖሚ ከሚያመነጨው ሀብት በግብር መልክ ምን ያህል ገንዘብ መንግስት ሰብስቧል የሚለው ነው። ከዚህ አንፃር የአውሮፓ አገራት፣ የአሜሪካና የኢንዶኔዥያ አገራት ከአጠቃላይ አመታዊ ምርታቸው ከ18 እስከ 25 በመቶ በግብር መልክ ይሰበስባሉ። የጐረቤታችንን ኬንያ ተሞክሮ

Scanned with CamScanner

ገ ያወበድ ኢኮኖሚዋን በአመት ከሚያመነጨው 15 በመቶ ነ
የምትሰበስበው:: አገራችን ከአጠቃላይ አመታዊ ምርት 12.5
በመቶ በመሰብሰብ ላይ ናት:: በቀጣይ 2 እና 3 አመታት በሁለተኛው
የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ማጠቃለያ 17.2 በመቶ ለማደግ
እየተሰራ ነው:: የግብር ስርዓቱ ውጤታማነት ከሚለካበት መስፈርት
አንፃር የአገራችን ሁኔታ ሲታይ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው::

አንድን አገር ወደ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ለማሸጋገር እና የዜጎችን
መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት ብሎም አገርን በቴክኖሎጂ የሰለጠነች
እንድትሆን ገቢ ወሳኝ ነው:: አገር የሚቆመው በግብር ነው:: የግብር
ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው::

የግብር አይነት እና አሳማ!!

በጥቅሉ ሲታዩ የግብር አይነቶች ሁለት ናቸው:: እነሱም ቀጥታ እና ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች ይባላሉ:: ቀጥታ ታክስ ማለት ቀጥታ ከተጠቃሚው የሚሰበሰብ ማለት ነው:: ለምሳሌ የደመወዝ ግብር፣ የቤ ግብር ይጠቀሳሉ:: ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች ከተጠቃሚው የሚሰበሰ ሲሆን ለምሳሌ ተርንኦቨር ታክስ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስና ኤክሳይዝ ታክስ ናቸው:: እነዚህ የታክስ አይነቶች በአገራችንም ሆነ በዓለማቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረጉ ከመሆኑም በላይ የታክስ መሠረቱን ለማስፋት የሚያግዙና የመጨረሻው ተጠቃሚ የሚከፍላቸው ናቸው:: የአገራችን የግብር ስርዓት ከ10 እስከ 35 በመቶ የሚደርስ አዳጊ (ፕሮግረሲቭ) የሚባል ነው:: ለመሆኑ የግብር መሰረታዊ አላማ ምንድነው? የሚለ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም:: መነሳቱም ተገቢ ይሆናል:: ግብር በርካታ አላማዎች አሉት:: በቀዳሚነት የሚጠቀሱት ግን የሚከተሉት ናቸው::

- ፍትሐዊ የገበያ ውድድር እንዲኖር ማድረግ፣

ለልማትና አገራዊ እድገቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

- ታክስና ግብርን በተመለከተ የወጡ የህግ ማዕቀፎች ፍትሐዊ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩ ማድረግ፣
- የአገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት መሰብሰብ፣
- በብቃት የተሰበሰበውን ገቢ ለአገር ልማት እንዲውል ማድረግ እና
- የአገር እድገት ተመጣጣኝ እንዲሆን ያደርጋል የሚሉት ዋና ዋና የግብር አላማዎች ናቸው::

የግብር ከፋዮች ደረጃ እና ግዴታዎች!!

ግብር ከፋዮች በሦስት ደረጃ ተከፍለው የሚታዩ ናቸው:: እነሱም፡-

- ከ46 ሚሊዮን ብር በላይ ዓመታዊ ሽያጭ (ገቢ) ያላቸው ከፍተኛ ግብር ከፋይ ይባላሉ፣
- ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ዓመታዊ ሽያጭ (ገቢ) ያላቸው መካከለኛ ግብር ከፋይ እና
- ከ1 ሚሊዮን ብር በታች ዓመታዊ ሽያጭ (ገቢ) ያላቸው አነስተኛ ግብር ከፋዮች ይባላሉ::

የታክስ ከፋዮች ደረጃ ከሚወጣባቸው ዋነኛ መስፈርት ውስጥ አንዱ ዓመታዊ የሽያጭ መጠን ነው:: የግብር ከፋይነት ደረጃ ከላይ የተገለፀው ቢሆንም ከግብር ከፋይነት ግዴታ አንፃር ግብር ከፋዮች በሶስት የተከፈሉ ናቸው፡-

1. አመታዊ የሽያጭ መጠናቸው ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ከሆኑ ወይም ካፒታላቸው 1 ሚሊዮን ብር ባይሞላም ኃ.የተ.የግ ማህበር ከሆነ የ"ሀ" ግብር ከፋይ ይሆናሉ፣

2. የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች አመታዊ ሽያጫቸው ከ500,000 እስከ 1,000,000 ብር የሆነ ሲሆን ኃ.የተ.የግ ማህበርን አይጨምርም
3. ደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የሚባሉት አመታዊ ሽያጫቸው ከ500,00 ብር በታች የሆኑ ናቸው።

የግብር ከፋይ ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ ግብር ከፋዮች ግዴታ አለባቸው። ደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች የሒሳብ መዝገብ እንዲይዙ በህግ ይገደዳሉ። ግብይታቸውም በደረሰኝ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጠቀም ይኖርባቸዋል። የሒሳብ መዝገብ አያያዝን በተመለከተ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች የሒሳብ ዝ ወጪ ንና የንብረት መዝገብ እንዲኖራቸው ግዴታ ተጥሎባቸዋል። የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ቀላል የሒሳብ መዝገብ ነው መያዝ የሚጠበቅባቸው። የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ግን የሒሳብ መዝገብ ቢይዙ ጥሩ ነው። ነገርግን በህግ አይገደዱም። የግብር አወሳሰኑ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በግምት ወይም በቁርጥ ግብር ተመን ዘዴ ሲሆን የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮች ግን በሚያቀርቡት የሒሳብ መዝገብ መሠረት ነው የገቢ ግብር የሚተመነው። የግብር ማስታወቅን በተመለከተ በትክክል የሰራውን እምኖ ግብሩን እንዲያሳውቅ እድል የሚሰጠው ለግብር ከፋዩ ነው። ግብር ከፋዮች በሶስት መንገድ ግብራቸውን ያሳውቃሉ።

1. ገቢ፣ ወጪና ትርፍን ለሰጠተው ያስዘኝ የግብር ሠዘን ደሂ ነው ብሠ ያሳውቃስ፤
2. ገቢ፣ ወጪ፣ ከገቢው ሳይ ወጪውን በማቀናነስ ከሰሬያሰዘ ብሠ ሲያሳውቀ ይችሳስ፤
3. ገቢ ወጪ እና ከገቢው ሳይ ወጪ ሲቀነስ ከሠንገስት ተሠሳሽ ልስ ብስሠ ማሳሠት ይችሳስ፤
4. ምንም ስሬ እልሰሬሀም ብሎ ሲያሳውቀ ይችሳስ።

ይሄን ሁሉ የማድረግ መብት የተሰጠው ለግብር ከፋዩ ነው። ነገር ግን ግብር ከፋዩ በተደጋጋሚ ኪሳራ የሚያሳውቅ ከሆነ፣ በተደጋጋሚ ተመላሽ የሚጠይቅ ከሆነ ወይም ብዙ የሚያሳውቅትና በተደጋጋሚ ደግሞ አትርፌያለሁ ብሎ የሚያሳውቀው የገንዘብ መጠን ዝቅተኛ እና የሚታመን ካልሆነ ግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ኦዲት ያደርጋል። በኦዲት ሒደቱ ክፍተቶች ከተገኙ ማለትም ግብር ከፋዩ መክፈል እየተገባው ሳይከፍል የቀረው ገንዘብ ካለ ከነወለዱና መቀጫው እንዲከፍል ይደረጋል። ከሰነድ ማጭበርበር ጋር በተያያዘ የህግ መተላለፍ ፈፅሞ ከሆነም በህግ ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል።

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር ግብርን ባለመብቱ ያሳውቃል ሲባል መረጋገጥ ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ መዘንጋት የለበትም። ለምሳሌ ግብር ከፋዩ ስራውን የሚያካሂደው ደረሰኝ እየቆረጠ መሆኑ እና በአግባቡ ግዴታውን እየተወጣ ስለመሆኑ ግብር ከፋዩ መስሪያ ቤት የተለያዩ የመረጃ ማጣሪያ ስርዓቶችን በመዘርጋት የማረጋገጥ ስራ ይሰራል። በማጣራት ሒደት የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን የማይጠቀም ከሆነና በደረሰኝ ስራውን የማይሰራ ከሆነ በህግ ተጠያቂ ይሆናል።

ከዚህ አከፋፈል አንፃር ግብር ከፋዩ ተጨማሪ እሴት ታክስን በየወሩ ያሳውቃል፣ ተርንኦቨር ታክስ በየሶስት ወሩ እና ዓመታዊ ግብርን አመቱን ጠብቆ እንዲያሳውቅ ይጠበቅበታል። ከዚህ ውጭ ግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት የመረጃ ባለሙያዎችን በተለያዩ መንገዶች በማሰማራት ግብር ከፋዩ ስራውን በትክክለኛ መንገድና ግዴታን በአግባቡ መንገድ እየፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስራ ይሰራል ማለት ነው።

Scanned with CamScanner

ተደራራቢ ግብርን በተመለከተ

በመሠረቱ ተደራራቢ ግብር የሚባል ነገር የለም:: ተደራራቢ ግብር እስ ተብሎ የሚነሳው ሒደቱን ካለመገንዘብ ነው:: ለምሳሌ የተጨማሪ እሴት ታክስ መሠረታዊ ከሆኑ አላማዎቹ አንዱ ተደራራቢ ታክስን ማስቀረት ነው:: ለምሳሌ አንድ ድርጅት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ግብር ከፋይ ቢሆን የሚገዛው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገበ ድርጅት መሆን አለበት:: ሲሸጥም የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ በመቁረጥ ነው:: ስለሆነም ድርጅቱ በሚገዛበት ጊዜ የከፈለውን ተጨማሪ እሴት ታክስ በሽያጭ ወቅት በመቀነስ ለመጨረሻው ተጠቃሚው ያስተላልፈዋል ማለት ነው:: በታክስ ህጉ መሠረት የተጨማሪ እሴት ተመዝጋቢ ድርጅት የከፈለውን እንዲያቀናንስ እድል ተሰጥቶታል:: ስለሆነም ድርጅቱ የራሱን ቀንሶ ስለሚያስቀር ደብል ታክስ የሚከፍልበት ሁኔታ የለም:: ነገር ግን ታክሱን የሚከፍለው የመጨረሻው ተጠቃሚ ነው::

የግብር ከፋዩን ትክክለኛነት ማረጋገጥ!!

አንድ ከፋይ በስራው ልክ ትክክለኛውን ግብር እያሳወቀ መክፈሉን ለማረጋገጥ የተዘረጉ የቁጥጥር ስርዓቶች አሉት:: ዋና ዋና የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው:-

- ግብር ከፋዩ በደረሰኝ እየሰራ መሆኑ ግዴታውን በአግባቡ እየተወጣ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፤
- በጉምሩክ በኩል እቃዎች ይመዘገባሉ፤
- የገቡ እቃዎች ከተሸጠውና መጋዘን ውስጥ ካለው ጋር በኦዲት የማገናዘብ ስራ ይሰራል:: በዚህ ሒደት የግብር ግዴታውን ካልተወጣ ወደ ኋላ እስከ 5 ዓመት ድረስ በመሄድ የሚጠየቅበት የህግ አሰራር አለ::
- የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመረጃ ሰራተኞች የሚኖራቸውን መረጃና ስጋቶችን መሠረት በማድረግ የማጣራት ስራ ይሰራሉ:: በተለያዩ የመረጃ አማራጮች ግብር ከፋዩ ትክክለኛውን ግብር መክፈሉን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል::

በጉምሩክ በኩል እቃዎች ይመዘገባሉ፣

የገቡ እቃዎች ከተሸጠውና መጋዘን ውስጥ ካለው ጋር በኦዲት የማገናዘብ ስራ ይሰራል:: በዚህ ሒደት የግብር ግዴታውን ካልተወጣ ወደ ኋላ እስከ 5 ዓመት ድረስ በመሄድ የሚጠየቅበት የህግ አሰራር አለ::

የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመረጃ ሰራተኞች የሚኖራቸውን መረጃና ስጋቶችን መሠረት በማድረግ የማጣራት ስራ ይሰራሉ:: በተለያዩ የመረጃ አማራጮች ግብር ከፋዩ ትክክለኛውን ግብር መክፈሉን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል::

በግብር ከፋዩ እና በግብር ወሳኝ መ/ቤት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ስህተቶች!!

በግብር ከፋዩም ሆነ በግብር አወሳሰን ሂደቱ የሚታዩ ችግሮች ሰፊ ናቸው:: ዋና ዋና የሚባሉትን ማየት ይጠቅማል::

በግብር ከፋዩ የሚፈፀሙ ስህተቶች!

- ትክክለኛ ግብርን አሳውቀ የመክፈል ባህል በሚፈለገው ደረጃ አለማደግ
- ደረሰኝ ዘይቶ ያለመቀበልና በወቅቱ ግብይት ስተፈፀመበት ምርትም

Scanned with CamScanner

ሆነ አገልግሎት ደረሰኝ ቀርጦ አለመስጠት ችግር በስፋት ይታያል። በደረሰኝ ግብይት በመፈፀሙ ግብር ይከፈላል ማለት አይደለም፣ ነገርግን የድርጅቱን ገቢ ግን ያሳያል:: ለምሳሌ ዳቦ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ነው:: ዳቦ ቤቶች ግን ደረሰኝ እንዲሰጡ የሚያስፈልገው ዓመታዊ የሽያጭ መጠኑ ሲታወቅ የግብር ከፋይነት ደረጃንና የግብር መጠን በመረጃ ላይ ተመስርቶ ለመወሰን ያስችላልና ነው:: በአጠቃላይ ደረሰኝ የመረጃ ስርዓት ነው:: አንድ ድርጅት ደረሰኝ አልቆረጠም ማለት መረጃ እያጠፋ ነው ማለት ነው::

- በደረሰኝ አለመስራት፣
- በመክፈያ ማሽን አለመስራት፣
- ሀሰተኛ ሰነድ የማተምም ሆነ የመጠቀም ችግሮች ይታያሉ:: ሀሰተኛ ሰነድን ተጠቅሞ ኪሳራን ማሳወቅ አልሰራሁም ማለትና ተመላሽ የመጠየቅ ድርጊቶች ይፈፀማሉ::
- ያልተገዛን እቃ እንደተገዛ በማድረግ ሐሰተኛ ሰነድ አቅርቦ ተመላሽ መጠየቅ፣
- ግብይት ሳይኖር ግብይት እንዳለ ማስመሰል የሚሉ ችግሮች በተደጋጋሚ የሚታዩ ናቸው::

በግብር አወሳሰኑ የሚታዩ ክፍተቶች!

- ኮንትሮባንድ በግብር ስርዓቱ ላይ የሚታይ ሌላው ችግር ነው
- የግብር ከፋዩ ሒሳብ አሰርቶ በሚያመጣውና በባለስልጣን መ/ቤቱ ኦዲተሮች መካከል አንዳንዴ አለመግባባት ይታያል:: በእርግጥ ሁሉም ግብር ከፋይ ማህበረሰብ በራሱ ሙያተኞች ኦዲት አስደርጎ የሚያመጣው የኦዲት ሪፖርት የተጭበረበረ ነው ማለት አይቻልም:: የሒሳብ ባለሙያዎችም

በዶ/ር አቡሽ አያሌው
ፋይናንስ ማኔጅመንት

ሆኑ የንግዱ ማህበረሰብ ሒሳባቸውን በአግባቡና በትክክል አሰርተው ወደ ግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የሚያመጡ አሉ:: አንዳንድ ግብር ከፋዮች ደግሞ ትክክለኛ ሒሳብ ለማሳወቅ ሳይሆን የኦዲት ቴክኒኮችንና ሰነዶችን በመጠቀም ተአማኒነት የሌለው ነገርግን ደረጃውን የጠበቀ የሒሳብ መዝገብና ሪፖርት አዘጋጅተው የሚመጡ ግብር ከፋዮች አሉ:: ደረጃውን ስለጠበቀ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት አይደለም:: ስለሆነም የቀረበውን የሒሳብ መዝገብና ሪፖርት በሌሎች ማረጋገጫ መንገዶች ማረጋገጥ ይገባል::

ለምሳሌ ምን ያህል እቃ ወደ አገር ውስጥ እንዳስገባ ፣ ካስገባው እቃ ምን ያህሉን እንደሸጠና በመጋዘን ውስጥ ምን ያህል አለ ተብሎ የሚወሰድ አይደለም:: በአጠቃላይ በግምት ላይ የተመሰረተው የቀን ገቢ ግምት የታክስ ስርዓት ለስህተት የተጋለጠ በመሆኑ የግብር ስርዓቱን ፍትሀዊነት ጥያቄ ውስጥ መክተቱ አይቀርም:: ይሄንን ለማስተካከል የሚሰሩ ስራዎች አሉ:: የሒሳብ መዝገብ የሚይዙ ግብር ከፋዮችም ቢሆኑ ተመሳሳይ ገቢና ወጪ ይኖራቸዋል ተብሎ አይጠበቅም:: አንዳንዱ እያንዳንዱን ነገር በደረሰኝ ይሸጣል:: ገቢውንና ወጪውን በትክክል የሚያሳውቅ ግብር ከፋይ አለ:: በሌላ በኩል ወጪውን የሚያገርና ገቢውን የሚቀንስ ግብር ከፋይ አለ:: ወጭን ማናርና ገቢን መቀነስ ውጤቱ ትርፍን ዝቅተኛ ያደርገዋል:: ትርፍ የለሽ ይሆናል ወይም ኪሳራ ሊያመላክት ይችላል:: እንዲህ ያሉ ችግሮች የግብር ስርዓቱ ፍትሀዊነትን ያዛባሉ:: ይሄ እንደተጠበቀ ሆኖ የንግድ ድርጅቶች የሚከተሉት የማርኬቲንግ ስትራቴጂ አንዳቸውን የበለጠ ትርፋማ ሊያደርጋቸው ሌላውን ደግሞ ለኪሳራ ሊዳርግ ይችላል::

ስለሆነም የሒሳብ መዝገብ ስለያዙ፣ በተመሳሳይ የካፒታል መጠንና በተመሳሳይ ገቢ፣ ወጪና ትርፍ ይኖራቸዋል ተብሎ አይጠበቅም:: እነዚህ ሁኔታዎች በታክስ ስርዓቱ ላይ የፍትሀዊነት መዛባትን

Scanned with CamScanner

ያስከትላሉ:: ይህ ሁሉ የሚያሳየን ችግሩን ለመፍታትና ዘመናዊ የታክስ ስርዓት ለማስፈን መስራት እንዳለበት ነው::

በግብር ከፋዩ ላይ የህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ጉዳዮች!

ግብርን በወቅቱ አሳውቆ አለመክፈል በተለያዩ ደረጃዎች ተጠያቂነትን ያስከትላል:: በወቅቱ ያልተከፈለ ግብር ካለ ባልተከፈለው ግብር ወለድና መቀጮ ተጨምሮ እንዲከፈል ይደረጋል:: ግብር ከፋዩ ግብርን ባለመክፈል የሄደበት መንገድ ማጭበርበርን ያስከተለ ከሆነ የፍትህ ብሄርና የወንጀል ተጠያቂነትን ያስከትላል:: ለምሳሌ ደረሰኝ ተጠቅመህ መስራት ሲገባህ አለደረሰኝ ሲሰራ ቢገኝ በአንድ ደረሰኝ ብቻ ከ25,000- 50,000 የገንዘብ መቀጮ ይጣልበታል:: እስከ 5 አመት ደግሞ በእስራት ይቀጣል:: በሌላ በኩል ሐሰተኛ ሰነድ በመጠቀም ግብይት ሲፈፅም ከተገኘ እስከ 100,000 የሚደርስ ገንዘብ ይቀጣል:: በተጨማሪም ከ7 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል:: ይሁን እንጅ በሐሰተኛ ሰነድ ጥቅም ላይ የዋለው ደረሰኝ ከ100,000 ብር በላይ ከሆነ የገንዘብ መቀጮው የሚሆነው ደረሰኙ ላይ ያለው ገንዘብ ይሆናል:: እስራቱ ደግሞ ከ10 እስከ 15 ዓመት ይሆናል:: በግብር አስተዳደሩ አዋጁ ላይ በግልፅ የተቀመጠ ጉዳይ ነው:: ሌላው ጉዳይ ከማተሚያ ድርጅቶች ጋር የተያያዘው ነው:: ፈቃድ ላልተሰጠው ማንኛውም ድርጅት ደረሰኝ አትሞ ቢገኝ በ200 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል:: ለሁለተኛ ጊዜ አትሞ ቢገኝ የማተሚያ ማሽኑ ይወረሳል::

የግብር ስርዓቱን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ከማዘመን አንፃር!

የአገሪቱን የግብር ስርዓት ለማዘመን በባለስልጣን መ/ቤቱ የተለያዩ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ይውላል:: በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥ ሲክታስ የሚባል ሶፍትዌር ጥቅም ላይ ውሏል:: ይህ ሶፍትዌር የግብር ከፋዩን ታክስ በራሱ አስልቶ የማውጣትና መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ የማደራጀት ተግባርን ያከናውናል:: ሌላው የሽያጭ መመዝገቢያ ማሽን ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ወደ ግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ሳይመጣ ባለበት ሆኖ ግብሩን የሚያሳውቅበት ሲስተም ተዘርግቷል:: ግብር ከፋዩ ግብሩን ባለበት ከማሳወቅ ባሻገር ባለበት ሆኖ ታክሱን የሚፈፅምበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የኢ-ፔይሜንት የአሰራር ስርዓት እየተሰራበት ነው:: በጉምሩክም በኩል አሲኩዳ በሚባል ሶፍትዌር የጉምሩክ መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ የሚይዝ ነው:: የአስመጪዎች አጠቃላይ እንቅስቃሴ በዚሁ ሶፍትዌር በዘመናዊ መንገድ መረጃው ይያዛል:: ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እቃዎች የስጋት ደረጃ የሚጣልበት ማለትም ከፍተኛ ስጋት ያለበት ቀይ፣ መካከለኛ ስጋት ቢጫ እና ዝቅተኛ ስጋት አረንጓዴ በሚል የሚፈረጅበት ስርዓት ተዘርግቷል:: በከፍተኛ ስጋት ማለትም በቀይ ደረጃ የተፈረጀ ከሆነ ሰነዱም ሆነ እቃው ከጉሙሩክ ሳይወጣ እቃውም ሆነ ሰነዱ እንዲመረመር ይደረጋል:: የስጋት ደረጃው ቢጫ ወይም መካከለኛ ከሆነ እቃው ተለቆ ሰነዱን የማጣራት ስራ ይሰራል:: በሌላ በኩል የስጋት ደረጃው ዝቅተኛ ወይም አረንጓዴ ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ ሰነዱም ሆነ እቃው ይለቀቅና በድህረ -ኦዲት የማጣራት ስራ ይሰራል::

ይህ የሚሆነው አገልግሎቱን ለማዘመን እንደዚሁም ሁሉንም ግብ ከፋይ በተፈለገው ፍጥነት መድረስ ስለማይቻል ስጋትን መሠረ ያደረገ የአመራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ለማድረግ ነው

Scanned with CamScanner

በዓለም አቀፍም ደረጃ ያለው የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ተሞክ ከአገራችን ጋር ተቀራራቢነት ያለው ነው:: ከዓለም አቀፍ የጉሙሩክ ድርጅት ጋር ተመሳሳይ በሆነ አሰራር ነው የአገሪቱ የጉሙሩክ ሬ እየተሰራ ያለው::

የታክስና የንግድ ስርዓቱ ከፍትሐዊነት አንፃር!!

የታክሱም ሆነ የንግድ ስርዓቱ በአገራችን ፍትሀዊ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም:: ሰዎች የሚሰሩት በመሆኑ ከሒሳብ አመዘጋ ጀምሮ ወጣ ገባነት ይስተዋላል:: የቀን ገቢ ትመናው የሚሰራ በግምት ነው :: የግምት ግብር አጣጣል ደግሞ ከፍ የማለት፣ ዝ የማለትና ትክክል የመሆን እድል ያለው ነው:: የቀን ገቢ ትመና ሲሰራ የግብር ከፋዩን ተባባሪነት የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል:: ስለሆነም ግብር ከፋዩ ሀብረተሰብ በቀን ገቢ ትመናው ወቅት በቦታው በመገኘት ትክክለኛና አሳማኝ መረጃ በማቅረብ የቀን ገቢውን፣ ወጪውንና ትርፉን ማሳወቅ ይጠበቅበታል:: ሌላው በሚተምነው አካል ያለው ችግርም ፍትሃዊነትን ለማዛባት የራሱን ሚና ይጫወታል:: ምንም እንኳን በተመሳሳይ ካፒታልና በተመሳሳይ የንግድ አካባቢ ያሉ ድርጅቶች ቢሆኑም ተመሳሳይ ሽያጭ ፣ ተመሳሳይ ወጪና ተመሳሳይ ትርፍ ይኖራቸዋል ብሎ የቀን ገቢ ግመታ ማካሄድ ትክክል አይደለም::

ውጤታማ ግብር ከፋዮችን የማበረታታት ስርዓቱ!!

የንግድ አዋጁ በትክክል ግዴታቸውን የሚወጡና ታማኝ ግብር ከፋዮች መሸለምና እውቅና መሰጠት እንዳለበት ይደነግጋል:: ነገር የአገሪቱ የመረጃ አያያዝ ዘመናዊ ፣ የተጠናከረና ውጤታማ ባለመሆ ትክክለኛውንና ተአማኝ የሆኑ ግብር ከፋዮችን በላቂ በሆነ መንገድ ለመለየት ያስቸግራል:: ዛሬ ትክክለኛ ግዴታውን በአግባቡ የሚወጣ

ታማኝ ነው ተብሎ የተሸለመና እውቅና የተሰጠው ግብር ከፋይ ነገ ደግሞ ግብር በማጭበርበር ተግባር ላይ ተሰማርቶ የሚገኝበት እድል ሰፊ ነው:: እንደዚህ ያለው ሁኔታ ለማንም አስተማሪ አይሆንም:: ይሄም ሆኖ ግብር ከፋዩን ለማበረታታት የሚሰሩ አገራዊ ስራዎች አሉ:: ለምሳሌ በተለያዩ ምክንያቶች ወለድና ቅጣት ያለበት ድርጅት ግዴታውን በ30 ቀን የሚከፍል ከሆነ ከወለዱና ከቅጣቱ እስከ 80 በመቶ ድረስ ተቀናሽ የሚደረግበት የማበረታቻ ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል::

በሌላ በኩል ከጉሙሩክ ስርዓቱ ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ እቃ የሚያስገቡ ድርጅቶች ዝርዝር መረጃቸው በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን በመታገዝ በየጊዜው ተመዝግበው ይያያዛሉ:: የሚያስመጡቸውን እቃዎች በተመለከተ ምንም አይነት ስህተት ያልፈፀመ ከሆነ ወደ አገር ውስጥ ሲያስገባ ያሳወቀው እውቅና በፍተሻ የተገኘው ተመሳሳይ ከሆነ ከዚህ ጋር በተያያዘ በቀደመ ታሪኩ ምንም አይነት የተፈፀመ ስህተት ከሌለ፣ የሚያስመጣቸውን የእቃ አይነቶች፣ እቃው የተሰራበትን አገር፣ እቃዎችን ከሚያስመጣበት አገር አንፃርና ሌሎች የጉሙሩክ መስፈርቶች መሠረት ተመዝነው የተሻለ ግብር ከፋዮች ተለይተውና ታማኝ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ተብለው የሚያስመጡት እቃ ያለምንም ፍተሻ ወደ መጋዘናቸው በቀጥታ እንዲገባ ይደረጋል:: ፍተሻ እንኳን ቢኖር ፍተሻው የሚካሄደው በራሳቸው መጋዘን ውስጥ ነው:: ይሄ በአገሪቱ ተግባራዊ ከሚደረጉ የማበረታቻ ስርዓቶች ውስጥ የሚታይ ነው:: ሌሎችም የማበረታቻ ስርዓቶች ያሉ ሲሆን ደረጃ በደረጃ እንደ ሁኔታው ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው::

የግብር ጉዳይ ለመንግስት ወይም ለአንድ ድርጅት የሚተው አይደለም:: ግብር የሁሉም ዜጋና የህልውና ጉዳይ ነው:: አንድ አገር የማደግ ያለማደግ፣ ዜጎች የስራ እድል የማግኘት ያለማግኘት፣ የማህበራዊ ተቋማትን የማስፋፋትና ያለማስፋፋት፣ የአገር ሰላምና

ደህንነትን የማረጋገጥ ወይም ያለማረጋገጥ ጉዳይ ነው። ማንም አገሬን እወዳለሁ የሚል ዜጋ ለግብር ውጤታማነት ይጠበቅበታል። እውነተኛና ታማኝ መሆን ያስፈልጋል። ለራስ ነው። ምክንያቱም አንድ ቀን መታወቁ አይቀርምና። ደግሞ መልካም ስምንና ዝናን ያጠፋል። የህሊና ወቀሳን ዜግነታዊ ኃላፊነታችንን መወጣት ይጠበቅብናል።

ሣብዕ ትረካ TUBE

የስራ ማስኬጃ ካፒታልን በምርጥ ደረጃ ለማስተዳደር

‹‹ገንዘብህ ወደኪስህ ከመግባቱ በፊት ስባከንህ ስትጨርሰው!›› ቶማስ ጀፈርሰን



በአንድ ድርጅት ውስጥ በየቀኑ የሚተገበሩ ልዩ ልዩ ድርጊቶች ወይም ስራዎች አሉ። ድርጅት ማለት የድርጊቶች ጥርቅም ማለት ነው። በየትኛውም የድርጅቱ ዲፓርትመንት ውስጥ የሚደረጉ ክንውኖች ደግሞ በሁለት ይከፈላሉ፤ ገንዘብ የሚያመጡ (ገቢ ለማድረግ የሚያስችሉ) ወይም ገንዘብ ወጪ የሚያደርጉ ተብለው። የክንውኖቹ አይነት ይለያያል፤ ይሁን እንጂ ወይ ገንዘብ አስወጪ ናቸው ወይም አስገቢ ናቸው። ገንዘብ እያስወጡ ወደ ገቢ የማይቀየሩ ክንውኖችን ደግሞ ብክነት አምጭ ክንውኖች እንላቸዋለን።

Scanned with CamScanner

የስራ ማስኬጃ ካፒታል ምንድን ነው?

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

የስራ ማስኬጃ ካፒታል ማለት ድርጅቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ያለውን ስራ ሊሸፍን የሚችል በባንክ ያለ ገንዘብ የስራ ዘመን ወደ ገንዘብ ሊቀየሩ የሚችሉ ንብረቶችን በአንድ በኩል ያለ ገንዘብና በፍጥነት በኩል ደግሞ ድርጅቱ በአንድ ዓመት የስራ ዘመን ውስጥ (በአብዛ ሁለት ወራት) የስራ ዘመን ውስጥ ላሉት የስራ ክንውኖች ወጪ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ተከፋይ እዳዎችን ያመለክታል።

በሌላ አገላለፅ በአንድ ዓመት የስራ ዘመን ውስጥ ተከፋይ የሚሆኑ የስራ ክንውኖችን ለመሸፈን የሚያስችል ባንክ ውስጥ ያለውን የገንዘብ መጠንና በፍጥነትም ወደ ገንዘብ የሚቀየሩ ልዩ ልዩ ንብረቶች (ለምሳሌ የሚመነዘሩ ቼኮችና የሚሸጡ የጥሬ ዕቃ፣ ከፊል ያለቀላቸውና ሙሉ በሙሉ ያለቀላቸውን የምርት ክምችቶችን እንዲሁም ተሸጠው ያልተሰበሰቡ የምንመራበት የማኔጅመንት ችሎታ ነው።

አንድን ቢዝነስ በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ ለማስተዳደር የሚያስፈልግ የካፒታል መጠን ‹‹ ኔት ወርኪንግ ካፒታል ›› በመባል ይጠራል። ኔት ወርኪንግ ካፒታል ወይም የተጣራ የስራ ማስኬጃ ካፒታል የምንለው ድርጅቱ በአንድ ዓመት ውስጥ ሊከፍላቸው የሚገቡትን ክፍያዎች ሊሸፍንለት የሚችለው ያለው የሃብት መጠን ነው። የተጣራ ስራ ማስኬጃ የምንለውም የአጭር ጊዜ ተከፋይ ዕዳዎችን ከአጭር ጊዜ ሃብቶች ላይ በመቀነስ የሚገኝ ምጣኔ ሲሆን እነዚህንም ከድርጅቱ የሃብትና እዳ ሚዛን መግለጫ ሪፖርት ላይ ማግኘት ይቻላል። የአጭር ጊዜ ሃብቶች የምንላቸው በአካውንቲንግ ቋንቋ ‹‹Short Term Assets›› ወይም ‹‹Current Assets›› በመባል የሚጠሩ ሲሆን በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙት በድርጅቱ አካውንት ላይ አሁን ላይ በእጅ (በባንክ)ያለ ጥሬ ገንዘብ (Cash)፣ የጥሬ ዕቃ

ክምችት መጠን (Inventory)፣ እንዲሁም ለደንበኞች ተሸጠው ነገር ግን ያልተሰበሰቡ ገቢዎች (Account Receivable) ናቸው። የድርጅቱ የአጭር ጊዜ ተከፋይ ዕዳዎች የምንላቸው ደግሞ በአካውንቲንግ ቋንቋ ‹‹Short Term Liabilities or Current Liabilities›› በመባል ይጠራሉ። በዚህ ውስጥ የሚካተቱት ድርጅቱ ከአቅራቢዎች እቃዎችን ገዝቶ ክፍያ ያልፈፀመባቸውንና በበጀት ዓመቱ ውስጥ ሊከፍላቸው የሚገቡ የብድር እዳዎችን ነው። እነዚህ ሁለት ተከፋይ ወጭዎች ‹‹አካውንት ፔየብልስ›› (Account Payables) በመባል ይጠራሉ።

የአንድን ድርጅት የተጣራ የስራ ማስኬጃ ካፒታል መጠን ከላይ የተጠቀሱት ምጣኔ የሚወስኑት በመሆኑ እነዚህን በሚገባ ማስተዳደር የቻለ ድርጅት ውጤታማ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው። እነዚህ የአንድ ድርጅት የስራ ማስኬጃን መጠን የሚወስኑ ጉዳዮች መጠናቸው (ዋጋቸው) ከአንድ ድርጅት ወደ ሌላ ድርጅት እንደ ንግድ ዘርፉ ዓይነት ባህሪያቸው ይለያያል። አንዳንድ ድርጅቶች ለምሳሌ እንደ ሱፐርማርኬቶችና ሬስቶራንቶች ያሉ ለደንበኞች የሚሸጧቸውን ሸቀጦችና አገልግሎቶች ወዲያውኑ የሽያጭ ገንዘቡን ስለሚቀበሉ የተሰብሳቢ ሽያጭ መጠናቸው (አካውንት ሪሲቬብልስ) እጅግ አናሳ ነው። አንዳንድ ከፍተኛ አምራች ድርጅቶች በጥሬ ዕቃ ክምችት መልክ በመጋዘናቸው የሚይዙት ኢንቬንተሪ መጠን ደግሞ ከፍተኛ ነው። እንደ ቶዮታ የመሰሉ መኪና መገጣጠሚያ ኩባንያዎች የ‹‹Just In Time›› ፍልስፍናን ስለሚከተሉ ለሚገጣጥሟቸው መኪኖች የሚያስፈልጓቸውን ዕቃዎች በፈለጉ ጊዜ ከአቅራቢዎች በማዘዝ ወዲያው ስለሚያመጡላቸው ቶዮታ አምራች ድርጅት ቢሆንም የኢንቬንተሪ መጠኑ ግን ዜሮ ነው። ስለሆነም የተጣራ ስራ ማስኬጃ አስተዳደር እንደ የድርጅቱ አይነትም የትኛውን ትኩረት ሰጥቶ ማስተዳደር እንደሚያስፈልግ መለየት ያስፈልጋል።

Scanned with CamScanner

የሚከተለውን ቀመር እንመልከተው

የተጣራ ስራ ማስኬጃ = የአጭር ጊዜ ንብረቶች - የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳዎች

የአጭር ጊዜ ንብረቶች = ጥሬ ገንዘብ ‹‹+›› ተሰብሳቢ ገቢ ‹‹+›› ኢንቬንተሪ

የአጭር ጊዜ እዳዎች = የዱቤ ገዥ ‹‹+›› ለአበዳሪዎች የሚከፈል

በስራ ማስኬጃ አስተዳደር ውስጥ ትልቁ ትኩረት የተጣራ ስራ ማስኬጃ መጠን ኔጌቲቭ እንዳይሆን ሲሆን ኔጌቲቭ መሆኑ የሚያሳየው ድርጅቱ የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳዎቹን ለመክፈል የሚያስችል ገንዘብና በቀላሉ ወደገንዘብ የሚቀየሩ ሌሎች ንብረቶች በበቂ ሁኔታ እንደሌሉት ያሳያል፡፡ ይህም ሆነ ማለት ድርጅቱ ስራውን የማስተጓጎል አደጋ ይፈጠርበታል፡፡ በመሆኑም ሌሎች የአጭር ጊዜ የብድር አማራጭ ምንጮችን ወደማፈላለግ ለማምራት ይገደዳል፡፡ ይሁን እንጅ የተጣራ ስራ ማስኬጃችን ውጤቱ ‹‹ፖዘቲቭ›› ም ቢሆን እንኳን የሽያጭ ገቢዎቻችንን ለመሰብሰብ የሚወስድብን ጊዜ ረዥም ቀናትን ከፈጀ፣ ተከፋይ እዳዎቻችንን ለመክፈል ደግሞ የሚጠበቅብን ጊዜ አጭር ከሆነ ድርጅቱ ችግር ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡ በመሆኑም የስራ ማስኬጃን በምርጥ ደረጃ ማስተዳደር ማለት የስራ ማስኬጃ መጠኑን መጠበቅ ላይ ብቻ ሳይሆን መክፈል የሚገባቸውን ክፍያዎች በተገቢው ጊዜ ውስጥ ለመክፈል በቂ የጥሬ ገንዘብ ምጣኔን ማስተካከሉ ላይ ነው፡፡

የስራ ማስኬጃ ካፒታልን በሚገባ ማስተዳደር የቻሉ አመራሮች የድርጅቱን ዕለታዊ ስራዎች ያለምንም የገንዘብ እጥረት ለመሸፈን የሚችሉ ሲሆን ድርጅቱ የሚያስፈልገውን የስራ ማስኬጃ ካፒታል መጠን በቀነሱ ቁጥር ደግሞ በባንክ ውስጥ ያለው የድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ መጠን እንዲጨምር ብሎም በዚህ ገንዘብ ተጠቅሞ ተጨማሪ

ፋይናንስ ማኔጅመንት

የማስፋፊያ ኢንቬስትመንቶችን እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል፡፡ ወይም ደግሞ ተቀማጭ ጥሬ ገንዘቡ መጠን መጨመሩ ድርጅቱ ለባለቤቶች በትርፍ ክፍፍል መልክ የተሻለ መጠን መክፈል እንዲችል ያግዘዋል፡፡ ማለትም አንድ ድርጅት በስራ ማስኬጃ ካፒታል የአጠቃቀም ብቃቱን ኤፊሼንት ካደረገ ማለትም ወጭና ብክነት ቀጣቢ በሆነ መንገድ ከተጠቀመ ብቻ በዓመት ውስጥ አንድ መቶ ሺህ ብር ቢቀንስ ይህን ያህል ገንዘብ ለባለቤቶች ለማከፋፈል ወይም መልሶ ኢንቬስት ለማድረግ ተጨማሪ እቅም ፈጠረ ማለት ነው፡፡ አንድ የድርጅት አመራር ዋናው ተልዕኮው የድርጅቱን የገበያ ዋጋ ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር ነው፡፡ ይሁን እንጅ የድርጅቱ የገበያ ዋጋ ሊያድግ የሚችለው በካዝናው ውስጥ ያሉት የጥሬ ገንዘቦች መጠን ባደጉ ቁጥር ነው፡፡ የአንድ ድርጅት ደግሞ ዋና ተልዕኮ የባለቤቶቹን ሃብት በእጅጉ ማሳደጉ ላይ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ለበለጠ መረጃ በፋይናንስ ማኔጅመንት 2 መፅሐፍ ውስጥ የቀረበውን የሚለውን ትንታኔ ማንበብ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ የስራ ማስኬጃ ማኔጅመንት ስንል የተሰብሳቢ ሽያጮች ማኔጅመንት፣ የተከፋይ እዳዎች ማኔጅመንት፣ የክምችት ማኔጅመንትና የጥሬ ገንዘብ ማንጅመንት ናቸው፡፡

የስራ ማስኬጃ ካፒታል ለአንድ ድርጅት ምን ያህል ወሳኝ የማኔጅመንት ክፍል ነው?

እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ አንድ ኩባንያ ትልቅም ይሁን ትንሽ ድርጅቱ ለስራ ማስኬጃው በቂ የሚባል ገንዘብና ወደ ገንዘብ በቶሎ የሚቀየሩ ንብረቶች ከሌሉት የተለያዩ እድሎች ያመልጡታል፤ ወይም ደግሞ ሙሉ በሙሉ የድርጅቱን ውጤታማነት አደጋ ላይ የሚጥለው ነው የሚሆነው፡፡

Scanned with CamScanner

የመጀመሪያው ድርጅቱ በቂ የስራ ማስኬጃ ገንዘብ ከሌለው ሊያመልጠው የሚችለው እድል መኖሩ ነው። ለምሳሌ ከጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች የሚገኘ ቅናሽ ቢቀርብለት የቅናሽ ዕድሉን ለመጠቀም አቅራቢው በሚፈልገው ቀን ውስጥ ለመክፈል የሚያስችለው አቅም ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ እቃ አቅራቢው በ10 ቀን ውስጥ ለሚከፈል ክፍያ ወትሮ ከነበረው ዋጋ በእያንዳንዱ ዕቃ ላይ 15 ብር ቅናሽ ዕድል ቢሰጠው የዕቃው የመግዣ ዋጋ 65 ብር ቢሆንና በአጠቃላይም 1000 እቃዎችን ቢገዛ በአስረኛው ቀን የግድ (50 x1000) = 50,000 ብር ለመክፈል የሚችል መሆን አለበት። በቂ የስራ ማስኬጃ ገንዘብ የሌለው ድርጅት ከሆነ ይህን መክፈል ስለማይችል ዕድሉ ያመልጠዋል። ሌላኛው ተወዳዳሪ ይህን መሰል አጋጣሚ ከተጠቀመ በገበያ ላይ በዋጋ ተወዳዳሪ መሆን ይሳነዋል። ወይም ሽያጭ ይቀንስበታል።

እንዲሁም አንድ ድርጅት የተበደረውን የባንክ ገንዘብ ለመመለስ ይቸገራል። ይህ በሆነ ቁጥር ለአላስፈላጊ የወለድ ክፍያ ከመጋለጡ ባሻገር ድርጅቱ በአበዳሪዎች ዘንድ የሚኖረው ታማኝነት *(Credit rating)* እየወረደ ይመጣል።

አንዳንድ ጊዜ የሞቀ ገበያ ይፈጠራል። በዚህ ወቅት ታዲያ በደንብ ማምረትና ለገበያ ማቅረብ ያስፈልጋል። ይህን የመሰለ የገበያ እድል ከወትሮ ከፍ ያለ ምርትን በማምረት መጠቀም የሚቻል ይሁን እንጂ ይህ ግን ሊሆን የሚችለው ተጨማሪ ምርት ለማምረት የሚያስችል በቂ የስራ ማስኬጃ ካፒታል ላለው ድርጅት ነው። ከዚህ መሰል አጋጣሚ ሊገኝ የሚችለውን ዕድል *(opportunity profit)* ያሳጣናል።

ዝቅተኛ የስራ ማስኬጃ ካፒታል መኖር ትዕዛዞችን ሰርቶ የማስረከቢያ ወይም ለገበያ የማቅረቢያ ጊዜን ያራዝማል። አንድ ምርት ተመርቶ ለገበያ የሚውልበት ቀን 30 ቀናት ሊሆን ቢችል ይሁን እንጂ በስራ ማስኬጃ እጥረት የተነሳ ይህ ጊዜ ግን ወደ 40 እና 50 ቀናት ሊራዘም

በዶ/C አቡሽ አያሌው

ይችላል። ይህ ደግሞ የሽያጭ መጠናችንንም ሆነ ከሽያጩ ልናገኝ የምንችለውን ትርፍ ይቀንስብናል።

እንዲሁም አንድ ድርጅት በስራ ማስኬጃ ገንዘብ እጥረት የተነሳ ቋሚ ንብረቶቹን በወቅቱ ለማሳደስ ሊቸገር ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ቋሚ ንብረቶቹን በሚፈለገው ደረጃ ሳንጠቀማቸው የምንችል ሲሆን በመከከሉም የንብረቶቹን ምርታማነት እንጎዳለን። ይህም ካለንበት ዘርፍ ውስጥ ካሉ ሌሎች ተወዳዳሪዎች በታች ምርታማነታችን ይቀንሳል። የእደሳ ጊዜያቸው ካለፈም ለባሰ ወጪ ልንዳረግም እንችላለን።

ይህ ብቻ አይደለም ላልተፈለገ ወለድ ልንጋለጥ እንችላለን። ይህ የሚሆነው በሁለት መልኩ ነው። የመጀመሪያው ጉዳይ ለአበዳሪዎች በወቅቱ ባልከፈልን ቁጥር የሚንረው ውዝፍ ወለድ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለድንገተኛ የአጭር ጊዜ የገንዘብ ችግራችንን ለመሸፈን ስንል ከባንክም ይሁን ከሌሎች አበዳሪዎች ከፍ ላለ ወለድ በመጋለጥ ነው። በዚህ ረገድ በአገራችን እስከ አራጣ ብድር ድረስ እስከመሄድ የደረሱ ቀላል የማይባሉ የንግድ ሰዎች አሉ። እንዲሁም ተከፋይ ግብሮች በወቅቱ ባለመከፈላቸው ላልተገባ የወለድ ቅጣት መጋለጥም ይኖራል።

በተጨማሪም የስራ ማስኬጃ ገንዘብ አለመኖር ሰርተን ልናገኘው የምንችለውን ሽያጭ በመቀነስ ከአጠቃላዩ ኢንቬስትመንት ሊገኝ የሚችለውን ተመላሽ ትርፋማነት *(ROI)* በእጅጉ እንዲቀንስ ሊያደርገው ይችላል።

የስራ ማስኬጃ ካፒታል እጥረት መኖር በቂ የሚባል የምርት ክምችት (ስቶክ) እንዳይኖር በማድረግ ሊጎድልብን ይችላል። ይህ ባለመኖሩ ልናገኝ የምንችለውን የሽያጭ ገቢ የሚያሳጣን ሲሆን *(Stock out)*፤ ወደፊትም ልናገኝ የምንችለውን የሽያጭ ገቢ በማሳጣት፤

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

ደንበኞቻችን ወደ ተወዳዳሪዎቻችን እንዲሄዱ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ይህ ብቻ አይደለም ድርጅቱ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር (በተለይ ከአበዳሪዎችና አቅራቢዎች ጋር) የሚኖረው ታማኝነትና ስም ሊጠፋ ይችላል:: በቂ የስራ ማስኬጃ ካፒታል አለመኖር የሰራተኞችንም ሆነ የቋሚ ንብረቶች ከስራ ውጪ እንዲሆኑ በማድረግ የማምረቻ የስራ ጊዜያቸውና እውቀታቸው ይባክናል:: ይህ ሁሉ ደግሞ ሄዶ ሄዶ የድርጅቱን ትርፋማነት በእጅጉ የሚጎዳው ይሆናል::

በመጨረሻም ለኢንቬስተሮቹ ሊሰጥ የሚችለው የትርፍ ክፍፍል ላይኖር ስለሚችል በእነዚህ ባለቤቶቹ ትሬታ ሊፈጠርና እነሱም በቀጣይ እዚህ ድርጅት ላይ ተጨማሪ የገንዘብ ኢንቬስትመንት ለማድረግ እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል::

ይህ መሰል ችግር እንዳይፈጠር ምን መደረግ ይኖርበታል?

እንግዲህ አንድ ድርጅት ከላይ ያሉት ችግሮች እንዳይገጥሙት ውጤታማ በሆነ የፋይናንስ አጠቃቀም መንገዝ ይጠበቅበታል:: ተገቢ የሆነ የፋይናንስ ማኔጅመንት ሊኖር ያስፈልጋል:: ተገቢ የሆነ የገንዘብ አስተዳደር መኖር ከላይ ያሉት ችግሮች እንዳይፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ድርጅቱ የተሻለ ምርታማነቱና ተወዳዳሪነቱ የላቀ እንዲሆን ያግዘዋል::

አንድ ድርጅት ትክክለኛ የገንዘብ አስተዳደር አለው ለማለት ደግሞ በቅድሚያ የገንዘብ አስተዳደር ስርአት ሊኖረው የሚገባ ሲሆን በዚህ ስርዓት መሰረትም ለመተዳደር አስተዳዳራዊ ባህል ሊያዳብር ይገባል:: የገንዘብ አስተዳደር በፋይናንስ ዲፓርትመንት ላይ ብቻ የተወሰነ ስራ ሳይሆን በእያንዳንዱ የድርጅቱ የስራ ክንፍ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችና አመራሮችም የሚመለከታቸው ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ

ግዥን በተመለከተ የግዥ ዲፓርትመንት ኃላፊና ሰራተኞች፤ ሽያጭን በተመለከተ የማርኬቲንግ ዲፓርትመንት ሰራተኞች፤ የጥሬ ዕቃና የምርት ክምችትን በተመለከተ የምርት ክፍል ዲፓርትመንት፣ የሰው ሀይል ተገቢ ምጣኔና ምርታማነት በተመለከተ የሰው ሀይል ዲፓርትመንት እያለ ይቀጥላል:: በዋናነት ግን የድርጅቱ የበላይ አመራሮች ታላላቅ ውሳኔዎችን የሚያደርጉ በመሆናቸው የድርጅቱ የካፒታል እጥረት ወይም ትክክለኛ ክምችት የእነሱ የማኔጅመንት የውሳኔ ችሎታና ባህሪ ነፀብራቅ ነው::

በመሆኑም ምርጥ የስራ ማስኬጃ ካፒታል አስተዳደር ወለድ ከመክፈል ወጥቶ ወለድ ወደ ማግኘት፣ የወለድ ክፍያን ወደ መቀነስ፣ የድርጅቱን ምርታማነት ወደ ማሳደግ፣ ድርጅቱ ከአበዳሪዎች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የማጠናከር፤ የድርጅቱን ዋጋ በገበያ ላይ ከፍተኛ እንዲሆን ያግዘዋል:: በስራ ማስኬጃ ካፒታል እጥረት የተነሳ በኪሳራ የሚዘጉ ድርጅቶች ያሉ ሲሆን በምርጥ ስራ ማስኬጃ አስተዳደር ብቃት ሳቢያ ወደ እድገት ግስጋሴ እንዲገባ ሊያደርገው ይችላል:: እንዲሁም ምርጥ የገንዘብ አስተዳደር ስርዓት ትክክለኛ ዓመታዊ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላል:: ከዚያም ባሻገር አመራሮች ትክክለኛ ገንዘብ ነክ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣ ስለወደፊቱ እንዲያስቡና እንዲተነብዩ፤ በዚህም ላይ ተንተርሰው እንዲያቅዱ፣ በእቅዳቸው መሰረትም አፈፃፀማቸውን እንዲገመግሙና በግምገማቸው መሰረትም እየተጣሩ እንዲሻሻሉ ትልቅ አቅጣጫን ይፈጥርላቸዋል:: እንዲሁም የስራ ማስኬጃ ካፒታልን መሰረት ያደረገ ምርጥ የአመራር ስርዓት በድርጅቱ ያሉ ልዩ ልዩ ዲፓርትመንቶች እንዲናበቡና ተቀናጅተው እንዲሰሩ ከፍተኛ እድልን ይሰጣቸዋል:: የስራ ማስኬጃ ካፒታል አስተዳደር የሁሉም ዲፓርትመንቶች የጋራ ኃላፊነት ነውና::

Scanned with CamScanner

የስራ ማስኬጃ ካፒታልን በብቃት ለማስተዳደር ተግባራዊ ሲደረጉ የሚገባቸው ጉዳዮች!!

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

የመጀመሪያው ጉዳይ ትክክለኛ የገንዘብ ስርዓትን መተግበር ነው። ይህም ስርዓት የስራ ማስኬጃ ካፒታል አጠቃቀምን ለመመዘን (ለመለካት) የሚያግዝ መሆን ይኖርበታል።

የስራ ማስኬጃ ካፒታል የሚለካው መቼ ነው?

በንድፈ ሃሳብ ደረጃ በየዕለቱ ቢሆን ጥሩ ነው። ምክንያቱም በየዕለቱ የሚደረጉ ውሳኔዎችና ክንውኖች ያሉ በመሆናቸው። በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ከትንሽ እስከ ትልቅ ክንውኖች (ግዥ፣ ምርት፣ ሽያጭና ሌሎችም) የድርጅቱን የስራ ማስኬጃ ካፒታል የሚነኩ ናቸውና። ሆኖም በየቀኑ ማድረግ ካልተቻለ ግን ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ማመዘኛ ግምገማ ሊደረግለት ይገባል። ይህን ለማድረግም የፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። ይህም ስርዓት በድርጅቱ ውስጥ ያለውን የባንክ አካውንት ገንዘብ መጠን፣ በዱቤ የተደረጉ የሽያጭ መጠኖችንም ሆነ እስባሰባቸውን የሚያሳውቅ፣ በመጋዘን ውስጥ ያሉትን ክምችቶች ወይም ኢንቬንተሪ ማለትም (የጥሬ ዕቃ ክምችት፣ በመመረት ያሉትንና ያለቀላቸው የምርት ክምችቶችን) መጠን የሚያሳውቅ እንዲሁም ድርጅቱ ለአበዳሪዎች የዱቤ ግዥዎች ሊከፍል የሚገባውን የገንዘብ መጠን የሚያመላክት የገንዘብ ስርዓት ሊሆን ይገባል።

በሁለተኛ ደረጃ አመራሮች ሊያደርጉት የሚገባው የዘንድሮውን የስራ ማስኬጃ በጀት ከባለፈው ዓመት አንፃር በመነሳት ትክክለኛ እቅድ ሊይዙ ይገባል። ከባለፈው ዓመት ተሞክሮ ከፍተኛ ስራ ማስኬጃ ገንዘብ የሚጠይቁ ወሮች የትኞቹ እንደሆኑ (ለምሳሌ በአዲስ ዓመት

ካሉ ክምችት በመያዝ የሽያጭ ከበረ በዓል የሚጨምሩ ሽያጮች ወራት የሚባሉት ላይ አነስተኛ ጊዜን ለመጨመር)፤ ዝቅተኛ የሽያጭ ትምህርቶችን መቅሰም ክምችት በመያዝ ገንዘብን ላለማሰርና ሌሎችንም ያስፈልጋል።

እንዲሁም የስራ ማስኬጃ ካፒታልን በትክክል ለመምራታችን ከሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች መማርና ከእነሱም ተሽሎ ለመገኘት መጣር ያስፈልጋል። ይህም የሚሆነው የስራ ማስኬጃ ካፒታል አስተዳደር በገበያ ላይ ያለውን ተወዳዳሪነት የሚወስን በመሆኑ ነው። ለምሳሌ የሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶች ለደንበኞች በዱቤ የሸጧቸው ምርቶች (አገልግሎቶች) በምን ያህል ጊዜ እንደሚሰበሰቡ፤ ከእቃ አቅራቢዎቻቸው በዱቤ የወሰዱ ከሆነም በምን ያህል ጊዜ እንደሚከፍሉ፤ በምን ያህልስ የምርት ክምችት ሽያጭ ፍጥነቱ ከፍተኛ እንደሆነ ለማወቅ መሞከር እና ከዚህም አንፃር ራሳቸውን የተሻለ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በመሆኑም አንድ ድርጅት የስራ ማስኬጃ ካፒታሉ የት ላይ እንዳለ ለማወቅ የሚከተሉትን ቀመሮች በመጠቀም መገምገም ይኖርበታል።

1. የክምችት ቀናት (Inventory Days)፡- ይህ ማለት የጥሬ እቃዎችን ይሁን የሸቀጦችን የክምችት መጠን እና ምን ያህል ጊዜስ በድርጅቱ መጋዘን ውስጥ እንደሚቆዩ የሚያሳይ ነው። የአንድ ድርጅት የክምችት ቀናት በጨመሩ ቁጥር ክምችቱ በድርጅቱ መጋዘን ውስጥ ተከማችቶ ረዘም ያለ ጊዜ ቆየ ማለት ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ ድርጅቱ ለዕለት ከዕለት ስራው የሚያስፈልገውን የጥሬ ገንዘብ መጠን እንዲታሰርበት ይሆናል። በመሆኑም የድርጅት አመራሮች የስራ ማስኬጃ ካፒታልን ከማስተዳደር አንፃር ለድርጅቱ ስራ በትክክል የሚያስፈልገውን ተመጣጣኝ መጠን ያለውን ኢንቬንተሪ መያዝ ይኖርባቸዋል። ክምችት ማብዛትም ሆነ ማሳነስ የራሱ ጥቅምና ጉዳት ያለው በመሆኑ ሁለቱንም ማመጣጠን ያስፈልጋል። በመሆኑም "የክምችት ቀናት" የሚለው

Scanned with CamScanner

መለኪያ የሚያሳየን ያልተሸጡ ዕቃዎች ለምን ያህል ጊዜ ሳይሸጡ ቆ... የሚለውን ሲሆን በየወሩም ድርጅቱ ይህን የክምችት ቀን በማነጻ... ያልተሸጡ ዕቃዎች ክምችት ለምን ያህል ቀን እንደቆዩ ለመገንዘብ ያስችለዋል:: ቀኑ ከፍ ባለ ቁጥር ድርጅቱ ለምን ክምችቱን ሳይሸጥ ረዥምም ጊዜ ሊይዛቸው በቃ? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ወደ ቀጣይ መፍትሄ ለመሸጋገር ያግዘዋል::

የክምችት ቀናት = የክምችቱ አጠቃላይ ዋጋ / የተሸጠው የክምችቱ አሰታዊ የማምረቻ ወጭ

የተሸጠው የማምረቻ ወጭ በአካውንቲንግ ስያሜው ‹‹Cost of Goods Sold›› በመባል የሚጠራ ሲሆን የተሸጡትን ምርቶች ዕለታዊ ወጭ ለማወቅ ከድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ አጠቃላዩን የማምረቻ ወጭ (Cost of Goods Sold) ለዓመቱ ቀናት (365 ቀናት) በማካፈል የሚመጣ ነው:: ይህም ማለት

‹‹የኢንቬንተሪ ቀናት = በመጋዘን ያለው ክምችት አጠቃላይ ዋጋ / የዓመታዊ ሽያጭ የማምረቻ ወጭ/365

= በመጋዘን ያለው ክምችት አጠቃላይ ዋጋ X 365 / የዓመታዊው ሽያጭ የማምረቻ ወጭ

2. የተሰብሳቢ ቀናት (Account Receivable Days):

- ይህ የሚያሳየው ድርጅቱ ምርቱን ለደንበኞች ሸጦ በምን ያህል ቀናት ውስጥ ገንዘቡን በእጁ ያስገባል የሚለውን ልኬት ነው:: የሽያጭ ገቢዎች የሚሰበሰቡበት ቀን በረዘመ ቁጥር ቀጣይ መፍትሔን በማበጀት የመሰብሰቢያ ጊዜውን ማሳጠር ያስፈልጋል::

ተሰብሳቢ ቀናት = የተሰብሳቢ መጠን / ዕለታዊ የሽያጭ መጠን

‹‹ዕለታዊ የሽያጭ መጠን›› ምን ያህል እንደሆነ ለማግኘት የዓመቱን የሽያጭ መጠን በመውሰድ ለዓመቱ አጠቃላይ ቀናት ማለትም በ‹‹365›› ቀናት በማካፈል የሚገኝ ነው::

የተሰብሳቢ ቀናት = የተሰብሳቢ መጠን / ዓመታዊ የሽያጭ መጠን /365

= የተሰብሳቢ መጠን X 365 / ዓመታዊ ሽያጭ

የድርጅቱን የተሰብሳቢ መጠን በወቅቱ ከተሰራው የድርጅቱ የሀብትና ዕዳ መግለጫ (ባላንስ ሽት) ሪፖርት ላይ ማግኘት ሲቻል፤ ‹‹አመታዊ ሽያጭ›› መጠንን ደግሞ ከድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ መውሰድ ይቻላል::

3. የተከፋይ ዕዳዎች ቀን (Account Payable Days):-

ይህም ማለት ድርጅቱ በምን ያህል ቀናት (በአማካይ) የአጭር ጊዜ ዕዳዎቹን መክፈል ይችላል የሚለውን የሚጠቁመን ነው:: ዝቅተኛ የመክፈያ ቀን መኖሩ የሚጠቁመን ድርጅቱ ክፍያውን በተራዘመ ቀናት ውስጥ ለተከፋዩ የመክፈል ዕድልን ያልተጠቀመ መሆኑን ነው:: ማለትም ክፍያ የማራዘም ብልሃትን ለመጠቀም አለመሞከሩን ነው::

የዕዳ መክፈያ ቀናት = የዕዳው መጠን / የተሸጡት ዕቃዎች ዕለታዊ የማምረቻ (የመግዣ) ወጭ

የሽያጩ ዕቃ ዕለታዊ የማምረቻ (የመግዣ) ወጭ ማለት በተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው መጠን ነው::

4. ሊኩይዲቲ ሬሾዎ:-

ይህ የድርጅቱ የአጭር ጊዜ ሃብቶች ከድርጅቱ የአጭር ጊዜ እዳዎች አንፃር ያላቸው ጥመርታ ምን ይመስላል የሚለውን የሚያሳይ ሲሆን ምን ያህል የድርጅቱ የአጭር ጊዜ ንብረቶች

Scanned with CamScanner

እያንዳንዷን ተከፋይ ዕዳ ብር መሸፈን ይችላሉ የሚለውን የሚያሳየን ነው። ይህ ጥመርታ አንዳንዴም ‹‹ ከረንት ሬሽዮ›› (Current Ratio) በመባል ይጠራል።

ሊኩይዲቲ ሬሽዮ = የድርጅቱ የአጭር ጊዜ ሃብቶች÷ የድርጅቱ የአጭር ጊዜ ዕዳዎች

ይህ ውጤት ለአምራች ድርጅቶች 2.3 እና ከዚያ በላይ፣ ለአገልግሎት ሰጭ እና ለችርቻሮ ተቋማት‹‹1.5›› እና ከዚያ በላይ ቢሆን ይመከራል።

$$\text{ኲዊክ ሬሽዮ} = \frac{\text{የአጭር ጊዜ ሃብቶች - ኢንቬንተሪ}}{\text{የአጭር ጊዜ ተከፋዮች}}$$

ይህ ከላይኛው የሚለየው ‹‹ኢንቬንተሪ›› ወይም ‹‹ የክምችት መጠን›› የተባለውን ክፍል ከአጭር ጊዜ ሃብቶች ውስጥ መቀነሳችን ሲሆን ይህም የሚሆነው ድርጅቱ ክምችቱን በቀላሉ ወደ ገንዘብ ለመቀየር ጊዜ ስለሚወስድበት ለክፍያ የሚሆን ገንዘብን ልናገኝ ስለማንችል በኢንቬንተሪ ላይ እንዳንተማመን በሚል ነው። ይህ ጥመርታ ውጤቱ ለአምራች ድርጅቶች 1.6 እና ከዚያ በላይ፣ ለችርቻሮ ድርጅቶች 0.73፣ ለአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ደግሞ 1.4 እና ከዚያ በላይ ቢሆን ይመከራል።

ከእነዚህ መለኪያዎች አንፃር አንድ ድርጅት ምን ቢያደርግ ጥሩ ነው?

ለምሳሌ ፈጣን የክምችት ሽያጭ ሊኖረው ይገባል፣ የዱቤ ሽያጭን በፍጥነት መሰብሰብ ይጠበቅበታል፣ በዱቤ ከአቅራቢ የገዛቸውን ዕቃዎችንና አገልግሎቶች ደግሞ ዘግየት አድርጎ ቢከፍል ይመከራል።

እነዚህን ለማሻሻልና የበለጠም ምርጥ ለማድረግ ያሉ መንገዶች ምን ይመስላሉ?

ለምሳሌ ፈጣን የሸቀጦች ክምችት ሽያጭን እውን ለማድረግ (Fast Stock turn over)፤ እንደ አመራር ቶሎ ባልተሸጡ ሸቀጦች ክምችት የስራ ማስኬጃ ካፒታሉን ላለማሰር መጀመሪያውኑ ሸቀጦችን ከመግዛቱም ሆነ ከማምረቱ በፊት በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ የሽያጭ መጠን ትንበያን ማከናወን ይኖርበታል። ገና ለገና በስሜታችን በመገፋት ገበያ ላይ ሊፈለግ ይችላል በማለት (Just in case)፤ ወይም (ሸቀጡን በብዛት ካልተረከብኩ) ጥሬ ዕቃውን በብዛት ካልገዛሁ፤ ኋላ ስፈልገው ሊያልቅ ይችላል በሚል አስተሳሰብ ከመጠን በላይ ከማምረት (ከመግዛት) መቆጠብ ያስፈልጋል። እንዲሁም የጥሬ ዕቃ (የሸቀጥ) ክምችትን ምን ያህል እንዲሆን ለማወቅ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት (Stock-Control System) ሊኖረን ይገባል። ይህም ከሚፈለገው በታችም የሚጠቀመው ከመጠን በላይ እንዳይከማች፤ ድርጅቱ የጥሬ ዕቃ ክምችት እንዳያንስ ለማድረግ ነው። እንዲሁም ወዲያውኑ ሊያቀርቡ የሚችሉ እንዳይፈጠርበት ከፈለገም በፈለገ ጊዜ አስተማማኝ አቅራቢዎችን (Just in Time Suppliers) ቢይዝ ይመከራል። ያለቀላቸው ሸቀጦች ክምችት ካጋጠመም ቶሎ የሚሸጡበትን መንገድ ማፈላለግ ያስፈልጋል። ከሸቀጦች ጋር በተያያዘም በጣም ዝግ ብለው የሚሸጡ ሸቀጦችን መለየትና ማስወገድም ታሳቢ ሊሆን ይገባል። በተቻለ መጠንም በተለያየ ቦታ ማከማቻ መጋዘን ከመያዝ ይልቅ አንድ ማዕከላዊ መጋዘን ቢኖር የበለጠ ለቁጥጥር ይመቻል።

የዱቤ ሽያጭ ተጠቃሚ ደንበኞችን ደግሞ በትክክል ለማስተናገድ ማለትም እነሱ ጋር ያለው ገንዘብ በፍጥነት ተከፋይ እንዲሆን የሚያደርግ ስርዓትን መከተል ያስፈልጋል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ

Scanned with CamScanner

በመጀመሪያ ግዥውን ከፈፀሙ ደንበኞች ጋር ከቃል ይልቅ ፅሁፍ ላይ የሰፈረ ስምምነት እንዲኖር ማድረግ፣ እንዲሁም በክፍያ ስሌቶቹ መሰረት ስለመክፈላቸው ያላሰለሰ ክትትል ማድረግ፣ ውጤታማ የሆኑ ሽያጭ አመላለስ መመሪያን መቅረፅና ይህንንም ተግባራዊ ማድረግ፣ የሚከፈሉ ክፍያዎች ክፍያቸውን በተሟላ መልኩ ስለመፈፀማቸው ማረጋገጥ (የተቆራረጠ አከፋፈል ስለሚኖር)፤ በተቻለ መጠን ከውላቸው ቀድመው ለከፈሉ የቅናሽ ዕድል ተጠቃሚነትን መስጠት፤ ከውላቸው ዘግይተው ለሚከፍሉ ተጨማሪ ወለድን የማስከፈል መመሪያ ስምምነትን ተግባራዊ ማድረግ፣ የዘገዩ ተከፋይ ክፍያዎችን በግዝር በመገኘት ማስፈፀም፣ አወዛጋቢ ተከፋይ የዱቤ ሽያጮችን በፍጥነት መፍትሄ መስጠት፣ የሽያጭ ሰራተኞች ተሰብሳቢ ገንዘቦችን በፍጥነት እንዲሰበስቡ ለማበረታታት ከሽያጭ የሚያገኙትን ኮሚሽን ሽያጩ ሲፈፀም ሳይሆን ገንዘቡ ወደ ባንክ ገቢ ሲሆን እንዲከፈሉ ማድረግ የሚሉ ይገኙበታል፡፡

እንዲሁም የስራ ማስኬጃ ካፒታል አስተዳደርን በተመለከተ ሌላው ተፅዕኖ የማሳረፍ ሀይል ያላቸው ለድርጅቱ በዱቤ የሚሸጡ አቅራቢዎች ወይም ደግሞ ገንዘብ አበዳሪ የገንዘብ ተቋማት ናቸው። እነዚህ ድርድቶች ጋር የሚኖሩን የአሰራር ጥራትና የጊዜ አጠቃቀም ሁኔታ የስራ ማስኬጃ ካፒታላችንን መጠንም ሆነ ቀጣይ ጥሩ መተማመን በሚያሳድግ መልኩ በመመዘን ሊተገበር ይገባል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የዱቤ ግዥ ስምምነትን ወይም የብድር ውል ስምምነትን ተግባራዊ ማድረግ አፋጣኝ ነው፡፡ በተቻለ መጠንም እስከ ውሉ የመጨረሻ መክፈያ ቀን ድረስ ክፍያን ማዘግየት ጥሩ ነው፡፡ እስከዚህ ቀን ድረስ ገንዘቡን ለማሽከርከር ያስችላልና፡፡ ምናልባት ቀድሞ መክፈሉ በአቅራቢዎች ዘንድ የቅናሽ ዋጋ ተጠቃሚነት ዕድልን የሚሰጥ ከሆነም ቀድሞ መክፈል ሊኖር የሚችለውን ጥቅም አዘግይቶ መክፈል ከሚያመጣው ጥቅም ጋር አነፃፅሮ በማስላትም እንደ ሁኔታው ቀድሞ መክፈል ሊያዋጣም እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በዶ/ር አቡሽ አያሌው

የጥሬ ገንዘብ ክምችትን በላቀ ደረጃ ለማሳደግና ለማስተዳደር የሚያስችሉ መላዎች

‹‹ሠሳም የሚያመጣ ገንዘብ የሚባለው ብዙ ገንዘቦችንና ንብረቶችን ማጋበሱ አይደለም፤ ከምታገኘው ገቢ በታች በመኖር ለሌሎችም ለመርዳትና ኢንቬስት ለማድረግ የሚያስችል ትርፍ ገንዘብን ማሳደግ እንጂ፡፡ ይህን እስከታደርግ ድረስ ሠላም የለንተ ልትሆን ለትችልም፡፡›› ዴቭ ራምሴይ

የትኛውም ስቃይ የራሱ መነሻ ምክንያት አለው፡፡ ትክክለኛ መነሻውን መለየትም መፍትሔውን ለመስጠት ያስችለናል፡፡ አንዳች ውጤት ካለአንዳች ምክንያት አይከሰትም፡፡ የድርጅቱ አካውንት ላይ የጥሬ ገንዘብ መጠን እጥረት በመከሰት ድርጅቱንም ሆነ ባለቤቶቹን ወደ ውጥረትና ስቃይ የሚወስዳቸው በዋናነት አመራሩ በተለይም ደግሞ

የድርጅቱ የበላይ አመራር (ዋና ሥራ አስፈፃሚ) ወይም በዚህ የኃላፊነት ሚና ላይ እየሠራ የሚገኘው የድርጅቱ ባለቤት ነው:: ምክንያቱም ማናቸውም የበታች ውሳኔዎች የሚወሰኑትና ድርጅቱ የሚመራበትን ለዚህ መሠል ችግር የበቃበትን የፋይናንስ ባህል የሚቀርፀው ይሄው የበላይ አመራሩ በመሆኑ ነው::

የመጀመሪያው ነገር የድርጅቱ አካውንት ላይ ያለው የጥሬ ገንዘብ መጠን የድርጅቱን አሠራር የሚረብሽ በመሆኑ የተነሳ ለድርጅቱ አመራሮችና ባለቤቶች ራስ ምታት በመሆን ሠላም እያሳጣ መሆኑን ማወቅ ነው:: ማለትም ከድርጅቱ የካሽ ፍሎው ችግር መነሻ ያስፈልጋል:: ድርጅቱን ለችግር (ቀውስ) በመዳረግ አመራሮቹም ለአዕምሮ ውጥረት መዳረጋቸውን በትድሚያ መለየትና እውቅና መስጠት ያስፈልጋል:: በካሽ ፍሎው የተነሳ ድርጅቱም ሆነ አመራሮቹ ስቃይ ውስጥ መሆናቸው ነው ወደ መፍትሔው እንድንሄድ የሚያስገድደን:: በዚህ ስቃይ የተነሳ የድርጅቱ አጋሮችም ስቃይ ውስጥ እንዲገቡ ድርጅቱ ምክንያት መሆኑም በራሱ ወደ መፍትሄው እንድናመራ ያስገድደናል::

እነዚህ የድርጅቱ አጋሮች እነማን ናቸው? ስንል ከውስጥ ሠራተኞችንና አመራሮችን ፣ ከላይ ባለቤቶችን ፣ ከኋላ አቅራቢዎችን (የጥሬ እቃና የካፒታል ማለትም ባንኮችን) ፣ ከፊት ደግሞ ደንበኞችንና ከድርጅቱ ጋር በትብብር የሚሠሩ ሌሎች አጋር ድርጅቶችን ጭምር ያካትታል:: ድርጅቱ በካሽ ፍሎው ችግር የተነሳ ለእነዚህ ልዩ ልዩ አጋሮቹ ማለትም ‹‹ስቴክ ሆልደርስ›› በወቅቱ መክፈል ባለመቻሉ የሚፈጠሩ ቅሬታዎች ይኖራሉ:: እነዚህ ቅሬታዎች ደግሞ በድርጅቱ ላይ ዘላቂነት ያለው ተፅዕኖን ሊያሳድሩበት ይችላሉ:: ለምሳሌ የድርጅቱ አቅራቢዎች የዱቤ ግዥ ሊከለክሉት (ወይም ፍፁም መገዘያየትን ሊያቆሙ) ይችላሉ:: ባንኮች ደግሞ ሳያበድሩት ከመቻላቸውም ባሻገር የአሁኑን ክፍያ በጊዜው መክፈል ባለመቻሉ ወደመያዣው ቤት አልያም

ሀገፃ ወይም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሊያመሩ ይችላሉ:: በቀጣይም የድርጅቱ የዱቤ ግዥንቱና የተበዳሪነት ታማኝነቱ (Credit Worthiness) ጥያቄ ውስጥ ይገባል:: በካሽ ፍሎው እጥረት የተነሳ ደንበኞቹ በሚፈልጉት ብዛት ፣ ጥራትና ጊዜ ውስጥ ባለመቅረቡ ሊያገኙ የሚገባውን ጥቅም ወይም ትርፍ ባለመስጠቱ ወደሌላ ተወዳዳሪ ሊቀይሩ ይችላሉ:: በደንበኞች ዘንድ እምነቱን (Trust Worthiness) ያጣል:: አብረዋቸው የሚሠሩ የንግድ አጋሮች (Corporate Partners) የሚኖረው የሥራ ትስስር ይበደላል:: በቀጣይነት አብረው ለመስራት ሊቸገሩ ይችላሉ:: የሠራተኞች ወርሃዊ ደመወዝ ሊጓተት ይችላል ወይም ተጨማሪ ክፍያ (እድገት) ለማድረግም ሊቸገር በመቻሉ የተነሳ ሠራተኞች ላይ ቅሬታ ያሳድራል:: ቁልፍ ሠራተኞችም ወደ ሌላ ተወዳዳሪ እንዲሄዱ ያስገድዳቸዋል:: እነዚህ ሁሉ በአንድም በሌላም መንገድ የድርጅቱን ቀጣይ ተወዳዳሪነት ችግር ውስጥ በማስገባት ከሥራ ውጭ ሊያደርጉት ይችላሉ::

ካሽ ፍሎው በሀገር ደረጃ!!

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሚ/ር ዶ/ር አብርሃም ተከስተ በሠኔ ወር 2010 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ኢትዮጵያ የገጠማትን የጥሬ ብርም ሆነ የዶላር እጥረት በተመለከተ ማብራሪያ ሠጥተው ነበር:: ማብራሪያውም አገሪቱ ሊኖራት ስለሚገባው በብር ጥሬ ገንዘብ ክምችትና የዶላር ጥሬ ገንዘብ ክምችት ጉዳይ ላይ ነበር፤ ‹‹Birr cash flow›› ወይም ‹‹Dollar cash flow››:: ለምሳሌ አገሪቱ ባጋጠማት የዶላር እጥረት የተነሳ የኢንዱስትሪዎችን አመታዊ የዶላር ፍጆታ መጠን መሙላት ባለመቻሏ ብዙ አምራቾች ጥሬ እቃ ከውጭ እያስገቡ የሚያመርቱ በመሆናቸው በዶላር እጦት ምክንያት የአቅማቸውን 10 በመቶ ብቻ እስከመጠቀም (90 በመቶ አቅማቸው እንዲባክን) በመደረጉ ለከፍተኛ

Scanned with CamScanner

ወጪና ለዝቅተኛ የገበያ ተወዳዳሪነት በመዳረጋቸውና ሠራተኞቻቸውን በመበተን ድርጅታቸውን ወደመዝጋት የመሩ

በኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ምንጮች ተብለው የሚዘረዘሩ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦች፣ ከንፈረንሶችና የቱሪስት መስህቦች፣ ውስጥ የሚገቡ የውጭ ኢንቨስተሮች፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ከውጭ የሚገኙ ብድሮች ፣ ከውጭ የሚላኩ የዲያስፖራ ገንዘብ እንዲሁም በአይነትና በገንዘብ የሚደረጉ ልዩ ልዩ እርዳታዎች ናቸው። መንግስት የውጭ ምንዛሬን በመጠቀም ትልልቅ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ ከውጭ ልዩ ልዩ እቃዎችንና የውጭ አማካሪዎችን ይቀጥራል። እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚሠሩ የውጭ ባለሃብቶች በትርፍ ክፍፍል ወቅት የድርሻቸውን ከተካፈሉ በኋላ ወደአገራቸው ገንዘቡን ይዘውት የሚሄዱት በውጭ ምንዛሬ መልክ ነው። መንግስት በውጭ ምንዛሬ መልክ የተበደረውን ዋናውን ከነወለዱ የሚከፍለው በዚሁ የውጭ ምንዛሬ መልክ ነው። ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ (ለጉብኝት፣ለስብሰባ፣ ለንግድ፣ለትምህርትና ለህክምና) ኢትዮጵያውያን መንገደኞች የውጭ ምንዛሬ ይፈቀዳል። በዋናነት ደግሞ በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፍ ያሉ ድርጅቶች ለማብለት የሚሆኗቸውን ጥሬ እቃዎችና እንዲሁም ማሽነሪዎችና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች በውጭ ምንዛሬ ነው የሚያስመጡት። እንዲሁም ለሠፊው ማህበረሰብ ለኑሮ ፍጆታ የሚሆኑ (ምግብ ፣ ልብስ ፣ መድሐኒት ፣ መኪና ፣ ሌሎች ሸቀጦች) የሚመጡት በዚሁ በውጭ ምንዛሬ ገንዘብ ነው።

ስለዚህ በተለያዩ መንገዶች የውጭ ምንዛሬ ወደ አገር ውስጥ ይገባል፣ በተለያዩ ምክንያቶች ከአገር ውጭ ይወጣል። ይህ መሠሉ (የሚገባ ሲቀነስ የሚወጣ ምንዛሬ) የውጭ ምንዛሬ ሚዛን ልዩነት ለአንዳንድ አገራት ልዩነት ማለትም አዎንታዊ ትርፍ ሊኖረው ይችላል፣ ለአንዳንዱ ደግሞ ልዩነቱ ጉድለት ሊያሳይ ወይም ኔጌቲቭ ሊሆን

ይችላል።

የምንዛሬው ክምችት ልዩነት እጅግ ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ ሲሰፋ ማለትም ኢትዮጵያ እንደገጠማት የ2010 ዓ.ም የውጭ ምንዛሬ ቀውስ ጉዳዩ አደገኛ ወደሆነ ደረጃ ይሸጋገራል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ የገቢና ወጭ መጠን ክፍተት 13 ቢሊዮን ዶላር የደረሰ ሲሆን ይህም ማለት ወጭ የሆነው መጠን 16.5 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን ከውጭ ንግድ የተገኘው ደግሞ 3.5 ቢልዮን ዶላር ብቻ ነው። ይህም የሚያሳየው ከምናመርተው በላይ የምንጠቀመው (ፍጆታችን) ከፍተኛ መሆኑን ነው። ለዚያም ነው ጉድለቱ ከዲያስፖራዎች ከሚላክ (ሬሚታንስ)፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቬስትመንት፣ በብድርና በእርዳታ ሊሞላ የሚገባው።

ይሁን እንጂ አገሪቱ ያለባትን የምንዛሬ ቀውስ ለመፍታት እንደ አንድ አማራጭ መበደር ሲኖርባትም አሁን ካለበት ከፍተኛ የብድር ጫና አንፃር ተጨማሪ ብድር የማስተናገድ አቅም የሌላት ሲሆን አበዳሪዎችም የአገሪቱን የብድር ጫና በመመልከት ብድር ለመስጠት አይደፍሩም። በመንግስት ስር ያሉ ኢንተርፕራይዞች ያለባቸውን ዕዳ ሳይጨምር የአገሪቱ የብድር መጠን በ2010 ሠኔ ወር ላይ 24.7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን፣ በአጠቃላይ ያለበት እዳ ደግሞ ከአመታዊ የምርት መጠኗ *(GDP) (Debt to GDP ratio)* አንፃር ከ40 በመቶ እንዳይበልጥ ይመከራል። የኢትዮጵያ እንግዲህ ጣሪያ ላይ የደረሰ መሆኑን ያሳየናል። እንዲሁም የአገሪቱ የወጭ ቀጥታ ኢንቬስትመንት በፖለቲካዊ አለመረጋጋት ሳቢያ በዚህ የበጀት አመት የቀነሰ መሆኑም ተመልክቷል። ወደ አገር ውስጥ የሚፈሰው የዲያስፖራው ገንዘብም በአግባቡ በህጋዊ መንገድ ሳይሆን በጥቁር ገበያ በኩል የማለፉ ነገር ሌላኛው የክምችት መጠኑን የጎዳው ሁኔታ ነበር። መንግስት የወጭ ንግዱን ተወዳዳሪነት ለማበረታታት የ15 በመቶ የብር ማዳከም ሥራ ቢሰራም ብዙ አምራች ድርጅቶች ለግብአት የሚጠቀሟቸውን

Scanned with CamScanner

እቃዎች ከውጭ በማስመጣታቸው፣ የአገር ውስጥ ግብአቶችም ወይም የአመራረት ወጭዎች በመጨመራቸው የብር ማዳከሙ አቅጣጫ የታለመውን ያህል ከወጭ ንግድ ሊገኝ የሚችለውን የውጭ ምንዛሬ ገቢ ከፍ ማድረግ አለመቻሉ ተመልክቷል:: ይህም ምክንያቱ የላኪዎች ተወዳዳሪነት አለመሻሻሉን ነው:: ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦች ዋጋ (ነዳጅን ጨምሮ) ዋጋቸው እንዲንር በማድረጉም የኑሮ ውድነት (ኢንፍሌሽን) ወትሮ ከነበረው ከ 10 በመቶ በታች ምጣኔ (ነጠላ አሃዝ) ወደ 15 በመቶ እንዲንር አድርጓታል:: አንዳንድ ዘርፎች ላይ(ኮንስትራክሽን) እንደ ብረት የመሰሉ ግብአቶች ዋጋ በመናሩ ኢኮኖሚው ተዳክሟል:: የስራ አጥ ቁጥሩ ጨምሯል::

ወደ ብር ክምችት መጠን ስንሄድ ደግሞ የብር ክምችትም እንዲሁ ከፍተኛ እጥረት መኖሩ ነው የታወቀው:: መንግስት አመታዊ የአገሪቱን መንግስታዊ በጀት ሲያፀድቅ አላማው የመንግስትን አፈፃፀም ለማሳደግ የሚውሉ፣ የተለያዩ መንግስታዊ ኢንቬስትመንቶችን እንዲሠራ፣ የወደፊት ዘላቂ የእድገት ግቦችን ለማጠናከርና ለሌሎች ጉዳዮች ይበጀታል:: ለምሳሌ የአገሪቱ አመታዊ በጀት ሠኔ/2010 ዓ.ም ይፋ ሲደረግ 346.9 ቢሊዮን ብር ሲሆን ይህም ወጭ የሚደረግ በጀት የሚገኘው መንግስት ከሚሰበስባቸው ግብሮች፣ ብድሮች ፣ የውጭ እርዳታዎች ፣ በመንግስት ስር ከሚተዳደሩ ኢንተርፕራይዞች ከሚገኙ ገቢዎች ፣ ከመንግስት የአገልግሎት ክፍያዎች ከሚሰበሰቡ ገቢዎች ነው:: በሠኔ 2010 በገንዘብ ሚኒስትሩ የቀረበው ሪፖርት እንደሚያሳየው ከግብር የሚሰበሰበው ገንዘብ የቀነሰ ሲሆን ያልተሰበሰበ 50 ቢሊዮን ብር ያህል ገንዘብ መኖሩንም ተናግረዋል:: እንዲሁም አንዳንድ የመንግስት መ/ቤቶች በተመደበላቸው በጀት በትክክል ከመተዳደር ይልቅ የማባከን ወይም በአግባቡ ካለመጠቀም በዋናው ኦዲተር ቢሮ ግምገማ የ20 ቢሊዮን ብር ያህል ክፍተት መታየቱም

ተመልክቷል:: አንዳንድ እንደ ስኳር ፣ ግድብ ፣ ባቡር የመሳሰሉ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ባለመግባታቸው ከታቀደላቸው የኢንቬስትመንት ካፒታል በላይ በየአመቱ ገንዘብ የሚፈልጉ ሆኑ:: ይህ ደግሞ አዋጭ ኢንቬስትመንትን አውቆ ወይም መርጦ የመጀመር ችግር እንዳለና ፕሮጀክቱ ተመርጦ ከተጀመረ በኋላ ደግሞ ፕሮጀክቱን በታቀደለት ጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያልቅ ባለማድረግ ለተጨማሪ የእቃዎች ዋጋ ጭማሮ (ኢንፍሌሽን) እንዲሁም ለውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ አደጋ *(Exchange risk)* ለመጋለጥ በቅቷል:: ስለዚህ ተጨማሪ የካፒታል በጀት እንዲፈልጉ አድርጓቸዋል::

እንዲሁም መንግስት ከአገር ውስጥ ባንኮች የወሰደውን ገንዘብ (በጥሬ ወይም በቦንድ መልክ) በተባለበት ጊዜ ውስጥ መክፈል ያለበት ሌላኛው የብር ክምችትን የሚያሳሳ ሂደት ነው:: እነዚህ በጥሬ ብር የሚደረጉ ገቢዎች ማነስና ወጪዎች መብዛት አገሪቱ ለብር ክምችት ቀውስ *(Liquidity risk)* ለመጋለጥ በቅታለች:: ይህም ማለት ተከፋይ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል በቂ ገቢዎች አንሠዋል::

ከላይ ባሉት ሁለት ችግሮች ማለት የምንዛሬ ክምችትና የጥሬ ብር ክምችት ችግር ውስጥ መግባት የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ በመግታት አገራዊ ምርታማነትንና ግብይትን በእጅጉ በመጉዳት የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲቀዛቀዝና በሂደትም ወደ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ እንዲገባ ያደርጋል:: ይህም የኢኮኖሚ ቀውስ መፈጠሩ ትልልቅ ቀጣሪ ድርጅቶች ደመወዝ መክፈል ወዳለመቻል ስለሚያደርሳቸው ሠራተኞችን ወደመበተን ያመራሉ:: በየአመቱ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እየተመረቁ የሚወጡ ወጣቶች የሥራ እድል አያገኙም:: የሠው ሃይል ክፍያ ተመን በእጅጉ ይቀንሳል:: የሥራ አጥ ቁጥሩ በከተማዎች አሁን ካለበት የ16.5 በመቶ በቀጣይ በእጅጉ ያድጋል:: በ2010 በጀት አመት

Scanned with CamScanner

ከ20-25 ሚሊየን ሠዎች በድህነት ውስጥ የሚገኙ ሲሆን አገሪቱ ወደኢኮኖሚ ቀውስ ስታመራ የድሆች ቁጥር በእጅጉ ይጨምራል። አገሪቱ በ2017 ዓ.ም አሳካዋለሁ ብላ ያቀደችው የመካከለኛ ገቢ ግብ ተርታ የመሠለፍ ግብ ሌሎች አመታትን ይጠብቃል።

መንግስት ያለበትን የብር እጥረት ለመፍታት በብሔራዊ ባንክ በኩል ብር ማተም የሚችል ቢሆንምና ኢኮኖሚውን በአንድ በኩል ቢያግዘውም በሌላ በኩል ደግሞ ይህ እሴት ሳይጨምር የመጣ ገንዘብ በኢኮኖሚው ውስጥ የኑሮ ውድነትን የሚያስከትል በመሆኑ ነው። በግንቦት 2010 ዓ.ም የአገሪቱ የግሽበት መጠን 13.6 በመቶ ሲሆን ይህም መንግስት አሳካዋለሁ ብሎ ካቀደው ባለአንድ ዲጂት ግሽበት አንፃር ከፍ ብሎ መገኘቱን ሲሆን ‹‹በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ›› ይሉ ዘንድ በዚህ ግሽበት ላይ የብር ማተም ሚናው ጉዳዩን የበለጠ የሚያባብሰው ነው የሚሆነው። ይህ ምንም እንኳን ኢኮኖሚውን በማነቃቃት የሥራ አጥ ቁጥሩን የመቀነስ ውጤት የሚያመጣ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ግሽበቱ በቋሚ ደመዎዝ የሚተዳደሩትን የሚጎዳ ይሆናልና አንዱን መምረጥ ያስፈልጋል።

እውሮፓዊቷ ግሪክ በ2009 (እ.ኤ.አ) የዓለም የገንዘብ ቀውስ ከተከሰተ በኋላ የገጠማት የኢኮኖሚ ቀውስ ኢትዮጵያ በ2010 ዓ.ም ከገጠማት ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ይታያል። ለዚህ ምክንያቱ የመንግስት ወጪዎች በእጅጉ መብዛታቸው ፣ የንግድ ሚዛን ጉድለት ፣ የኢኮኖሚ እድገቱ መቀዛቀዙ ፣ የመንግስት ብድር መብዛቱ፣ በመንግስት መ/ቤቶች በኩል የነበረው በበጀት ልክ የመተዳደር ችግር አይነተኛ ምክንያቶች ነበሩ። በወቅቱ የግሪክ የሥራ አጥ ቁጥር ከነበረበት 4 በመቶ ወደ 10 በመቶ ያደገበት፣ የሠው ሃይል ዋጋ በ20 በመቶ የረከሰበት አጋጣሚ እንደነበር ይነገራል።

የኢትዮጵያ መንግስት ካለበት የውጭ ምንዛሬም ሆነ ከገንዘብ ቀውስ ለመውጣት ታላላቅ ድርጅቶች ማለትም የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኢትዮ ቴሌኮም ፣ ባህር ትራንዚት፣ ስኳር ኮርፖሬሽን፣ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ፣ የምድር ባቡር ድርጅትና ሌሎችንም በከፊል ለውጭና ለአገር ውስጥ ባለሃብት ለማስተላለፍ እንዲወስን አድርጎታል።

የበላይ አመራሩ ለድርጅቱ የካሽ ፍሎው ችግር እንዴት መንስኤ ይሆናል?

ለአንድ ድርጅት የካሽ ፍሎው ችግር ብቻ ሳይሆን ለአንዲት አገር ኢኮኖሚ መዛባት የበላይ አመራሩ የሚወስዳቸው ገንዘብ ነክ ወይም ኢኮኖሚ ነክ ውሳኔዎችና ፖሊሲዎች አብይ ምክንያት ናቸው። ዋናው መንስኤ ግን አሁንም ከድርጅቱ አመራር በስተጀርባ ያለው የአወሳሰን መንፈስ ነው መመርመር ያለበት። ድርጅቱን ለተለያየ የካሽ ፍሎው ቀውስ የሚያጋልጡ ዋና ዋና የገቢ ማስገኛና ከከፍያ ወጭዎች በስተጀርባ ያለው ውሳኔ ነው መፈተሽ የሚኖርበት። ምንጊዜም ቢሆን ውሳኔዎች በጉጉትና በስጋት መሃከል የሚወሰኑ ከሆነ የጉጉትና የስጋት ስሜቶች ምክንያታዊ ባለመሆናቸው ድርጅቱ (አጋር) አደጋ ላይ መውደቃቸው አይቀርም።

ድርጅቱን ለካሽ ፍሎው ስጋት የሚጥሉ መንስኤዎች!!

ለአንድ ድርጅት የካሽ ፍሎው እጥረትም ሆነ መትረፍረፍ ሚና የሚጫወቱ ዋና ዋና መንስኤዎች የምንላቸው የድርጅቱ የአትራፊነት ደረጃው (ዝቅተኛ ወይም ከፍተኛ)፣ ድርጅቱ ጥሬ እቃዎችን ሲገዛ የሚፈጠረው ክምችት (ኢንቨንተሪ ወይም ስቶክ መጠን)፣ ድርጅቱ የሚፈጠረው ክምችት ... ያለቀላቸውን ምርቶች ገዝቶ ያለቀላቸውን ምርቶች ሲያመርት ወይም ያለቀላቸውን ምርቶች ገዝቶ

Scanned with CamScanner

መልሶ በመሸጥ ላይ የተሰማራ ቸርቻሪ ከሆነ የእነዚህ ያለቀላቸው ምርቶች ክምችት (ኢንቨንተሪ ወይም ስቶክ መጠን) ፤ ድርጅቱ ቋሚ ንብረቶችን ሲገዛ (መሬት፣ ህንፃ ፣ መኪና ፣ ማሽነሪ) ያደረገው የኢንቨስትመንት ውሳኔ ፤ የድርጅቱ አመራር ቀድሞውኑ ይህን ቢዝነስ እንደስራ ፈጣሪ ሲጀምረው የወሰነበት የኢንቬስትመንት ውሳኔ አይነት፣ ድርጅቱ ለደንበኞቹ የሸጠላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች የዱቤ ሽያጭ ክምችቶች (ሪሲቬብልስ) እንዲበዙ የተደረጉበት ውሳኔዎች የድርጅቱን ካሽ ፍሎው የሚቀንሱ ሊሆኑ ይችላሉ።

እንግዲህ ከላይ ያሉ ዋና ዋና የካሽ ፍሎው (የጥሬ ገንዘብ መጠንና ዝውውርን) የሚወስኑ ዘዋሪ ምክንያቶች *(Cash flow drivers)* የሚዘወሩት በድርጅቱ የበላይና መካከለኛ አመራሮች ውሳኔ ሲሆን ከውሳኔው በስተጀርባ ያለው ነገር ነው ዋናው የውጤቱ መነሻ። ይህን የውጤት መነሻ መለየቱ ነው ወደ ዘላቂ መፍትሔው ሊወስደን የሚችለው።

ዘላቂ መፍትሔው ምንድነው?

የአንድ ድርጅት ዘላቂ የካሽ ፍሎው መፍትሔ የምንለው በድርጅቱ የባንክ አካውንት ላይ የሚኖረው የጥሬ ገንዘብ ክምችት መጠን ከድርጅቱ የገንዘብ ፍላጎት በላይ እንዲሁም ከድርጅቱ ባለቤቶች የገንዘብ ፍላጎት በላይ መሆን ሲችል ነው። ይህም ማለት ድርጅቱ ለአቅራቢዎች ፤ ለሠራተኞች ፤ ለአበዳሪዎች መክፈል ያለበትን ገንዘብ በስምምነቱ የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ መክፈል ሲችል እንዲሁም የድርጅቱ ባለቤቶች ከድርጅቱ በአመቱ መጨረሻ መውሰድ የሚችሉትን የትርፍ ክፍፍል *(Dividend)* መክፈል ሲችል ፤ ድርጅቱ ለአገር ውስጥ ገቢ መክፈል ያለበትን ልዩ ልዩ ግብሮችን በተገቢው ጊዜ ውስጥ መክፈል የሚያስችለውና በመጨረሻም ለማስፋፊያም ሆነ ለአዳዲስ ኢንቨስትመንቶች የሚያስፈልጋ ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብ በአካውንቱ ውስጥ መኖር ሲችል ድርጅቱ ወደ ዘላቂ መፍትሔ ውስጥ ገባ ለማለት እንችላለን።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን አንድ ድርጅት ከድርጅቱ ፍላጎት በታች በእጅጉ ያነሰ ወይም ከድርጅቱ ፍላጎት በላይ በእጅጉ የበዛ የጥሬ ገንዘብ ክምችት ማለትም ‹‹*Excess cash*›› ሊኖረው ይችላል። ሁለቱም ታዲያ በድርጅቱ ላይ ውጥረትን ያስከትላሉ። ውጥረት ደግሞ በራሱ ስቃይ ነውና ሁለቱም መፍትሔ ያስፈልጋቸዋል። ካሽ ሲበዛም ሲያንስም ድርጅቱንም ሆነ አሠራሩን ያስጨንቃል እንደማለት ነው።

በድርጅቶች ላይ የሚታዩ የካሽ ፍሎው ችግር ዓይነቶች!!

የተለያየ አይነት የካሽ ፍሎው ስቃይ አለ። አንዳንድ ድርጅቶች ከተመሠረቱ ጀምረው የባንክ አካውንታቸው የማያልፍለት ሲሆን ይችላል። ማለትም ለረዥም ጊዜ የድርጅቱ አካውንት በጥሬ ገንዘብ ድርቅ የሚያውቀው በመሆኑ የተነሳ ድርጅቱም ሆነ አመራሮቹ ለረዥም ጊዜ አብረው ስቃይ የሚፈራረቅባቸው ይሆናሉ። ይህን መሰል ስቃይ ‹‹ስር ሠደድ የካሽ ፍሎው ችግር›› ወይም *(Pervasive cash flow suffering)* እንለዋለን። ሌላኛው አይነት የካሽ ፍሎው ስቃይ ደግሞ ቀድሞ በተፈጠረው የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ቀውስ የተነሳ ድርጅቱ ሌላ ቀውስ ውስጥ የሚገባበት አይነት ነው። ይህም ማለት ድርጅቱ በውጥረት ውስጥ ሆኖ እያለ አመራሮቹ እንደ መፍትሔ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ሌላ የገንዘብ ቀውስ የሚፈጥሩ በመሆናቸው (ለምሳሌ መክፈል የማይችሉትን ብድር በመውሰድ፣ ወይም ትርፍ የማያመጣ ቴክኖሎጂ፣ መኪና ፣ ማሽነሪ መግዛት ወይም ሌላ ቢዝነስ መጀመር) አልያም ደግሞ ቀድሞ በተፈጠረው ቀውስ ሳቢያ አብረዋቸው

የሚሠሯቸው (አቅራቢ ፣ አበዳሪ ፣ ተረካቢ) አጋሮች ከእነሱ ጋር መስራት ሲያቆሙ ሌላ ተጨማሪ ስቃይን ወደ ማስተናገድ ያመራሉ። ይህ እንግዲህ የመጀመሪያው ቀውስ ያስከተለው ሌላ ቀውስ መሆኑ ነው።

በሶስተኛ ደረጃ ድርጅቱ በሆነ ጊዜ ላይ በጣም አስደሳች የሚባል የጥሬ ገንዘብ ክምችት ይኖረዋል። ይህ መሠል ካሽ ፍሎው መር "የጫጉላ ሽርሽር" ታዲያ የሚቆየው ለተወሰነ ጊዜ ይሆንና እንደገና ከትንሽ ሳምንታት በኋላ ድርጅቱም ሆነ ባለቤቱ መልሰው ውጥረት ውስጥ ይገባሉ። ይህ መሠሉ እንደበልግ ዝናም ያዝ ለቀቅ የሚያደርግ የካሽ ፍሎው ስቃይም *(cyclical cash flow suffering)* ራሱን የቻለ ዘላቂ መፍትሄ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

እንግዲህ አንድ ድርጅት ከላይ ባሉት በአንዱ ወይም በሁለቱ ወይም በሶስቱም ሊያልፍ ይችላል። በእርግጥ በአራተኛ ደረጃ በጥቂት ድርጅቶች ላይ የሚከሰተውና ከፍተኛ የሚባል (የተትረፈረፈ የጥሬ ገንዘብ ክምችት) ወይም *(the suffering of excess cash)* መኖር ነው። ይህም ራሱን የቻለ ችግር በመሆኑ መፍትሔ ያስፈልገዋል። ይህ መሠሉ የካሽ ፍሎው ችግር በድርጅት ላይ ብቻ ሳይሆን በአንድ አገር የገንዘብ ካዝና ወይም የውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይ የሚከሰትም ሲሆን በግለሰቦች ደረጃም የሚስተዋል ሊሆን ይችላል።በዚህ የተነሳ የድርጅቱን የሃብት አጠቃቀም ብቃት ዝቅ እንዲልና *(Less Asset Turnover)*፣ ከባለቤቶች ሃብት አንፃር የድርጅቱ ትርፍ እንዲወርድ *(Less ROE)*፣ ድርጅቱ ገንዘቡን ሌላ ቦታ ኢንቨስት ቢያደርገው የሚያገኘውን ጥቅም ቢያጣ፣ እንዲሁም ጥሬ ገንዘብ ኢንቨስት ባለማድረጉ ለግሽበት ሊጋለጥ የሚችል ሲሆን ብርም ከዶላር አንፃር በመመምሪያ እንዲዳከም ከተደረገ የበለጠ ዋጋው ይቀንሳል።

አንድ ድርጅት ሊኖረው የሚገባ የካሽ ፍሎው መጠን!!

አንድ ድርጅት ሊኖረው የሚገባው የካሽ ፍሎው መጠን በጣምም ያልበዛ በጣም ያላነሰ መሆን አለበት፣ የተመጠነ የጥሬ ገንዘብ ክምችት ሊኖረው ይገባል። ይህም ማለት ከድርጅቱና አጋሮቹ (ኢንቨስተሮች ከሚጠብቁት ትርፍ ክፍፍል፣ አበዳሪዎች ከሚጠብቁት ተከፋይነት) ድርጅቱ ከሚያስፈልገው ዓመታዊ የስራ ማስኬጃ ወጭ እና በመጠባበቂያነት ከሚኖረው ገንዘብ በተጨማሪ ለማስፋፊያ ወይም የአዳዲስ ኢንቬስትመንቶች በቂ ገንዘብ ያለው መሆን አለበት። የድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ በጣም የበዛ ከሆነ ወደ ተመጠነው ክምችት *(optimal cash flow)* ይቀየር ዘንድ የድርጅቱ የበላይ አመራሮች ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ማሳለፍ ይኖርባቸዋል(በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ተገልጿል)።

በዋናነት ግን ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ድርጅቱን ለጥሬ ገንዘብ ድርቅ ያጋለጠውን የውሳኔ ምክንያት ማስተካከል ያስፈልጋል። የድርጅቱን የሽያጭ ገቢና ትርፍ ለማሳደግ በሚል የሚያደርጓቸው ጉጉት መር ውሳኔዎች መሬት ላይ ካለው እውነታ ጋር የማይጣጣሙ ይሆንና ድርጅቱን ለካሽ ፍሎው ችግር ሊዳርገው ይችላል። እንደሚታወቀው የኢኮኖሚክስ መርህ እንደሚያምነው ትርፍ ደግሞ ነጋዴዎችን የበለጠ የሚያተጋው የትርፍ ጉጉት ነው። ብዙውን ጊዜ ሥራ ፈጣሪዎችን ከገበያ መሟሟቅ ጋር ይተሳሰራል። ገበያቸው ሲቀዘቅዝ ፊታ የሚያደርጋቸው ገበያቸው ሲደራ ነው። ገበያቸው ሲቀዘቅዝ ፊታ የሚያደርጋቸው ገበያቸው ሲደራ ነው። ሙዳቸውም አብሮ ምች እንደመታው ሠው ቆሌያቸው ይገፈፋል፣ ሙዳቸውም አብሮ ምች እንደመታው ሠው ቆሌያቸው ከገበያው ስሜት ጋር የተሳሰረ ይቀዘቅዛል። ደስታቸውና ትካዜያቸው ከገበያው ስሜት ጋር የተሳሰረ ነው።

ገበያው ሲደራ ለምን ፊታ ይላሉ? ቢባል ደግሞ ከደራ ገበያ በስተጀርባ አማላይ ትርፍ ስለሚኖር ነው። ከዚህ ትርፍ ደግሞ ብዙ

ገንዘብ ወደ ግል ባንክ አካውንታቸው የሚፈስ ይሆናል። ይህም በግል ህይወታቸው ውስጥ ያስደስታል ብለው የሚያስቡትን ነገር በመግዛት ይጠቀሙበታል። ብዙውን ጊዜ ሥራ ፈጣሪዎችን በእጅጉ ገበያ ሲደራ የሚያስደስታቸውም መጀመሪያውንም ሪስክ ወስደው ወደ ንግድ የገቡበት ምክንያትም ከትርፉ በስተጀርባ ያለው አማላይና አስደሳች የተቀናጣ አኗኗር ነው። በዚህ መሠል ከብዙዎች ገበያ ተኮርና ትርፍ ተኮር ጉጉት ውስጥ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ታዲያ ከእውቀት ይልቅ ስሜት ላይ የተንተራሱ ይሆናሉ። የጉጉት ስሜት ውሳኔውን በትክክለኛ እውቀትና መረጃ ላይ እንዲንተራስ ስለማያደርገው ልዩ ልዩ የግዥ፣ የብድር፣ የሽያጭና የኢንቬስትመንት ውሳኔዎች ውጤታቸው በተጠበቀው መልኩ ሳይሆን ይቀራል። ይህን የትርፍ ጉጉት ለማሳካት ሲባል ደግሞ ገበያንና ትርፋማነትን ለፈተና ሊያጋልጡ ይችላሉ የሚባሉ እስኪ ጉዳዮች ሌላ የውሳኔ ምንጭ ሊሆኑም ይችላሉ። ‹‹ምናልባት እንዲህ ቢሆንስ›› በሚል አስተሳሰብ እስኪ ጉዳዮች የሌላቸውን ጥንካሬ በማጉላት ስጋት መር የሆነ ግዥ ፣ አመራረት፣ አሻሻጥ፣ ኢንቬስትመንት ፣ ብድር ውስጥ ይገባል። ይህ ሁሉ የውሳኔ አይነት ደግሞ ከበስተጀርባው በቀጣይ ከሚወጣ ወጪ ወይም ይገባል ተብሎ ከሚታሰብ ገቢ ገንዘብ ጋር የተያያዘ ነው። ይሁን እንጂ በስጋት ላይ የተንተራሰው ውሳኔ በሂደት የሚያመጣው ውጤት ግን እንደተጠበቀው ሳይሆን የሚቀርበት እድሉ ከፍተኛ ነው። በዚህ መሃከል የድርጅቱ የካሽ ፍሰው መጠን ችግር ውስጥ ይገባል። መልሶም የውሳኔው አካል የሆነው የበላይ አመራሩ በዚህ ውጥረት ሳቢያ አብሮ ችግር ውስጥ ይዘፈቃል።

የድርጅቱን የካሽ ፍሰው ችግር የሚፈጥሩት ጉጉትና ስጋት መር ውሳኔዎች ናቸው?

እነዚህ ጉጉትና ስጋት መር ውሳኔዎች በአመዛኙ ስሜት ተኮር ውሳኔዎች ናቸው። በስሜት ውስጥ ችኮላ እንጂ ተረጋግቶ ማሰብ በምክንያት ማሰብ ይጠይቃል። በምክንያት አይኖርም። ተረጋግቶ ለማሰብ በምክንያት ማሰብ ይጠይቃል። ትክክለኛና በቂ ለማሰብ ደግሞ መረጃዎችን መሰብሰብ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ በጉጉትና መረጃዎችን ለመሰብሰብ በቂ ጊዜ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ በጉጉትና በስጋት በሚመራ ውሳኔ ውስጥ ችኮላ እንጂ በቂ ጊዜ የለም። በዚህ የተነሳ ውሳኔው መሬት ላይ ያለውን ነገር ያላገናዘበ ስለሚሆን ነው ችግር የሚከተለው። በመሆኑም ከጉጉቱና ከስጋት ውሳኔ በስተጀርባ አላዋቂነት አለ ማለት ነው።

የመጀመሪያው አላዋቂነት ሥራ ፈጣሪዎች ራሳቸውን በሃብት መጠን ወይም በሃብት በሚገዙ ነገሮች ላይ የበላይነት ስሜትን ወይም መደሰትን መሠረት ማድረጋቸው ነው። ይህ መሠሉ ራስን በገንዘቡ መጠን ልክ ለማስደሰት ማሰብ ሲታይ በመጨረሻ የሚያመጣው ስቃይ እንጂ እውነተኛ ደስታ አለመሆኑን መረዳት አለመቻል ነው። ትርፍ ላይ የተጣበቀ ጉጉት ራስ ወዳድነትን በእጅጉ በማጉላት ስለሌሎች የድርጅቱ አጋሮች ጥቅም ለማሰብ አያስችልም። ትርፍ እስከመጣ ድረስ፣ ገበያ እስከመጣ ድረስ ደንበኛውንም ሆነ አቅራቢውን ለወደፊቱ ለመያዝ የሚያስችልን አሠራር ከመከተል ይልቅ አለታዊውን ገቢና ትርፍ ላይ ብቻ ወደመንተራስ ይወስዳል። በአንዳንድ ነጋዴዎች ላይ የሚታዩ የተጭበረበሩ ምርቶችና አነጋገዶች መነሻቸው ይሄ ነው።

ይሁን እንጂ በቁጥር ትንሽም ቢሆኑ በቢዝነስ ውስጥ ትልቁ ደስታቸውን ሰዎችን ማስደሰት ቅድሚያ የሚሠጡት የተሻለ አካሄድ አላቸው። ትርፉ እንደተጠበቀ ሆኖ በስራውና ስራው በሚያመጣው

Scanned with CamScanner

ውጤት የሚደሰቱ ነጋዴዎች የካሽ ፍሎው ችግር አይገጥማቸውም። ምክንያቱም ከራስ ወዳድነት ጉጉትና ስጋት ነፃ በመሆናቸው ውሳኔያቸውን ሲወስኑ ጊዜ ወስደውና አመዛዝነው ነው። ውሳኔ የበለጠ ደንበኛን ይጠቅማል፣ የበለጠ ገቢን ያመጣል ፣ በዚህ ውሳኔስ የድርጅቱ ሠራተኞችና አቅራቢዎች እንዳይጎዱ ምን ሊደረግ ይገባል? የሚሉ አስተሳሰቦችን ቀድመው የሚያስቡ ሲሆን አንድን ውሳኔ ከመወሰናቸው በፊት ወደተመሳሳይ ውጤት ሊወስዱ የሚችሉ ሌሎች የውሳኔ አማራጮችን አወዳድረው ነው።

የተለያዩ የውሳኔ አማራጮችን በመጠቀም ውሳኔዎቹ ከሚያመጡት ጥቅምና ጉዳት አንፃር ለመመዘን በቂ መረጃን ይጠቀማሉ። ዛሬን የሚመለከቱት በዛሬነቱ እንጂ ዛሬ ልክ እንደነሁን ቀደሙ ያለ ተመሳሳይ ጊዜነው በሚል አይደለም። ዛሬ ላይ ያሉ ለውጦችን የሚረዱት በመረጃ ላይ ተንተርሰው ነው። ይሁን እንጂ በጉጉትና በስጋት ውስጥ የሚወስኑ ግን ከአሁን ቀደም ያሰጋቸውን ጉዳይ ዛሬም ውስጥ ሊኖር እንደሚችል፣ ካሁን ቀደም ወስነው የተሳካላቸውን ገንዘብ ነክ ውሳኔ ዛሬም ላይ ቢጠቀሙበት ያንኑ ውጤት ሊደግሙ እንደሚችሉ በማሰብ ይወስናሉ። ዛሬን በዛሬነቱ ሳይሆን በትናንትነቱ ውስጥ ሆነው ይወስናሉ። ይህ ነው ጥበብ የጎደለው ውሳኔ የሚባለው። ይህ መሠሉ አለማወቅ ጉጉትንና ስጋትን ይወልዳል፣ ጉጉትና ስጋት ደግሞ መልሶ የካሽ ፍሎው ስቃይን ይወልዳል።

ዘላቂ መፍትሔው ምንድነው?

ዘላቂ መፍትሔው ይህን የውሳኔ ባህሪ መቀየር ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ድርጅቶች ለምንድነው ለረዥም ጊዜ በካሽ ፍሎው ችግር ውስጥ የሚገቡት? ስንል ለችግሩ የሚያጋልጣቸው ይህ መሠሉን የውሳኔ ባህሪ በተለያየ ጊዜ መልሰውና መላልሰው ስለሚጠቀሙበት ነው። ችግሩን በፈጠረው አስተሳሰብ ችግሩን ከማወሳሰብ የዘለለ ፋይዳ የለውም። በፈጠረው አስተሳሰብ ... ዛሬን የሚወስኑት ከአሁን ቀደም ባዳበሩት የውሳኔ ልማድ ሳያውቁት ዛሬን የሚወስኑት ከአሁን ቀደም ባዳበሩት የውሳኔ ልማድ ውስጥ ሆነው ነው። የከዚህ ቀደሙ ልማዳቸው በዛሬው ውሳኔያቸው ላይ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል። ስለዚህ የካሽ ፍሎውን ውጤት መቀየር አልቻሉም።

ይህን መሠል ባህሪ ለመቀየር የመጀመሪያው መፍትሔ በቅድሚያ ሠዎችን በማገልገል ውስጥ የሚደሠቱ መሆናቸውን እንጂ ከንግዱ የሚያገኙት ገንዘብ ዋናው ምክንያታቸው መሆኑን ሲያቆሙ ነው። ትክክለኛው ደስታ በስራቸውና ስራቸው በሚያመጣው ሌሎችን የማስደሰት ውጤት ጋር የተያያዘ በሆነ ቁጥር የበለጠ የድርጅቱ ትርፋማነት ይጨምራል። ትርፍ ዋና ግባቸው ስለሆነ አይደለም፣ ትርፍ ከፊል ግባቸው ነው። ሌሎችን ማስደሰት ላይ የተንተራሰ ቢዝነስ ስንል ሠራተኞች ደስ ብሏቸው የሚሠሩበት፣ ደንበኞች ደስ ብሏቸው የሚገበዩበትና በገበዩት ምርት (አገልግሎት) የበለጠ ተጠቃሚ በመሆናቸው መደሠታቸው፣ ከድርጅቱ ጋር የሚሠሩ አቅራቢዎችና ሌሎች አጋር ድርጅቶች ከድርጅቱ የሚጠብቁትን ክፍያዎች በማግኘታቸው መደሰታቸው ነው የድርጅቱ ትልቁ ሃብት። ይህ በሆነ ቁጥር ሠራተኞችም፣ ደንበኞችም ፣ አቅራቢዎችም፣ አበዳሪዎችም፣ አጋሮችም ወደፊት አብረው ለመስራትና ለመገበየት ድርጅቱን በእጅጉ ይመርጡታል። ይህ የማይታይ እና በቁጥርም የማይቆጠር ድርጅታዊ ሃብት የሚቆጠረውንና የሚታየውን ገንዘብና ቁስ አካላዊ ሃብት ይፈጥራል፣ ያበዛልም። እንዲህ መሠል የንግድ ሰዎች ብዙ ደስታቸውን የሚያገኙት በዚህ መሠሉ የማይታይ ድርጅታዊ ሥራና ትስስር ውስጥ ነው። ከፊሉ ደስታ ነው ከገንዘብ ትርፍ የሚገኘው። ይህ መሠሉ ባህሪያቸው ደግሞ የድርጅቱን የበዛ የጥሬ ገንዘብ ለግል

መደሰቻና ቅንጦት ላይ ከማዋል ይልቅ ሌሎችን ሊጠቅም ወደሚችል ኢንቬስትመንት ላይ መልሰው የሚያውሉ በመሆናቸው የካሽ ፍሰው መትረፍረፍ ካልሆነ በስተቀር የካሽ ፍሰው እጥረት የሚያጋጥማቸው አይደሉም። ከባንክ ገንዘብ ሲበደሩ ድርጅቱ ከዚህ ገንዘብ እንዴት ሊጠቀም ይችላል፤ ድርጅቱ ተወዳዳሪነቱን እንዴት ሊያሳድግ ይችላል፤ ድርጅቱ ደንበኞቹን እንዴት የበለጠ ሊያስደስት ይችላል በሚል ነው እንጂ ከዚህ ብድር (ድርጅቱ ብድሩን ቢከፍለውም) ‹‹እኔ›› እንዴት ልጠቀምበት እችላለሁ በሚል አይደለም። ውሳኔያቸው ግልፅና ሃቅን የተንተራሰ ነው። ገንዘቡም የሚበረከትላቸው በዚህ የተነሳ ነው።

በመሆኑም ባህሪን ለመቀየር መሠረታዊ መፍትሔው ተገቢ ገንዘብ ነክ የውሳኔ መርህን ደጋግሞ በመተግበር ውስጥ በመለማመድ ነው። ይህን መሠል ምክንያታዊና መረጃ መር ድርጅታዊ ውሳኔ ከትንሿ ገንዘብ ጀምሮ መለማመድ ከተቻለ አዕምሮ የድሮውን የውሳኔ ልማድ በመቀየር አዋጭውንና የድርጅቱን ካሽ ፍሰው ችግር በዘላቂነት ሊፈታ የሚችልን ባህል ይላበሳል። ይህ መሠል የውሳኔ ባህሪ በድርጅቱ የበላይ አመራር ሲዳብርም በሂደት የአመራሩ ባህሪ የድርጅቱ ባህሪ ወደ መሆን ያመራል። ሌሎችም የበታች አመራሮች ይህን መሠል የተረጋጋ ምክንያታዊና መረጃ መር የውሳኔ ባህሪ ይጋባባቸዋልና ነው።

እንዲሁም የድርጅቱ የበላይና የበታች (የዲፓርትመንት) አመራሮች ጭምር ሊከተሉት የሚገባ የአወሳሰን ስርአት መኖር አለበት። ግዥ ላይ፣ የጥሬ እቃና የምርት ክምችት አስተዳደር ላይ ፣ ሽያጭ ላይ ፣ ኢንቬስትመንት ላይ ፣ ዋጋ አወጣጥ (አተማመን ላይ) ፣ ወጭ ቁጠባ ላይ ፣ ትርፍ አስተዳደግ ላይ፤ ብድር አወሳሰድ ላይና በሌሎችም። ለዚህ መሠሉ ውጤታማ ድርጅታዊ የገንዘብ ባህል ታዲያ ሁሉም በጋራ የሚመራበት የአወሳሰን ፕሮቶኮል ያስፈልጋል። በዚህ መፅሐፍ ደራሲ የተዘጋጀውም ‹‹ የገንዘብ ህጎች›› የተሰኘው መፅሐፍም ሲቀረፅ

ዓላማው የድርጅቱን ካሽ ፍሰው ለማሳደግ የሚጠቅሙ የልዩ ልዩ ዲፓርትመንቶች ውጤት ፈጣሪ መመሪያ ላይ በተንተራሰ መልኩ ነው። የፋይናንስ ሲስተም የምንለውም ይህንን ቅደም ተከተላዊ የአወሳሰን ስልት የያዘ በመሆኑ ነው።

‹‹በፋይናንስ ስርዓት›› መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት የፋይናንስ ፖሊሲዎች የድርጅቱን ባህል የሚቀይሩት እንዴት ነው?

በስነ-እንጎል ሳይንስ ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ባለሙያዎች እንደሚናገሩት ከሆነ አንድ ግለሰብ አንድን መጥፎ ልማድ ለመቀየር ከፈለገ ጥሩው ልማድ ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚከናወን በትክክለኛ ባለሙያ ቅደም ተከተላዊ አፈፃፀሙን በመመሪያ መልክ (*Instruction or Policy*) ሊቀረፅለት ይገባል። ይህ ቅደም ተከተላዊ አተገባበር ታዲያ ተደጋግሞ ሲተገበር ግለሰቡ ትክክለኛውን ልማድ ያዳብራል፤ በመጨረሻም ባህሪው ያደርገዋል። በግላችን የምናከናውናቸው ትንንሽ ልማዶች ለምሳሌ ፊት መታጠብ፣ ውሃ ዋና ፣ አመጋገብ ፣ መኪና መንዳት እና የመሣሠሉ ችሎታዎችን አሠልጣኞቻችን (ወላጆቻችን) በትደም ተከተል መልክ በነገሩንና ባሳዩን መሠረት ደጋግመን ስለተገበርናቸው ነው። መጀመሪያ ላይ አስቸጋሪ ሥራ መስሉም ከአጠገባችን ሆነው በቅደም ተከተሉ መሠረት እንድንከውን ስናጠፋም እያረሙን ስላደግን ነው ዛሬ ላይ ልማዶቹ ሊዳብሩ የቻሉት። ዛሬ ላይ ታዲያ ፊታችንን ስለመታጠባችን ትዝ አይለንም። አንዴ ልማድ ስለሆነ ሳናውቀው እንታጠባለን፤ ስንበላም እንዴት መብላት እንዳለብን እያሰብንም አይደለም፤ ውሃ ዋናም ውስጥ ዘለን ስንገባ እንዴት መዋኘት እንዳለብን ሳናስብ ነው፤ መኪና ስንነዳም በየደቂቃው እንዴት

Scanned with CamScanner

ነበር መንዳት ያለብኝ በማለት አይደለም:: አንድ ጊዜ በልማድ መልክ ዳብሯልና:: እነዚህ ነገሮች ታዲያ ቀድሞውኑ ከተሳሳቱ ህፃኑ ልጅ የተሳሳተ ልማድ ይዞ ያድጋል:: በኋላም ልማዱ ካስከተለበት ችግር ለመውጣት ይከብደዋል:: በጎልማሳ ዘመናቸው አስቸጋሪ የሚባሉ ሠዎች የመጥፎ ልማዶች ባለቤት ስለሆኑ ነው:: ይህ ደግሞ በተገቢው ሳይሆን በተሳሳተ ትዕዛዝና አሳዳጊ ስላደጉ ነው::

ገንዘብ ነክ ውሳኔዎችም የልማድ ውጤቶች ናቸው:: ብዙውን ጊዜ ታዲያ በልጅነት በቤተሰብ ውስጥ፣ በት/ቤትና በኮሌጅ ውስጥ ህጎችን የገንዘብ አወሳሰን ስርአትን ስለማንማራቸው ወደ ቢዝነስ ውስጥ ሲገባ የምንወስንበት እውቀትም ሆነ ያለፈ ልምድ የለንም:: ትደም ተከተላዊው የአወሳሰን መርህ ባለመኖሩም የሰከነና ትክክለኛ ውሳኔን በእጅጉ በሚጠይቀው የቢዝነስ ዓለም ውስጥ ስለምንቸገር ነው በመጨረሻም ለድርጅቱ የካሽ ፍሎው ጣጣ ውስጥ መዳረጉ የሚመጣው::

ልማድ ደግሞ አንዴ ከዳበረ እኛ ከዚህ መሠል የኋላ የውሳኔ ስህተት ለመውጣት ስለፈለግን ብቻ በሚፈለገው ደረጃ ፍጥነት መውጣት አስቸጋሪ ነው:: ለዚያም ነው ትክክለኛውን መመሪያ እንዲህ ከመሠሉ መፅሐፍት ልንማረውና ልናዳብረው የሚገባው::

‹‹የገንዘብ ህጎች›› የሚለውም መፅሐፍ ዋና ዓላማው ይህ ነው:: መፅሐፉ በተለያዩ ድርጅቶች (በግልም ሆነ በመንግስት) ውስጥ ያሉ አመራሮች በትክክል ሊማሯቸውና ሊመሩባቸው የሚገቡ ገንዘብ ነክ የውሳኔ መርሆችን የያዘ ነው:: እነዚህን መርሆዎች በተለይ የበላይ አመራሩ ቀጥሎም በየዲፓርትመንቱ ያሉ አመራሮች በጋራ የሚከተሏቸው በሆኑ ቁጥር የድርጅቱ የፋይናንስ ባህል ወደላቀ ደረጃ ይሸጋገራል:: ይህም የፋይናንስ ባህል በጊዜ ሂደት ውስጥ ራሱን ወደላቀ ደረጃ ሲያሸጋግር የድርጅቱም እድገት በዚያው ልክ እያበበ ይመጣል:: ድርጅቱ ራሱን ወደ ግዙፍ ደረጃ ያሸጋግራል፤ ሌሎች እህት

ድርጅቶችንም ይፈጥራል:: እነዚህም እህት ድርጅቶች የሚኖራቸው የገንዘብ ማኔጅመንት ባህል ይሄው ውጤታማው ባህል በመሆኑ እነሱም ራሳቸውን ወደ ትልቅ ደረጃ ያሸጋግራሉ:: ለዚያም ነው ከትልልቅ ድርጅቶችና ባለሃብቶች በስተጀርባ ትልቅ ገንዘብ ነክ ግለሰባዊና ድርጅታዊ ባህል አለ የሚባለው:: ግለሰባዊም ሆነ ድርጅታዊው ገንዘብ ነክ ድህነት (የካሽ ፍሎው ቀውስ) ደካማ የሆነ የገንዘብ አወሳሰንና አስተዳደር ባህል የሚፈጥረው ውጤት ነው::

በመሆኑም በግልም ይሁን በድርጅት (የመንግስትም ይሁን የግል)፤ ይህን የፋይናንስ መመሪያ በግዥ ፣ በሽያጭ፣ በክምችት አስተዳደር፣ በኢንቬስትመንት እንዲሁም በቁጠባ ውስጥ በመጠቀም አዲስ ባህል መገንባት ያስፈልጋል:: ደጋግመን በመጠቀም ውስጥ የድሮ የውሳኔ ልማዶች እያገረሹ ቢያሳስቱንም ራሳችንን እያረምን መፅሐፉንም ደጋግመን እያነበብን ወደ ላቀ ምርጥ የፋይናንስ ልማድነት ራሳችንንም ሆነ ድርጅታችንን መቀየር እንችላለን:: ድርጅት ያልመሠረቱ ግለሰቦች በግል ህይወታቸው ላይ ከተለማመዱት ነገ የራሳቸውን ድርጅት ሲከፍቱና ሲመሩ ይህን ያሳደጉትን ምርጥ ልማድ በመመንዘር ስለሚጠቀሙበት ለውጤት ይበቁበታል:: ድርጅት ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ አመራሮች በየጊዜው በመመሪያዎቹ ላይ እየተወያዩ፣ እየተራረሙ ፣ እየተማማሩ በሄዱ ቁጥር በልማድ መልክ ራሳቸውን ለማዳበር ጊዜ አይወስድባቸውም:: የድርጅቱም ባህል ቶሎ ይዳብራል:: የፋይናንስ ባለሙያዎቻቸው ደግሞ በዚህ ረገድ የበለጠ ግልፅ ያልሆኑ ፋይናንስ ነክ ቃላትንና ትርጉሞችን ሊያግዟቸው ይችላሉ::

የድርጅቱ ካሽ ፍሰው የአወሳሰን መመሪያዎች!!

ከውሳኔዎች በስተጀርባ ከላይ ያሉትን ስሜቶችና ልማዶች ማስተካከል ካልቻሉ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የማይቻል መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል። በዚህ ከተግባባን ታዲያ አንድ ድርጅት ለገጠመው የጥሬ ገንዘብ እጥረት ፤ ውጥረትና ስቃይ ሊወስዳቸው የሚገቡ ጉዳዮችን እንደሚከተለው እንያቸው።

የመጀመሪያው ጉዳይ ለድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ትልቅ ማነቆ የሆኑት ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ከመለየት መጀመር ነው። ይህም ማለት ለጥሬ ገንዘቡ ጉድለት (ቀውስ) እንደመንስኤ የሆነው ምክንያት ምን እንደሆነ መለየት ያስፈልጋል። ይህም ማለት የቋሚ ንብረቶች ግዥ፣ የጥሬ እቃዎች ክምችት መብዛት፣ ለሽያጭ ተብለው የተመረቱ (የተገዙ) ምርቶች (ሸቀጦች) መብዛት፣ በዱቤ ስራ የተሠራላቸው (ሸቀጥ የገዙ) ሠዎች ያልከፈሉት ገንዘብ መብዛትና መሠል ጉዳዮች በሚገባ መጤን ይኖርባቸዋል። በእነዚህ ነገሮች ላይ የሚወሠዱ ቀጣይ እርምጃዎች የገንዘብ ዝውውሩን እንዲነቃቃ ያደርጉታል።

ምን ማድረግ ይቻላል?

ቋሚ ንብረት ከመግዛታችን በፊት የተለያዩ አማራጭ መንገዶችን ስለመጠቀማችን መረዳት ያስፈልጋል። ቋሚ ንብረቶች አንድ የድርጅት አመራር የሚወስደውን የኢንቬስትመንት ውሳኔ ተከትሎ የሚገዛ ሊሆን የውሳኔው ብቃትና ድክመት በድርጅቱ የገንዘብ ዝውውር ላይ አዎንታዊ (አሉታዊ) ውጤትን ያስከትላል። በዚህ ዙሪያ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ በኢንቬስትመንት አወሳሰን መርሆዎች ዙሪያ የቀረበውን ትንታኔ በሚገባ ያንብቡ። በመሆኑም ቀድሞ በተገዙ ቋሚ

ንብረቶች (*Fixed assets*) ላይ ጥሬ ገንዘብ ታስሮ ስለመሆኑ መለየት ያስፈልጋል። እንዲሁም ጥቅም ላይ ባልዋለ ወይም በሽያጭ ቢወገድ ተዕፅኖ በማያመጣ ንብረት ላይ ገንዘቡ ታስሮ መሆኑንም ማጤን ሌላኛው ጉዳይ ነው።

ቋሚ ንብረት መግዛት ያለበት ሊያመጣ የሚችለው ካሽ ወይም ሊያድንልን የሚችለው በገንዘብ መልክ የሚወጣ ወጪ መኖር ያለበት ሲሆን ነገርግን ከእነዚህ ውጭ በሆነ ስሜት የተገዛ ስለመሆኑና ለድርጅቱ ጥሬ ገንዘብ ዝውውር መንስኤ ስለመሆኑ መታየት ይኖርበታል። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ንብረቱ መገዛቱ በጣም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ በቀጥታ ጥሬ ገንዘብ ከድርጅቱ ባንክ አካውንት አውጥቶ ከመግዛት ይልቅ በሌላ አማራጭ ለምሳሌ በሊዝ መልክ መግዛት ይቻል ነበር። ስለሆነም ንብረቱ አስፈላጊ ሆኖ እያለ ንብረቱ እንዲመጣ የምናደርግባቸውን አማራጮች ባለማየት የተገዛም ሊሆን ይችላል። አዲስ ንብረት ከመግዛት ያገለገለ ሆኖ ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝን ንብረት መግዛት ይቻል እንደነበርም ማጤን ያስፈልጋል (ለምሳሌ መኪና)። እንዲሁም ገንዘቡ የወጣበት ንብረት የሚሠጠውን አገልግሎት ሊተካ የሚችል ዝቅተኛ ወጭ የሚያስወጣ ዘዴ ሊኖር እየቻለ ለአላስፈላጊ ብክነት ተዳርገንም ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ ውድ ቴክኖሎጂ ከመግዛት ስራውን በርካሽ የሠው ኃይል ዋጋ ልናሠራው ከቻልን እንደማለት ነው)። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለድርጅቱ ምንም አይነት ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የማይጫወቱ ንብረቶች ሊገዙ ይችላሉ። ይህ የሚሆነው ለክብርና ለዝና በሚል ሊሆን ይችላል (ለምሣሌ የቅንጦት መኪና) ። በመሆኑም የጥሬ ገንዘብ ዝውውርን ተፅዕኖ ውስጥ ከሚከቱ ጉዳዮች ውስጥ በንብረቶች ላይ የሚፈሱ ገንዘቦች በመሆናቸው ትክክለኛ የኢንቨስትመንት መርሆዎችን ተከትሎ መወሰን በእጅጉ ያስፈልጋል።

Scanned with CamScanner

ሌላው በጥሬ እቃዎችና የሚሸጡ ምርቶች ክምችት መጠን ላይ የምንወስዳቸው ውሳኔዎችን በሚገባ መፈተሽ ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ ከጥሬ እቃ ወይም ደግሞ ከሸቀጥ አቅራቢዎች በሚገቡልን ጥቅም ከ ማባበያዎች (ለምሳሌ ከብዛት ጋር የተያያዘ ወጭ ቅነሳ) ላይ በመንተራስ ከሚያስፈልገን በላይ ልንገዛ እንችላለን። በዚህ የተነሳ ለአላስፈላጊ የጥሬ እቃ ወይም የሸቀጥ ምርቶች ክምችት እንዳረጋለን። እንዲሁም በጥሬ እቃ ግዥና ትራንስፖርት እንዲሁም ቅብብሎሽ (ትራንዚትና ጉምሩክ ነክ ጉዳዮች ወይም ሌሎች ምክንያቶች) ሳቢያ ከግዥ እስከ ርክክብ ድረስ ጊዜ ጎታች አሠራሮች ካሉ ወይም ወጪ ጨማሪ አሠራሮች ካሉ ለጥሬ ገንዘቡ ዝውውር መፋጠን አያግዝም።

በዛ ያለ የጥሬ እቃ ወይም የምርት ክምችት መያዝ የራሱ ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉት። ስለሆነም የጥሬ እቃ ወይም ያለቀባቸው ሸቀጦች ክምችት ማነስም ሆነ መብዛት የራሳቸው ጥቅምም ሆነ ጉዳት ያላቸው በመሆኑ የግዥ ውሳኔው አግባባዊ የክምችት መጠን ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መለየትም ይኖርበታል። ብዛት ያለው ክምችት እንዲኖረን የምንወስን ከሆነም ክምችቱን ለመያዝ የምናወጣውን ወጭ፣ በብድር የተገኘ ከሆነ ክምችቱን በመያዝ የምናገኘው ጥቅም ለብድሩ ከምናወጣው የወሰድ ወጪ የበለጠ ስለመሆኑ፣ ከራስ ገንዘብ ከሆነ ደግሞ በስቶክ መልክ የምንይዘው መጠን፤ ገንዘቡን ሌላ ቦታ ላይ ብንጠቀምበት እናገኝ ከነበረው ጥቅም ይልቅ የበለጠ ስለማምጣቱ ፤ እንዲሁም ክምችቱን ለማስቀመጥ የምናወጣውን የመጋዘን ወጭና ክምችቱ ጊዜ በሄደ ቁጥር ዋጋው እየቀነሰ የመሄድ እድል እንዳለውና እንደሌለው ማጤንም ያስፈልጋል።

በአንድ ድርጅት ውስጥ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ማለት በአንድ ሰው ላይ እንዳለ የደም ዝውውር ይቆጠራል። ደም ዝውውር አንድ ቦታ ሲቋረጥ የሚከተለው አደጋ ለተቋረጠበት የሰውነት ክፍል በጣም ከፍተኛ

ነው የሚሆነው። አንድ ድርጅት በባንክ ያለው የጥሬ ገንዘብ ክምችት መጠን የድርጅቱን የስራ እንቅስቃሴ በማቀላጠፍ ወይም በማስተጓጎል ይታወቃል። የገንዘብ ዝውውርን የሚወስነውና ካሽ ፍሎው በመባል የሚታወቀው በአንድ በሆነ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ድርጅቱ የሚያወጣውና ወደ ድርጅቱም የሚያስገባው ገንዘብ ማለት ነው። የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ክምችት መጠንም የድርጅቱን ውጤታማ አሰራር ብቃት ያመለክታል። ይህን የጥሬ ገንዘብ መጠን መለካትም የሚጠቅመው የቢዝነሱን ወይም የፕሮጀክቱን ገንዘብ ነክ አፈፃፀም ደረጃ ለማወቅ ነው።

አንድ ድርጅት ጥሩ የጥሬ ገንዘብ ዝውውር እንዳለው ማወቅ ምን ይጠቅማል?

የመጀመሪያው ነገር የድርጅቱ ስራዎች በገንዘብ እጥረት የተነሳ እንዳይስተጓጎሉ ይረዳል። ከዚህ አንጻርም ድርጅቱ በቂ ጥሬ ገንዘብ በካዝናው ውስጥ ይኖረው ዘንድ በወቅቱ አስፈላጊ ውሳኔዎችን ለማድረግ ትልቅ ማሳያ ይሆናል።

በሁለተኛ ደረጃ ድርጅቱ መክፈል የሚጠበቅበትን ክፍያዎች ያለ እንዳች ስጋትና እንቅልፍ ማጣት መክፈል የሚችል አቅም እንዳለውና እንደሌለው ያሳየናል። በሰላም ተኝቶ ለማደር በተለይም ቋሚ ወርሃዊ ወጪዎች (የቢሮ ኪራይ፣ የሰራተኛ ደመወዝ፣ የባንክ ብድር) እንዲሁም ከአቅራቢዎች ጥሬ ዕቃዎችን ለመግዛት የሚያስፈልገውን ያህል ጥሬ ገንዘብ መኖሩ በጣም መሰረታዊ ነው። በአንፃሩ ግን ድርጅቱ ይህን ማድረግ ካልቻለ የሚከተለው አቅጣጫ በድርጅቱ መሄድ በሚገባው ትክክለኛ መንገድ ላይ ላይሆን ይችላል።

ይህን ነገር በግለሰብ ደረጃ እንዴት እናየዋለን?

በግለሰብ ደረጃም ቢሆን የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ይመለከተናል። ለምሳሌ አንድ ሰው በስሙ የሚከፍተው የባንክ አካውንት ይኖረዋል። በየወሩ የሚያገኘውን ደመወዝ ወደ ቁጠባ ባንኩ ውስጥ ያስገባል። ይህ እንግዲህ ወደ ቁጠባ አካውንቱ የሚደረግ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መሆኑ ነው። ከዚህ የባንክ አካውንትም ለተለያዩ ወርሃዊ ወጭዎች ያወጣል። እንዲሁም በተወሰነው ገንዘብ ደግሞ ኢንቬስት ለማድረግ አክሲዮን ይገዛል። ወርሃዊ የኑሮ ወጪ ብቻ አይደለም። ካሁን ቀደም የተበደራቸው ብድሮች ካሉም ከእነሱ ውስጥ የተወሰኑትን ይከፍላል። ስለዚህ አንድ ግለሰብ ሶስት የተለያዩ ዓይነት ወጪዎች ያወጣል። ለኑሮ የሚያስፈልጉ ወጪዎችና ግዥዎች፣ ለቢዝነስ ኢንቬስትመንት እንዲሁም ብድሮችን ለመክፈል። በተመሳሳይ መልኩ አንድ ድርጅት ከሶስት አይነት አቅጣጫዎች ገንዘቡን ወደ ባንክ አካውንቱ ገቢ ያደርጋል። በወር ውስጥ የሚያገኘውን የስራ ገቢ (ከደመወዝ)፣ በወር ውስጥ ቢዝነስ (ኢንቬስት) ካደረገበት የገቢ ምንጭ እንዲሁም ከብድሮች (ከመ/ቤት፣ ከጓደኞች ወይም ከቤተሰብ)።

በመሆኑም ከተለያዩ ምንጮች የሚመጡና ወደ ባንክ የሚዘዋወሩ ጥሬ ገንዘቦች መጠን በወር ውስጥ ከባንኩ የሚወጡ ተከፋይ ጥሬ ገንዘቦች በታች በሆነ ቁጥር ግለሰቡ የገንዘብ ቀውስ (ፋይናንሻል ክራይሲስ) ውስጥ ገባ እንላለን። በመሆኑም ወጪው ትክክለኛ ይሁን አይሁን ሌላ ጉዳይ ሆኖ ግለሰቡ ግን የሚፈልጋቸውን ተከፋይ ወጪዎች ለመሸፈን የሚያስችለው የገንዘብ መጠን ሲኖረው ካልቻለ ሰላሙን ያጣል። ወይም ደግሞ የሚገባለት ገንዘብ ወደ ባንክ አካውንቱ ከሚገባበት ጊዜ በፊት ቀድሞ የሚከፈል ገንዘብ ካለ በጊዜ ከፍተት የተነሳ አሁንም ችግር ውስጥ ይገባል። በመሆኑም አንድ ግለሰብ በኑሮው ውስጥ ከፍተኛ

ገንዘብ ነክ ጭንቀት ውስጥ ሊገባ የሚችለው በሁለት ምክንያት ነው፤ የመጀመሪያው ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚያገኘው የገንዘብ መጠን በዚያ ጊዜ ውስጥ ከሚያስወጡት የተለያዩ ወጪዎች ከሚያስፈልጉት መጠን በታች ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ገንዘቡ ወጪ በሚደረግበት ጊዜ ውስጥ ወይም ገንዘብ ወጪ ለማድረግ በሚፈልግበት ጊዜ ውስጥ ገቢ መሆን ካለበት ጊዜ በላይ ከዘገየ የሚሉት ናቸው። በአስፈላጊ ከፍያ ወቅት ተፈላጊው ገቢ የሚደረግ ገንዘብ ከዘገየ ጭንቅና ውጥረት ይፈጠራል። ሊከፈላቸው ከሚገቡና እንዲከፈላቸው ከሚጠብቁ ግለሰቦች ጋር አላስፈላጊ መጋጨት ይፈጠራል። ግለሰቡ የአዕምሮ ሰላሙን ያጣል። እንግዲህ በግለሰብ ደረጃ ያለው የጥሬ ገንዘብ ዝውውር በትክክል መተዳደር ካልቻለ የሚከሰተው ይህን ነው የሚመስለው።

አንድ ሰው በትክክል ማስተዳደር ያለበት ጥሬ ገንዘቡን ነው ወይስ የጥሬ ገንዘብ ዝውውሩን?

ሁለቱንም ነው መሆን ያለበት። ጥሬ ገንዘቡ የገንዘቡ ዝውውር ባህሪ የፈጠረው ነው። ምንም እንኳን ተፈላጊው ነገር በባንክ አካውንቱ ላይ ያለው የጥሬ ገንዘብ መጠን ይሁን እንጂ ይህን መጠን የሚወስነው ግን የገንዘቡ ዝውውር መጠንና ጊዜ ነው። ስለሆነም ሁለቱንም ማስተዳደር ይጠበቅብናል። ዋናው ቁም ነገሩ በባንክ አካውንት ላይ ያለው የጥሬ ገንዘብ መጠን በየወሩ ወይም በዓመት ውስጥ ድርጅቱ ከሚከፍላቸው ወይም ከሚያወጣቸው ልዩ ልዩ ወጪዎች በላይ መሆን ይኖርበታል።

ይህን በምሳሌ መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ አንድ ድርጅት የውሃ ታንከር አለው እንበል። በድርጅቱ ውስጥ ያሉት ሰራተኞችና ድርጅቱ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች (ለዕዳት፣ ለአትክልቶች፣ ለመጠጥና ሌሎችም) ከዚህ ታንከር ውሃ ይጠቀማሉ። ይሁን እንጅ የውሃ ታንከሩ የሚሞላው

ከቧንቧና ከዝናም ነው:: ወደ ታንከሩ የሚፈሰው የቧንቧም ሆነ የዝናም መጠን እስተማማኝና ቋሚ አይደለም:: በመሆኑም በአብዛኛው ጊዜ በውሃ ታንከሩ ውስጥ ያለው ተቀማጭ የውሃ መጠን ለፍጆታ የሚውለውን ተፈላጊ የውሃ መጠን በአንድ በኩል፣ ወደ ታንከሩ የሚገባን የውሃ መጠን በሌላ በኩል ታሳቢ በማድረግ ሚዛንን ሊጠብቅ ይገባል:: የውሃ ፍጆታው ብዙ ሆኖ ነገርግን ወደ ታንከሩ የሚገባው የውሃ መጠን እናሳ ከሆነ ድርጅቱ የውሃውን ፍጆታ ለመሸፈን የግድ ውሃን በአስቸኳይ ከሌላ ቦታ ሊያመጣ ይገባዋል (ከሱቅ በመግዛት፣ ወይም በጀሪካን ከሌላ በመግዛት፣ አለያም ከጐረቤት በመበደር):: ይህን ተምሳሌት ወደ አንድ የድርጅት የገንዘብ መጠንና ፍሰት ወስደን ስንመለከት ደግሞ የድርጅቱን ባንክ አካውንት እንደ ውሃው ታንከር ብንመስለው፤ ልዩ ልዩ የውሃ ፍጆታዎችን ደግሞ የድርጅቱ ልዩ ልዩ ወጪዎች እንደማለት ይሆናሉ:: ወደ ድርጅቱ ታንከር የሚገቡ የውሃ መጠኖችም ወደ ድርጅቱ የባንክ አካውንት የሚገቡ ልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች እንደማለት ናቸው:: በታንከሩ ውስጥ ያለው የውሃ መጠን ማለትም በድርጅቱ አካውንት ውስጥ ያለው የጥሬ ገንዘብ መጠን ሲሆን ይህም የድርጅቱን የገንዘብ ፍላጐት (ዲማንድ) እና የድርጅቱን የገቢ መጠን (ሰፕላይ) ከግምት ውስጥ ባስገባ መጠን ተመጣጣኝ ክምችት መኖር ይጠበቅበታል::

ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

ተገቢ የጥሬ ገንዘብ ቁጥጥር ያስፈልጋል:: በዚህ መሰል አስተዳደር ላይ ገንዘብ የት ቦታ ላይ ሊታሰር እንደቻለ ለማወቅና አስፈላጊውን ውሳኔ ለማድረግ ያግዛል:: በምን የተነሳ የገቢ ፍሰቱ መጠን ሊቀንስ እንደቻለ፤ በምንስ ሁኔታ የገንዘብ ፍሰቱ ፍጥነት ሊዘገይ እንደቻለ፤ የትና መቼስ ይህ ማነቆ እንደተፈጠረ በመገንዘብ እንዲሁም የትኛው

ወጪ እንደ ጨመረና አስቸኳይ የገንዘብ ክፍያ እንደተፈጠረ መረዳት ያስፈልጋል:: ይህም መሰል ችግር ሌላ አደጋ ከማስከተሉ በፊት ከወዲሁ ጉዳቱን ለመቀነስ ያግዛል::

በመሆኑም ገንዘብ በጥሩ ሁኔታ መሽከርከር መቻል ይኖርበታል:: በጣም ያነሰ የካሽ መጠን ወይም ማናቸውም ሰላማዊና ቀጣይነት ያለውን የገንዘብ ፍሰት የሚያሰናክል ነገር ችግር ፈጣሪ መሆኑ አይቀርም:: ያለበቂ የገንዘብ ዝውውር ለጊዜው ድርጅቱ አትራፊ ቢመስልም በሂደት ግን መውደቁ አይቀርም:: በተለይ ለአዳዲስና ትንንሽ ድርጅቶች ከቢዝነስ ስራ ውስጥ ለመውጣት ይህ ጉዳይ እንደ አቢይ ምክንያትነት ይቆጠራል::

በአንድ ድርጅት ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ የገንዘብ ፍሰት አይነቶች!!

የመጀመሪያው ነገር ድርጅቱ አካውንት ሲከፍት ባለቤቶቹ መነሻ ገንዘብ ወደ ድርጅቱ አካውንት ያስገባሉ:: ይህ እንግዲህ በኢንቬስትመንት መልክ ወደ ድርጅቱ አካውንት ገቢ የሆነ የገንዘብ ፍሰት ነው:: ወደፊት ደግሞ ድርጅቱ ቢዝነሱን ሲያስፋፉ እነዚሁ ባለቤቶች ተጨማሪ ገንዘብ ያስገባሉ:: ይህም ከኢንቬስትመንት የተገኘ ገቢ መሆኑ ነው:: ይህን መሰል የገንዘብ ገቢ በአካውንቲንግ ቋንቋ ‹‹ኢንቬስቲንግ›› በማለት እንጠራዋለን:: ይህም በኋላ ለባለቤቶቹ በትርፍ ክፍፍል ወቅት መልሶ ሊሰጥ ይችላል:: መስራቾች ከራሳቸው ውጭ ከባንክ ወይም ከነጋዴና ዘመድ የተገኙ ብድሮችን እንደ መነሻ ወይም በኋላ ለማስፋፊያ ሲበደሩና ገንዘቡም ወደ ድርጅቱ ባንክ አካውንት ገቢ ይደረጋል:: ይህ በብድር መልክ የገባ ገንዘብ መሆኑ ነው፤ በአካውንቲንግ ቋንቋ ፋይናንሲንግ ይባላል:: ለእነዚህም አበዳሪዎች በስምምነት መሰረት ተከፋይ ሲሆን

ከዚሁ የባንክ አካውንት ወጪ ይሆናል::

በመቀጠል ድርጅቱ ወደ ስራ ሲገባና በስራም ውስጥ ሲቀጥል በዱቤ መልክ ከአቅራቢዎች አስፈላጊ ጥሬ ዕቃና አገልግሎቶችን ሊገዛ ይችላል:: ይህ በአካውንቲንግ ቋንቋ የዱቤ ግዥ ወይም የክሬዲት ግዥ ይባላል:: ምናልባትም ግዥው ወደ ምርት የሚቀየሩ ጥሬ ዕቃዎችን ወይም ደግሞ ተመልሰው የሚሸጡ ያለቀላቸውን ምርቶች ከጅምላ አከፋፋይ መግዛትም ሊሆን ይችላል:: ከቢሮ ዕቃዎች መኪኖችንና ቢሮዎችን ወይም ህንፃዎችን ወይም መስሪያ ቦታዎችን ሊገዛም ይችላል:: ይህ ሁሉ የሚሆነው ታዲያ መጀመሪያ የድርጅቱ ባለቤቶች ሲጀምሩ በኢንቬስትመንት መልክ ካስቀመጡትና በብድር መልክ ከተገኘና በአካውንቱ ውስጥ ከተቀመጠው ገንዘብ ላይ ነው:: እንዲሁም ገንዘብ በደመወዝና በኮሚሽን መልክ ተከፋይ ሊደረግ ይችላል:: እንዲሁም በየጊዜው ወጪ የሚደረጉ የዕህፈት መሳሪያዎችም አሉ:: የቢሮ ኪራይን ጨምሮ:: ድርጅቱ አምርቶም ሆነ ከሌሎች አቅራቢዎች ያለቀላቸውን ምርቶች ገዝቶ ለደንበኞች ይሸጣል:: ሽያጩ የምርት ብቻ ሳይሆን የአገልግሎትም ሊሆን ይችላል:: ደንበኞች ምርቶችንም ሆነ አገልግሎቶችን ሲገዙ በዱቤ ወይም በቀጥታ ክፍያ ሊሆን ይችላል:: በዱቤ ከሆነ ሽያጩ የዱቤ ሽያጭ ተብሎ ይታወቃል:: በተባለው ጊዜ ውስጥ ሲከፍሉ ገንዘቡ ወደ ድርጅቱ የባንክ አካውንት ገቢ በመሆን የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ምጣኔ ከፍ ያደርገዋል:: አሁንም የገንዘብ ፍሰቱ ይቀጥላል:: በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ ገንዘብ ከድርጅቱ አካውንት ውጭ ተደርጉ የተገለፁ ልዩ ልዩ ግብሮች (ታክስ) ተከፋይ ይሆናሉ:: እንዲሁም በዱቤ መልክ የገዛናቸው ግዥዎች በስምምነቱ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ተከፋይ ይሆናሉ:: ቋሚ ንብረቶች የተገዙት በዱቤ ወይም በሊዝ መልክ ከሆነም አስፈላጊውን ክፍያና ወለድ ተከፋይ ይሆናል:: በሆነ ጊዜ ውስጥ ድርጅቱ ለባለቤቶቹ ዓመታዊ የትርፍ ክፍፍልን ሲያደርግ ገንዘቡ ከድርጅቱ ውጭ ይደረጋል:: እነዚህ ሁሉ እንግዲህ የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ክምችት መጠን የሚቀንሱ ናቸው::

በመሆኑም በድርጅቱ ባንክ አካውንት ውስጥ ለድርጅቱ ስራ ማስኬጃ ለምሳሌ ለጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ወቅታዊ ክፍያ ካልተከፈለ ድርጅቱ ዕለታዊ ስራውን ለማከናወን የሚቸገር ይሆናል:: በዚህ ወቅት የድርጅቱ ስራ እንዳይገታና ለችግር እንዳይጋለጥ ያልተጠበቀውን የገንዘብ ቀውስ ሊታደጉ የሚችሉ የአጭር ጊዜ የገንዘብ አቅርቦት ምንጮችን *(Short Term Financing)* ሊያፈላልጉ ይገባል::

13ቱ የካሽ ማኔጅመንት መፍትሔዎች!!

> ‹‹የተፈጠረው መጥፎ ስህተት ዋናው ጉዳይ ስይደለም፤ ስህተቱን ስመፍታት የምከርንበት ስዎንታዊው መንገድ ስንጂ››
>
> ዚግ ዚግላር

ድርጅቱን ወክለው የሚሠሩ የበላይና የበታች አመራሮች የሚወስኗቸው ውሳኔዎች የድርጅቱን የገንዘብ ዝውውር ደካማ ወይም ጠንካራ፣ ፈጣን ወይም ዘገምተኛ ፣ የተሳለጠ ወይም የተሰናከለ ሊያደርጉት ይችላሉ:: ይህ በመሆኑም የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ክምችት መጠን ድርጅቱ ከሚያስፈልገው ሥራ ማስኬጃ በላይ ተርፎ ለኢንቨስትመንት እንዲውል ወይም ለባለሃብቶች የትርፍ ክፍፍል ሊሆን በሚችል መልኩ ይበዛል:: ወይም ደግሞ የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ክምችት እጅግ ዝቅተኛ ወይም ባዶ በመሆኑ ለሥራ ማስኬጃ የሚሆን ገንዘብ እጦት ሊዳርግ፤ አንዳንዴ ደግሞ ድርጅቱ የመበደር አድሉም ባለማግኘቱ የመበደር ወሠኑ ላይ በመድረሱም ተጨማሪ ብድር ከባንክ ባለማግኘቱ ... ድርጅቱ ከሥራ ውጭም ሊሆን ይችላልና ነው:: እንደ ማጠቃለያ ድርጅቱ ከሥራ ውጭም ሊሆን ይችላልና ነው:: እንደ ማጠቃለያ ድርጅቱ ... ለመምራት [illegible] የድርጅታቸውን የጥሬ

Scanned with CamScanner

የሚከተሉትን መፍትሔዎች በሚገባ ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡

1. ሽያጭ ማሳጠር ግዥ ማራዝም:- ይህ በድርጅቱ ግዥና ለሻጩ በሚደረግ ቀጣይ ገንዘብ ክፍያ መካከል ያለ ጊዜ ሊያጥር ወይም ሊረዝም ይችላል፡፡ ይህ በአካውንቲንግ አጠራር ‹‹የግዥ ዑደት›› ወይም ‹‹ፐርቼዝ ሳይክል›› በመባል ይጠራል፡፡ ለአቅራቢ ትእዛዝ የመስጠት፣ ጥሬ እቃዎቹን መቀበል ቀጥሎም ክፍያ መፈፀም የግዥ ዑደት ነው፡፡ የሚከፈለው ገንዘብ ከየት ይመጣል? የሚለውን ስንመለከት ደግሞ ምርት ይመረታል፣ ለደንበኞች ይሸጣል፡፡ ከዚያም ደንበኞች በገዙት (በተረከቡት) መሠረት ክፍያ ይፈፅማሉ፡፡ ይህ መሠሉ በግዥና በቀጣይ የመክፈያ ጊዜ መሃከል ያለ ዑደት ‹‹የሽያጭ ዑደት›› ወይም ‹‹ሴሊንግ ሳይክል›› በመባል ይጠራል፡፡ በሽያጭ ዑደት ውስጥ ያለው ጊዜ ማለት ገንዘቡ ከገዥዎች ተሰብስቦ ወደ ባንክ አካውንት እስኪገባ ድረስ እንደ የድርጅቱ ዓይነት አጭር ወይም ረዥም ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ድርጅቱ ካፊቴሪያ ከሆነ ወዲያው ተሽጦ ወዲያው ነው ደንበኞች ገንዘብ የሚከፍሉት፡፡ በመሆኑም እንደ ድርጅቱ አይነት ወደ ድርጅቱ አካውንት ገንዘብ የሚገባበት የሽያጭ ገቢና ከድርጅቱ ገንዘብ በሚወጣበት የግዥ ወጪ መካከል ያለው ልዩነት አጭር ወይም ረዥም ሊሆን ይችላል፡፡ ልዩነቱ ረዥም በሆነ ቁጥር ድርጅቱ ለጥሬ ገንዘብ እጥረት ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ያልተሰበሰቡ ገንዘቦች ተከፋይ እስኪሆኑ ጊዜ ስለሚወስዱ በግዥ ዑደትና በሽያጭ ዑደት መካከል ያለው የጊዜ ልዩነት አጭር በሆነ ቁጥር የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ክምችት ይጨምራል፡፡ ከደንበኞች ገንዘቦች ቶሎ ቶሎ ስለሚከፈሉ፡፡

2. የወደፊቱን ማቀድ:- ይህ የመጀሪያው ነገር ነው፡፡ መጨረሻን አውቆ መጀመር ብልህነት ነውና፡፡ ድርጅቱ የመጭው በጀት ዓመት ገቢዎቹንና ወጭዎቹን በውል ከመረዳት ሊጀምር ይገባል፡፡ ይህ መሰሉ የቀጣይ ዓመቱን ገቢ ፈጣሪ የሆኑት የቢዝነሱ ምርቶችና አገልግሎቶች

ሊደርስ እንደሚችል ከባለፈው ዓመት አፈፃፀምና ሽያጫቸው ምን ያህል ሊደርስ እንደሚችል ከባለፈው ዓመት አፈፃፀምና ከገበያው መረጃ በመንተራስ ለመተንበይ መሞከር ይኖርበታል፡ እንዲሁም ይህን የተተነበየ ሽያጭ ለማስመዝገብ ልዩ ልዩ ታሳቢ ወጭዎች ምን እንደሚመስሉ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ ምን ያህል የጥሬ ዕቃ ወይም የምርት ግዥዎችን ከአገር ውስጥ ወይም ከውጭ ሊገዛ እንደሚገባም እንዲሁ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ ምን አይነት ተጨማሪ መሳሪያዎች፣ መኪናዎች፣ ማሽነሪዎች መግዛት እንዳለባቸውም እንዲሁ፡፡

የቀጣዩን ዓመት ወይም ደግሞ የቀሩትን የበጀት ዓመት ወራት ገቢዎችና ወጭዎች እንዲሁም የካፒታል እቃዎች ወጭዎች ከተረዱ በኋላ የድርጅቱን የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ የየወሩን ሪፖርት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ የየወሩን የሃብትና ዕዳ ሚዛን መግለጫ ሪፖርትም ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህ የተተነበዩ ሪፖርቶች በመነሳት የድርጅቱን ወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ መግለጫ ሪፖርት ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ በዚህ ሪፖርት መሰረት የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ምጣኔ በቂ ክምችት ወይም ጉድለት የሚያሳይ ስለመሆኑ ለመረዳት ይረዳዋል፡፡ በገንዘብ ነክ የትንበያ ስልቶች(ፋይናንሻል ፎርካስቲንግ) ዙሪያ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ በሌላ ክፍል በሚገባ የተዳሰሰ በመሆኑ እንባበው ይጠቀሙበት፡፡

3. ጥሬ ገንዘቡ በቂ መሆኑን ማረጋገጥ:- ከላይ በተሰራው የወርሃዊ የጥሬ ገንዘብ መግለጫ *(Monthly Cash Flow)* መሰረት ጉድለት የሚያሳይ ከሆነ ድርጅቱ ይህን ያህል መጠን ያለው ገንዘብ ከሌላ ቦታ ማግኘት ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ከድርጅቱ የሃብትና ዕዳ ሪፖርት *(Balance Sheet)* በመነሳት የድርጅቱን የተጣራ የስራ ማስኬጃ ካፒታል ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ይችላል፡፡ ይህ የተጣራ የስራ ካፒታል የድርጅቱን የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳዎች ከድርጅቱ ማስኬጃ ካፒታል

Scanned with CamScanner

የአጭር ጊዜ ተከፋይ ሃብቶች በመቀነስ የሚገኝ ሲሆን ውጤቱ ኔጌቲቭ ከሆነ ያን ያህል መጠን ያለው የስራ ማስኬጃ ጉድለት እንደሚገጥመው መረዳት ይጠበቅበታል:: እንዲሁም ከዚህ ጋር በተመሳሳይ ከተተነበየው የሃብትና ዕዳ ሚዛን ሪፖርት በመነሳት የድርጅቱን የስራ ማስኬጃ መጠን ጠቋሚ መለኪያዎችን በመጠቀም ማስላት ያስፈልጋል:: እነዚህም በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የተገለፁ ‹‹የኢንቬንተሪ ቀናት››፣ ‹‹የተሰብሳቢዎች ቀናት››፣ ‹‹የተከፋዮች ቀናት›› ፣ የሊኩይዲቲ ሬሽዮና የኩዊክ ሬሽዮና ካሽ ሬሽዮ ናቸው:: እነዚህ መፈተሻዎች የሚጠቅሙት ከተተነበየው የድርጅቱ የሒሳብ መግለጫ አንፃር የድርጅቱ የስራ ማስኬጃ ካፒታል በምን ደረጃ ላይ እንዳለ፣ በቂ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ትርፍ ጥሬ ገንዘብ ማለትም ‹‹*Excess cash*›› እንዳለው፣ ወይም ደግሞ ጉድለት እንደሚያሳይና ይህ ጉድለት ከወዲሁ ማስተካከያ ስልት ካልተፈለገለት የድርጅቱ ስራ በቀጣይ የሚስተጓጎል መሆኑን የሚጠቁሙን ናቸው::

4. የጥሬ ገንዘብ ጉድለትን የሚሞሉ አማራጮችን መፈለግ:- ከድርጅቱ የተተነበየ የጥሬ ገንዘብ መግለጫ ሪፖርትም ላይ ሆነ የተለያዩ የስራ ማስኬጃ ካፒታልን ጤናማነት ከሚጠቁሙ መለኪያዎች የተመለከትነው ውጤት የካፒታል ጉድለት የሚያሳይ ከሆነ ከወዲሁ የገንዘብ ማግኛ አማራጮችን ማፈላለግ ይኖርብናል:: ‹‹ማቺንግ ፕሪንሲፕል›› በሚለው የአካውንቲንግ ህግ መሰረት ለረዥም ጊዜ የካፒታል ጉድለቶች የረዥም ጊዜ የካፒታል ምንጮችን ማፈላለግ ሲኖርብን፣ ለአጭር ጊዜ የካፒታል ጉድለቶች ደግሞ ለአጭር ጊዜ ቆይታ የሚሰጡ የገንዘብ ምንጮችን ነው ልናፈላልግ የሚገባው:: ለምሳሌ ጉድለቱ በታየበት ጊዜ ውስጥ የመሳሪያ ግዥ የምናደርግ ከሆነ የረዥም ጊዜ የፋይናንስ አማራጮችን መፈለግ ያለብን ሲሆን ይሁን እንጂ የአጭር ጊዜ የስራ ማስኬጃ ካፒታልን ለመሙላት የሚያስችሉ የአጭር ጊዜ የፋይናንስ አማራጮችን መጠቀም እንችላለን:: ሁሉቱም

ዓይነት የፋይናንስ ምንጮች (በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ተዳሰዋል)

5. ወጪንና ብክነትን ማፅዳት:- የስራ ማስኬጃ ካፒታልን በሚገባ ለማስተዳደር ትልቁ ጉዳይ ያለው ስራዎችን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ እንዴት እናከናውናቸው የሚል መሆን አለበት:: ከገንዘብ ውጭ ስራዎች እንዴት መሰራት እንዳለባቸው ወትሮ ከምንከተላቸው የወጪ አጠቃቀሞች በመውጣት ፈጠራዎችን በማከል በውስን ሃብትና በጀት ከፍተኛ መጠን ያለውን ስራ መስራት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡ ፡ ይህን ለማድረግ በቅድሚያ የድርጅቱን ልዩ ልዩ የወጪ አይነቶች በምድብ በምድብ መዘርዘር ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ከእነዚህ ወጪዎች ውስጥ ከአንዳንዶቹ ላይ ከወትሮ ወጪአቸው 15% ከሌሎቹ ላይ 10% እንዲሁም ከጥቂቶች ላይ 5% ወጪ ልንቀንስ እንችላለን:: ይህንንም ስናደርግ የስራው ጥራት ሳይጓደል ስራው እንዴት መስራት እንደሚቻል ማጤን ያስፈልጋል:: ይህ የጥሬ ገንዘብ ክምችቱን የሚያስጠብቅልን መላ ነው:: ባንክ ሄዶ ‹‹ብድር ስጡን›› ከማለት! ከአቅራቢዎች ጋር ‹‹ዱቤ ስጡን›› ከማለትና ‹‹ዕዳዎቻችንን አራዝሙልን›› ከማለታችን በፊት፣ እንዲሁም ድርጅታዊ ስራውም ከመስተጓጎሉ በፊት የራስን ሃብት አሟጦ የመጠቀምና ያለውን ገንዘብ አብቃቅቶ ስራ ላይ የማዋል ባህል ሊኖረን ይገባል::

6. አስተማማኝ የጥሬ ገንዘብ ክምችት የሚያመጡ ኢንቨስትመንቶችን ቀድሞውኑ መለየት:- እንደሚታወቀው አንድ ድርጅት የጥሬ ገንዘቡ ከፍ ወይም ዝቅ እንዲል የሚያደርገው ጉዳይ ቢኖር መጀመሪያውኑ የገባበት የንግድ ዘርፍ አይነት ነው:: የቢዝነሱ አይነት ከፍ ያለ ትርፍን የሚያመጣ በሆነ ቁጥር የድርጅቱ ካሽ ፍሰሙ መጠን ከፍ የማለት ዕድሉ የላቀ ነው:: እንዲሁም የቢዝነሱ አይነት በባህሪው ዝቅተኛ ትርፋማነት ያለበት ንግድ ዘርፍ በሆነ ቁጥር በመሆኑም ቀድሞውኑ የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ መጠንም ዝቅ ይላል::

Scanned with CamScanner

ወደ ቢዝነስ ከመግባታችን በፊት ይህን ማሰብ የሚገባን ሲሆን እንዲሁም ወደ ቢዝነሱ ከገባን በኋላ ደግሞ በቀጣይ በቢዝነሱ ውስጥ የምናደርጋቸው የኢንቬስትመንት መረጣዎችና ውሳኔዎች ለድርጅቱ አስተማማኝና የላቀ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ስለማምጣታቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል። አዳዲስ ምርቶችን ከማበልፀጋችን በፊት፤ አዳዲስ ማስፋፊያዎችንና ቅርንጫፎችን ከማድረጋችን በፊት ፕሮጀክቶች መመዘን ያለባቸው በሚያመጡት የጥሬ ገንዘብ መጠንና ፍጥነት ላይ ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ በኢንቬስትመንት አወሳሰን ዙሪያ ላይ የሚያተኩረውን የመፅሀፉን ክፍል ያንብቡ። ይህን በሚገባ ማጤን ያስፈልጋልና።

7. ፈጣን የሽያጭ ገቢ አሰባሰብ:- ወደ ሽያጭ ክፍሉ ስንሄድ ደግሞ ከሽያጭ የሚገኙ ተከፋይ ገንዘቦች *(Account Receivables)* በበዙ ቁጥር የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ክምችት ይበዛ ዘንድ ደንበኞች የሚከፍሉበትን ጊዜ ማሳጠር ገንዘብ ወደ ድርጅቱ አካውንት የሚያደርገውን የአገባብ ጊዜ ያፈጥነዋል። ለአቅራቢዎች የምንከፍለውንም የጊዜ ርዝማኔ ያቀላጥፈዋል። ከፍተኛ ሽያጭን ፣ በትጋት ላይ የተመሠረተ የገቢ አሰባሰብን ወይም ፈጣን የሽያጭ ገቢ አሰባሰብን መተግበሩ የዚህ ክፍል ኃላፊዎች ሥራ መሆን ይኖርበታል እንደማለት ነው።

8. የምርቶችንና አገልግሎቶችን ትርፋማነት መከታተል:- አንድ ድርጅት ከአንድ በላይ ገቢ የሚያመጡ ምርቶችና አገልግሎቶች ሊኖሩት ይችላሉ። አንዳንድ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች አትራፊነታቸው እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም ይዘናቸው እንቀጥላለን። አንዳንዶቹ ደግሞ ድርጅቱ ከሚያወጣባቸው ወጪ አንፃር የሚያስገኙት የሽያጭ ገቢ ከፍ ያለና አስተማማኝ አይነት ነው። ይሁን እንጂ የምርትና አገልግሎት ትርፋማነትንካላሰላንና ካልተከታተልን አንዳንድ ምርቶች ጥሬ ገንዘብ ጨራሽ ተምች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ አይነቶቹን ተምች ምርቶች ቀድሞ በመረዳት ወይ. ወይ.ተሻለ ትርፋማነት መቀየር

አለበለዚያም ከገበያ ማስወጣት ነው የሚሻለው።

9. ያልተመረቱ ወይም ያልተሸጡ የምርት ክምችቶች ጉዳይ:- በግዥም ሆነ በምርት ክፍል እንዲሁም በሽያጭ ዲፓርትመንት ውስጥ ተዘውትሮ የሚታይ ችግር ደግሞ ያልተመረቱ የጥሬ ዕቃ ክምችቶች ወይም ደግሞ ያልተሸጡ ያለቀላቸው ክምችቶች ጉዳይ ነው። ይህ ‹‹ኢንቨንተሪ›› ወይም ‹‹ስቶክ›› በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሲሆን ግዥ ዲፓርትመንት ምናልባት ወደፊት አሁን እየተሸጠ ባለበት ዋጋ ላላገኘው እችላለሁ ወይም ጥሬ እቃው በቀጣይ ሊጠፋ ይችላል፤ ወይም ደግሞ ምርት ክፍሉ ሊያጥረው ይችላል፤ ወይም አሁን ያለው ገበያ ጥሩ ስለሆነ በዛ ተደርጎ ቢገዛ ያዋጣል፤ ወይም በብዛት መግዛትና ማምረት ዋጋ የሚያስቀንስ በመሆኑ ጥሬ ዕቃ ግዥ ማብዛት፤ በብዛት ማምረት ወይም ያለቀላቸው ምርቶችን በብዛት መግዛት ወጭ ይቀንሳል በሚሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ። እንዲሁም ምርት ክፍሉም ተመሳሳይ አመለካከትን በመያዝ *(Just in case)* ገበያ ላይ ሊፈለግ ይችላል በሚል ቀና አስተሳሰብ በብዛት ሊያመርት ይችላል። የገበያ ልማት ዲፓርትመንቱም ገበያው በብዛት ሊኖር ይችላል በሚል ሠበብ ምርት ክፍሉን በብዛት እንዲያመርት ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል። ይሁን እንጂ መሬት ላይ ያለው እውነት ግን ከዚህ የተቃረነ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ይሆንና ብዙ የጥሬ እቃ ወይም ያለቀላቸው ምርቶች ክምችት ይፈጠራል። ይህ መሠሉ ክምችትም ብዙ ገንዘብ ይዞ ይቀመጣል። በድርጅቱ የባንክ አካውንት የጥሬ ገንዘብ ክምችት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖን የሚያሳድር በመሆኑ የእነዚህ ሶስት ዲፓርትመንቶች አመራሮች ውሳኔያቸው እርስ በእርስ ተናባቢና ከስሜት የፀዳ ሊሆን ይገባል። በዚህ ደራሲ የፋይናንሻል ፖሊሲ መፅሐፍ ውስጥም በዚህ መሠሉ የኢንቨንተሪ አስተዳደር ስርዓት የቀረበ በመሆኑም የድርጅቱ መመሪያ ማድረግ በጣም ይበረታታል።

Scanned with CamScanner

10. አቅራቢዎችን በተመለከተ፡- አንድ ድርጅት አምራች ከሆነ ጥሬ እቃዎችን ከአቅራቢዎች ይገዛል፣ በችርቻሮ (መርችንዳይዝ) ቢዝነስ የተሠማራ ከሆነ ደግሞ ያለቀላቸውን ምርቶች ከአምራቾች ይረከባል። እነዚህ ምርቶች(ሸቀጦች) ወይም ደግሞ ካፒታል እቃዎች (ለምሳሌ መኪኖች) ከውጭ ወይም ከአገር ውስጥ ተረክቦ የሚሸጥ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም በድርጅቱ የማይሠሩና በሌላ ድርጅት ወኪልነት አውትሶርስ ተደርገው የሚሠሩ ስራዎች ይኖሩታል፡፡፡ በመሆኑም ጊዜያዊ የጥሬ ገንዘብ እጥረትን ለመፍታት በቅድሚያ በጥሩ ዋጋ ተደራድሮ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን መግዛት የመጀመሪያው ህግ ነው። በዚህ ረገድ ግዥ ክፍሉ የተመጠነ መጠን ያለውን ጥሬ እቃ ወይም ምርት መግዛትና ሲገዛም በጥሩ ቅናሽ ዋጋ ተደራድሮ መግዛት የተከፋይ ገንዘቡን መጠን ይቀንሰዋል። ይህንንም በጨረታ መልክ ሲገዛ ይችላል፣ ወይም በጥሩ ድርድር ከነባር ደንበኛ ሲገዛ ይችላል።

ሌላው ሊደረግ የሚችለው ደግሞ ከአቅራቢው ጋር በመደራደር ሙሉውን ወይም ከፊሉን ክፍያ ረዘም ባለ ጊዜ ውስጥ ለመክፈል በሚል ተደራድሮ ሲገዛ ይችላል። ይህም ጊዜያዊ እፎይታን ይፈጥርለታል። ለዚህ መሠሉ የዱቤ ግዥ ደግሞ ከአሁን ቀደም የሚኖረው ጥሩ የደንበኝነት ግንኙነት ትልቅ ሚናን ይጫወታል። በተለይ ደግሞ የገንዘብ አቅማቸው ጥሩ የሆኑ አቅራቢዎችን መምረጡ ለዚህ መሠል የዱቤ ግዥ እድልን ይሰጣል። ይሁን እንጂ የገንዘብ አቅማቸው ደከም ያሉና ከገዥው ያልተሻሉ ከሆኑ ግን የአከፋፈል የጊዜ እፎይታን ላይሰጡ ይችላሉ። በመሆኑም አቅራቢዎችን ከገንዘብ አቅጣጫዎች አንፃር መምረጥ የሚጠቅመው ለዚህ ለዚህ አጋጣሚ ነው።

ከአቅርቦት ግዥ ጋር በተያያዘ በአገር ደረጃ የአገር ውስጥ አምራቾች በዶላር እጥረት የተነሳ ከውጭ የሚያስገቧቸውን ጥሬ እቃዎች መግዛት ስላልቻሉ ብሔራዊ ባንክ የአቅራቢዎች ብድር አገልግሎትን እንዲጠቀሙ

ማመቻቸቱ ይታወቃል። ይህ ‹‹ሰፕላየርስ ክሬዲት ፋሲሊቲ›› በመባል የሚጠራ የግዥ ስልት የሚያተኩረው በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በ2010 ዓ.ም ዋስትና በውጭ አገር ያሉ አቅራቢዎች ለአገር ውስጥ አምራቾች ከ6 ወር እስከ አንድ አመት ባሉ ጊዜያት ውስጥ ሊከፈላቸው በሚችል ድርድር የዱቤ ግዥን እንዲያቀርቡ የሚያደርግ ነው። ይህ መሠሉ የአገዛዝ ምቹነት አገሪቱ በተፈጠረባት የውጭ ምንዛሬ ካሽ ፍሰው እጥረት የመጣ መፍትሔ ነው። ከአገር ውስጥ ጥሬ እቃዎችንም ሆነ ያለቀላቸውን ሸቀጦች የሚገዙ አምራቾችና ቸርቻሪዎችም ይህን መሠል መንገድ በመጠቀም ከአቅራቢዎቻቸው ጋር የክሬዲት ግዥን በመስማማት እቃዎቹን ለመግዛት ሲያዙ ወይም ሲረከቡ ወዲያውኑ ከመክፈል የተወሰኑ ሳምንታትን ወይም ወራትን እፎይታን ያገኙ ዘንድ ሊዋዋሉ ይችላሉ።

ይህም ሆኖ ደግሞ በተባለው ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ለመክፈል የሚያስቸግርበት አጋጣሚ ይፈጠራል። በመሆኑም የደንበኝነት ትስስሩን ላለማበላሸት ከመክፈያ ጊዜው ቀደም ብሎ ያለውን ሁኔታ በማስረዳት የጊዜ ማራዘሚያን ማስፈቀድ ይቻላል። ይሁን እንጂ ከዚህ መሠል የክፍያ ቀጠሮ ውጭ ግን በቀጣይ ማራዘሙ ከአቅራቢዎች ጋር ያለውን መተማመን የሚያጠፋ በመሆኑ በቀጣይ ተመሳሳይ የዱቤ ግዥ እድልን ለማግኘት የሚያዳግት በመሆኑ ታማኝ ከፋይነትን ተግባራዊ በማድረግ ታማኝ የዱቤ ደንበኝነትን ማሳደግ ያስፈልጋል፣ «*Credit worthiness*»።

የግዥ ክፍሉ የሚያደርገው አግባብ የድርጅቱን የገንዘብ አቅም ችግር ውስጥ የማይከት እንደውም የድርጅቱን የገንዘብ አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ሊሆን ይገባል። በዚህ መሠረትም የአንድ ድርጅት የግዥ ሂደት ምን መምሰል እንደሚገባው በዚህ ደራሲ የተዘጋጀውና የገንዘብ ህጎች የተሰኘውን የ‹‹ፋይናንሻል ፖሊሲ›› መፅሐፍ ውስጥ የተቀረፀውን የግዥ ስርአት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም

Scanned with CamScanner

የግዥ ክፍሉ የሚያደርገው አከፋፈል ከሽያጭ ክፍሉ የገንዘብ አገባብ አንፃር የተሳሰጠ መሆን ይኖርበታል። በተቻለ መጠን የመክፈያ ጊዜውን አቅራቢውን በማያስቀይም መልኩ በተራዘመ መጠን ማድረግ የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ መጠን ያሳድገዋል።

11.ከበቂ በላይ ለተከማቹ ጥሬ ገንዘቦች መላ ማበጀት፡ - ከላይ ከሰራነውና ከስራ ማስኬጃ ትንበያው እንደተረዳነው ለድርጅቱ ከሚያስፈልገው ዓመታዊ በጀት መጠን በላይ ትርፍ ጥሬ ገንዘብ ከታየ ይህን ጥሬ ገንዘብ ምን ማድረግ እንደሚገባ ከወዲሁ ማቀድ ያስፈልጋል። ከድርጅቱ የአንድ ዓመት የስራ ማስኬጃ ካፒታል በላይ የጥሬ ገንዘብ መኖር በትርፍ ክምችትነት የሚመዘገብ ሲሆን ይህንን ትርፍ ክምችት ይዞ ማቆየትም የራሱ ጉዳት ያለው በመሆኑ የተለያዩ አማራጭ ጉዳዮችን ለማድረግ ማቀድ ያስፈልጋል። ተጨማሪ ኢንቬስትመንት ማድረግ፣ ለባለቤቶች ከወትሮው ጠቀም ያለ የትርፍ ክፍፍልን ማድረግ፣ የብድርና የዱቤ እዳዎችን ከፍሎ መዝጋት፣ ከድርጅቱ ባለቤቶች በጥሩ ዋጋ የባለቤት ድርሻቸውን መልሶ መግዛትና የመሳሰሉትን መወሰን ያስፈልጋል።

12. በየጊዜው መሻሻል፡- ከተራ ቁጥር 1-7 ያሉትን የስራ ማስኬጃና የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መርሆዎችን በየጊዜው በማድረግ ስህተቶችንና ደካማ ጐኖችን እየለዩ የማረም፤ ጠንካራ ጐኖችን ደግሞ የበለጠ እያሻሻሉ ማጐልበት የሚያስፈልግ ሲሆን በጊዜ ሂደት ውስጥ ምርጥ ወደሚባል የስራ ማስኬጃ ካፒታል አስተዳደርና የኢንቬስትመንት አወሳሰን ጥበባችን ባህላችን በእጅጉ እየዳበረ ይሄዳል።

13. የፋይናንስ ስርአት መዘርጋት፡- የመጀመሪያው ጉዳይ አንድ ድርጅት ‹‹የገንዘብ ህግ›› በሚለው የዚህ መፅሐፍ ደራሲ ውስጥ በተገለፀው መንገድ የድርጅቱን የፋይናንስ ስርአት መዘርጋትና በዚህ የፋይናንስ መተዳደሪያ ፖሊሲ መሠረትም አሠራሩን ተግባራዊ

ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ የድርጅቱን የገንዘብ ዝውውር የሚመሩ የፋይናንስ ዲፓርትመንት አመራሮች ከአቅርቦትና ግዥ አንፃር ወጪ ቆጣቢን ፣ ጥራት ያላቸውና ብዙ ክምችት የማይፈጥሩ ጥሬ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በትክክል ለመግዛት የግዥ ስርአትን ተግባራዊ ማድረግ፣ የምርት ክፍል ዲፓርትመንት ገበያ ሊኖራቸው በሚችልና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ነገርግን ከሚገባው በላይ ክምችት የማይፈጥር አመራረትን ይከተሉ ዘንድ መተዳደሪያ ፖሊሲ መሠረትም ያስፈልጋል።

Scanned with CamScanner

በአጣብቂኝ ችግር ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ምንጮች!

‹‹ጥያቄው መሆን ያለበት ‹‹ማን ወደፊት እንድገዛ እድል ይሰጠኛል?›› ሳይሆን ‹‹ማን ወደፊት ከመግዛ ያቆመኛል?›› የሚለው ነው!›› አያን ራንድ

በሥራ ማስኬጃ አስተዳደር ሂደት ውስጥ ለማየት እንደሞከርነው የአንድ ድርጅት የጥሬ ገንዘብ ፍሰት በተለያዩ ምክንያቶች የሚያጥር በመሆኑ ይህን ክፍተት ወይም የገንዘብ ጉድለት ቶሎ በመሙላት ሥራውን ጤናማ ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው። ምንም እንኳን የሚከፈሉ እዳዎችን እንዲሁም ተሰብሳቢ የሽያጭ ገቢዎችን ማስተዳደርና ለማስተዳደርም ጥብቅ መመሪያ ቢያስፈልግም ይህም ሆኖ የድርጅቱን አሠራር ፈተና ውስጥ የሚከት ጊዜያዊ የገንዘብ እጥረት ሊገጥመው ይችላል።

Scanned with CamScanner

ድንገተኛ አጋጣሚዎች በተለያዩ ሠዎች ላይ እንደሚከሰቱ ሁሉ ድርጅትም ድንገተኛ አደጋ ሊደርስበት ይችላል፡፡ እነዚህ ድንገተኛ አደጋዎች በተለይም ባልተጠበቀ ሁኔታ በአንድ ድርጅት ላይ የሚፈጥር የገንዘብ እጥረት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን መሠል ያልተጠበቀ የገንዘብ እጥረት አደጋ የፋይናንስ ባለሙያዎች ‹‹ኔጌቲቭ ካሽ ፍሎው ሾክ›› በማለት ይጠሩታል፡፡ ‹‹ሾክ›› ማለት በድንገት ህሊናን መሳት ነው፤ በደም እጥረት የተነሳ ድንገተኛ ኮማ ሊያጋጥመው ይችላል፤ ስለዚህ አስቸኳይ እገዛ ያስፈልገዋል ማለት ነው፡፡ ድርጅቱም አስቸኳይ የገንዘብ ልገሳ ያስፈልገዋል ማለት ነው፡፡ ይህ መሠል ችግር ለምሳሌ ባልተጠበቀ ሁኔታ የድርጅቱ የማምረቻ ማሽን ቢሰበርና ድርጅቱም ይህንን ማሽን ለመጠገን የሚያስችል በቂ ጥሬ ገንዘብ ከሌለው ለእቃው የሚያወጣው ወጭ *(Capital Expenditure)* ድርጅቱ ካለው ጥሬ ገንዘብ ጋር ቢደመር የጥሬ ገንዘብ ሚዛኑ ኔጌቲቭ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በባንክ ያለው ጥሬ ገንዘብ 500 ሺህ ብር ቢሆንና የሚያስፈልገው ወጭ ደግሞ አንድ ሚሊዮን ብር ቢሆን የ500 ሺህ ብር የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ይጠብቀዋል፡፡ ይህ ማሽን ቶሎ ታድሶ ወደ ሥራ ካልገባ ደግሞ ሥራው ቀጥ አለ ማለት ነው፡፡ ለዚያም ነው ‹‹ሾክ›› ውስጥ ገባ የምንለው፡፡ ማሽኑ ከታደሰ ግን ድርጅቱ ወደሥራ ስለሚመለስ የገንዘብ ጤናማነቱ በፍጥነት ይስተካከላል፡፡ ድንገተኛው ክስተት ግን ድንገተኛ የገንዘብ እገዛን ይጠይቃል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አንድ ድርጅት አማላይ የገበያ ትእዛዝ ይቀርብለታል፤ ወይም ደግሞ የኮንስትራክሽን ኩባንያ ከሆነ አዲስ ጨረታ ያሸንፋል፡፡ ይሁን እንጂ ሥራውን በትክክለኛ ጥራትና በተባለው ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ተጨማሪ የሠው ሃይልና ማሽነሪዎች ያስፈልጉታል፡፡ ይህን ድንገተኛ የገበያ አጋጣሚ ለመጠቀም የሚያስችል ተጨማሪ ጥሬ ገንዘብ ቢጠይቀውም ድርጅቱ በባንክ ውስጥ ያለው የጥሬ ገንዘብ መጠን

አይደለም፡፡ ይህ ድርጅት የገጠመው የጥሬ ገንዘብ ግን ለዚህ የሚበቃ ችግር ቢፈታ በቀጣይ የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ክምችት የሚያንበሸብሽ ያልታሰበ የገበያ አጋጣሚ በመሆኑ የፋይናንስ ባለሙያዎች ክስተቱን ‹‹ፖዘቲቭ ካሽ ፍሎው ሾክ›› ይሉታል፡፡ እንግዲህ የመጀመሪያው የማሽን ስብራት የድርጅቱን ካሽ የሚቀንስ የወጪ አጋጣሚ ሲሆን ሁለተኛው ይህ አጋጣሚው ደግሞ የድርጅቱን ካሽ የሚያሳድግ የገቢ አጋጣሚ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ድንገተኛ የገንዘብ ልገሳ ያስፈልገዋል፡፡

በእርግጥ ድርጅቶች ከድንገተኛ አጋጣሚዎች ውጭ እያሰለሱ የሚከሰቱ የጥሬ ገንዘብ እጥረት ክስተቶችም ያጋጥሟቸዋል፡፡ ይህ የሚሆነው በተለይ አንዳንድ ድርጅቶች የሽያጭ ገቢያቸው ከወር ወደ ወር ቋሚ ባልሆኑባቸው ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ድርጅቶች በየወሩ ቋሚ ወጪዎች ይኖሩባቸዋል፡፡ ሆቴሎች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው፡፡ በሆቴል ዘርፍ ውስጥ የሞቀ የገበያ ወቅት የሚባልና ቱሪስቶች የሚበዙባቸው ወቅቶች ለምሳሌ ኮንፈረንሶች (ለምሳሌ የአፍሪካ ህብረት አመታዊ ስብሰባዎች) ሲኖሩ ፤ አንዳንድ ወቅቶች ላይ ደግሞ ጭር የሚልባቸው አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በሞቀ ገበያ ወቅት ድርጅቶች ከፍተኛ ጥሬ ገንዘብ ሲኖራቸው በቀዝቃዛ የገበያ ወቅቶች ደግሞ ዝቅተኛ ጥሬ ገንዘብ ይኖራቸዋል፡፡ ምንም እንኳን ከፍተኛ ጥሬ ገንዘብ የመጣባቸው ወቅቶች ላይ ያለውን ገንዘብ ዝቅተኛ ገበያ ባለበት አጋጣሚ የሚጠቀሙበት ቢሆንም ጊዜዎቹ ግን ሊለያዩ ስለሚችሉ፤ የሆኑ ሳምንታት ወይም ወራት ላይ ያልተጠበቀ የጥሬ ገንዘብ እጥረቶች ይፈጠሩባቸዋል፤ ይህ መሠሉ የጥሬ ገንዘብ ድርቅ አፈጣጠር ‹‹ሲዝናል›› (ወቅት እየጠበቀ የሚከሠት) በመባል ይጠራል፡፡ ዞሮ ዞሮ ይህም ሲፈጠር የገንዘብ ልገሳ (ድጎማ) የሚጠይቅ አጋጣሚ ነው፡፡

እንዲህ መሠል የጥሬ ገንዘብ እጥረቶችን ለመፍታትና ሥራውን ጤናማ በሆነ መንገድ ለማስኬድ፤ የሚገኙ የቅናሽ ግዥ እድሎችን

Scanned with CamScanner

ወይም ድንገተኛ የገበያ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም፤ እንዲሁም ድንገተኛ ገንዘብ የሚፈልጉ ወጭዎችን ለመፍታት ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

በአጠቃላይ የሥራ ማስኬጃ ካፒታልን በትክክል ለማስተዳደር ጥሬ ገንዘብን በትክክል ማስተዳደር የሚያስፈልግ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል። የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ በትክክል ለማስተዳደር ደግሞ ድርጅቱ ወደፊት ወይም በአንድ አመት የሥራ ዘመን ውስጥ ምን ያህል ገንዘብ ሊያስፈልገው እንደሚችል ከመተንበይ መጀመር የግድ ይሆናል። ይህ ‹‹ካሽ በጀት›› በመባል የሚጠራ ሲሆን አንድ ድርጅት በየወሩ ወይም በየሩብ አመቱ ምን ያህል የገንዘብ ገቢዎችና ወጭዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ የአንድ አመት ትንበያ ማድረግ ይኖርበታል። ማለትም ዛሬ ላይ ሆኖ የወደፊቱን ወርሃዊ ወይም በየሶስት ወሩ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪ መጠን ማስላትና በቁጥር ማስቀመጥ ይኖርበታል።

ይህን ከመስራት አንፃር አንድ ነገር ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህም ምንድነው አንድ በዚህ ወር የተሸጠ ሽያጭ ሙሉ በሙሉ በዚህ ወር ላይሰበሰብ ይችላል፤ ወይም ባቀድነው ሩብ አመት ውስጥ ይሰበሰባል ያልነው የሽያጭ ገቢ 100% ላይሰበሰብ ይችላል። ስለሆነም ከባለፈው አመት ልምድ በመነሳት ተሰብሳቢ ገቢዎች ምን ያህል ሊሆኑ እንደሚችሉ ማወቅ ያስፈልጋል። ባለፈው ወር 75 በመቶ ሽያጭ የተሰበሰበ ከሆነ 25 በመቶ ቀሪው ሽያጭ በዚህ ወር ሊሰበሰብ ይችላል፤ በዚህ ወር ደግሞ የራሱ 75 በመቶ ተሰብሳቢ ገቢ ይኖራል። የወሩ ደግሞ የሽያጭ መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊልም ይችላል።

ለምሳሌ በየሩብ አመቱ የሽያጭ ገቢውን የሚያሠላ ድርጅት ነው ብንል፤ የመጀመሪያው ትንበያ ድርጅቱ በየሩብ አመቱ ምን ያህል ሽያጭ ሊኖረው እንደሚችል ከማወቅ ይጀምራል። ይህ ‹‹ሴልስ ፎርካስት›› ወይም የሽያጭ መጠን ትንበያ በመባል ይጠራል። በየሩብ አመቱም

ከዚህ ሽያጭ ላይ ምን ያህል የባለፈውን ሩብ አመት ያልተሰበሰበ ገንዘብና የወቅቱን የሩብ አመት ሽያጭ ሊሰበሰብ እንደሚችል ከባለፈው አመት ተሞክሮ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ድርጅት ልምድ በመነሳት ማስላት ይኖርበታል።

‹‹የዚህ ሩብ አመት ተሰብሳቢ ሽያጭ መጠን= 25 በመቶ የባለፈው ሩብ አመት ሽያጭ + 75 በመቶ የአሁን ሩብ አመት ሽያጭ››

እንደ ተሰብሳቢ ሽያጭ የሌላቸው ለምሳሌ በእርግጥ ሱፐርማርኬቶች፣ሬስቶራንቶች ደንበኛ ወዲያው ስለሚከፍላቸው የሽያጭ ትንበያ ገቢው በመቶ ፐርሰንት የሚሰበሰብ ስለሆነ ባለበት መውሰድ ይችላሉ። እንዲሁም በቀጣይ ድርጅቱ በየሩብ አመቱ የሚከፍላቸውን ቋሚ ወጪዎች (የሠራተኛ ፣ የኪራይ ፣ የብድር ወለድ እንዲሁም ግብሮችን) ጨምሮ መተንበይ ያለበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ለአቅራቢዎች የሚከፍሉትንም ጥምር ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ለአቅራቢዎች ተከፋይ መሆን ያለባቸው የባለፈው ሩብ አመት ውዝፍ እዳዎች (አከሯልስ) በየሩብ አመቱ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል።

በዚህ መሠረትም እንዳንዶቹ ሩብ አመት ላይ ወደ ባንክ የገባው የተጣራ ጥሬ ገንዘብና ለተለያዩ ወጭዎች ከባንክ በሚወጣው ጥሬ ገንዘብ መሃከል ያለውን ልዩነት (ሊቀናንስ) ትርፍ ሊያመጣ ወይም ጉድለት ሊያሳይ ይችላል። ለምሳሌ የአንድን ድርጅት ‹‹የካሽ ፍሎው ፎርካስት›› ወይም የጥሬ ገንዘብ የየሩብ አመት ትንበያዎችን እንመልከት።

[illegible]	ሩብ 2011	ሩብ 2011	[illegible]	[illegible]
[illegible]	5,000	15,500	9,500	-500
[illegible]	11,500	-5,000	-11,000	4,000
[illegible]	16,500	10,500	-1,500	2,500
[illegible]	1,000	1,000	1,000	1,000
[illegible]	15,5000	9,500	-500	5,000

የ2011 ዓ.ም የ ‹‹ሚዲያክ›› ድርጅት የጥሬ ገንዘብ ሚዛን ማሳያ

ማብራሪያ፡- ከላይ በዲያግራሙ ላይ እንደታየው ‹‹ባንክ የነበረው ገንዘብ›› ማለት ከባለፈው ሩብ አመት ማለትም ከ2010 ዓ.ም የመጨረሻው ሂሳብ መዝጊያ (ለምሳሌ ሠኔ 30/2010 ዓ.ም) ላይ በባንክ ያለው ገንዘብ በማለት ነው፤ በአካውንቲንግ ቋንቋ *‹‹Beginning Cash Balance››* በመባል ይጠራል፡፡ በተከታታይ ያሉ ሩብ አመታት ላይም የባለፈውን ሩብ አመት ባንክ ያለ የመጨረሻ ገንዘብ እየወሰድን እንጀምራለን፡፡ ለምሳሌ የሁለተኛው ሩብ አመት (2011) ባንክ ያለ ገንዘብ 15,500 ሲሆን ይህም የመጣው ከመጀመሪያው ሩብ አመት (2011 የመጨረሻ ረድፍ ላይ በቀሪነት የተመዘገበውን ነው፡፡ በሁለተኛው ረድፍ ‹‹የተጣራ ጥሬ ገንዘብ›› የሚባለው ደግሞ ከላይ ተዳሷል፡፡ በዚህም መሠረት በየሩብ አመቱ በትክክል የተሰበሰበው የገንዘብ መጠንና በዚያ ሩብ አመት ተከፋይ በሚሆኑ ወይም በሚወጡ የገንዘብ መጠኖች መሃከል ያለውን ልዩነት ነው፡፡ ይህ የተተነበየ የጥሬ ገንዘብ ሪፖርት ነው(በፋይናንስ ትንበያ) ዙሪያ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተዳሷልና ይመልከቱ፡፡ ይህ የተጣራ ገንዘብ መጠን በመጀመሪያውና በመጨረሻው ሩብ አመታት ትርፍ ጥሬ ገንዘብን ሲያሳይ፤ በሁለተኛውና ሶስተኛው ሩብ አመታት ደግሞ ጉድለትን ያሳያል፡፡ በሠንጠረዥ ቁመት ወደ ታች ስንሄድ በአምስተኛው ረድፍ ላይ ‹‹ዝቅተኛ ተቀማጭ ጥሬ ገንዘብ ››

ማለት ሁልጊዜ በየሩብ አመቱ ሊኖር የሚገባና የማይነካ ለማለት ነው፤ መጠኑም ‹‹1,000›› ነው፡፡ ይህ መጠን እንደየድርጅቶቹ ይለያያል፤ በዲያግራሙ የመጨረሻ ረድፍ ላይ የምናገኘው ደግሞ በድርጅቱ ባንክ አካውንት ላይ ተወራርዶ የሚገኘው መጠን ሲሆን ከዚህ አንፃር በሶስተኛው ሩብ አመት ላይ ጉድለት ይታያል በ‹‹1,500›› መጠን፡፡

ካሽ በጀት በቀጣይ በምን መልክ ሲጠቅም ይችላል?

ይህ የሚጠቅመው ድርጅቱ መቼ ላይ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ሊገጥመው እንደሚችል ሲሆን ይህን ጉድለት ከወዲሁ በማወቅም የጥሬ ገንዘብ ጉድለቱን *(Cash shortfall)* በምን መልኩ መሙላት እንዳለበት እንዲያቅድና መፍትሔ እንዲያፈላልግ ያግዘዋል፡፡ ይህ መሠሉ የካሽ ፍሎው ትንበያ የገንዘብ ጉድለትን የማጣጣም መርህን እንድንከተል ያደርገናል፡፡ የገንዘብ ጉድለትን የማጣጣም መርህ፤ ‹‹ማችንግ ፕሪንሲፕል›› በመባል የሚጠራ ሲሆን የአጭር ጊዜ የሥራ ማስኬጃ ጥሬ ገንዘብ ጉድለት ለአጭር ጊዜ ገንዘብን ከሚሰጡ ምንጮች መሙላትን ሲያመላክት፤ የረዥም ጊዜ ወይም ቋሚ የሥራ ማስኬጃ የገንዘብ ጉድለት ደግሞ ለረዥም ጊዜ ገንዘብን ከሚያቀርቡ ምንጮች መሞላት እንደሚኖርበት የሚያሳየን ነው፡፡

ከዚህ አንፃር የሥራ ማስኬጃ ካፒታል በሁለት ይከፈላል፤ ይህም ቋሚ የሥራ ማስኬጃና ጊዜያዊ የሥራ ማስኬጃ በማለት፡፡ ቋሚ የሥራ ማስኬጃ የምንለው የድርጅቱን ቀጣይ ስራዎች ለማከናወን የመጀመሪያውን ሊመደብ የሚገባ የካፒታል መጠን ነው፡፡ ለምሳሌ አዲስ ጀማሪ ቢዝነስ በጀመረበት አመት ውስጥ ለሚጠበቁበት የአመት የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች የግድ ሊመደበው የሚገባ መጠን ሲሆን ይህ ‹‹ቋሚ የሥራ ማስኬጃ ወጪ›› በመባል ይጠራል፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን ታዲያ

Scanned with CamScanner

በረዥም ጊዜ ተከፋይ ሊሆኑ ከሚችሉ የገንዘብ ምንጮች ማለትም ከድርጅቱ ባለቤቶች (በኢንቬስትመንት) መልክ ወይም ደግሞ በረዥም ጊዜ በሚከፈል የአበዳሪ ተቋማት ሊመጣ ይችላል፤ ይህ ‹‹Long Term Financing›› የሚባለው ነው።

አሁን ደግሞ ከላይ በዲያግራሙ ላይ ባየነው መሠረት ድርጅቱ በስራ ውስጥ እያለ በየመሃከሉ ለሚገጥመው ጊዜያዊ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ‹‹በማችንግ ፕሪንሲፕል›› የማጣጣም መርህ መሰረት ከአጭር ጊዜ የገንዘብ አቅራቢ ምንጮች ጉድለቱን የሚሞላበት መርህ ነው። ይህ የአጭር ጊዜ የሥራ ማስኬጃ ጉድለት ‹‹ጊዜያዊ የሥራ ማስኬጃ›› በመባል የሚጠራ ሲሆን የአጭር ጊዜ ገንዘብ አቅርቦቱን ደግሞ ‹‹Short Term Financing›› በማለት እንጠራዋለን።

ምን አይነት የአጭር ጊዜ የገንዘብ አቅራቢዎችን ልንጠቀም እንችላለን፤ የትኛውስ የተሻለ ነው?

የአጭር ጊዜ የፋይናንስ አቅራቢዎች የተለያዩ ያሉ ሲሆኑ እነዳቸው ከሌላኛቸው በሚሠጡት የገንዘብ መጠን ልክ፤ በሚያስከፍሉት የወለድ መጠን እንዲሁም በሚፈቅዱት የመመለሻ ጊዜ መጠንና በቅድመ ሁኔታ መልክ በሚያስቀምጡት መስፈርት ይለያያሉ። እነዚህን የአጭር ጊዜ የገንዘብ ምንጮችን እንደሚከተለው ልንመለከታቸው እንችላለን።

የመጀመሪያው አማራጭ ባንክ ነው። ይህም በተወሰነ የጊዜ ሠሌዳ ውስጥ ተመላሽ የሚሆን ብድር አንዱ ሲሆን ይህም በድርጅቱና በባንኩ መሃከል በሚደረግ የውል ስምምነት መሠረት ተግባራዊ ይሆናል። ይህ የአንድ ጊዜና በጊዜ ገደብ ውስጥ የሚወሰድ የባንክ ብድር በስምምነቱ መሠረት ሶስት ነገሮችን ያካተተ ውልን ይይዛል፤ የብድሩን መጠን፤ የወለዱን መጠን እና የጊዜ ገደብን።

በሁለተኛ ደረጃ ያለው የባንክ ብድር አማራጭ ‹‹ላይን ኦፍ ክሬዲት›› በመባል የሚጠራ ሲሆን ባንኮች ለተበዳሪ ድርጅቶች እስከተወሰነ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ድረስ በፈለጉ ጊዜ ብድር መውሰድ የሚችሉበት መንገድ ነው። በዚህም መሠረት ድርጅቱ በፈለገ ጊዜ ለአጭር ጊዜ የሥራ ማስኬጃ ጉድለቱን ለመሙላት የሚጠቀምበት መንገድ ነው። ባንኮች ይህን መሠል እድል በተለይ የሚያመቻቹት ለሚተማመኑባቸው ድርጅቶች ማለትም ጥሩ የገንዘብ ጤናማነትና አቅም ላላቸውና ተበድረው በመመለስ ደረጃ ከባንኮቹ ጋር ጥሩ ግንኙነት ላላቸው ነው። ከመጀመሪያው የባንክ ብድር የሚለየው ድርጅቱ በፈለገ ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ ገንዘብ መውሠድ መቻሉ ነው።

በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ አንድ ድርጅት ለረዥም ጊዜ ብድር ሊጠይቅ ይችላል። ይሁን እንጂ ባንኩ ይህን ብድር እስኪለቅለት ድረስ ለጊዜው ድርጅቱ በስራ ማስኬጃ እጥረት እንዳይጎዳ የተወሰነውን መጠን ቀድሞ ሊለቅለት ይችላል። ይህ መሠሉ ለአጭር ጊዜ ማስተንፈሻነት የሚውል የብድር ስልት ‹‹ብሪጅ ሎን›› በመባል ይጠራል፤ መሸጋገሪያ ብድር እንደማለት ነው።

የአጭር ጊዜ የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ጉድለትን ለመሙላት ከባንክ ወጣ ስንል ደግሞ ሌሎች አማራጮችን ልንጠቀም እንችላለን። ምክንያቱ ደግሞ የባንክ ብድር በተፈለገው ጊዜና መጠን ላይገኝ ስለሚችል ወይም ደግሞ ድርጅቱ የባንኮችን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት ሳይችል ሲቀር ነው። እንዲሁ ደግሞ የብድር እድሉ እለው ግን ደግሞ ከክፍያ ወጪ(ወለድ) እና ከገንዘብ መክፈያ ጊዜውና ከሚፈለገው የገንዘብ መጠን አንፃር የተሻሉ አማራጮችን ከሌሎች ምንጮች ሊጠቀም ይችላል። በዚህ መንገድ እንደ አማራጭ ልናያቸው የሚገቡ የገንዘብ አቅራቢ ምንጮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

የመጀመሪያው ከተበዳሪ ድርጅቱ ጋር አብረው የሚሠሩ ድርጅቶች (ለምሳሌ አቅራቢዎች) በአበዳሪነት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ይህም የሚሆነው ተበዳሪው ድርጅት ያልተሰበሰቡ የሽያጭ ገቢዎች ይኖሩትና በወቅቱ ግን የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ሊያጥረው ይችላል። በዚህ አጋጣሚ ውስጥ ድርጅቱ ያሉትን ተሰብሳቢ ገቢዎች ለአበዳሪ ድርጅቱ በሽያጭ መልክ የተሰብሳቢዎቹን 80 በመቶ ወይም 90 በመቶ በሆነ ዋጋ ሊሸጣቸው ፤ ሊበደርባቸው ይችላል። ምናልባት ኢንቮይስ የተቆረጠላቸው ተሰብሳቢ ገንዘቦች በ60 ቀናት ውስጥ የሚመጡ ከሆነና መጠናቸው አንድ ሚሊዮን ብር ቢሆን አበዳሪው በዚህ ቀን ውስጥ ሊመለስለት የሚገባ የአጠቃላይ መጠኑን 800 ሺህ ወይም 900 ሺህ ብር ሊያበድረው ይችላል። የተበዳሪው ድርጅት ደንበኞች ገንዘቡን በቀጥታ የሚከፍሉት ግን ለአበዳሪው ድርጅት ብቻ ይሆናል፤ ይህም በውል ስምምነት ውስጥ የሚካተት ይሆንና ለደንበኞቹም ይህን ያልተሰበሰበ ክፍያ ለአበዳሪው በቀኑ መክፈል እንዳለባቸው ይነገራቸዋል። በተባለው ቀን ደንበኞች ባይከፍሉ ተጠያቂው ተበዳሪው ይሆናል። ይህ መሠሉ የብድር ስምምነት በእርግጥ ድርጅቱ ከተከፋይ ገንዘቦች ለምሳሌ 80 በመቶ ወይም 90 በመቶ የሆነ ዋጋቸውን ለአበዳሪው እንደመሸጥ የሚቆጠር ነው። ይህም ማለት አንድ ሚሊዮን የሚሆነውን ተሰብሳቢ ገንዘብ በ60 ቀን ለሚሰበሰበው መጠን 800 ሺህ ወይም 900 ሺህ ብር መሸጥ አበዳሪው እንደ ስምምነቱ 200 ሺህ ወይም 100 ሺህ ብር ትርፍ ያገኛል ማለት ነው፤ ይህም ትርፍ በሌላ አገላለፅ የአጭር ጊዜ ወለድ መሆኑ ነው።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ኖሮት ነገር ግን ተሰብሳቢዎቹን ገንዘቦች (ኢንቮይስ) እንደ ኮላተራል በመያዣነት በመጠቀም ከአበዳሪ ድርጅቶች ሊበደርባቸው ይችላል። አበዳሪ ድርጅቱ የትኛውን ተሰብሳቢ ገንዘብ እንደመያዣ ይዞ ማበደር እንዳለበት በቅድሚያ ተሰብሳቢዎቹን ገቢዎች

እንዳቸውን ከሌላኛቸው የማመዛዘን ሥራ የሚሠራ ሲሆን ከመረጣቸው ውስጥ እስከ 75 በመቶ ሊያበድረው ይችላል። የተበዳሪው ድርጅት ደንበኞችም መክፈል ያለባቸውን ገንዘብ ለአበዳሪው ባይከፍሉ ተበዳሪ ድርጅቱ ተጠያቂነት ይኖርበታል።

ሌላኛው የብድር ስምምነት ድርጅቱ ገንዘቡን ተጠቅሞ ከሚያገኘው ትርፍ ላይ ለአበዳሪው በማጋራት ላይ የተመሠረተም ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንድ ድርጅት የአጭር ጊዜ ገንዘቡን ተጠቅሞ የሚያገኘው ትርፍ ይኖራል። አበዳሪው በትርፉ ካመነበት እንደስምምነታቸው ከ 30-40 በመቶ ከትርፉ ላይ አበዳሪው እንዲጠቀም በማድረግ ሊሆን ይችላል። ይህ ዘዴ ምንም እንኳን ከትርፉ ከፍ ያለ መጠን መስጠቱ ከባንክ ወለድ በላይ ሆኖ ቢታይም ሌሎች የገንዘብ ምንጮች በሌሉበት አጋጣሚ ሊመጣ የነበረው የትርፍና ጥቅም በገንዘብ ጉድለት ሳቢያ ጭራሽ እንዳይቀር እንደመጨረሻ አማራጭ ሊወሰድ የሚችል የአጭር ጊዜ የገንዘብ ጉድለት መሙሊያ መንገድ ነው።

እንዲሁም ድርጅቶች የጥሬ እቃ ወይም ያለቀላቸው ምርቶች በመጋዘናቸው ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ ክምችቶች ዋጋ ቢወጣላቸው የራሳቸው የካፒታል መጠን ያላቸው ናቸው። ይሁን እንጂ ለድርጅቱ የአሁን ጊዜ የገንዘብ ፍላጎት ጥሬ እቃዎቹ ወደምርት ተሸጠው ገንዘብ እስካልመጡ ድረስ አላመጡለትም፤ ያለቀላቸው ምርቶችም ገበያው እስከፈለጋቸው ድረስ የሚቆዩ በመሆናቸው ገንዘብ ይዘው የተቀመጡ ናቸው። ይሁን እንጂ በቀጣይ በምናየው ስልት ግን ሊበደርባቸው ይችላል፤ እነሱን በመያዣነት በመጠቀም።

የመጀመሪያው መንገድ የጥሬ እቃዎችን ወይም ያለቀላቸውን ሸቀጦች ዝቅ ባለ ዋጋ ለአበዳሪዎች መሸጥ ነው። እንግዲህ ይህ ማለት ከሚያወጡበት ዋጋ በታች ወይም ከ 20-30 በመቶ ቅናሽ ሲሸጡ ገንዘቡን ለማግኘት ለገዥው ይህን ያህል ወለድ እንደመክፈል

Scanned with CamScanner

ይቆጠራል። ይህ መንገድ ጉዳቱ ምንድነው? ወለዱ ከፍ ማለቱ ብቻ ሳይሆን በክምችቶቹ አለመኖር ድርጅቱ የሚያጣው ገቢ መኖሩና በቀጣይም እነሱን ለመተካት ጥረት ሲያደርግ ወጪ የሚጨምርበት በመሆኑ ውድ ዋጋ የሚያስከፍል አማራጭ ነው። ይህ ዘዴ ብዙውን ጊዜ እንደመጨረሻ አማራጭ የሚወሠድ ነው።

ከዚሁ ሳንወጣ አሁንም እነዚህን የጥሬ እቃ ወይም ያለቀላቸውን ሸቀጦች በመጠቀም ነገር ግን የተወሰኑትን ብቻ በማስያዣነት የሚበደርባቸው ሲሆን እቃዎቹ ከመሸጣቸው በፊት ግን የተወሰደው ብድር መከፈል ይኖርበታል። በዚህ መንገድ የመኪና አስመጭዎች ከመኪና አምራቾች ብድር የሚወስዱበት መንገድ ጥሩ ምሳሌ ሲሆን መኪኖቹ በዱቤ ቢገዙም ወኪሎች ግን መኪኖቹን ከመሸጣቸው ቀደም ብሎ ግን ተከፋይ ይሆናሉ።

የውጤታማ ኢንቨስትመንት መንገድ!!

‹‹ባንክ በመቀጠብ ብቻ ስንት ሠው ነው ሃብታም የሆነው ? ከፈለጋችሁ የስኒንም ታሪክ ማየት ትችላላችሁ!›› ሮበርት ስበን

በዓለም ላይ በርካታ አዳዲስ የቢዝነስ ድርጅቶች በየጊዜው ይከፈታሉ። ይሁን እንጂ የተከፈቱ ድርጅቶች ሁሉ ይዘልቃሉ ማለት አይደለም። አዲስ ከሚከፈቱ የቢዝነስ ድርጅቶች መካከል ምን ያህሉ 10ኛ አመታቸውን ያከብራሉ? በሚል በአሜሪካን አገር አንድ ጥናት ተጠንቶ ነበር። አዲስ ከተከፈቱ የቢዝነስ ድርጅቶች ውስጥ 95 በመቶ የሚሆኑት 10ኛ አመታቸውን እንደማያከብሩ የጥናት ውጤቱ አመላክቷል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ በአገራችን አገር አቀፍ ጥናት አልተጠናም እንጂ በአንፃራዊነት ሲታይ ውድድሩ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ የእኛ አገር ሁኔታ የተሻለ ነው ማለት ይቻላል።

ለቢዝነስ ድርጅቶች መውደቅ መንስኤ የሚሆኑ ጉዳዮች በርካታ ናቸው። ዋና ዋና የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፦

1. የቢዝነስ ድርጅቶችና የግል ሐብትን መቀላቀል ወይም ለይቶ አለማየት፦ አንድ የቢዝነስ ድርጅት ከባለቤቱ የተለየ ህልውና ሊኖረው ይገባል። የድርጅቱ ሀብት ከባለቤቱ ሀብት ጋር መቀላቀል የለበትም። ከተቀላቀለ ድርጅቱ ያትርፍ ወይም ይክሰር በትክክል ማወቅ አይቻልም። ብዙጊዜ በአገራችን አዳዲስ ድርጅቶች ተመስርተው ማትረፍ ሲጀምሩ ባለሀብቶቹ ከድርጅቱ ሀብት ላይ በዘፈቀደ ገንዘብ እየወሰዱ የግል ቤት፣ መኪናና ሌሎች እቃዎችን የመግዛት እንዲሁም አትራፊነቱ ያልተሞከረ ሌላ አዲስ ድርጅት የመክፈት ሁኔታዎች በስፋት ይታያሉ። የንግድ ድርጅት እንደ ልጅ ይወለዳል በሂደትም ያድጋል። ልጅ ሲወለድ

Scanned with CamScanner

ብዙ ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ አዲስ የተመሰረተ የንግድ ድርጅትም በመጀመሪያዎቹ ጊዚያት አካባቢ ብዙ ገንዘብ ይፈልጋል:: ከጊዜ በኋላ ግን የገንዘብ ፍላጎቱ ቀንሶ ትርፍ የሚያመነጭ ይሆናል:: ስለሆነም የሚገኘውን ትርፍ መልሰን ኢንቨስት በማድረግ አትራፊነቱ የተረጋገጠውን ድርጅት ማስፋፋት እና አስተማማኝ ትርፍ እንዲሰጥ ማድረግ ይገባል:: በአገራችን ያለው ልምድ ግን ከዚህ እውነታ ጋር የተቃረነ ነው:: አዲስ የንግድ ድርጅት ከተቋቋመ በኋላ አድጐ ገንዘብ መስጠት ሲጀምር ድርጅቱን ጉዳት ላይ በሚጥል መልኩ ገንዘቡን ለግል አገልግሎት የማዋል አዝማሚያ ይስተዋላል:: በሌላ በኩል አትራፊ ከሆነው ድርጅት ገንዘብ ተወስዶ ማትረፉ ባልተረጋገጠና አዲስ የንግድ ድርጅት ላይ ኢንቨስት ይደረጋል:: የድርጅትና የግል ሒሳብ ባለመለየቱ ብዙ ባለሀብቶች በአመቱ መጨረሻ ላይ የመንግስት ግብር መክፈል የማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ:: የትርፍ ግብር የሚባለው ከድርጅቱ አመታዊ ሽያጭ ላይ ወጪ ተቀንሶ ከተጣራ ትርፍ 30 በመቶ የሚከፈል ነው:: ነገርግን ድርጅቱ ትርፍ እያለው ጥሬ ገንዘቡን ሌላ ቦታ ካዋለው የሚጠበቅበትን ግብር መክፈል ያቅተዋል::

ማንኛውም የንግድ ድርጅት መጠኑ ይለያይ እንጅ ካፒታል፣ ጥራት ያለው የሰው ኃይልና ጥራት ያለው የግብዓት አቅርቦት ይፈልጋል:: ይሄን ፍላጎት ማሟላት ካልተቻለ ድርጅቱ ተወዳዳሪ መሆን አይችልም:: በስተመጨረሻም መውደቁ አይቀርም::

2. የንግድ ድርጅቶች በራሳቸው እንዲቆሙ ብቃት ያለው ድርጅታዊ አቋም እንዲዳብር አለማድረግ:- በየትኛውም መመዘኛ ጠንካራ ድርጅታዊ አቋም ያለው የንግድ ድርጅት ባለቤቱ ኖረም አልኖረ በራሱ መቀጠል ይችላል:: ሳይንሱም የሚለው ይሄንኑ ነው:: በአገራችን በብዛት የሚታየው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው:: ባለቤቶቹ ሳይኖሩ ቢዝነሱም አብሮ ሲወድቅ ይታያል:: የዚህ ምክንያቱ ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር

አለመኖርና ተፈላጊውን ሰው በተፈለገው ቦታ ያለማስቀመጥ ችግር ነው:: ድርጅቶች ራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ማድረግ ይገባል::

3. የትርፍ ግብርን አስቀድሞ አለማቀድና አለመተግበር› የትርፍ ግብር በመሰረታዊነት አስቀድሞ መታቀድ አለበት:: ነገርግን አገራችን እንዲህ ያለው ዘመናዊ አሰራር ባለመኖሩ የትርፍ ግብርን የንግድ ድርጅቶች አስቀድመው አያቅዱም:: በዚህም ሳቢያ ድርጅቶች የሚያተርፉትን ባለሀብቶች ከስር ከስር ገንዘቡን ይወስዱታል:: በመሆኑም በአመቱ መጨረሻ ብዙ ድርጅቶች የትርፍ ግብር ለመክፈል በከፍተኛ ሁኔታ ይቸገራሉ:: ከዚህ ችግር ለመውጣት ቢቻል በየወሩ ካልተቻለ በየሶስት ወሩ ሒሳብን በመስራት ትርፉን ማወቅና ከትርፉ ውስጥ ለግብር የሚሆነውን ገንዘብ አቅዶ ማስቀመጥ ይገባል:: ይህ ካልሆነ ታክስ መክፈል ባለመቻል ድርጅቱ ሊዘጋ ይችላል:: እዚህ ላይ ‹‹ታክስና ሞት አይቀሩም›› የሚለውን አባባል ማስታወስ ጥሩ ነው:: ታክስ ከሌለ መንግስት የለም:: መንግስት ከሌለ አገር የለም:: መንግስትና ሰላም በሌለው አገር መኖር የሚፈልግ ሰው የለም:: ስለሆነም ታክስ መክፈል ፀጋ መሆኑን ማወቅ፣ እኔ የምከፍለው ታክስ አገሬን እያቆመ ነው ብሎ ማመን ያስፈልጋል:: ስለሆነም ታክስን አስቀድመን ማቀድ ያስፈልጋል:: በአመቱ መጨረሻ ታክስ መክፈል እንደሚጠበቅብን አውቀን በየወሩ ለታክስ የሚሆነውን ክፍያ አቅደን ማስቀመጥ ይኖርብናል:: ለዚህም ከታክስ ጋር የተያያዘው ችግር በእቅድ ሊፈታ ይችላል:: ማንም ሰው በሚረዳው መንገድ ሰነድን ማደራጀት ያስፈልጋል::

4. የድርጅቱን ተቋማዊ አደረጃጀት በየጊዜው እያጠናከሩ አለመሄድ፡ የትኛውም ድርጅት ለብዙ አመታት ሊቆይ ይችላል:: ሰዎች ግን የተወሰነ እድሜ ነው ያለን:: ስለሆነም የድርጅት መሪዎች (ባለቤቶች) በጡረታ ሊገለሉ፣ ሊያልፉ፣ ሐሳባቸውን ሊቀይሩና ሌላ ስራ መስራት ሊፈልጉ ይችላሉ:: በመሆኑም አስቀድሞ ከስር

ከስር ተተኪዎችን ማፍራት (ማዘጋጀት) ይገባቸዋል:: ይሄን በማድረግ ድርጅቱ እንዳይወትድ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: በአገራችን እንደዚህ ያለው አሰራር ያልዳበረ በመሆኑ አንድ ጉብዝ የፋይናንስ ማናጀር ወይም የድርጅቱ ባለቤት በተለያዩ ምክንያቶች ሲለቁ ድርጅቱ አብሮ ይወድቃል::

የተጀመረትንም ሆነ አዲስ የሚጀመሩ ኢንቨስትመንቶችን ውጤታማ ማድረግ እና ውጤታማነታቸውን የመስኪያ ዘዴዎች!!

በእኛ አገር ሁኔታ ኢንቨስትመንት ብዙ ገንዘብ ካለው ሰው ጋር እያይዘን ነው የምናየው:: ነገርግን አንድ ሰው ኢንቨስተር ለመባል ወይም ኢንቨስት ለማድረግ ብዙ ገንዘብ አያስፈልገውም:: ማንኛውም ሰው ያለውን ገንዘብ ያክል ኢንቨስት ማድረግ ይችላል:: ለምሳሌ በአክሲዮን የሚቋቋም ባንክ ቢኖር እና የአንድ አክሲዮን ዋጋ 1000 ብር ቢሆን አንድ ሺህ ብር ከፍሎ ኢንቨስት ማድረግ ይቻላል:: የኢንቨስትመንት መሠረታዊ ሐሳብ ያለመገንዘብ ችግር አለ:: አንድ ሰው ሀብታም የሚሆነው ሀብታም ሁኖ ስለተወለደ ሳይሆን በራሱ ትጋት ሀብት ለመፍጠር ባደረገው ጥረት ነው:: ስለሆነም ስለ ኢንቨስትመንት ያለንን አስተሳሰብ ማስተካከል ይገባል:: ኢንቨስትመንት ገንዘብ ነክና ገንዘብ ነክ ያልሆነ ኢንቨስትመንት በሚል በሁለት መክፈል ይችላል:: ለምሳሌ አንድ ሰው በአንድ ሙያ ብቁ ከሆነ የተወሰነ ገንዘብ ካለው ባለሃብት ጋር አብሮ በመሆን ሙያውን ኢንቨስት ያደርጋል፣ ባለሀብቱ ደግሞ ገንዘቡን ያዋጣል:: በሁለቱም መንገድ ማንኛውም ግለሰብ ኢንቨስትመንት ውስጥ ሊገባ ይችላል::

በሌላው በኩል አንድ ድርጅት ተመስርቶ የተወሰነ ጊዜ ከሰራ በኋላ ተጨማሪ ካፒታል ሊያስፈልገው ይችላል:: በዚህ ጊዜ ኢንቨስትመንቱን ለማስፋት የሚመጣልን ሃሳብ ባንክ ነው:: ነገርግን ካፒታልን ለማሳደግ የሚያስችል ፋይናንስ ለማግኘት ባንክ የመጀመሪያ አማራጭ ሳይሆን ይችላል:: ከባንክ ውጭ ያሉ የገንዘብ አማራጮችን ማየት ይገባል:: ለምሳሌ ገንዘብ ይዘው አትራፊ ድርጅት የሚፈልጉ ኢንቨስተሮች አሉ:: እነዚህ ኢንቨስተሮች አትራፊ ድርጅቶች ላይ ኢንቨስት በማድረግ የሚተዳደሩ ናቸው:: ኢንቨስት ስለሚያደርጉለት ድርጅት ቴክኒካዊ እውቀት አያስፈልጋቸውም:: የሚያስፈልጋቸው ነገር የድርጅቱ አትራፊነት ነው:: አትራፊነት ሲባል የተወሰነ ገንዘብ ኢንቨስት በማድረግ እና ቶሎ ባልሆነ መንገድ ከፍተኛ ትርፍ ማግኘት ማለት ነው:: በሌላ በኩል ኢንዱስትሪ ኢንቨስተርስ የሚባሉ አሉ:: ለምሳሌ አንድ አነስተኛ ሳሙና ፋብሪካ አለ ብለን እንነሳ:: ይሄ ፋብሪካ አምርቶ የሚሸጥ፣ አትራፊና ምርቱም በማህበረሰቡ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ነው:: ይሄን ፋብሪካ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ፋብሪካውን ማስፋፋት የተሻለ አማራጭ ተደርጎ ቢወሰድ እና ካፒታል ቢፈለግ ባንክ ብቸኛ አማራጭ ሳይሆን ይችላል:: ወደ ባንክ ብድር ከመሄዳችን አስቀድሞ በአገር ውስጥም ሆነ በዓለማቀፍ ደረጃ በሳሙና ኢንዱስትሪ ዘርፍ በቂ እውቀትና ልምድ ያላቸው ኢንቨስተሮች በእውቀት፣ በገንዘብ፣ በማሽነሪና በቴክኒክ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ማድረግ ይቻላል:: በእነዚህ አማራጮች የገንዘብ ክፍተቱን ለመሙላት መጣር ይገባል:: ስለሆነም አማራጮች አስቀድመው በአግባቡ ሳይታዩ ወደ ሌሎች የገንዘብ ማግኛ አማራጮች ባንክ ብድር መሄድ ተገቢ አይደለም::

የኢንቨስትመንት ውጤታማነት ዋነኛ መለኪያው ምን ተጠቅመን ምን አተረፍን? የሚለው ነው:: የተጠቀምነው ካፒታልና ያመጣነውን መለካት ይቻላል:: ኢንቨስትመንቱ ውጤት ፋይናንሻል በሆነ መንገድ

Scanned with CamScanner

ከፋይናንሻል ውጤታማነት በተጨማሪ በፈጠረው የስራ እድል እንዲሁም ለአካባቢው በአመጣው አዳዲስ እድሎች መታየት አለበት። የኢንቨስመንት ውጤታማነት ከፋይናንሻል አንፃር ሲሰላ ያተረፍነውን ትርፍ በአመቱ ኢንቨስት ላደረግነው ካፒታል በማካፈል ስሌት የሚገኘው ውጤት የአንድን ኢንቨስትመንት ውጤታማነት ያመለክታል። ለምሳሌ አንድ የስቴሽነሪ ሱቅ በአመት 500,000 ብር ተጠቅሞ 1,000,000 ብር ቢያተርፍ፣ ሌላው ተመሳሳይ ድርጅት ደግሞ 1,000,000 ብር ተጠቅሞ 1,000,000 ብር ቢያተርፍ 500,000 ተጠቅሞ 1,000,000 ያተረፈው ውጤቱ 2 ነው። በሌላ በኩል 1,000,000 ተጠቅሞ 1,000,000 ያተረፈው ድርጅት ውጤቱ 1 ነው። የ1,000,000 ትርፍ ኢንቨስት ከተደረገው ካፒታል አንፃር ሲሰላ 500,000 ብር ተጠቅሞ ካተረፈው እኩል ውጤታማ ነው ማለት አይቻልም። በሌላ በኩል ደግሞ የአንድ ኢንቨስትመንት ውጤታማነት በስራው ላይ ምን ያህል ሰው ተሳተፈ? የሚለውም ይታያል። በአጠቃላይ አንድ ኢንቨስትመንት አትራፊ መሆኑ የሚለካው በትርፉ ብዛት ብቻ ሳይሆን ያተረፈው ትርፍ ለተጠቀመው ካፒታል ተካፍሎ በሚገኘው ውጤት ነው።

ሌላኛው መለኪያ የምንጠቀምበት ካፒታል ውድ ነው ወይስ እርካሽ ነው? የሚለው ነው። ይሄም ማለት ለስራው (ለምርቱ ወይም ለአገልግሎቱ) የሚውል ግብዓት ለመግዛት፣ የሰው ኃይል ለመቅጠርና ቤት ለመከራየት ገንዘብ ያስፈልገናል። የሚፈለገው ገንዘብ እንደማንኛውም ሀብት ዋጋ አለው። አሁን ባለው የባንክ ወለድ ለገንዘቡ ከ15 እስከ 18 በመቶ ልንከፍል እንችላለን። ይሄ ማለት የገንዘቡ ዋጋ ነው። ስለሆነም በቅድሚያ ካፒታልን መመንዘርና በተለያዩ መመዘኛዎች ዋጋውን በትክክል ማወቅ ይገባል። ካፒታል ከባንክ ስንበደር የራሱ ዋጋ አለው። ካፒታል አክሲዮን በመሸጥም ይሁን በሌላ መንገድ ስናመጣ ገንዘቡ የራሱ ዋጋ አለው። ሁሉቱን አመዛዝነን ቀለል ያለውን መምረጥ ያስፈልጋል ምክንያቱም ሁሉም ካፒታል እኩል ዋጋ የለውም። ርካሽ ካፒታል አለ ውድ የሚባል ካፒታልም አለ። ለእኛ የሚጠቅመንን መርጠን መውሰድ አለብን።

በቢዝነስ ውስጥ ዘላቂነት የሚባለው ቃል ወሳኝ ነው። አንዳንድ ቢዝነሶች ለተወሰነ ጊዜ ተፈላጊነታቸው ከፍ ይልና ከትንሽ ጊዜ በኋላ ተፈላጊነት ያጣሉ። ሌሎች ደግሞ ተፈላጊነታቸውን በጣም ለረዥም ጊዜ ይዘው ይቆያሉ። ቶሎ ቶሎ በሚለዋወጡ ቴክኖሎጂዎች ላይ ኢንቨስት ስናደርግ የምንጠብቀው ውጤት ከፍተኛ መሆን አለበት። በቀላሉ ገብቶ አትራፊ የሚሆን ድርጅት ብዙ ጊዜ ዘላቂነትም የለውም። ምክንያቱም በዚህ በቀላሉ የሚገባበት ቢዝነስ ስለሆነ ብዙ ሰው በቀላሉ ይገባበታል። በስተመጨረሻም ጊዜ የዘርፉ አትራፊነት በፍጥነት እየቀነሰ በመሄድ ለኪሳራ ይዳረጋል። በተቃራኒው ደግሞ በገንዘብም ሆነ ከገንዘብ ውጭ ባሉ ጉዳዮች የሚወሰደው ጊዜ ረዥም የሆነ ከባድ ኢንቨስትመንት በአብዛኛው ዘላቂ ነው። አትራፊነቱም ቀጣይነት ያለው ይሆናል። ስለሆነም ኢንቨስት ለማድረግ ስናስብ በቀላሉ መስራት የሚባለውን ነገር ብቻ ማሰብ የለብንም። ኢንቨስትመንቱ ከበድ እያለ ሲሄድ ከጀርባው ማሰብ ያለብን ትርፍ ማግኘት ከጀመርን ትርፉ ለረዥም ጊዜ ሊቀጥል ስለሚችል ኢንቨስትመንቱ አስተማማኝ ሊሆን ይችላል ብለን ነው። ኢንቨስትመንት ስናስብ ኢንቨስት የምናደርግበት ቢዝነስ ከሌላው ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው? የሚለውን በአግባቡ ማጤን ያስፈልጋል። ኢንቨስትመንቱ በአካባቢው ላይ ብቁ ተወዳዳሪ መሆኑን እና ልዩነት መፍጠሩን በሚገባ አጥንቶ ማረጋገጥ ይገባል።

Scanned with CamScanner

ዓለማቀፍ ተሞክሮ አዳዲስ የቢዝነስ ሀቦችን ወደ መሬት ከማውረድ አንፃር !!

ማንም ሰው አዳዲስ የቢዝነስ ሀሳቦች ይኖሩታል፡፡ ሀሳቡን መሬት ላይ አውርዶ ለመስራት ሲፈልግ ገንዘብ እንዲሁም አብረውት የሚሰሩ ሙያተኞች ያስፈልጉታል፡፡ ፋይናንስ ከተለያዩ ምንጮች ማግኘት ይቻላል፡፡ እንደኛውና በአገራችን ሁኔታ የተለመደው ከባንክ መበደር ነው፡፡ ሌላው የፋይናስ ምንጭ ካፒታልን ከሰዎች ማሰባሰብ ነው፡፡ ካፒታልን ማሰባሰብ አዳዲስ የቢዝነስ ድርጅቶችም ሆነ ነባር ድርጅቶች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ይሁንና የተፈጠረውን የቢዝነስ ሀሳብ የፋይናንስ ምንጮች ጠቀሜታውን በግልፅ መረዳት እንዲችሉ በጽሁፍ ማቅረብ ይገባል፡፡ በሂደቱም የሀሳቡን አዋጭነት አይተውና አምነው ኢንቨስት እንዲያደርጉበት ማድረግ ይቻላል፡፡

እኛ አገር ካፒታል ለማሰባሰብ የሚያስችል አመች ሁኔታ ብዙ አይታይም፡፡ አንድ ሰው ከንግድ ድርጅት አክስዮን መግዛት ቢፈልግ የት መሄድ እንዳለበት አያውቅም፡፡ ግልጽ የሆነ አሰራርም የለም፡፡ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የባንክ ስራ ያተርፋል ብሎ ወይም በኢንዱስትሪው ዘርፍ አትራፊ የሆኑትን በመምረጥ የተወሰነ አክስዮን ገዝቼ ተጠቃሚ እሆናለሁ ቢል የትና እንዴት መግዛት እንዳለበት በኢትዮጵያ ያለው አሰራር ግልፅ አይደለም፡፡ ባንኮችም ሆኑ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች አክስዮን መሸጥ መደበኛ ስራቸው አይደለም፡፡ በአገራችን ለአክሲዮን ግብይት ወይም ለካፒታል ማሰባሰቢያ የሚሆን የተደራጀና ራሱን የቻለ ገበያ የለም፡፡ በብዙ የአፍሪካ አገሮች የአክሲዮን ገበያ አለ፡፡ በእኛ አገር ይህ ባለመኖሩ ብዙዎች ለኢንቨስትመንት ሲመጡ ግራ ይገባቸዋል፡፡ ይሄን ነገር መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ማየት አለበት፡፡ የአክሲዮን ገበያ በአገራችን ቢደራጅ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

እንደኛ ኢንቨስትመንት የሚባለውን እሳቤ በጣም ከተትረፈረፈ ሀብት ጋር ብቻ አያይዘን እንዳናስብ ያደርገናል፡፡ አንድ ማህበረሰብ የቁጠባ ባህልን ያዳብራል፡፡ አሰራሩ ለህግና ደንብ ተገዥ ይሆናል፡፡ ኃላፊነት የሚሰማቸው የንግድ ኩባንያዎች በአገራችን እንዲስፋፉ ያግዛል፡፡ ዜጎች የአገራቸው ልማት እና እድገት ያገባኛል እንዲሁም ተሳታፊና ተጠቃሚ ነኝ እንዲሉም እድል ይሰጣል፡፡ የአንድ አገር ኢኮኖሚ በዚህን ያህል አድጓል ሲባል ‹‹ወደ እኔ ኪስ የመጣ ነገር የለም›› የሚሉ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ የአክሲዮን ገበያዎች ቢኖሩ ግን ከአትራፊ ኩባንያዎች ዜጎች እንደየአቅማቸው አክስዮን በመግዛት የኢኮኖሚው እድገት ተካፋይ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ሒደት ከአገሪቱ እድገት ተጠቃሚ አይደለሁም የሚለው አስተሳሰብ እየተወገደ ይመጣል፡፡ የእኔ ትንሽ ገንዘብ ምንም ሊሰራ አይችልም ብሎ አለአግባብ ማባከንም ይቀንሳል፡፡

የፋይናንስ እንቅስቃሴን ለማሳደግ አማራጭ መፍትሔዎች!!

አንድ ድርጅት አገልግሎት ሰጭ ወይም አምራች ቢሆን ድርጅቱ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት የሚያስችሉትን ግብአቶች ግዥ ማካሄድ አለበት፡፡ ግዥ ስንል ታሳቢ ከምናደርጋቸው ጉዳዮች ጥራትና ዋጋ ቀዳሚ ናቸው፡፡

ሁለቱም ግን ለሁሉም ድርጅት እኩል ይሰራሉ ማለት አይደለም ለአንዱ ጥራት ነው፡፡ ለአንዱ ጥራት ለምሳሌ ጥራት የሚመዘነው እንደአስፈላጊነቱ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ያለው ነገር ለሌላው ጥራት ላይኖረው ተሳታፊዎችን ማስተናገድ ድርጅት የሁለት ቀን ስብሰባ ቢኖረው ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ እስከቻለ ድረስ የሸራ ድንኳን ጥራት አለው ብሎ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ሌላው ደግሞ ሰዎችን ለአንድ አመት ለማስልጠን ቢፈልግ ድንኳኑ

Scanned with CamScanner

እንደማይሆነው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ጥራትን ስንወስን ከምንፈልገው አገልግሎት ጋር ማነፃፀር አለብን፡፡ ለሁሉም ሰው ጥራት መመዘኛው አንድ አይነት ሊሆን አይችልም፡፡

ጥራትን ከምንፈልገው ውጤት ጋር አይተን መወሰን አለብን፡፡ ሁለተኛው ጥራትና የገንዘብ ፍላጎት የቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ አንድ ነገር ጥራቱ በጨመረ ቁጥር ዋጋው ከፍ ይላል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ጥራቱ እየቀነሰ የሚሄድ ከሆነ በዚያው ልክ ዋጋው ይቀንሳል፡፡ ማንኛውም ምርት የራሱ የሆነ የቆይታ ጊዜ አለው፡፡ ለምሳሌ አንድ መኪና ያገለግላል ተብሎ የሚታሰበው ለ5 ዓመት ነው ቤት ደግሞ ለ20 አመት ሊቆይ ይችላል፡፡ ስለሆነም ለ20 አመት ማገልገል የሚገባው ቤት 5 አመት በሚያገለግል ግብዓት መስራት ትልቅ የጥራት መጓደል ይፈጥራል፡፡ ግዥ ስንፈፅም ለምን እንደምንፈልገው በትክክል ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ ጥራቱን መመዘን ያለብን ከአገልግሎት አኳያ ነው፡፡ በሌላ በኩል ጥራትና የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን በተቃራኒ አቅጣጫ ያሉ ስለሆነ በጣም ጥራት ያላቸውን ነገሮች ስንፈልግ የገንዘቡ ግብዓት እንዳያሳስተን መጀመሪያ የጥራት ውድድሩን ከዋጋ ውድድሩ በፊት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እቃ የሚያቀርቡ ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን በሁለት መንገድ ማለትም ቴክኒካልና ፋይናንሻል ሰነድ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ ቴክኒካል ሰነዱ ስለሚፈለገው እቃ ጥራት በዝርዝር የሚያስረዳ ነው፡፡ ፋይናንሻል ሰነዱ የሚፈለገውን እቃ ዋጋውን የሚያመላክት ነው፡፡

በሌላ በኩል የምንገዛው ነገር እኛ የምንፈልገውን ነው ወይስ የእኛ ድርጅት የሚያስፈልገውን ነው የሚለው ጉዳይ በአግባቡ መታየት አለበት፡፡ በግለሰብም ሆነ በአገር ደረጃ የፋይናንስ ሀብት ውስን ነው፡፡ ውስን የሆነውን ሀብት ለሚያስፈልገን ነገር ብቻ ለመጠቀም እኛ የምንፈልገውን ሳይሆን ድርጅታችን የሚያስፈልገው ነው መግዛት

ያለበት፡፡ የአንድ ድርጅት ስራ አስኪያጅ የቅንጦት መኪና ሊፈልግ ይችላል፡፡ የድርጅቱ ፍላጎት ግን ምርቶቹን ማጓጓዝ የሚችል የጭነት ተሽከርካሪ ሊሆን ይችላል፡፡ የሚፈፀሙ ግዥዎች በሙሉ ውስን የሆነውን የፋይናንስ አቅም በአግባቡ በመጠቀም የግለሰቦችን ፍላጎት ሳይሆን ድርጅቶች የሚያስፈልጋቸው መሆን አለበት፡፡

ጥራት የአንድ ሰሞን ጉዳይ አይደለም፡፡ አንድ ድርጅት የሚያመርተውን ምርት ጥራ እቃ የሚያቀርቡለት ድርጅቶች ጥራት ያለው እቃ አቀረቡ የሚባለው ለአንድ ቀን ሲያቀርቡ ሳይሆን ዘላቂነት ሲኖራቸው ነው፡፡ ጥራት በአጋጣሚ የሚመጣ ሳይሆን የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶለት የሚፈፀም ነው፡፡ ስለሆነም የአቅራቢዎችን ጥራት ለማረጋገጥ ድርጅታዊ መዋቅራቸውን መፈተሽ ይገባል፡፡

የፋይናንሽያል ውጤታማነት መለኪያዎች!!

የአንድን ድርጅት ገንዘብ ነክ ውጤታማነት መለኪያዎችን በተመለከተ የአንድን ድርጅት ከሌሎች በበለጠ ሁኔታ እየሰራ መሆኑን ለማወቅ የሚያስችሉ መለኪያዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

➢ ያልተጣራ ትርፍ በመቶኛ፡- የድርጅቶች ከፍተኛ ሽያጭ ወደ ትርፍ ሲኬድ ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌሎች ድርጅቶች ደግሞ በተወሰነ ሽያጭ በጣም አትራፊ የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በ100,000,000 ሽያጭ 1,000,000 ብር ትርፍ እና 10,000,000 ሽያጭ 1,000,000 ቢያተርፍ የበለጠ ወጤታማ የሚባለው 10,000,000 ሽያጭ ያለው ድርጅት ነው፡፡ ነገርግን በተወሰነ ትርፍ ህዝብን ለማገልገል በተቋቋሙ ድርጅቶች ደግሞ የሽያጭ ብዛት እንደ ከፍተኛ ስኬት ሊቆጠር ይችላል፡፡

➢ የሽያጭ ወጭ በመቶኛ፡- ለማስታወቂያና ለሽያጭ ያወጣነው

Scanned with CamScanner

ወጪ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ 10,000,000 ለሽያጭ አውጥቶ 1,000,000 ብር ያተረፈ ድርጅትና 100,000 ብር ለሽያጭ አውጥቶ 500,000 ብር ያተረፈ ድርጅት ቢነፃፀር ዝቅተኛ የሽያጭ ወጭ አውጥቶ 500,000 ያተረፈው ድርጅት የበለጠ ውጤታማ ነው፡፡ ምክንያቱ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ በመስራት ነው 500,000 ብር ያተረፈው፡፡

➢ ገቢ ከአሳተፈው የሰው ኃይል አንፃር፡- አንድ ድርጅት በጣም ብዙ ገቢ ያስገኛል የሚባለው ገቢው ብቻ በራሱ ተመዝኖ ሳይሆን ካሳተፈው ሰራተኛ ትርፋማነት አንፃር መመዘን አለበት፡፡ ለምሳሌ 10,000,000 ብር ያተረፈ ድርጅት 100 የሰው ኃይል አሳትፎ ሲሆን ሌላው ድርጅት ደግሞ 5,000,000 ብር ያተረፈው 10 የሰው ኃይል አሳትፎ ከሆነ 10 ሰው የተጠቀመው ድርጅት ትርፋማ ነው፡፡ ምክንያቱም የተጠቀመው የሰው ኃይል ወጪ ቆጣቢ በመሆኑ ነው፡፡ ትርፋማነትና ብዙ ትርፍ ማትረፍ የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል፡፡ ትርፋማነት ማለት ከተጠቀምነው ሐብት አንፃር የሚታይ ነው፡፡ ምን ያህል ሐብት አባክነው አሁን የተገኘውን ትርፍ ያገኙት የሚለው ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ ሽያጭ በስኩዌር ሜትር የሚባል መተመኛ አለ፡፡ 10 ስኩዌር ሜትር በ10 ስኩዌር ሜትር የሆነ ሱቅ በአመት 100,000,000 ብር ቢሸጥና 50 በ 50 ስኩዌር ሜትር ስፋት ባለው ሱቅ ትንሽ ከፍ ያለ ትርፍ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ሁለቱም ሱቆች የሸጡትን ገንዘብ ለተጠቀሙት ስኩዌር ሜትር ሲካፈል የሚገኘው ውጤት ከተጠቀመው የቦታ ስፋት አንፃር ሲታይ ሰፊ መሬት የወሰደው ሱቅ ትንሽ ነው ያተረፈው፡፡ ስለሆነም ትርፋማነት ለስራው ከተጠቀምነው ግብዓት ጋር ካልተነፃፀረ በስተቀር የተገኘውን ትርፍ ብቻ ማየት የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ያደርሳል፡፡

➢ የተጠቀምነው ካፒታል አትራፊነት፡- ለምሳሌ 1,000,000 ብር ኢንቨስት ያደረገ ድርጅት በአመት 10,000,000 ብር ቢያተርፍ ሌላው

ድርጅት 100,000 ብር ኢንቨስት አድርጎ 5,000,000 ብር ሊያተርፍ ይችላል፡፡ ሁለቱን ድርጅቶች ካደረጉት ኢንቨስትመንት መጠን አንፃር በመቶኛ ስናወዳድራቸው 5,000,000 ያተረፈው ድርጅት የበለጠ ውጤታማ ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘባቸው ኢንቨስት የሚያደርጉ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች የተገኘውን የትርፍ ብዛት ሳይሆን የተገኘው ትርፍ በምን ያህል የኢንቨስትመንት መጠን ነው የሚለውን በጥልቀት ማጤን ይኖርባቸዋል፡፡

➢ የገንዘብ አቅምና እዳ፡- ማንኛውም ድርጅት የገንዘብ አቅም እንዳለው ሁሉ እዳም ይኖርበታል፡፡ ቢያንስ በሚቀጥለው አንድ አመት ውስጥ የሚከፈል እዳ ይኖራል፡፡ የድርጅቱ የመክፈል አቅም ሌላው የፋይናንሻል ውጤታማነት መለኪያ ነው፡፡ ድርጅቱ ያለው የገንዘብ አቅም ሁለት እጅ እንዲሁም ድርጅቱ ያለበት ብድር ካለው የገንዘብ አቅም አንፃር ሲታይ አንድ እጅ ከሆነ ድርጅቱ ውጤታማ ነው፡፡ ነገርግን ድርጅቱ ያለው የገንዘብ አቅም በአንድ አመት ውስጥ ከሚከፈለው እዳ ያነሰ ከሆነ ድርጅቱ አደጋ ውስጥ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የአንድ ድርጅት የጥሬ ገንዘብ አመንጭነትና ትርፋማነት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ አንዳንድ ድርጅቶች ትርፋማ ሆነው ጥሬ ገንዘብ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ትርፍ ለማትረፍ ዋናው መመዘኛ ስራ መስራት ነው፡፡ ስራ ሲሰራ ሽያጭ ይገኛል፡፡ ሽያጩ ሁሉ ግን ዛሬ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ለአንድ ኩባንያ ተቀጥሮ የሚሰራ የኮስትራክሽን ድርጅቶች እንደ የኮንስትራክሽን ድርጅት አለ እንበል፡፡ የሚሰሩ ቢሆንም የስሩበትን በአብዛኛው በትላልቅ ድርጅቶች ተቀጥረው ውጣ ውረድ ያጋጥማቸዋል፡፡ ክፍያ ለማግኘት ሰፊ ሊባል የሚችል በአንፃሩ ደግሞ ግብአት አቅራቢዎችም ሆነ ተቀጣሪ ሙያተኞች የክፍያ ጊዜ የሚሰጧቸው አይደሉም፡፡ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች አስተማማኝ የሆነ የገንዘብ አቅም ከሌላቸው ጊዜ የማይሰጡ ግብዓት አቅራቢ

ድርጅቶችና ሙያተኞች ችግር ይፈጥሩባቸዋል። አንድ ድርጅት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ሲታሰብ ምን ያክል የፋይናንስ አቅም ሊኖረው ይገባል የሚለው ጥያቄ ከድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ አንጻር መታየት አለበት። በሌላም በኩል ለግብዓት አቅራቢዎችና የሙያተኞች የአከፋፈል ሁኔታን በጥልቀት ማጥናት ያስፈልጋል። ማንኛውም ኢንቨስተር ሀብቱን ኢንቨስት ከማድረጉ በፊት ኢንቨስት ስለሚያደርግለት ድርጅት የሚከተሉትን የሒሳብ መዛግብት ማየት ይገባቸዋል።

1. የድርጅቱን የንብረት መጠን
2. የድርጅቱን የትርፍና የኪሳራ መጠን
3. የድርጅቱ የገንዘብ ፍሰት ምንጭ
4. የድርጅቱን የሰው ሃይል ስብጥር

ቀደም ባለው ጊዜ ኢንቨስተሮች በአንድ ድርጅት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ እንደ ዋነኛ መመዘኛ የሚያዩት የድርጅቱን አትራፊነት ነበር። ነገርግን ብዙ ድርጅቶች አትራፊ ሆነው በገንዘብ እጥረት ምክንያት ይዘጋሉ። ስለዚህ ኢንቨስት የሚያደርጉ ባለሀብቶች ከትርፍና ኪሳራ በተጨማሪ የድርጅቱን የገንዘብ ፍሰት ዋና መመዘኛ አድርገው ማየትም ይጠበቅባቸዋል።

ስለተጋባዥ ጸሀፊው

አቶ ሚሊዮን ክብረት የቢዲኦ ኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅና የንግድ አማካሪ

ቢዲኦ ኢትዮጵያ የቢዲኦ ኢንተርናሽናል አባል ድርጅት ሲሆን ቢዲኦ ኢንተርናሽናል የአለማችን 5ኛው ግዙፍ በፋይናንስ እና ተያያዥ ሙያዎች ዙሪያ የተሰማራ ደርጅት ነው።ቢዲኦ በ162 ሀገራት 1,500 ቢሮዎች እና 73,800 ሰራተኞች አሉት።

አቶ ሚሊዮን ክብረት የቢዲኦ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከመሆናቸው በፊት በኤክስት ኮንሰልት ኃ/የተ/የግል ማህበር በዋና ስራ አስኪያጅነት በኧርነስት ኤንድ ያንግ ኢትዮጵያ በፋይናንስ አማካሪነት እንዲሁም በሂሳብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን በኦዲተርነት አገልግለዋል።

አቶ ሚሊዮን ጃክ ዌልች ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ከተባለው በአሜሪካን ሀገር ከሚገኝ ተቋም በንግድ ስራ አመራር በማስተርስ ዲግሪ በከፍተኛ ማዕረግ ሲመረቁ የጃክ ዌልች ስኮላር የሚል ክብር አግኝተዋል።ይህ ተቋም ጄኔራል ኤሌክትሪክ የተባለው ግዙፍ የአሜሪካን ሀገር ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ የነበሩት ሚስተር ጃክ ዌልች ያካበቱትን የህይወትና የስራ ልምድ ለዘመኑ የንግድ መሪዎች ለማካፈል የመሰረቱት ተቋም ነው።ሚስተር ጃክ ዌልች ጄኔራል ኤሌክትሪክን የመሩበት ብቃት የክፍለ ዘመኑ የአሜሪካ ስራ አስፈጻሚ የሚል ክብር አስገኝቶላቸዋል።

Address:
BDO Consulting p.l.c
Bole subcity Wereda 03 Salfaz Building 5th Floor
P.o.box:- 14001 A.A Ethiopia
email:- ethiopic@bdo-ea.com
Website:- www.bdo.global

Scanned with CamScanner

የድርጅቶችን ትርፋማነት የሚያሳድጉ ልዩ ልዩ መንገዶች

‹‹ የምከተለው የትርፍ ቀመር ቀላል ነው፤ ማልዶ መነሳት፣ ለምሽት መስራትና ገንዘብ ባለበት ቦታ ሁሉ እየሄዱ መቆፈር ነው!›› ጂፒ ጌቲ

ትርፋማነትን ማሳደግ ማለት አንድ ድርጅት ከአጠቃላይ ወጭው በላይ አጠቃላይ ገቢው ሲበልጥ የሚፈጠር ነው። ምንም እንኳን አጠቃላይ የትርፍ እድገት አንዱ ወሳኝ ግብ ቢሆንም ከአጠቃላይ ሽያጭ ውስጥም ምን ያህል እንዳተረፍን የምንለካባቸው የወጭ ቆጣቢነት ውስጥም ምን ያህል እንዳተረፍን የምንለካባቸው የወጭ ቆጣቢነት

ጉዳይ የዚህ ዓመት ድርጅታዊ ትርፋማነቱ ሲሆን የባለቤቶችን እሴት ከማሳደግ አንፃር ደግሞ የዚህ ዓመት ትርፋማነቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ ወደፊትም እያተረፈ እንዲቀጥል የሚያስችሉትን ጉዳዮች የገነባ መሆኑም መፈተሽ ይኖርበታል፡፡

የአንድን ድርጅት ትርፋማነት በተሻለ ደረጃ ማሳደግ እንዴት ይቻላል?

የመጀመሪያው ትልቁ የትርፍ ምንጭ ተደርጎ የሚቆጠረው የምንሰማራበት የንግድ ዘርፍ አይነት ነው፡፡ አንዳንድ የንግድ ዘርፎች በባህሪያቸው ከፍተኛ ትርፍ ለማመንጨት አቅሙና ዕድሉ ያላቸው ሲሆን በሌላ አነጋገር እንደ ፈረንጅ ላም ብዙ የመታለብ አቅሙ ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ እንደ አበሻ ላም የሚሰጡት ዓመታዊ ትርፍ ውስን ነው፡፡ በመሆኑም ቢዝነስ ከመጀመራችን በፊት የንግድ ዘርፍ መረጣ ትኩረት ልናደርግበት የሚገባ አንዱ ጉዳይ ሲሆን ጥሩ የትርፍ ሳቢነት ያለው የንግድ ዘርፍ ቢሆንም እንኳን የድርጅቱ ጠንካራ ተወዳዳሪነት መታየት የሚኖርበት ሌላኛው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ድርጅት ከሌሎች የዘርፉ ተወዳዳሪዎች አንፃር የሚያመርታቸውና የሚሸጣቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ተወዳጅና ተመራጭ በሆኑ ቁጥር ድርጅቱ በብዛት መሸጥ ይችላል፡፡ የተወዳዳሪነት አቅሙ የላቀ ድርጅት የመሸጥ አቅሙ በእጅጉ የጐላ በመሆኑ ዓመታዊ ገቢው ያድጋል፡፡ ይህ የሚሆነው ድርጅቱ በሚፈጥረው ከፍተኛ የገበያ ሀይል ወይም ማርኬት ፓወር ነው፡፡

ይሁን እንጅ የገበያ ሀይል ፈጣሪነቱ ከፍተኛ የገበያ ድርሻ ብሎም ከፍተኛ ሽያጭ እንዲያስመዘግብ ቢያስችለውም ይህን ያህል ሽያጭ ለማስመዝገብ ያስቻለው ድርጅታዊ ጥቅል ትጋት ግን ወጭ የሚጠይቅ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የአንድ ድርጅት አመራር ዋና ዋና ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ትርፋማነትን በየጊዜው የላቀ ማድረግ ነው (*Profit maximization*)፤ ይሁን እንጅ አንዳንድ አመራሮች ከፍተኛ ገቢ ስለፈጠሩ ብቻ ስኬታማ የሚሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ ከፍተኛ ገቢ ማሳደግ የስኬታቸው ግማሽ መንገድ መሆኑን የሚገነዘቡት ግን ዘግይተው ነው፡፡ የሽያጭ ገቢያቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ ወጭ ማውጣታቸው ሳይታያቸው ይቀርና በዓመቱ መጨረሻ ትርፉ አነሶ ይታያል፡፡ የዚህ ጉዳይ አቢይ ምክንያት ድርጅታዊ ትጋቱ ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሽያጩን ማሳደግ ባለመቻሉ ነው፡፡ ለዚያም ነው በተለይ የድርጅቱን የትርፍና ኪሳራ እንዲሁም የሃብትና ዕዳ ሚዛን ሪፖርቶች በየሩብ ዓመቱ በማዘጋጀት የድርጅቱን የትርፍ ህዳጐች ማለትም ‹‹ግሮስ ማሪጂን፣ ኦፕሬቲንግ ማሪጂንና ኔት ፕሮፊት ማሪጂን›› በፐርሰንት ማስላት ያለብን፡፡ ሽያጩስ ተመነደገ ለመሆኑ ከእያንዳንዱ ሽያጭ ምን ያህል እያተረፍን ነው የሚለውን ለማለት እነዚህ መለኪያዎች ያግዛሉና ነው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም ወጭ ቆጣቢነት ማለትም ‹‹ኤፊሼንሲ›› ማሳደግ እንደተጠበቀ ሆኖ ካሉን ሀብቶች አንፃር ምን ያህል ሽያጭ እያሳደግን መሆኑን ምርታማነታችንን ጭምር ማየት ያስፈልጋል፡፡ የሽያጭ ገቢያችን ካሉን አጠቃላይ የሰራተኞች ብዛት አንፃር፣ የሽያጭ ገቢያችን ካሉን አጠቃላይ የሰው ሀይል ሰዓቶች (*Labor Hour*) አንፃር፣ የሽያጭ ገቢያችን ካሉን አጠቃላይ የማሽን ስራ ሰዓት (*Machine Hour*) አንፃር፣ የሽያጭ ገቢያችን ካለን አጠቃላይ ድርጅታዊ ሀብቶች (*Asset Turnover*) አንፃር እንዲሁም የሽያጭ ገቢያችን ካሉን ቋሚ ንብረቶች (*Fixed Asset Turnover*) አንፃር በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማስላት ያስፈልጋል፡፡ በየጊዜው ድርጅታዊ ትርፋማነትን እዚህ ጋር ልብ ማለት ያለብን ሌላ ቦታ ላይ ቢውሉ ኖሮ ሊያመጡት ማሳደግ ማለት ሀብቶቻችን

ከሚችሉት የትርፍ ጥቅም በላይ መሳካቱ ነውና። ትርፍን ማሳደግ ማለት በቢዝነስ ቋንቋ *(Above Average Profit)* ማለታችን ነው። ትርፍን ማሳደግ ማለት ካወጣነው ሃብት አንፃር ያገኘነውን የትርፍ ጥቅም በየጊዜው ማሳደግ *(Return on Investment)* ሆኖ ይህ ትርፍ ግን ሌላ ቦታ በካፒታሉ ኢንቬስት ብናደርግ ኖሮ ልናገኘው ከምንችለው ትርፍ ልቆ ከተገኘ ብቻ ነው። የኢንቬስትመንት ካፒታልን በየዓመቱ እየጨመሩ ትርፍን መጨመር ብቻ አይደለም ቁም ነገሩ፤ ያለውን ውስን ሃብት አብቃቅቶ በመጠቀም ትርፋማነትን ማሳደግ እንጅ። በመሆኑም ሽያጭን ማሳደግ አንዱ የትርፋማነት መዘውር ቢሆንም ወጭ ቆጣቢነትን እውን ማድረግ ደግሞ ሌላኛው የትርፋማነት ሞተር ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ የምርቶችን ስብጥር በውል መረዳትም ያስፈልጋል። የትኞቹ ምርቶችና አገልግሎቶች ከየትኞቹ ጋር ተጣምረው *(Product mix)* ወደ ገበያ ቢቀርቡ የተሻለ ሽያጭና ከወጪቸው አንፃር የተሻለ ገቢን ማምጣት እንደሚችሉ ማጤን ያስፈልጋል። ሁሉም ዓይነት ምርቶችና አገልግሎቶች እኩል የሽያጭ አቅም የላቸውም። አንዳንዶች የምርት ስብጥሮች ደግሞ የሽያጭና የጥቅም አመንጭነታቸው ደረጃ ውስን ነው። በመሆኑም የተሻለ ትርፋማ የሆኑ ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ›› የተባሉ ምርቶችን የበለጠ ለመሸጥ ማምረት፣ ‹‹ሐ›› እና ‹‹መ›› የተባሉትን ደግሞ የአቅርቦት መጠናቸውን መቀነስ፤ ‹‹ሠ›› እና ‹‹ረ›› የተባሉትን በመለየት ደግሞ ጭራሽ ከገበያ እንዲወጡ የምናደርጋቸው ምርቶች ሊኖሩ ይገባል። በዚህ ረገድ በፋይናንስ ማኔጅመንት ቁጥር 2 ላይ መፅሐፍ ውስጥ የተቀመጠውን የቢሲጂ ማትሪክስ በመጠቀም የምርት ስብጥሮችን ማየት ያስፈልጋል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ የአንድን ድርጅት ትርፋማነት ለማሳደግ ድርጅቱ ያለውን ቋሚ ሀብትም ሆነ ጥሬ ገንዘብ በሚገባ ሊጠቀምባቸውና ወደ

ትርፍ አመንጭነት ሊቀይራቸው ያስፈልጋል። የድርጅቱ የጥሬ የገንዘብ ካፒታል በተለያየ ምክንያት ሊታሰር ይችላል፤ ለምሳሌ ከፍተኛ የጥሬ ዕቃ ወይም ያለቀላቸው ምርቶች በመጋዘን አላግባብ በማብዛት ሊሆን ይችላል። በዚህ ረገድ ተመጣጣኝነቱን የጠበቀ ክምችት ላይ ማተኮር በክምችት ውስጥ የተያዘውን ካፒታል ነፃ በማድረግና ወደ ስራ በመቀየር ትርፋማነትን ማሳደግ ይቻላል። እንዲሁም ገንዘቦች ባልተከፈሉ ተሰብሳቢ ገቢዎች ውስጥ ሊታሰሩ ይችላሉ። እነዚህ ተሰብሳቢ ገቢዎች በዙ ቁጥር ድርጅቱ ገንዘቦቹን በወቅቱ ቢያገኛቸው ኖሮ ሊያመጣቸው የሚችሉትን ትርፎች እያሳጡት ነው። በመሆኑም የዱቤ ሽያጭ ገቢን በጥብቅ መመሪያ መከታተልና ማስከፈል ያስፈልጋል።

እንዲሁም ከእኛ ይልቅ ሌሎች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ቢሰሯቸው የተሻለ ወጭ መቆጠብ እንችላለን የምንላቸውን ስራዎች መወከል ሌላኛው የወጭ መቆጠቢያ መንገድ ነው። የቢዝነሱን አቢይ ስራ በድርጅታችን ውስጥ እንዲሰራ አድርገን ጥራታቸውን ጠብቀው በተሻለ ወጭ ለሚሰሩ ድርጅቶች ‹‹Outsource›› ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህም ባሻገር ወጭ የሚያበዙ ንብረቶችን በመቀነስ፣ በውስን ቢሮ፣ በውስን መሬት፣ በውስን የህንፃ መጠን ስራውን እንዴት መስራት እንደምንችል፤ ቴክኖሎጅን በመጠቀም ስራውን እንዴት ቀልጣፋና ምርታማ እንዲሁም ወጭ ቆጣቢ ማድረግ እንደምንችል ማጤን ያስፈልጋል። አላስፈላጊ ብክነቶችንም መቀነስ እንዲሁ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ በዶ/ር አቡሽ በተፃፈው ‹‹ ካይዘን›› መፅሀፍ ውስጥ ያለውን የካይዘን ፍልስፍናን በመተግበር ከብክነት ጋር የተያያዙ ብዙ ወጭዎችን ማዳን እንችላለን።

የአንድን ድርጅት ትርፋማነት ከማሳደግ አንፃር ሌላው ሊያግዝን የሚችለው የዋጋ ጭማሪ ማድረግ ነው። የመሸጫ ዋጋ በጨመርን ቁጥር ከአንድ ምርት ልናገኝ የምንችለውን የሽያጭ ትርፍ ማሳደግ

Scanned with CamScanner

ያስችለናል። ይሁን እንጅ በንግድ ዘርፉ ውስጥ ሌሎችም ተወዳዳሪዎች በጋራ ዋጋ ማሻሻያ ካላደረጉ ወይም ደግሞ ድርጅቱ በንግድ ዘርፉ ውስጥ ብቸኛ የአገልግሎቱ (የምርቱ) አቅራቢ (ሞኖፖሊ) ካልሆነ ዋጋ በራሱ ጊዜ መጨመሩ የሽያጭ መጠናችንን ሊቀንሰው ይችላል። በእርግጥ የምርት ወይም የአገልግሎት የፈጠራ ማሻሻያ በማድረግ ዋጋን ማሻሻል ይቻላል። እንዲሁም ደግሞ ደንበኛው ለትንሽ ዋጋ ጭማሪ የሽያጭ መጠኑን የሚቀንስብን ካልሆነ ዋጋ ማሻሻል ትርፋማነትን ያሻሽላል። ይሁን እንጅ የደንበኛው ዋጋ ስሱነት *(Price sensitivity)* ከፍተኛ ከሆነ እንዲሁም በንግድ ዘርፉ ውስጥ ዋጋ ሁነኛ መወዳዳሪያ ከሆነ የዋጋ ማሻሻያ ሲደረግ የሽያጭ መጠን ሊቀንስ ስለሚችል ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሣብዐ ትረካ TUBE

የወጭ አመራር ጥበብ

> "ገራቸው፤ዋጋ መክፈል እንደሆነ። ሁሉንም ደግመህ ንገራቸው። ማግኘትቸው፤ዋጋ መክፈል እንደሆነ። ሁሉንም ደግመህ ንገራቸው። በህይዎታችን የምናደርጋቸው ማናቸውም ውሳኔዎች ነጻ ሲደደሉም፤ ምንጊዜም ወጭ አላቸው።"
>
> ብራድ ሜልዘር (The Inner Circle)

«ወጭ ከሌለ ገቢ የለም» የሚባል አንድ አባባል አለ። ስራ ካልተሰራ ገቢ የለም፤ ስራ ለመስራት ደግሞ ወጭ ማውጣትን ይጠይቃል ነው ነገሩ። በተለይ በአሁኑ ውድድር ዘመን ውስጥ ስራን መስራት ብቻውን ገቢን አያመጣም። የተሰራው ስራ በአገልግሎት ወይም በምርት መልክ ተጠናቆ ገቢ ያመጣ ዘንድ የሽያጭ ስራን ይጠይቃል። ስለሆነም ለማምረት ብቻም ሳይሆን ለመሸጥም ታዲያ ወጭ ማውጣትን ይጠይቃል። ወጭ ቁጠባን ደግሞ ትርፍ መር የሆነ ምልከታ ባላቸው የግል ንግድ ድርጅቶች ላይ ብቻ ሳይሆን አትራፊ ባልሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጭምር የሚጋሩት መርህ ነው። ወጭ ቆጣቢነትንና ምርታማነትን የሚያሳድግ የአሰራር ስርዓትና ባህል ማስፈን በራሱ ገቢ ፈጣሪ ነው፤ የራስን ገንዘብ ከአላስፈላጊ ብክነት ይጠብቃልና። ለዚያም ነው ወጭን የመቆጠብና ምርታማነትን የማሳደግ አመራር ትርፋማነትን እንደማሳደግ የሚቆጠረው፤ *«cost minimization is profit maximization»* እንደሚባለው።

የግል ንግድ ድርጅቶችና ትርፋማነት

ለንግድ ወይም ለትርፍ የተቋቋመ ማንኛውም አምራች ድርጅት ወይም ያለቀላቸውን ምርቶች በማከፋፈልና በመሸጥ ላይ የተሰማራ ድርጅት በዋናነት ትርፋማነቱን በዘላቂነት ማረጋገጥ ግድ ይለዋል።

Scanned with CamScanner

ምክንያቱም አንድ የንግድ ድርጅት ትርፋማ መሆኑ የሚጠቅመው የድርጅቱን ሥራ ለማስፋፋትና ለማሳደግ በስሩ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ፤ እንደ ሀገርም በአገኘው የትርፍ መጠን ልክ ከአንድ ዜጋ የሚጠበቀውን ግብር ለመንግስት በመክፈል ለሀገር እድገት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ይረዳዋል። ለድርጅቱ ባለቤቶች ዓመታዊ ትርፍ ለማከፋፈልም ትርፋማነትን ማሳደግ አስፈላጊ ነው። ይህ ሲባል ግን የንግድ ድርጅቶች ማህበራዊ ሃላፊነትን እንደ አላማ ይዘው መንቀሳቀስ የለባቸውም ማለት አይደለም የህንንም ማህበራዊ ሃላፊነት ለመወጣት ትርፋማ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በተቃራኒው ደግሞ አንድ ድርጅት ትርፋማ ካልሆነ የሰራተኞቹ የሥራ ዋስትናና ተጠቃሚነት አደጋ ላይ ይወድቃል። መንግስትም ከድርጅቱ ማግኘት የሚገባውን የትርፍ ግብር መሰብሰብ አይችልም። ያማለት ደግሞ መንግስት ለማህበረሠቡ በሚሠጠው አገልግሎት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።በሀገርም እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ስለዚህ አንድ ድርጅት በአጠቃላይ ባለሀብቱን በዘላቂነት ተጠቃሚ ለማድረግ፤ ሠራተኛውም የሥራ ዋስትናው ተረጋግጦ በዘላቂነት ተጠቃሚ እንዲሆን መንግስትም ለማህበረሰቡ የሚሠጠውን ማንኛውም መንግስታዊ አገልግሎት ይሠጥ ዘንድ፤ድርጅቶችም ማህበራዊ ሀላፊነታቸውን ይወጡ ዘንድ የንግድ ድርጅቶች ትርፋማነታቸውን በዘላቂነት ማሳደግና ማረጋገጥ ዋና አላማቸው አድርገው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ትርፋማነትን ለማሳደግ ገቢን ማሳደግ ወይስ ወጭን መቀነስ

እንደሚታወቀው ትርፍ ማለት በገቢና በወጪ መካከል የሚኖር ልዩነት ነው። ስለዚህ ሁለቱም አስተሳሰቦች ትክክል የሚሆኑበትም የማይሆኑበትም ነበራዊ ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

ይህ ማለት አንድ ድርጅት በውስን ወጭዎች ብዙ ገቢ መሰብሰብ ከቻለ ትርፋማነቱን ማሳደግ ይችላል። በሌላ መንገድ ደግሞ በውስን ገቢ ላይ የሚወጣውን ወጭ መቀነስ ከቻለ አሁንም ትርፋማነቱን ማሳደግ ይችላል።ነገር ግን በሁለቱም በኩል ገቢን የማሳደግ ጥረቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በሌላኛው ጎንም ወጪን ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ከቀጠለ ትርፍን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ይጠቅማል። ለዚያም ነው ማንኛውም ድርጅት ትንሽም ይሁን ትልቅ፤አምራችም ይሁን አከፋፋይ ወይም አገልግሎት ሰጭ ሁሉም እኩል ስለገቢያቸው(ሽያጫቸው) እድገትም ሆነ ስለወጪቸው ተመጣጣኝነት ሊጨነቁ ይገባል የሚባለው።

ለመሆኑ ወጪ ማለት ምን ማለት ነው?

በንግድ ስራ ውስጥ ወጭ ማለት አንድን የምርት ሂደት ለማከናወን ሽያጭን ለመፈፀም ወይም አገልግሎት ለመስጠት መውጣት ያለበት ወይም የሚወጣን ገንዘብ ማለት ነው ። በንግድ ስራ ውስጥ አንድ ወጭ በምርቱ ወይም በአገልግሎቱ ላይ ተጨማሪ እሴት የሚሠጥ ከሆነ ብቻ እንደ አስፈላጊ የንግድ ወጪ ይቆጠራል እንዲህ አይነት ወጪዎች እሴት ጨማሪ ወጭ *(Value Added cost)* ተብለው ይጠራሉ። ምክንያቱም ምርቱን የሚገዛው (የሚጠቀመው) ወይም አገልግሎቱን የሚጠቀመው አካል ለእንደዚህ ያሉ ወጭዎች የመክፈል ፈቃደኝነት

Scanned with CamScanner

ስላለው ድርጅቱ መልሶ በገቢ መልክ ያገኛቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በተለምዶ አሰራር እየተሠራ ያለ ተግባር እሴትም ሳይጨምር ድርጅቶች ወጭ የሚያወጡበት አሰራር ይኖራል። ነገር ግን ይህ ወጭ ምንም አይነት እሴት የማይጨምር እስከሆነ ድረስ አላስፈላጊ ወጭ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ድርጅቶች ወጭዎቻቸው በትክክል ለሚያመርቱትና ለሚሸጡት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት እሴት ይጨምራል ወይስ አይጨምሩም የሚለውን ትንታኔ በአግባቡ በመገንዘብና በማጥናት እሴት የማይጨምሩ ወጪዎችን ወይም ተግባሮችን በመቀነስ አጠቃላይ የንግድ ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን ጥቅል ወጪ በመቀነስ ትርፋቸውን ማሳደግ እንደሚችሉ መረዳት ይኖርባቸዋል።

ወጭ እንደ ወጭ የሚቆጠረው እንዴት ነው?

አግባብ ባለው አለማቀፋዊ የሂሳብ አያያዝ መርህ መሠረት አንድ የንግድ ድርጅት ያወጣውን ገንዘብ እንደ ወጪ መመዝገብ ያለበት ወጪው በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ድርጅቱ ከሚሠራው የንግድ ሥራ ማለትም ከሚያመርተው ወይም ከሚሸጠው ምርት እንዲሁም ከሚሠጠው አገልግሎት ጋር ተዛምዶ ወይም ግንኙነት ሲኖረው ብቻ ነው።ይህም ማለት የተጠቀሰው የንግድ ስራ ለመስራት አስፈላጊ የሆነ ወጭ ሲሆን እና ይህም ወጪ ህጋዊ የሆነ ማስረጃ ሲኖረው ድርጅቱ ወጪው በወጣበት ቀንና የሒሳብ ዘመን ወይም የሒሳብ መግለጫው በሚዘጋጅበት ዘመን ውስጥ የወጣ ወጪ መሆኑ ተረጋግጦ ይመዘገባል።

ቋሚና ጊዚያዊ ወጭዎች!!

አንድ የንግድ ድርጅት ወጪ የሚያወጣው ገቢ ለማግኘት ሲባል ብቻ ነው። ስለዚህ ያ የወጣ ወጪ ለምን ያህል ጊዜ ገቢ ሊያስገኝ ይችላል ሲባል የተወሠነው ወጪ በዛ የሒሳብ ዘመን(አመት) ለሚገኘው ገቢ ብቻ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ሌሎች ወጪዎች ደግሞ ከአንድ የሒሳብ ዘመን (ዓመት) በላይ ለተከታታይ አመታት ለሚገኙት ገቢዎች እገዛ ወይም አስተዋጾ ሊያደርጉይችላሉ።

በንግድ አለም ውስጥ ወጪዎች በሁለት ይከፈላሉ፤እነርሱም ቋሚና ጊዜያዊ ወጪበመባል ይጠራሉ። ቋሚ ወጪ የሚባለው ወጪው አንድ የሒሳብ ዘመን በላይ ወይም ከአንድ አመት በላይ የአገልግሎት ዘመን ሲኖረው ወይም እንዲህ አይነት ወጪዎች ለረዥም አመታት ገቢን የማስገባት የሚያስችሉ ሲሆኑ ነው። ጊዚያዊ ወጪዎች ግን በአንድ የሒሳብ ዘመን (አመት) ውስጥ ለሚገኝ ገቢ ብቻ ለማስገኘት የሚወጡ ወጪዎች ናቸው።

ለምሳሌ እንውሰድ ለንግድ አገልግሎት የምንጠቀምበትን መኪና ብንወስድ እነዚህን ሁለት አይነት ወጪዎች መመልከት እንችላለን። መኪናው የተገዛበት ወጪና መኪናው አገልግሎት እንዲሠጥ ለነዳጅ፤ለሾፌር እንዲሁም ለቅባትና ዘይቶች የሚወጡ ወጪዎችን እንመልከት።

መኪናው ከአንድ የሒሳብ ዘመን(አመት) በላይ አግልግሎት ሲኖረውና በነዛ አመታት ለሚገኘው ገቢ አስተዋጾ ሲኖረው ለአስራ ሁለት ወር የከፈልነው ደመወዝ ፤የነዳጅ፤ የዘይትና ቅባት ወጪዎች ግን በዛ የሒሳብ ዘመን ለተገኘው ገቢ ብቻ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል። ስለዚህ ከአንድ የሂሳብ ዘመን(አመት) በላይ ለሚገኝ ገቢ አገልግሎት የሚሠጥ ወጪ ቋሚ ወጪ ተብሎ በሒሳብ መዝገብ ውስጥ በቋሚ ንብረት ሲመዘገብ ለአንድ የሒሳብ ዘመን(አመት) ውስጥ ለሚገኝ ገቢ ብቻ እገዛ የሚያደርግ ወጭ ደግሞ ጊዜያዊ ወጪ(የአጭር ጊዜ ወጪ) ተብሎ በሒሳብ መዝገብ ውስጥ እንደወጪ ይመዘገባል።

Scanned with CamScanner

የቋሚና ጊዜያዊ ወጭዎች ተመጣጣኝነት

ድርጅቶች እንደተሰማሩባቸው የንግድ ዘርፎች የተለያየ መጠን ያላቸው ቋሚና ጊዜያዊ ወጭዎች ይኖራቸዋል፡፡ለምሳሌ፡- አምራች ድርጅቶችን ብንወስድ ከፍተኛ የሆነ ቋሚ ወጪ የሚጠይቅ የንግድ መስክ ነው፡፡ በሌላ በኩል በምርት አከፋፋይነት ወይም በችርቻሮ የንግድ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ከፍተኛ የሆነ ጊዜያዊ ወጪዎች ሲኖሯቸው ቋሚ ወጪቸው ደግሞ በጣም አነስተኛ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በዋናነት የሚሰማሩበት የንግድ ዘርፍና የሚሠሩት የሥራ ዓይነት ነው እነዚህን ነገሮች የሚወስኗቸው፡፡

ነገር ግን እነዚህ የተለያዩ ድርጅቶች ባሏቸው የቋሚ ወጭዎችና ጊዜያዊ ወጭዎች ስብጥር መለያየት ሳቢያ በድርጅቶቹ ላይ በሚኖረው ስጋት *(Risk)* እና ትርፋማነት *(Return)* ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖን ያሳድራል፡፡

ለምሳሌ፡- ገበያው ወይም ኢኮኖሚው እጅግ በጣም ጠንካራ በሆነበት ወቅትና የድርጅቱ ሽያጭ በዛው ልክ በሚጨምርበትና በሚያድግበት ወቅት ብዙ ቋሚ ወጭና መጠነኛ ጊዜያዊ ወጪዎች(በተነፃፃሪነት ነው) ያሉት የንግድ ተቋም ትርፋማነቱ እጅግ በጣም ሲጨምር በተቃራኒው ደግሞ የምርቱ ገበያ (ፍላጎት) በጣም በሚቀንስበት ወቅት ድርጅቱ ለከፍተኛ ኪሳራ ያጋልጣል፡፡

ስለዚህ ቋሚ ወጭ ማብዛት ጥሩ አይደለም የሚለው መከራከሪያ ሁሌም ትክክል ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ጠቃሚ የሚሆንበት ወቅትም ስለሚኖር፡፡ ነገር ግን ብዙ ቋሚ ወጪዎች ያሉባቸው ተቋማት ከፍተኛ የስጋት ደረጃ *(Risk)* ሲኖራቸው በዛው ልክም ከፍተኛ የሆነ ትርፍ *(Return)* ሊያስገኝላቸው እንደሚችል ይታሰባል፡፡ ይህ ነው

እንግዲህ፤ የኪሳራ ዕድል ቢኖረንም ትርፋማነታችን ያመዝናል በሚል እንድንወስን የሚያደርገን ''*Risk – Return Tradeoff*'' እንደሚባለው፡፡

ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች

ቀጥተኛ ወጭ ማለት አንድን ምርት ለማምረት፣ለመሸጥ ወይም አገልግሎት ለመስጠት ሲባል የሚወጣን ወጭ ነው፡፡ ይህን መሰል ወጪ በቀላሉ ጊዜንና ጉልበትን በሚቆጥብ መንገድ ማወቅ፣መወሠን፣ማስላት የሚቻል የወጭ አይነት ሲሆን ቀጥተኛ ያልሆነ ወጭ የምንለው ደግሞ ወጭው ምርቱን ለማምረት ፤ ለመሸጥ ወይም አገልግሎት ለመስጠት የወጣ ሆኖ በቀላሉ ግን የምርቱን ወጭ ለመወሠንና ለማስላት የማይቻል የወጭ አይነት ነው፡፡ለምሳሌ አንድን ጠረጴዛ ለማምረት ምን ያክል ወጪ አወጣን ብለን ብንጠይቅ የብረቱን መጠንና ወጭ የጣውላውን መጠንና ወጭ በቀላሉ ማወቅና ማስላት ሲቻል፤ጠረንጴዛውን ለመስራት ያወጣናቸውን እንደ ቫርኒሽ ፤ ማጣበቂያ(ማስቲሽ) እና ለሀይል ፍጆታ የወጣውን ወጭ በቀላሉ ወጭንና ጊዜን በሚቆጥብ መንገድ ማስላት አይቻልም፡፡

ለዚያም ነው እንደዚህ ያሉ ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎች በአንድ ላይ ይጠራቀሙና መጨረሻ ላይ ለሁሉም ምርቶች ተካፍለው ነው እያንዳንዱ ምርት በነጠላ የወጭ ድርሻውን እንዲወስድ የሚደረገው፡፡

ወጭዎችን ቋሚና ጊዜያዊ ብሎ የመከፈል ፋይዳ

ወጪዎችን ቋሚና ጊዜያዊ ብሎ መከፋፈል ዋናው ጥቅም በየሒሳብ ዘመኑ ድርጅቱ ያገኘውን ትርፍና ኪሳራ በአግባቡ ለመወሰን ይረዳ ዘንድ ወጪው የየትኛውን የሂሳብ ዘመን ገቢ ለማመንጨት የወጣ ነው የሚለውን እንድንለይ ይረዳናል፡፡ ምክንያቱም አንድን ቋሚ ወጪ

Scanned with CamScanner

ከአንድ በላይ በሆነ የሒሳብ ዘመን ውስጥ ለሚገኝ ገቢ አስተዋጽኦ እያደረገ ወጪው በመጣበት የሂሳብ ዘመን ለተገኘው ገቢ ላይ ብቻ እንደጊዚያዊ ወጪ በመቁጠር ተቀናሽ ብናደርገው የየዘመኑን ትርፍና ኪሳራ በአግባቡ መለካት አያስችልም። ይሁን እንጂ በአለማቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የሒሳብ አያያዝ ስርዓት ወጪን በሁለት መንገድ ማለትም :-

1. ሁሉንም ወጭ እንደ ጊዚያዊ ወጭ/*Cash Basis of Accounting*//
2. ወጪዎችን በሁለት መንገድ በቋሚና ጊዚያዊ ተከፋፍለው የሚመዘገቡበት መንገድ *(Accrual basis of accounting)* እንዳለ ይገልጽና ገቢና ወጭን በአግባቡ ይዞ ትርፍና ኪሳራን ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለመለካትና ለማወቅ ሁለተኛው መንገድ ጠቃሚ እንደሆነ ይመከራል።

በጥቅሉ ስንመለከተው አንድን ምርት ለማምረት የወጣን ወጭ በዚህ መልኩ መከፋፈል ያስፈለገበት ምክንያት ሁሉም የወጭ አይነቶች በቀላሉና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ስለሚያግዝ ነው። ለአንድ አይነት ምርት ለምሳሌ አንድ ጠርሙስ ለስላሳን ለማምረት ምን ያህል ወጪ ይጠይቃል የሚለውን ለመለካት ስለማይቻል መጀመሪያ በቀላሉና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መለካት የሚቻለውን ማለትም ቀጥተኛ ወጪ የሚባለውን ካሠላን በኋላ ቀጥተኛ ያልሆኑወጭዎችን ደግሞ በአንድ የሒሳብ ቋት በማጠራቀም መጨረሻ ላይ በዘመኑ ለተመረቱት ሁሉም የለስላሳ መጠጥ ጠርሙሶች በማካፈል ለአንዱ ጠርሙስ ምን ያህል ወጪ እንደወጣ ወይም እንደሚወጣ ይሠላል ማለት ነው። ስለዚህ በተግባር በቀላሉና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለአንድ የምርት/አገልግሎት አይነት ምን ያክል ወጪ ያስፈልጋል የሚለውን መወሰን ስለሚያስቸግር በቀላሉና ወጪን በሚቆጥብ መንገድ መለካት የሚቻለውን ወጭ «ቀጥተኛ»ስንለው ከዚህ በተቃራኒው ያለው

የወጭ አይነት ደግሞ «ቀጥተኛ ያልሆነ ወጭ» ተብሎ ይመደባል።

ወጭ ቆጣቢ ስርአትን ማስፈን ያለው ፋይዳ

ወጭን መቆጠብ ትርፋማነትን ብቻ ሳይሆን በዋጋም ተወዳዳሪ ያደርጋል። ወጭን መቀነስ ተወዳዳሪ የሚያደርገው እንዴት ነው? ስንል ንግድ የማከናወኛውን ወጭ መቀነስ ማለት ተጨማሪ እሴት በማይፈጥሩ ተግባራት ምክንያት ይወጣ የነበረን ወጭ መቀነስ ማለታችን ነው። ይህን መሰል አሠራር ደግሞ ትርፋማነትን ከማሳድጉም በተጨማሪ ድርጅቶች በዋጋና በጥራት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ይህም ማለት አንድ ድርጅት እሴት የማይጨምሩ ተግባራትን በማስቀረት የንግድ ስራ ማከናወኛ ወጭውን ቀነሰ ማለት ምርቱን አምርቶ ወይም አገልግሎቱን ለተጠቃሚ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ወጭ ቀነሰ ማለት ነው። ስለዚህ ከሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶች አንፃር ምርቱን አምርቶ ለተጠቃሚው ለማቅረብ የሚያስፈልገው ወጭ ዝቅተኛ ሆነ ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ከተወዳዳሪዎቹ አንፃር በዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ለተጠቃሚው ማቅረብ በመቻሉ ተወዳዳሪ እንዲሆንና የገበያ ድርሻውንም እንዲያሳድግ ያግዘዋል። ይህ በዚህ መልክ የገበያ ድርሻውን አሳደገ ማለት ገቢውን አሳደገ ማለት ነው። ገቢ ሲጨምር ደግሞ ድርጅቱን የበለጠ ትርፋማ እንዲሆን ያደርገዋል ማለት ነው።

ወጭዎችን መቀነስ የሚቻለው እንዴት ነው?

እዚህ ጋር ታዲያ ወጭዎችን መቀነስ የሚቻለው በዋነኛነት ስራን ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለማከናወን አሰራርን በመፈተሽና ስራን ወጪ ቆጣቢ በሆነ አሰራር መልሶ በማደራጀት ነው። በዚህ ስራን ወጪ ቆጣቢ በሆነ አሰራር መልሶ በማደራጀት ነው። በዚህ ሂደት በድርጅታችን ውስጥ እያከናወናት ያለችው እያንዳንዷ ተግባር

Scanned with CamScanner

በምናመርተው/በምንሸጠው ምርት ወይም በምንሰጠው አገልግሎት ላይ የሚኖራትን ጥቅም በደንብ ማጥናት ይኖርብናል። በዚህ መልኩ ስንፈትሽ አንዳንዱ ተግባር እሴት የሚጨምር (Value Adding) ሆኖ ሲገኝ ሌሎች ተግባራት ደግሞ እሴት የማይጨምሩ ሆነው ልናገኛቸው እንችላለን። ድርጅቶች ወጭ የሚያወጡት ለሚያከናውኗቸው ተግባራት ሲሆን ተግባሩ እሴት የማይጨምር ሆኖ ሲገኝ ከዛ ተግባር ጋር ተያያዥነት ያለው ወጭ እሴት የማይጨምር *(Non-Value adding Cost)* ስለሆነ ይህንን ተግባር ባለማከናወን ወጭን መቀነስ ይቻላል ማለት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ያለውን ሀብት (የሠው ሃይልም ሆነ ንብረት) በአግባቡ መጠቀም አጠቃላይ የንግድ ስራውን ለማከናወን የወጣውን ወጭ ዝቅተኛ ያደርገዋል። ይህም የቀነሰ ጥቅል ወጪ ለእያንዳንዷ ምርት ሲካፈል ለእያንዳንዷ ምርት ወጭው ዝቅተኛ እንዲሆን ስለሚያደርገው ድርጅቶች አትራፊና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

ቋሚ ወጭዎችን ከመቀነስ አንፃር

ቋሚ ወጭ ለምንላቸው ከአንድ የሒሳብ ዘመን በላይ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ላይ የምናወጣው ገንዘብ ሲሆን ይሆን ወጭ መቀነስ የሚቻለው በሁለት መንገድ ነው።

አንደኛው ለስራው አስፈላጊ የሆኑትን ንብረቶች ብቻ በመግዛትና በመጠቀም ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ እነዚህን አስፈላጊ ናቸው ተብለው የተገዙትንም ቋሚ ንብረቶች በአግባቡ በሙሉ አቅማቸው መጠቀም ስንችልና ጊዜያችንን ስናሳድግ አጠቃላይ ውጤታማ *(Efficient)* ስለሚያደርጉን ወጪችን ከእያንዳንዱ ምርት ወይም አገልግሎት አንፃር

ሲለካ ዝቅተኛ እንዲሆን ያስችለናል።

እንደ ንግድ አማካሪነቴ፤እንደ መምህርና ተመራማሪነቴ ከወጭ ቆጠባ አፈፃፀም አንፃር በአገራችን የንግድ ማህበረሰብ ዘንድ የታዘብኩት ጉዳይ ቢኖር በአገራችን ያሉ ነጋዴዎች ብዙውን ጊዜ ወጭ ቆጣቢ የሆነ አሰራር ተግባራዊ ሲያደርጉ አለመታየታቸው ነው። ብዙ ትኩረታቸው ገቢ ማሳደግ ላይ ያመዘነ ነው። በእርግጥ ገቢ ማሳደጋቸው የሚበረታታ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ገቢ አደገ ማለት በንግድ ስራ ውስጥ ትልቅ ትኩረት የሚያደርጉበትን ትርፍ ሁልጊዜ ያመጣል ማለት አይደለም። ገቢ አደገ ማለት ትርፍ አደገ ማለት አይደለም።እዚህ ጋር ልብ ማለት ይኖርባቸዋል።

የንግዱ ማህበረሰብ ወጭ ቆጣቢ አሰራርን ከመዘርጋት አንፃር

የንግድ ስራ በውስጡ በተለያዩ ክንውኖች የተሞላ ነው። እያንዳንዷ ክንውን ደግሞ የራሷ ወጭ አላት። ካለወጭ የሚተገበር ክንውን የለም። ሁሉም ክንዋኔ ደግሞ ለደንበኛው እኩል ፋይዳን አያበረክትም፤ ወይም እሴት አይጨምርም። በመሆኑም ወጭን ለመቀነስ በአግባቡ ለማምረት መጀመሪያ ድርጅቶች ለሚያመርቱት ምርት ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት እያከናወኗቸው ያሉትን ሁሉንም ተግባራት በደንብ ዘርዝረው ካወቁ በኋላ የትኛው ተግባር እሴት ጨማሪ እንደሆነ፤የትኛው ደግሞ እንዳልሆነ ከመለየት መጀመርና ማወቅ ይኖርባቸዋል። በመቀጠልም ይህን ካደረጉ በኋላ አሰራራቸውን ውጤታማና ወጭ ቆጣቢ ለማድረግ እሴት የማይጨምሩትን ተግባራት በማስወገድ የአሰራር ሂደታቸውን ውጤታማና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መልሰው ማደራጀት ይኖርባቸዋል። እሴት የሚጨምሩትንም

ክንውኖች አንድ ላይ ብንሰራቸው፣ ድግግሞሾችን ብናስወግዳቸው ወጭ የምንቀንስ መሆናችንን ማጤን፣ የትኞቹ ክንውኖች ከእኛ ይልቅ ለሌላ ሶስተኛ አካል ብናሰራቸው ወጭ እንደምንቆጥብ ፣ ምን የተለየ ቴክኖሎጂ ብንጠቀም ወጭ እንደምንቆጥብ ፣ የትኞቹን ክንውኖች በብዛት ብንሰራቸው ወጭ እንደምንቆጥብ (ለምሳሌ በብዛት ማምረት ወይም መግዛት ወይም ማጓጓዝ)፣ ወጭ ለመቀነስ ምን ዓይነት አገርና ሰፈር ልንጠቀም እንደምንችል ፣ ከጊዜ አንፃር ምን ዓይነት ክንውን መቼ ብንፈፅመው ፣ የትኛው ክንውን ሌላ ቦታ ከሚሰራ እኛ ጋር ቢሰራ ወጭ ሊቆጥብ እንደምንችል በመለየት፣ የወጭ ቁጠባ ስርአትና መመሪያ በመዘርጋት፣ ወጭ ቁጠባን ተግባራዊ የሚያደርግ የአስተሳሰብ ትኩረትና ባህል ማስፈን እንችላለን፡፡ በዚህ መንገድ ታዲያ ምርታማነታችንን፣ ተወዳዳሪነታችንንና ትርፋማነታችንን በዘላቂነት ማስጠበቅ እንችላለን፡፡ በእርግጥ ይህንን መሰል ወጭ ቆጣቢ ስርዓት *(efficient system)* ተግባራዊ ለማድረግ ስልጠናንና የባለሙያ እገዛን የሚሻ ቢሆንም ይህ መርህ ለአትራፊም ሆነ አትራፊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚሰራ መሆኑን ልብ ማለት ግን ያስፈልጋል እላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ስለ ባለሙያው ፕሮፋይል

ረዳት ፕሮፌሰር ዶ/ር ሰውአለ አባተ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ በአካውንቲንግና ፋይናንስ ዘርፍ መምህርና ተመራማሪ ፤ ከአሁን ቀደም በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግና ፋይናንስ ዲፓርትመንት በመምህርነትና በተመራማሪነት እንዲሁም በትምህርት ክፍል ኃላፊነት በምክትል አካዳሚክ ዲንነት በዩኒቨርሲቲው የኦዲት አገልግሎት ጽ/ቤት ኃላፊነትና በኮሌጁ የድህረ ምረቃ ምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት አስተባባሪነት ያገለገሉ ሲሆን በልዩ ልዩ የግል ድርጅቶች በአካውንቲንግና ፋይናንስ የማማከርንና የስልጠና አገልግሎትን እንዲሁም አጠቃላይ ድርጅታዊ ሲስተም ዝርጋታ ፣ በሪል እስቴት ዘርፍ ለበላይ አመራሮች ልዩ የፋይናንስና አካውንቲንግ አማካሪ በመሆን የረጅም ጊዜ ልምድ ያላቸው ናቸው

_ኢሜይል፣ sewale1000@gmail.com

Scanned with CamScanner

የአካውንቲንግና የፋይናንስ ልዩ ልዩ ቃላቶችና ትርጉማቸው

‹‹ባዶ ኪስ ማንንም ወደኋላ አስቀርቶ አያውቅም:: ባዶ ጭንቅላትና ባዶ ልብ እንጂ!!›› ኖርማን ቪንሴንት ፒል

በፋይናንስ ማኔጅመንት ሂደት ውስጥ የንግድ ማህበረሰቡና ሌሎች በፋይናንስ ዙሪያ ላይ ተመድበው የሚሠሩ ግለሰቦች በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ልዩ ትርጉም ያላቸውን ቃላቶች ከእነ ትርጉማቸው ሊረዷቸው ይገባል:: ይህም መሆን ያለበት በተለይ በተለያዩ ቢዝነስ ነክ ስብሰባዎችና ውይይቶች ውስጥ የሚነሱ የፋይናንስ ቃላቶችን በቀላሉ ለመረዳትና ለመግባባት የሚያግዛቸው በመሆኑ ነው:: ነጋዴዎች ከሌሎች ነጋዴዎች ጋር ፣ ከኢንቬስተሮች ጋር፣ ከንግድ አጋሮች ጋር ፣ ከባንክ ሰዎች ጋር፣ከግብር ሰብሳቢ ባለሙያዎች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ አብረው በመስራት ውስጥም ሆነ በውይይት ወቅት ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ይነሳሉ:: በመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ቢሆኑ ካሉዋቸው የድርጅት የሂሳብና ፋይናንስ ባለሙያዎች ባሻገር ከአበዳሪዎችና ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ይወያያሉ:: በውይይቱ መሃከልም የሚከተሉት የአካውንቲንግና የፋይናንስ ቃላቶች ይነሳሉ::

በመሆኑም በቃላቶቹ ለመግባባትም ሆነ ቃላቶቹ በድርጅትዎ ላይ የሚያሳድሯቸው አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖዎች ለመረዳት የሚከተሉት ልዩ ትርጉም ያላቸውን የፋይናንስ ቃላቶች ማለትም *‹‹Financial Terminologies››* ከመፅሐፉ ዝርዝር እውቀት ጋር በሚናበቡ መልኩ እንዲቀርቡ ተደርገዋል:: የእንግሊዝኛን ቋንቋ በሚገባ ለማወቅ ለዋለዋዊ አጠቃቀሙን መረዳት ብቻ ሳይሆን የቃላት ሃብታም መሆን እንደሚያስፈልግ ሁሉ የፋይናንስ ዘርፉንም የበለጠ ለማወቅ የእውቀት አጠቃቀሙን ብቻ ሳይሆን የፋይናንስ ቃላት ክምችት መኖር በጣም አስፈላጊ ነው:: ደጋግመው በማንበብም ቃላቶቹን ይሸምድዷቸው፤ ከመፅሐፉ ጋርም በማስተማር ይረዷቸው::

1. **አሴት *(Asset)*:-** ይህ ማለት «ሃብት» ወይም «ንብረት» ማለት ሲሆን አንድ ቢዝነስ ያሉትን ሃብትና የሃብት አይነቶች የሚያመላክት ነው:: የአንድ ድርጅት ሃብት ጊዜያዊና ቋሚ በመባል በሁለት መልኩ ተከፍለው የሚታወቁ ናቸው:: የድርጅቱን ጥሬ ገንዘብ፣ የጥሬ እቃ ወይም ያለቀላቸው ምርቶች ክምችት ፣ እንጨት ነክ የቢሮ ዕቃዎች (ፈርኒቸር) ፣ የንግድ ምልክት ፣ የቅጅን የፈጠራ መብቶች ፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ቋሚ ንብረቶችን ያካትታል:: እነዚህ ሁሉ በድርጅቱ የሃብትና እዳ ሚዛን መግለጫ *(Balance Sheet)* ላይ የሚመዘገቡ ሲሆን ለድርጅቱ አጠቃላይ የዋጋ ተመን (ቢዝነስ ቫልዩ) መጨመርና ማነስ ሚና ይጫወታሉ:: የድርጅቱ ሃብቶች *(Assets)* ለድርጅቱ ሥራ መቀላጠፍ አይነተኛ ሚና ያላቸው ሲሆኑ ድርጅቱ ችግር ውስጥ በሚገባ ጊዜም ተሸጠው ወደገንዘብ የሚለወጡ ናቸው:: በአጠቃላይም አሴት (ድርጅታዊ ሃብት ወይም ንብረት) የምንላቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለድርጅቱ ገቢ የሚያመጡትን ነው::

2. **ሊያቢሊቲ *(Liability)*:-** ‹‹ሊያቢሊቲ›› የምንላቸው ድርጅቱ ለሌሎች አካላት (የዕዳው ባለቤቶች) ተከፋይ የሚሆኑ ልዩ ልዩ እዳዎችን የሚያመላክት ነው:: አንድ ድርጅት ገና «ሀ» ብሎ ንግድ ሲጀምር፣ በስራ ላይ እያለ፣ ስራዎቹን ሲያስፋፋ ፣ እንዲሁም ሥራዎቹን ሲያስቀጥል ልዩ ልዩ እዳዎች ይኖሩበታል:: ከባንኮች ብድር ሲወስድ፣ በብድር መልክ ቦንድ ሲሸጥ፣ በዱቤ መልክ ከጥሬ እቃ አቅራቢዎች ሲገዛ፣ በብድር መልክ ከአምራቾች ያለቀላቸው ሸቀጦችን (ምርቶችን) ሲገዛ ፣ አገልግሎት በዱቤ ሲገዛ ፣ እንዲሁም እቁብ ሲገዛ ይችላል:: ጊዜያዊ ተከፋይ እዳዎች ወይም የረጅም ጊዜ «ሊያቢሊቲ» የምንላቸው

ተከፋይ እዳዎች በመባል ለሁለት ይከፈላሉ። «የአጭር ጊዜ ተከፋይ እዳዎች» የምንላቸው ብዙ ጊዜ ከአትራቢዎች በዱቤ የተገዙትን ሲሆን በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መከፈል ያለባቸውን የሚያመለክት ሲሆን «የረጅም ጊዜ እዳዎች» የሚባሉት ደግሞ ከአንድ አመት በላይ በሆነ ጊዜ ውስጥ የሚከፍሉትን ሲሆን ብዙ ጊዜም የባንክ ብድሮችን ያመላክታል።

3. ኤክስፔንስ ***(Expense)***፡- ይህ ማለት አንድ ድርጅት ሥራውን ለማከናወን በየወሩ የግድ ወጭ የሚያደርጋቸውን ወጭዎች ነው። አንዳንዴም ‹‹ኮስት *(Cost)* ›› በመባልም ይጠራሉ። አንድ ድርጅት እንደስራው መጠን ማነስና መብዛት ተቀያያሪ ወጭዎች ያሉበት ሲሆን የሥራው መጠን ይነስም ይብዛም በየወሩ የማይቀሩ ቋሚ የሚባሉ ወጭዎችም ይኖሩታል። ለምሳሌ ኪራይ (የቤት ፣ የቢሮ) ፣ የፍጆታ ወጭዎች፣ የሠራተኛ ደመወዝ ፣ የሽያጭና ማስታወቂያ እንዲሁም የግብር ፣ የወለድ ፣ የሊዝ ወጭዎች) ይኖሩበታል። አንድ ድርጅት በተቻለ መጠን የሥራውን ጥራትና ምርታማነት ባስጠበቀ መልኩ ወጭዎችን በተቻለ መጠን ዝቅተኛ እንዲሆኑ በማድረግ እንዲሰራ ይመከራል። በዚህ መፅሐፍ በወጭ አመራር የተረበውን ትንታኔ ማየት ይቻላል።

4. ካሽ ፍሎው ***(Cash Flow)***፡- ይህ የአንድን ድርጅት ወርሃዊ ወይም አመታዊ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት ወይም ዝውውር የሚያመላክት ነው። ይህንንም የጥሬ ገንዘብ ዝውውርም በድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ ሪፖርት መልክ የሚያቀርብ ሲሆን አላማው የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ አቅምና ብቃት ምን ላይ እንደሆነ በማመላከት ነው። በባንክ አካውንቱ ላይ ያለው የጥሬ ገንዘብ መጠን የድርጅቱን ሥራዎች ሳይቸገር በመክፈል የማስኬድ ጥንካሬውን ያሳያል። የድርጅቱን የጥሬ ገንዘብ ሚዛን ሪፖርቱ በቀረበበት ጊዜ ያለውን ***(Ending Cash Balance)*** እና ከበፊተኛው የጥሬ ገንዘብ ሪፖርት ***(Beginning cash Balance)*** ጋር

በማስተያየት የድርጅቱ የጥሬ ገንዘብ ምጣኔ እያደገ ወይም ዕየቀነሰ መምጣቱን ማነፃፀር ያስችለዋል።

5. ቦተም ላይን (Bottom line)፡- ይህ ማለት አንድ ድርጅት በየወሩ ወይም በየአመቱ መጨረሻ ላይ ከቢዝነሱ የተገኘውን ገቢና ለቢዝነሱ የወጣውን ወጭ በማቀናነስ በድርጅቱ የሒሳብ መዝገብ (ሌጀር) ላይ በመጨረሻ ድርጅቱ ያገኘውን የተጣራ ትርፍ ወይም የተጣራ ጉድለት የሚያመላክት ነው። የድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርትም ከግብር በኋላ ያለው የተጣራ ትርፍ (ጉድለት) ማለትም ነው። ቃሉ የአንድን ድርጅት የተጣራ ትርፍ አፈፃፀም ከባለፈው አመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር በማነፃፀር መቀነሱን (መጨመሩን) የምናውቅበትም ነው።

6. ፋይናንሻል ሪፖርት (Financial Report)፡- ይህ የአንድን ድርጅት አጠቃላይ የቢዝነስ እንቅስቃሴ ከገንዘብ አፈፃፀሙ አንፃር የሚገልፅና የሚያመላክት የሒሳብ መግለጫ ነው። የሒሳብ መግለጫ ሪፖርት ለድርጅቱ የውስጥ አመራር አካላት (ለተለያዩ ውሳኔዎቻቸው) እንዲሁም ለሚመለከታቸው ውጫዊ አካላት (ባንክና ኢንቬስተሮች) ተዘጋጅቶ ሊቀርብ የሚችል ነው። የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ፣ የሒሳብና እዳ መግለጫና የጥሬ ገንዘብ ዝውውር መግለጫ ዋና ዋናዎቹ የፋይናንሻል ሪፖርቶች ናቸው።

7. ፋይናንሻል ስቴትመንት (Financial Statement)፡- ልክ እንደ ፋይናንሻል ሪፖርት ሁሉ ይህም የአንድን ቢዝነስ ልዩ ልዩ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ክንውኖችን የሚያሳይ መግለጫ ነው።

8. ካሽ ፍሎው ስቴትመንት (Cash Flow Statement)፡- ይህ መግለጫ ደግሞ የሚያሳየው በሆነ የጊዜ ሡሌዳ ውስጥ ወደ አንድ ድርጅት የገባን የገንዘብ መጠንና አይነት እንዲሁም ከድርጅቱ ወጭ

የተደረጉ የገንዘብ መጠኖችንና አይነቶችን ነው። በአጠቃላይም አራት አይነት ክፍሎችን ይይዛል፤ እነዚህም ከቢዝነስ አሬዓሀም ጋር የተያያዙ ገንዘብ ነክ ክንውኖች፤ ከኢንቬስትመንት ጋር የተያያዙ ገንዘብ ነክ ክንውኖች፤ ከፈንድ አሰባሰብ ጋር የተያያዙ የገንዘብ ነክ ክንውኖችና ተጨማሪ አጋዥ ማብራሪያዎችን ነው።

9. ኢንካም ስቴትመንት (Income Statement)፡- ይህ አንዱ የፋይናንስ እንቅስቃሴ መግለጫ ሲሆን በሌላኛው መጠሪያው «የትርፍና ኪሳራ መግለጫ» (Profit & Loss Statement) በመባል ይጠራል። ይህ መግለጫ የአንድን ድርጅት ገቢዎችና ወጭዎች በማሳየት በመጨረሻም የድርጅቱ አፈፃፀም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ከወጭው በላይ የሆነ ገቢን በትርፍ መልክ ወይም ከወጭው በታች የሆነ ትርፍን በኪሳራ መልክ የሚያሳይ ነው።

10. ካፒታል (Capital)፡- ይህ ማለት በቢዝነስ አጠራር አንድ ድርጅት በሀገኙ፤ በልዩ ልዩ ሃብቶቹና በኢንቬስትመንቶች መልክ ያሉትን አጠቃላይ የገንዘብ ተመን የሚያመለክት ነው። አንድ ድርጅት ከሁለት ዋና ዋና ምንጮች አጠቃላይ የካፒታል መጠኑን የሚያደራጅ ሲሆን እነዚህም ከባለቤቶች (ባለሃብቶች) የሚዋጣ ካፒታል ማለትም «Equity» እና ከአበዳሪዎች ከሚገኝ ካፒታል ማለትም «Debt» ነው።

11. አካውንት ሪሲቨብል (Accounts Receivable)፡- ይህ ማለት አንድ ቢዝነስ ለደንበኞቹ በዱቤ መልክ ሸጦ ያልሰበሰበው ነገር ግን «ተሰብሳቢ» ተብሎ የሚያዝ ገቢው ማለት ነው። ይህም ብዙ ጊዜ ለባለእዳው ደንበኛ በክፍያ መጠየቂያ ደብዳቤ መልክ (ኢንቮይስ) ግን ክፍዩ ድርጅት በሆነ አግባብነት የሚያስጠይቀው ይሆናል። ምንም ላይ እንደገቢ የሚቆጠር ሲሆን በድርጅቱ የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት

(Balance Sheet) ላይ ደግሞ በድርጅቱ «ሃብት» (Asset) ስር ሪፖርት የሚመዘገብ ነው።

12. ዲፕሪሲሽን (Depreciation)፡- አንድ ቢዝነስ ለስራው መቀሳጠፍ ቋሚ ንብረቶችን ይገዛል። እነዚህ ሃብቶች ደግሞ በጊዜ ሂደት ዋጋቸው እየቀነሰ ይሄዳል ተብሎ ይታሰባል። ድርጅቱ ንብረቶቹን ሲገዛ የገዛበትን ዋጋ እንደ ኢንቬስትመንት በመቁጠር በድርጅቱ የሃብትና እዳ መግለጫ (Balance sheet) ላይ በሃብትነት (Asset) የሚመዘገቡ ሲሆን የንብረቶቹ የወጭ መጠን ግን በእርጅና ተቀናሽ መልክ በየአመቱ ታሳቢ እየተደረገ በድርጅቱ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ ዲፕሪሲሽን (የእርጅና ተቀናሽ) በሚል ስያሜ ይሰፍራል። ይህም ድርጅቱን ከሚከፍለው ግብር ላይ እንዲቀነስለት ይረዳዋል።

13. አካውንት ፔዩብል (Account Payable)፡- ይህም ማለት አንድ ቢዝነስ በዱቤ መልክ ከአቅራቢዎች የገዛቸውን ወይም ከአበዳሪዎች በብድር መልክ ያመጣቸውን ተከፋይ እዳዎች የሚያሳይ የገንዘብ ተመን ነው። በዚህ ስያሜ የሚታወቁት የድርጅቱ ተከፋይ እዳዎች የሚመዘገቡት በድርጅቱ የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት ውስጥ «ሊያቢሊቲ» (የድርጅቱ እዳ) በሚል ስር ነው።

14. አክሯል (Accrual)፡- በድርጅቱ የተከማቹ ውዝፍ እዳዎችን በተለይም ያልተከፈሉ ውዝፍ ደመወዝና ልዩ ልዩ ግብሮችን የሚያመለክት ነው።

15. ዎርኪንግ ካፒታል (Working Capital)፡- ይህ ማለት አንድ ድርጅት እለታዊ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉት የጥሬ ገንዘብም ሆነ በቀላሉ ወደጥሬ ገንዘብ ሊቀየሩ የሚችሉ ሃብቶቹን ነው። ይህ ስም ያስፈለገው ከድርጅቱ ቋሚ ካፒታል (Fixed Capital) ለመለየት ነው።

Scanned with CamScanner

16. ፊክስድ አሴት *(Fixed Asset)*፡- «ቋሚ ሃብቶች ወይም ቋሚ ንብረቶች» በመባል የሚጠሩ ሲሆን የሚጨበጡ ወይም በቀላሉ በገንዘብ የሚተመኑ (ታንጀብል) ፣ አንድ ድርጅት ለረጅም ጊዜ የሚጠቀምባቸው ፣ አሁን ባለው የበጀት አመት ውስጥም ለሌላ አካል በሽያጭ ለማስተላለፍ ያልታሰቡ ናቸው። ለአብነትም የቢሮ እቃዎች (ፈርኒቸሮች) ፣ ኮምፒውተሮች ፣ መሳሪያዎች (ማሽነሪዎች)፣ መሬት ወይም ግንባታዎች ናቸው።

17. ግሮስ ፕሮፊት *(Gross Profit)*፡- ይህ ‹‹ያልተጣራ ትርፍ›› የሚባለው ሲሆን በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ሪፖርት ላይ በሶስተኛው ረድፍ ላይ የሚገኘው ነው። ያልተጣራ ትርፍ የምንለው የተሸጡ የድርጅቱን ምርቶች (አገልግሎቶች) ለማምረትም ሆነ ለማከፋፈል በቀጥታ የወጡ ወጭዎችን *(Cost of sales)* ከድርጅቱ የሽያጭ ገቢ ላይ በመቀነስ የሚገኝ ነው። እነዚህ የተሸጡ ምርቶች ወጭዎች *(Costes of Sales)* ማለትም ለተሸጡ ምርቶች (አገልግሎቶች) ወጭ የተደረጉ ክፍያዎችን፣ ምርቱን ለማምረት በቀጥታ ለተሳተፉ ሠራተኞች ተከፋይ የተደረጉ፣ የማምረቻ ወጭዎችን ፣ምርቶቹን እንዲሸጡ ለማከፋፈል የወጡ የትራንስፖርት ወጭዎችን ፣ ምርቶቹ እንዲሸጡ ለማስተዋወቅና ለመሸጥ የወጡ ወጭዎችን ያጠቃልላል።

18. ኢንታንጀብል አሴት *(Intangible Asset)*፡- እነዚህ «ግዙፋዊ ህይዎት የሌላቸው ሃብቶች» ሲሆኑ የአንድ ቢዝነስ ሃብት ተደርገው ልዩ ቦታ የሚሠጣቸው ሲሆን የተለየ ባህሪያቸው ግን ተጨባጭነት ወይም ቁስ አካላዊነት የሌላቸው መሆናቸውና በተላሉም ተመናቸውን ቆጥረን ለመተመን የማንችላቸው ናቸው። በዚህ ልዩ ባህሪያቸው ሳቢያም በድርጅቱ የሃብትና እዳ መግለጫ ሪፖርት ላይ ተመዝግበው አናያቸውም። እነዚህ (ግዙፋዊ ህይዎት የሌላቸው ሃብቶች) ማለትም ቁስ አካላዊነት የሌላቸው ሃብቶች የሚባሉት

የድርጅቱ የፈጠራ መብቶች (ፓተንት) ፣ የቅጅ መብቶች (ኮፒ ራይት)፣ የስም ዝና (ብራንድ) ፣ የንግድ ምልክት (ትሬድ ማርክ) ፣ የድህረ ገፅ መጠሪያ (ዶሜይን ኔም) ፣ የድርጅቱ የቢዝነስ ምስጢር (ትሬድ ሴክሬት)፣ድርጅታዊ የስራ ባህሉ፣ ድርጅቱ የገነባው የደንበኛ ሐብት፣እና ኔትዎርክ ናቸው።

19. ሊኪውዲቲ *(Liquidity)*፡- ይህ ቃል የሚያሳየን አንድ ድርጅት አሉኝ የሚላቸው ሃብቶች ምን ያክል በገበያ ዋጋቸው ተመን ልክ በተፈለጉ ጊዜ በፍጥነት ወደጥሬ ገንዘብነት ይቀየራሉ የሚለውን የሚያመላክት ነው። አንድ ድርጅት ይህን መሠል ባህሪ ያላቸው በርከት ያሉ ሃብቶች ባሉት ቁጥር የበለጠ በድንገተኛ (ባልታሰቡ) የጥሬ ገንዘብ እጥረቶች የማይፈተን እንዲሆን ያስችለዋል።

20. ስቴትመንት ኦብ ሼር ሆልደርስ ኢኪውቲ *(Statement of Shareholders Equity)*፡- ይህ ማለት አንድ ድርጅት በኮርፖሬሽን መልክ ተቋቁሞ የባለቤትነት ድርሻን በመሸጥ ከኢንቬስተሮች በሚገኝ ካፒታል ስራውን እያከናወነ ከሆነ የድርጅቱ ባለቤቶች በድርሻቸው ላይ ያለውን ወቅታዊ ለውጥ ለማየት ሲፈልጉ ድርጅቱ የሚያዘጋጅላቸው የሂሳብ መግለጫ ነው። በዚህ ስር የባለቤቶች ነባር የተመዘገበ ካፒታል፣ አዲስ የተሸጠና የተከፈለ ካፒታል፣ ከድርጅቱ አመታዊ የተጣራ ትርፍ ላይ ለተቀማጭነት የተወሠደ *(Retained Earning)* እንዲሁም ለባለቤቶች የተከፋፈለውን መጠን (ዲቪደንድ) ያካተተ ነው የሚሆነው። በዚህ መዕሐፍ ውስጥ ማየት ይቻላል።

21. አኑዋል ፐርሰንቴጅ ሬት *(Annual Percentage Rate)*፡- ይህ አንድ ድርጅት ከአበዳሪ ተቋማት ገንዘብ ሲበደር ከዋናው ገንዘብ (ፕሪንሲፓል) ውጭ የሚከፍለው አመታዊ የወለድ ምጣኔና የአገልግሎት ወጭዎችን ነው ይህ ምጣኔ ታሳቢ የሚደረገውም ከዋናው የብድር መጠን *(Principal)* ላይ ሆኖ የሚገለፀውም በፐርሰንት መልክ

Scanned with CamScanner

ይሆናል። ይህም የሚጠቅመው ብድሩ ምን ያህል (ርካሽ ወይም ውድ እንደሆን ለማነፃፀር፣ የሚወሰድበት አላማ (ፕሮጀክት) ከሚያመጣው ትርፋማነት አንፃር አዋጭ መሆኑንና አለመሆኑን ለመረዳት፤ እንዲሁም የትኛው አበዳሪ ዝቅ ባለ የብድር ወጭ (ተከፋይ ወለድ)) እንደሚያበድር እርስ በእርስ ለማወዳደርና በመጨረሻም ለመወሰን ነው።

22. ባሉን ሉን *(Balloon Loan)*:- ይህ «ተለጣጭ» የሚወሰነው የብድር አይነት ሲሆን በተለይም ለጀማሪ ቢዝነሶች የተሻለ የአከፋፈል ስርአት አይነት ነው። ብድሩ በሚወጣለት ቋሚ ሠሌዳ የሚከፈል ሆኖ ነገር ግን ጀማሪ ቢዝነሶች ሲጀምሩ ገንዘብ ስለማያፕራቸው የመጀመሪያዎች ክፍያዎች ዝቅተኛ በመሆን ይጀምሩና ወደመጨረሻ አካባቢ ግን ተከፋይ መጠኑ እየበዛ የሚሄድ ይሆናል። (ባሉን ማለትም ከትንሽ ወደትልቅ የሚለጠጥ ፊኛ ማለት ነው)። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን መጀመሪያ አካባቢ የሚከፈለው አነስተኛ ቢመስልም የድርጅት መሪዎች ግን በመጨረሻ አካባቢ መከፈል ያለባቸውን ከፍተኛ ገንዘብ የመክፈል ችሎታው እንዳላቸው ቆም ብለው ሊያስቡበት ይገባል።

23. ባንክረፕሲ *(Bankruptcy)*:- ይህ ከፍተኛ የገንዘብ አጣብቂኝ ውስጥ ለገቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች በህግ ደረጃ የሚሠጣቸውን ጊዜያዊ ከለላ መሆኑን ያመለክታል። አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት በ‹‹ባንክረፕሲ›› ደንብ በፍ/ቤት ካመለከተ ድርጅቱ ለገባባቸውና መክፈል ላልቻላቸው እዳዎች (ንብረቱ ከመወረሱ በፊት) የእፎይታ ጊዜ እንዲሰጠው ያስችለዋል። አንዳንዴም እዳው እንዲቀነስለት ወይም ሙሉ በሙሉ እዳው እንዲሰረዝ ሊያደርግለት ያስችለዋል። ይሁን እንጂ ይህ ሪፖርት እጅግ አስገዳጅ ካልሆነ በቀር የግለሰቡን (የድርጅቱን) ቀጣይ የተበዳሪነት ታማኝነቱን በእጅጉ ይጎዳል።

24. ቡክ ኪፒንግ *(Book keeping)*:- ይህ በአጭር አጠራር ‹‹የሒሳብ መዝገብ አያያዝ›› በማለት ስንጠራው የአንድን ድርጅት ልዩ ልዩ የገቢና ወጭ እንቅስቃሴዎችን የሚደግፉ ዶክመንቶች ወዲያው ወዲያው የመያዝና፤ የመመዝገብና የማደራጀት ሥራ ላይ ያተኮረ የሒሳብ አያያዝ ዘዴ ነው። ትክክለኛ የሒሳብ መዝገብ አያያዝ በቀጣይ ለሚዘጋጁ የገንዘብ ወይም የሒሳብ መግለጫ ሪፖርቶች ትክክለኛነት ሚና ያለው ግብአት በመሆን የሚያገለግል ነው።

25. ካፒታል ጌይን *(Capital Gain)*:- ይህም ማለት የአንድ ድርጅት የኢንቬስትመንት ሃብት (ካፒታል) አመታዊ የእድገት መጠንን ሲሆን ይህም የሚሆነው በድርጅቱ ላይ ኢንቬስት ከተደረገበት መጠን በላይ ሆኖ ሲገኝ ነው። ለምሳሌ ከአንድ አክሲዮን ከተገዛበት ገንዘብ መጠን በላይ በዚህ ያህል ተመን ከተሸጠ የሽያጭ ካፒታሉ መጠን ከተገዛበት የካፒታል መጠን በላይ አድጓል እንላለን።

26. ኮምፓውንድ ኢንተረስት *(Compound Interest)*:- ይህ ‹‹ጥምር ወለድ›› ሲባል ይህም ማለት በባንክ ተቀማጭ ወለዶች ላይ ወይም ደግሞ በድርጅቶች ኢንቬስትመንት ላይ ታሳቢ የሚደረግ ወለድ ወይም ገቢ ነው። ወለዱ (ገቢው) የሚታሰበው መጀመሪያ በተቀበለው (ኢንቬስት በተደረገው ዋና ገንዘብ) ወይም ‹‹ፕሪንሲፕል›› ላይ ብቻ ሳይሆን ካሁን ቀደም ካሉት አመታት የተገኙትን ወለዶች ጭምር ታሳቢ አድርጎ ነው። ወለዱ በዋናው ገንዘብ ላይ ብቻ ሳይሆን በየአመቱ ባሉት ወለዶች ላይ ጭምር በመሆኑ አጠቃላይ መጠኑን በፍጥነት ያሳድገዋል። ይህ ‹‹ነጠላ ወለድ›› ወይም ‹‹*Simple Interest*›› ከተባለው የሚለይ ሲሆን ነጠላ ወለድ የሚታሰበው በዋናው ገንዘቡ (ፕሪንሲፕል) ላይ እንጂ በተከማች ወለድ ላይ ታሳቢ የሚደረግ ወለድን አያካትትም።

27. **ክሬዲት ስኮር** *(Credit Score)*፡- ይህ ከብድር ወይም ዱቤ አወሳሰድ ጋር በተያያዘ ብድርንም ሆነ የዱቤ ግዥን ለትክክለኛው ነገር መጠቀማችንንና በተገቢው ጊዜ ውስጥ መክፈላችንን ወይም ሳንከፍል ማንተታችንን የሚያሳይ ውጤት ነው፡፡ በትክክል ብድርን (ዱቤን) መፈፀም በቀጣይ ብድርን (ዱቤን) ለማግኘት የሚያግዝ ሲሆን ክሬዲት ስኮሩንም ከፍ ያደርገዋል፡፡

28. **ኢንፍሌሽን** *(Inflation)*፡- ይህ ‹‹የዋጋ ንረት›› ወይም ‹‹የዋጋ ግሽበት›› በመባል ይጠራል፤ ይህም ማለት በጊዜ ሂደት እየጨመረ የሚሄድን የጥሬ እቃ ፣ ያለቀላቸው ምርቶችንና አገልግሎቶችን የመሸጫ ዋጋ ነው፡፡

29. **ኢንተረስት** *(Interest)*፡- ይህ ‹‹ወለድ›› በመባል የሚጠራ ሲሆን የሌሎችን ገንዘብ ወስደን ለተጠቀምንበት የምንከፍለው ተጨማሪ ገንዘብ ነው፡፡ ለተበዳሪው የወለድ መጠኑ እንደወጭ የሚታሰብ ሲሆን ለአበዳሪው ደግሞ ወለዱ የሚታየው ካበደረው ገንዘብ እንደሚገኝ የገንዘቡ የኪራይ ገቢ ተደርጎ ነው፡፡ ቃሉ ኢንቨስተሮች ከኢንቨስትመንት የሚያገኙትን ትርፍንም የሚያሳይ ሲሆን ‹‹ኢንተረስት›› የሚለው ቃል በዚህ ጊዜ ‹‹ሪተርን ›› ወይም «ትርፍ» ወደሚል ስያሜ ይቀየራል፡፡

30. **ፕራይም ሬት** *(Prime Rate)*፡- ይህ በብሔራዊ ባንክ የሚተመን የወለድ አይነት ሲሆን ባንኮች እርስ በእርሳቸው ገንዘብ የሚበዳደሩበት የወለድ መጠን ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ባንኮች በጣም ታማኝ ለሆኑ ደንበኞቻቸው በዚህ በጣም ትንሽ በሆነ ወለድ መጠንም ያበድሯቸዋል፡፡

31. **ፕሪንሲፓል** *(Principal)*፡- ይህ የመጀመሪያ የኢንቨስትመንት ካፒታል ወይም በባንክ በተቀማጭነት የሚመዘገብ ወይም ባንኮች በተበዳሪዎች የተጠየቁትና የተፈቀደላቸው መጠን ማለት ነው፡፡ ‹‹ፕሪንሲፓል›› ወለድ የሚታሰብለትና የሚከፈልበት መጠን ማለትም ነው፡፡

32. **ቫሉዌሽን** *(Valuation)*፡- ይህ ‹‹የእቻ ትመና›› በመባል የሚጠራ ሲሆን አንድ ድርጅት ገንዘብ ከኢንቬስተሮች ለማምጣት ሲፈልግ የቢዝነሱን አጠቃላይ የተመን ዋጋ በቅድሚያ የሚያሠላበትና የሚያውቅበት መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም በስቶክ ማርኬት ግብይት ውስጥ አንድ ድርጅት የስቶኩን የመሸጫ ዋጋ ለመወሰን በስቶኩ ላይ የተመሠረተ የእቻ ትመና ሊያደርግ ይችላል፡፡

33. **ኔትዎርዝ** *(Net worth)*፡- ይህ ‹‹የባለቤቶች የተጣራ ሃብት›› የሚለውን ይገልፃል፡፡ ስያሜውም የአንድን ቢዝነስ አጠቃላይ ዋጋ የሚያሳይ ሲሆን ድርጅቱ ያለበትን አጠቃላይ ተከፋይ እዳ ከድርጅቱ አጠቃላይ ሃብት ላይ በመቀነስም ነው፡፡ የቅርብ ጊዜ የቢዝነሱን የሃብትና እዳ ሚዛን መግለጫ በመጠቀም በቀላል ፎርሙላ ማለትም ‹‹ሃብቶች - እዳዎች = ኔትዎርዝ›› በሚል ቀመር ማስላት ይቻላል፡፡

34. **ሪቴይንድ እርኒንግ** *(Retained Earning)*፡- ይህ ‹‹ተቀማጭ ትርፍ›› የምንለው ሲሆን አንድ ድርጅት ከአመታዊ የተጣራ ትርፉ ላይ ለባለቤቶች በትርፍ ክፍፍል መልክ ተቀንሶለት በድርጅቱ እነውንት ላይ ለቀጣይ የማስፋፊያ ወይም አዳዲስ ኢንቬስትመንት ተቀማጭ ሆኖ የማዛወተረውን ነው፡፡ በሌላ አጠራር ድርጅቱ ለቀጣይ ተፈላጊ ኢንቬስትመንቶች በቁጠባ መልክ ከአመታዊ ገቢው ላይ አያነሳ የሚቆጥበው ‹‹የውስጥ ፈንድ›› *(Internal Fund)* ሲሆን በሌላ አጠራርም ‹‹ቡትስ ትራፒንግ›› ይባላል፡፡

35. **አሞርታይዜሽን** *(Amortization)*፡- ይህ ቃል የሚያሳየው አንድ ድርጅት ያለበትን እዳ በየጊዜው በመከፋፈል የሚከፍልበትን እንድ ድርጅት ያለበትን እዳ በየጊዜው በመከፋፈል የሚከፍልበትን ሃብቶች መንገድ ነው፡፡ እንዲሁም የአንድን ድርጅት የማይጨበጡ ሃብቶች

Scanned with CamScanner

የዋጋ ተመኖቻቸውን ልክ እንደ የእርጅና ተተናሽ ወጭ ግብር ለማስቀነስ በሚረዳ መንገድ ተከፋፍሎ የሚመዘገብበትም ነው።

36. ዴት ፋይናንሲንግ *(Debt Financing)*፡- ይህ ‹‹በብድር የተሸፈነ ካፒታል›› በመባል የሚጠራ ሲሆን አንድ ድርጅት ለሥራ ማስኬጃም ይሁን ለኢንቨስትመንት ወለድ የሚከፍልበትን ገንዘብ በብድር መልክ ከአበዳሪዎች ሲወስድ ማለት ነው። ለድርጅት ብቻ ሳይሆን ግለሰቦችም በዚህ መልክ ይጠቀማሉ። ቦንድ በመሸጥ የሚሸፈንም ካፒታል በዚሁ ስር ይጠቃለላል።

37. ኢኩይቲ ፋይናንሲንግ *(Equity Financing)*፡- ይህ ‹‹በባለቤቶች የተሸፈነ ካፒታል›› የሚለውን መጠሪያ የሚይዝ ነው። ይህም መንገድ አንድ ግለሰብ ኢንቨስት ለማድረግ ወይም ነባሩን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት ሲፈልግ ለባለሃብቶች ድርሻ በመሸጥ የትርፍ ተከፋይነት መብትን በመስጠት ውስጥ ተፈላጊ ካፒታልን የሚያሰባስብበት መንገድ ነው።

38. ዴት ሠርቪስ ከቨሬጅ ሬሽዮ *(Debt - service Coverage Ratio)*፡- ይህም ማለት አንድ ድርጅት የተበደረውን የብድር መጠን ከእነ ወለዱ ለመክፈል ምን ያህል ጥሬ ገንዘብ አለው የሚለውን የሚያመለክት ነው። የአንድ ድርጅት የዚህ ጥመርታ ውጤት ከ‹‹1›› ቁጥር በላይ ከሆነ ድርጅቱ ብድሩን ለመክፈል በቂ ገቢ ያለው መሆን ይጠቁማል።

39. ሼር *(Share)*፡- ይህ ‹‹የድርሻ መጠን›› የሚባል ሲሆን በአክሲዮን መልክ በተመሠረቱ ኮርፖሬሽኖችና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ውስጥ የባለቤትነት መጠንን የሚያሳይ ነው።።

40. ስቶክ *(Stock)*፡- በመቶኛ ሲገለፅ የባለቤትነት መብት መጠንን የሚያሳይ ነው። አንድ ድርጅት 100 ሼሮች ቢኖሩትና ከእነዚህም

ውስጥ አንድ ሠው 10 ሼሮች ቢገዛ፣ ይህ ሠው በድርጅቱ ውስጥ የ10 በመቶ የባለቤትነት መብት አለው ማለት ይሆናል።

41. ፊክስድ ኢንተረስት ሬት *(Fixed Interest Rate)*፡- ‹‹ቋሚ ወለድ›› ማለት ሲሆን አንድ ጊዜም ለአንድ ድርጅት መጀመሪያ እንዲከፍል የሚተመነው የወለድ መጠን እስከ መጨረሻው ድረስ በዚያው የሚቀጥል መሆኑን ነው። ይህ ቋሚ በጀት ለመያዝ በተለይ ለትንንሽ ድርጅቶች ይረዳል።

42. ፍሎቲንግ ኢንተረስት ሬት *(Floating Interest Rate)*፦ ‹‹ተቀያያሪ ወለድ›› የምንለው ሲሆን እንደ ገንዘብ ወቅታዊ ገበያው እየታየ ወለዱ ማሻሻያ ይደረግበታል። በሌላ መጠሪያው *"Variaible Rate"* ወይም *"Adjustable Rate"* በመባል ይታወቃል።

43. ሎንግ ተርም ዴብት *(Long Term Debt)*፡- ‹‹የረጅም ጊዜ ብድር›› በመባል የሚጠራ ሲሆን ማናቸውም ከአንድ አመት በላይ በሆነ ጊዜ ውስጥ ሊከፈል የሚችል ብድር በዚህ ውስጥ ይካተታል።

44. ሲኪውርድ ሎን *(Secured Loan)*፡- ይህ ‹‹ዋስትና ያለው ብድር›› ማለት ሲሆን ብዙ አበዳሪዎች ገንዘብ ሲያበድሩ ለብድሩ መያዣ (ኮላተራል) ንብረትን ታሳቢ ያደርጋሉ። ብድሩ በታሰበው መንገድ ባይመለስ ለዋስትናው የተያዘውን ንብረት በመሸጥ ብድሩን ከነወለዱ ይሸፍናል ማለት ነው። ያለመያዣ የሚሠጡ ብድሮች ‹‹ዋስትና የሌላቸው ብድሮች›› ወይም *"Unsecured loan"* በመባል ይጠራሉ።

Scanned with CamScanner

"ፋይናንስ ማኔጅመንት - 2"

ስቶክ ማርኬት የኢንቨስትመንት ጥበቦች

መጫወት ብቻውን አሸናፊ አያደርግም!!

ኢንቬስትመንት የቁማር ጨዋታ ነው፤ ወይ ይበላሉ አልያም ያስበላሉ:: እነሆ እንጡራ ሐብትዎን ላለማስበላት ከፈለጉ (ላሰው ይጨመርለታል እንዲሉ) ሊያውቋቸው ስለሚገቡ የጨዋታ ህጎች በ"ፋይናንስ ማኔጅመንት - 2" መጽሐፍ ላይ ያገኙዋቸዋል::

- በአለማችን በየትኛውም አገር ውስጥ ያለው እውነታ ይህ ነው:: ሃብታሞች በየጊዜው የበለጠ ሃብታም እየሆኑ ነው:: ብዙሃኑ ግን በየጊዜው ሃብቱ እየቀነሰ ነው:: አሳዛኙ ነገር ይህ እውነት ወደፊትም የማይቀየር መሆኑ ነው:: የማቅሚያ መንገዱ ከሶስቱ ቃላት የተገነባ ነው፤ "ፋይናንስ መር ኢንቬስትመንት"::
- የአለማችን ሃብት ወደ 40 ትሪሊየን ዶላር ይገመታል:: የአለማችን ህዝብ 7 ቢሊየን ነው:: 10 በመቶ የሚሆነው የአለማችን ህዝብ ማለትም 700 ሚሊየኑ 90 በመቶ የሚሆነውን የአለማችንን ሃብት 36 ትሪሊየን ዶላር የያዘ ነው:: 90 በመቶ የሚሆነው ህዝብ ማለትም 6.3 ቢሊየን ህዝብ 10 በመቶ የሆነውን የአለማችንን ሃብት ማለትም 4 ትሪሊየን ዶላር በጋራ ይቀራመታል:: ለምን አብዛኛው የአለም ሃብት በጥቂቶች ብቻ ተያዘ? መልሱን "ፋይናንስ ማኔጅመንት - 2" መጽሐፍ ከእነመፍትሔው ይዞ ቀርቧል::
- ከየትኛውም ኢንቬስትመንት በፊት ሊከተሏቸው የሚገቡ 10 ቀዳሚ ተከተላዊ የአወሳሰን መርሆዎች
- በኢንቬስትመንት ውስጥ ውዳሴ የሚያነሳውም ሆነ ወደታች የሚጥለውም ኢንቬስተሩ የተከተለው የአወሳሰን ዘይቤ ነው::

- ኢንቬስትመንት ሳይንስ ነው:: እነዚ አራቱ የሳይንስ ሳይክሎችን በመጠቀም ራስዎን ወደ ምርጥ ኢንቬስተርነት ያሸጋግሩ::
- ሠዎች ኢንቬስተር የሚሆኑት ከፍተኛ የገንዘብ ትርፍ ለመፍጠር ነው:: ይሁን እንጂ በኪሳራም ያላቸውን ሲያጡ ይችላሉ:: እርስዎ የገንዘብ ተጠቃሚነትን በከፍተኛ ደረጃ እያገኙ ፤ የኪሳራ እድልዎን በላቀ ደረጃ እንዴት እንደሚቀንሱ ሊያደርጓቸው የሚገቡና የማይገቡ ጉዳዮች አሉ!! "ፋይናንስ ማኔጅመንት - 2" ውስጥ ያገኙዋቸዋል::
- ‹‹ድሃ ክብር የለውም፤ ድህነት ያስጠቃል፣ የሠው ልጅ ትልቁ ጠላቱ ድህነቱ ነው፣ ድህነት የኩነኔ መገለጫ ነው፤ ድህነት የሁሉም ችግሮች መነሻ ነው!›› የሚሉ አባባሎችን በተደጋጋሚ ሠምተናል፤ አንብበናል:: ከድህነት ለመውጣት ብቸኛው መንገድ ኢንቬስተር መሆን ብቻ ነው:: ድህነትን የሚጠሉ ከሆነ አላማዎ ሃብትን መፍጠር ሊሆን ይገባል:: ወደሃብት ማማ ለመጠጋት ደግሞ የኢንቬስትመንት ጥበቦች ያስፈልግዎታል:: "ፋይናንስ ማኔጅመንት-2" መፅሐፍ›› በፋይናንስና ኢንቬስትመንት ዙሪያ የተደራጁ እውቀቶችን አካቶ ቀርቧል::
- ‹‹ሃብታም መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይቀላል›› የሚለው አባባል እንከን አይወጣለትም:: ሃብትን ለመፍጠርም ሆነ የተፈጠረውን ለማስቀጠል ፤ በሃብቱም ሠላም ለማግኘት መንፈሳዊ ባህሪያትን መላበስ ይጠይቃል:: መፅሐፉ መንፈሳዊ የሐብት መገንቢያ ስልቶችን አካቷል::
- እርስዎ ቀጣዩ የአገራችን ባለሐብት ለመሆን ተዘጋጅተዋል? እንግዲያውስ "ፋይናንስ ማኔጅመንት - 2" መፅሐፍ ያስፈልግዎታል!!
- ሠዎች ሐብታም ከሆኑ በኋላ እንደገና ለምን ይከስራሉ?
- ‹‹መተኮስ ወይም መከሸፍ!›› ምርጫው ያንተ ነው!! ያለንበት አለም እንደ መንደር እየሆነች በመጣችበትና ውድድሩ እየከረረ ባለበት 21ኛው መቶ ክ/ዘመን ውስጥ ባለንበት የአኗኗርና የሃብት ደረጃ መቀጠል አትችልም::

Scanned with CamScanner

ምርጫው በኢንቬስትመንት ጥበቦች ውስጥ ወደፊት መተኮስ አለያም መክሸፍ ነው። መተኮስን ከመረጡ ግን ይህን መፅሐፍ ማንበብ ትክክለኛ ምርጫ ነው።

- ❖ ሠዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሃብታም ለመሆን ከፈለጉ ምን ላይ ኢንቬስት ቢያደርጉ ጥሩ ነው? እነሆ ለፈጣን ሃብት የሚያበቁ የኢንቬስትመንቶች አይነቶችንና መምረጫ ስልቶችን በመፅሐፉ ውስጥ ያገኛሉ!
- ❖ ብዙዎች ኢንቬስት ማድረግ እየፈለጉ፤ በአዋጭነቱ አማላይ የሆነ የንግድ ሃሳብ ይዘው በገንዘብ ላቢያ ይገታሉ። ለኢንቬስትመንት የሚውሉ የፋይናንስ አቅራቢ አማራጮች የትኞቹ ናቸው? እንዴትስ የተሻለውን ይመርጣሉ?
- ❖ ለስኬታማ ኢንቬስትመንት የሚያበቁ ምርጥ የሚባሉ 20 ልዩ ልዩ እውቀቶች!!
- ❖ ለገንዘብ ነፃነት የሚያበቁ 9 ወሳኝና በቀደም ተከተል የሚፈፀሙ የሐብት መገንቢያ መሠሳሉች
- ❖ በ2020 በሚከፈተው የሃብት ማፍሪያ ገበያ "ስቶክ ማርኬት" ራስዎን አዘጋጅተዋል?
- ❖ በስቶክ ማርኬት ውስጥ ተሳታፊ በመሆን ሃብት ለማፍራት ከፈለጉ የኢንቨስትመንት ጥበቦችን ቀድመው ይገንዘቡ
- ❖ ስቶክ ማርኬት የቁማር ወይስ የኢንቨስትመንት ጨዋታ? ስቶክ ማርኬትን በእውቀት ሲጠቀሙ ኢንቨስትመንት ሲሆን ያለ እውቀት ለሚገቡበት ደግሞ እንደቁማር ገንዘብዎን የሚያከስሩበት አስገራሚ ቦታ ነው!!

እነሆ "ፋይናንስ ማኔጅመንት 2" መፅሐፍ ብዙ ጉዳዮችን ግልፅ ያደርጋል



Scanned with CamScanner

የአማርኛ ትርጉም	English Translation
የአሰራር መመሪያዎች.	Manuals
የአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ መርሆች	IFRS
ደጋፊ ሌጀር	Subsidiary ledger
ዋና ሌጀር	General Ledger
ግዙፋዊ ህልዎት ያላቸው ንብረቶች	Tangible assets
ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው ንብረቶች	Intangible assets
የመልካም አፈጻጸም ስም	Good will
የማግኛ ወጪ	Acquisition cost
ቀጥተኛ የእርጅና አቀናነስ ዘዴ	straight line method of amortization
ቀጥተኛ ጥሬ እቃዎች	Direct Materials
ቀጥተኛ ያልሆኑ ጥሬ እቃዎች	Indirect Materials
ቀጥተኛ የሆነ የሰው ሃይል	Direct Labor
ቀጥተኛ ያልሆነ የሰው ሀይል	Indirect labor
ኮስት ማዕከል (የዋጋ ቋት)	Cost Centers
የጥቃቅን ወጭዎች መክፈያ ገንዘብ	Petty cash
ዘላቂታነት ያለው ድርጅት አሳቢ	Going Concern Concept
አግባብነት	(Relevance)
አስተማማኝነት	(Reliability)
ወጥነት	(Consistency)
ጥንቃቄ	(Prudence)
ከቅርጽ ይልቅ ይዘት	(Substance over Form)
በቂ መረጃ	(Adequate Disclosure)
ጉልህነት	(Materiality)
ጥምር የአካውንቲንግ ዘዴ	(double-entry system)
እንደ ምንጭነት የሚያገለግሉ ሰነዶች	(Source Documents)
የመመዝገቢያ ቮውቸሮች	(Recording vouchers)
ኮንትሮል አካውንት	(Control ledger)
ጆርናል ቮውቸሮች	(Journal Vouchers)
ሂሳብ መዝጋት	(Closing of Book of Accounts
አመታዊ ኦዲት	(Annual Audit)
ገዢ ሁኔታዎች	(Governing Factors)
የሂሳብ አመት	(Financial Year)
ሀብቶች	(Assets)
የትርፍ እና የኪሳራ መግለጫ	(Profit & Loss Statement)
ካፒታል	(Capital)

ገቢ	(Revenue)
የማምረቻ ዋጋ	(Cost of Production)
የተሸጡ እቃዎች ወጪ	(Cost of goods sold)
የመሸጫ እና የአስተዳደር ወጪ	(Selling, & Administrative Expense)
እዳዎች	(Liabilities)
ቋሚ ንብረቶች	(Fixed Assets)
ይዞታዎች፣ ፋብሪካ እና መሳሪያዎች	(Property, plant and equipment)
የእርጅና ተቀናሾች	(Depreciation and Amortization)
በጥቅል የእርጅና አቀናነስ ስርአት	(pooling depreciation method)
ተሰብሳቢዎች	(Debtors /Receivables/)
ከደንበኞች የሚሰበሰብ	(Trade Debtors)
ቅድመ ክፍያዎች	(Prepayment)
ማስያዣ	(Deposit)
ከስታፍ የሚሰበሰብ	(Staff debtors)
ሌሎች ተሰብሳቢዎች	(Sundry Debtors)
ጥሬ ገንዘብ እና የባንክ ባላንስ	(Cash and Bank Balance)
በእጅ ያለ ገንዘብ	(Cash on Hand)
የጥቃቅን ወጭ ገንዘብ	(Cash on Hand)
በቅርብ ጊዜ የሚከፈሉ እዳዎች	(Current Liabilities)
የተወዘፈ እዳ	(Accrued Liability)
ቀድሞ የተሰበሰበ ገቢ	(Deferred Revenue)
ማስያዣዎች	(Deferred Liabilities)
የረጅም ጊዜ ብድር	(Long term loans)
ሽያጭ	(Sales)
ሌሎች ገቢዎች	(Other Income)
የምርት ዋጋዎች	(Production Costs)
የስራ ማስኬጃ ወጪዎች	(Operating expenses
የፋይናንስ መግለጫዎች	(Financial Statements
የፋይናንስ አቋም መግለጫ	(Statement of Financial position)
የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ	(Profit and Loss Account
የጥሬ ገንዘብ ፍሰት መግለጫ	(Statement of Cash flows)
የውስጥ ቁጥጥሮች	(Internal controls)
የባንክ ማስታረቂያ	(Bank Reconciliation)
ግዢዎች	(Purchase)
ምዝገባ	(Accounts Recording)

Scanned with CamScanner



የንግድ ሥራን ያለፋይናንስ ዕውቀት እና ስርዓት ማካሄድ ይቻላል። በሌላ በኩል እንደን የንግድ ድርጅት መሠረታዊ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓትን ተከትሎ ማከናወንም ይቻላል። የመጀመሪያው አማራጭ በርግጥም ስለሚቻል ከጥቂት ሥራውን የጀመሩበት ቀን ከመርገም ጀምረው በኪሳራ መዝጋት ብቻ ሳይሆን የሚፈለግባቸውን ግብርና ሌሎች ዕዳቸውን መክፈል ባለመቻል ወህኒ ቤት አድርሷቸዋል። ከሃገር ተሰደዋል። በጭንቀትና በፍርሃት እንዲኖሩ ሆነዋል። ሁለተኛው አማራጭ ድርጅቱን በፋይናንስ እውቀትና ስርዓት መምራት ሲሆን ድርጅቱን ተፈጥሯዊ (organic) በሆነ መንገድ ከማሳደጉም በላይ ለመስራቾቹና ሠራተኞቹ ሰላምና ብልፅግና ይሰጣል። ድርጅቱም የሃገር ባለዕዳ ሳይሆን ሀገራዊ ሃብት ይሆናል። ከሁለቱ መንገዶች አንዱን መምረጥ የአልበርት አንስታይንን ጭንቅላት የሚጠይቅ አይደለም። ሁለተኛውን መንገድ ለመረጡ ብቻ ግን ይህ መፅሃፍ ተዘጋጅቷል።

(ሚሊዮን ከብረት፣ በ BDO Ethiopia የንግድ አማካሪ)

ይህ መፅሃፍ መደበኛ በሆነው የትምህርት ስርዓ[illegible] የገንዘብ አስተዳደር መሰረታዊ እውቀት ለሌላቸው [illegible] በመስክ የትምህርት ዝግጅት ያለፉ መሠረታዊ የሆነውን [illegible] ገብ ሆኖ አገኝቼዋለሁ[illegible]

(ዶ/ር ሰውአለ አበተ[illegible])

ዶ/ር አቡሽ አያሌው ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን በሜዳልያ በመመረቅ ከአሜሪካው ሊንከን ዩኒቨርሲቲ ያገኙ ሲሆን ከኢትዮጵያ ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በቢዝነስ; በማኔጅመንትና በኢንቨስትመንት ጉዳዮች ዙሪያ የማማከርና የማሠልጠን ዕውቅና ያላቸው ባለሙያ ናቸው። በአሁኑ ወቅት በንግድ አማካሪነትና በዩኒቨርሲቲ ሌክቸረርነት በመስራት ላይ ይገኛሉ።

ዶ/ር አቡሽ አያሌው
(ሰርቲፋይድ ማኔጅመንት ኮንሰልታንት)

SELL

ዋጋ ብር 250 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር)

Scanned with CamScanner

መልካም የቢዝነስ ኑሮ

ሣብዕ ትረካ TUBE

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner